© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

# የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ

## አሥራ ሁለተኛ ክፍል

አዘጋጆች:-

ጌታቸው እንዳሳማው (ረ/ፕ)

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ

ወንድወሰን አዳነ

አርታኢ:-

የኋላሸት ደሳለኝ

ገምጋሚዎች:-

ወርቁ አድማስ

ተስፋዬ ወ/ሚካኤል

መኮንን አስማማው

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

## ምስጋና

የዚህ መጽሐፍ ዲዛይን ህትመትና ስርጭት ማከናወኛ ገንዘብ የተገኘው በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ኘሮጀክት (GEQIP) አማካኝነት ነው:: የኘሮጀክቱ ዋና ዓላማ በአገሪቱ በሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከ1ኛ-12ኛ ክፍሎች የሚሰጠውን የትምህርት ጥራት ማሻሻል ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለGEQIP የዋለውን ገንዘብ ያገኘው በብድር/በእርዳታ ሲሆን ብድሩን/ እርዳታውን የሰጡት ዓለምአቀፍ የልማት ማህበራት (IDA)፣ ፋስት ትራክ ኢንሼትቭ ካታሊቲክ ፈንድ (FTI CF) እና ሌሎችም የልማት አጋሮች ማለት የፊንላንድ፣ የኢጣሊያ የልማት ማህበር፣ የኔዘርላንድና የታላቋ ብሪታኒያ የእርዳታ ድርጅት አለምአቀፍ የልማት ዋና ክፍል (DFID) ናቸው::

ሁሉንም በዝርዝር መጥቀስ የማይቻል ይሁን እንጂ በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ይህ የተማሪ መጽሐፍና የመምህር መምሪያ እውን እንዲሆኑ ያልተቆጠበ ድጋፍቸውን ሰጥተዋል:: በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር ምስጋናውን ያቀርባል::

© በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
1ኛ እትም፣ 2004 ዓ.ም
ISBN 978-99944-2-259-3

የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት
የፖ.ሳ.ቁጥር 5613
ዱባይ፣
የተባበሩት የአረብ ኤሜሬት እና

ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
የፖ.ሳ.ቁጥር 100767
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በመተባበር ይህን መጽሐፍ ለኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር አዘጋጅተውና አትመው፣ አሰራጭተዋል::

ሁሉም የህትመት መብቶች ተከብረዋል::
የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም እንደማይቻል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዲራል ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 410/2004 የኮፒራይትና የተዛማጅ መብቶች ጥበቃ አዋጅ 10ኛ አመት ቁጥር 55 አዲስ አበባ ጁላይ 19, 2004 ይከለክላል::

የስዕሎችን የኮፒ ራይት መብቶች ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል:: ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን::

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


መግቢያ ................................................................ i

**ምዕራፍ አንድ:-** ቋንቋና ሕብረተሰብ ................................ ፩

**ምዕራፍ ሁለት:-** የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ........ ፳

**ምዕራፍ ሦስት:-** ሒስ ............................................. ፵፬

**ምዕራፍ አራት:-** ሥነጽሑፍ ....................................... ፷፯

**ምዕራፍ አምስት:-** ሰብዓዊነት .................................... ፹፬

**ምዕራፍ ስድስት:-** ጥናታዊ ጽሑፍ .................................. ፻፲፫

**ምዕራፍ ሰባት:-** ሥነግጥም .......................................... ፻፵፩

**ምዕራፍ ስምንት:-** ውሳኔ ላይ መድረስ ............................ ፻፷፱

**ምዕራፍ ዘጠኝ:-** ህብረተሰብና ጤና ................................ ፻፸፯

ተቀፅላ

ለተጨማሪ ንባብ የተመረጡ መጻሕፍት ዝርዝር ................ ፪፻

ዋቢ ፅሑፎች ............................................................ ፪፻፩

ቃላት ከነፍቻቸው ...................................................... ፪፻፫

ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው ..................................... ፪፻፯


© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

# መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማጐልበትና የሥነጽሑፍና የሥነልሳን እውቀትን ማዳበር ናቸው፡፡ እነዚህ ዓላማዎችም በመርሐ-ትምህርቱ ላይ በግልጽ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል የመማሪያ መጽሐፍ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ነው፡፡ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ደግሞ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በየጊዜው ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል፡፡ አንደኛው የመርሐ ትምህርቱን አላማዎች በማስፈፀም ረገድ የመፅሐፉን አቅም ለማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መርሐ ትምህርቱ ላይ ማሻሻያ ወይም ለውጥ ሲደረግ ነው፡፡

ይህ የ፲፪ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሆነበት ምክንያትም በ፳፻፩ ዓ.ም. መርሐ ትምህርቱ እንዲሻሻል በመደረጉ ነው፡፡ መጽሐፉ መርሐ ትምህርቱ ትኩረት የሰጠባቸውን ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ጥረት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ፣ ማብራሪያዎቹና መልመጃዎቹ መርሀ ትምህርቱን መነሻ በማድረግ በክሂልና በእውቀት ዘርፍ ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡

ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ፣ ግልፅና ሳቢ፣ መልመጃዎቹ ደግሞ አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ በየምዕራፉ ማብቂያ ዐበይት ነጥቦች በማጠቃለያ መልክ ከመቅረባቸውም በላይ፣ ተማሪዎች የየምዕራፉን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዱ የሚያመሳክሩባቸው የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘጋጅተዋል፡፡ ተማሪዎች በነዚህ ነጥቦች እየተመሩ የትምህርቱን ዓላማዎች በመፈፀም ረገድ በራሳቸው ያሉበትን ደረጃ መገምገምና ጉድለቶቻቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም መጽሐፉ ትምህርቱን በሚፈለገው መንገድ ለመከታተልና የትምህርቱን ዓላማዎች ለመጨበጥ ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሑፎቻቸውን ያዋሱንን ሁሉ እያመሰገንን፣ ስለመጽሐፉ ከመምህራን፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች የሚቀርቡ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልፃለን፡፡

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

# ምዕራፍ አንድ

## ቋንቋና ህብረተሰብ

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቤተሰቦችና ንኡሳን ቤተሰቦች ትናገራላችሁ፤
- ድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍን ተረድታችሁ፣ በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይታችሁ ትጽፋላችሁ፤
- በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ፤ ትተነትናላችሁ፤
- በመዝገበ ቃላት በመታገዝ  የቃላትን ቀጥተኛ ፍች ትገልጻላችሁ፤
- በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ የተደረጉ የምርምር ውጤቶችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፤
- ዓረፍተ ነገሮችንና አጫጭር ጽሑፎችን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ትተረጉማላችሁ፤
- ምሳሌያዊ አነጋገር የሚገኝበትን ዐውድ በመፍጠር አጭር ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፤
- ዋቢ መጻሕፍትን ትጠቀማላችሁ፡፡

© MoE FDRE Not to be reproduced

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ርዕስ በማየት ምንባቡ ሊመልስልን ይችላል የምትሏቸውን ጥያቄዎች ዘርዝሩ፡፡ ከዚያም አንብባችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ጥያቄዎቻችሁ መልስ ማግኘት አለማግኘ ታቸውን አረጋግጡ፡፡
2. ብዙ ጊዜ እንደሚጠቀሰው አገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚገኙባት አገር በመሆኗ በርካታ ቋንቋዎችም የሚነገሩባት ናት፡፡ ለመሆኑ ምን ያህል ቋንቋዎች የሚነገሩባት ይመስላችኋል?
3. ብዙ ጊዜ ቋንቋ፣ ዘዬ ሲባል ትሰማላችሁ፤ ለመሆኑ በቋንቋና በዘዬ መካከል ልዩነት አለ ብላችሁ ታምናላችሁ? ካመናችሁ ልዩነቱን በዝርዝር ተናገሩ፡፡

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ዝምድናቸው

ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩ ቋንቋዎች ይህን ያህል ናቸው ብሎ በእርግጠኝነት ለመግለጽ አዳጋች ነው፡፡ ሆኖም ካሉት መረጃዎች በመነሳት በኢትዮጵያ ከ75-80 የሚደርሱ ቋንቋዎች ይነገራሉ ለማለት ይቻላል፡፡ ቁጥራቸውን በትክክል ለመግለጽ አዳጋች የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው፣ የቋንቋዎችን ዓይነት የሚዘረዝሩ ጽሑፎች የተጠቀሙባቸው አንዳንድ ስያሜዎች የአንድ ቋንቋ መጠሪያ ሳይሆኑ፣ በውስጣቸው የተለያዩ ቋንቋዎች የያዙ የቡድን መጠሪያ ስያሜ መሆናቸው ነው፡፡ ሁለተኛውና ዋነኛው ምክንያት ደግሞ በጣም ተቀራራቢ የሆኑ ግን በተለያየ ስያሜ የሚጠሩ የንግግር ዓይነቶች (ቋንቋዎች) ራሳቸውን የቻሉ ቋንቋዎች ወይም የአንድ ቋንቋ የተለያዩ ዘዬዎች መሆናቸው በውል በጥናት ባለመታወቁ ነው፡፡ አንዳንዶች ተቀራራቢ የሆኑ የንግግር ዓይነቶችን ራሳቸውን እንደቻሉ ቋንቋዎች ሲዘረዝሯቸው፣ አንዳንዶች ደግሞ እንደአንድ ቋንቋ ይገልጹዋቸዋል፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

በሥነልሳን ሳይንስ አንድ የንግግር ዓይነት ራሱን የቻለ ቋንቋ ወይም የአንድ "ሌላ" ቋንቋ ዘዬ መሆኑን በማያወላዳ መልኩ መናገር ይቻላል። ሁለት የተለያዩ የንግግር ዓይነት ተናጋሪዎች፣ የየራሳቸውን የንግግር ዓይነት በመጠቀም ሀሳባቸውን መለዋወጥ ከቻሉ ሁለቱ የንግግር ዓይነቶች የአንድ ቋንቋ ዘዬዎች ናቸው ይባላል። መግባባት ካልቻሉ ደግሞ፣ ሁለቱ የንግግር ዓይነቶች ሁለት ቋንቋዎች ተደርገው ይቆጠራሉ። ይህን በምሳሌ እንመልከት፤ አንድ የጎጃም ገበሬና አንድ የአዲስ አበባ ሰው የየቀያቸውን ዘዬ በመጠቀም መግባባት ይችላሉ። በእርግጥ አንዱ ከሚናገረው ውስጥ ሌላው የማያውቃቸው የተወሰኑ ቃላት ወይም አገላለጾች ሊኖሩ ይቻላሉ። እነዚህ ለአንደኛው ወገን ባዕድ የሚሆኑ አጠቃቀሞች ግን አዲስ አበቤውንም ሆነ ጎጃሜውን ፈጽሞ መግባባት እስከማይችሉበት ደረጃ የሚያደርሱ አይደሉም፤ ምክንያቱም ውሱን ናቸውና። ይህም በመሆኑ ነው ጎጃም የሚነገረው አማርኛና አዲስ አበባ የሚነገረው አማርኛ የአንድ አማርኛ ዘዬዎች ናቸው የሚባለው። በእነዚህ ሁለት የንግግር ዓይነት ተናጋሪዎች መካከል መግባባት የማይቻል ቢሆን ኖሮ፣ ሁለቱ የንግግር ዓይነቶች የተለየዩ ቋንቋዎች ተደርገው ይቆጠሩ ነበር። ለምሳሌ አንድ የአማርኛ ተናጋሪ አርጎብኛን ለመጀመሪያ ጊዜ ቢሰማ፣ የአማርኛ ዘዬ ሊመስለው ይቻላል። ምክንያቱም በነዚህ ሁለት የንግግር ዓይነቶች መካከል በርካታ መመሳሰሎች ስለሚታዩ ነው። ነገር ግን ንግግሩን በደንብ አድምጦ ለመረዳት ቢሞክር፣ እጅግ አዳጋች ይሆንበታል። ለዚህ ነው አርጎብኛ ራሱን የቻለ ቋንቋ ተደርጎ የሚቆጠረው። ከላይ ከቀረበው ነጥብ አንድ ቁም ነገር ልንገነዘብ እንችላለን። አንድ ቋንቋ በውስጡ የተለያዩ ዘዬዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ፣ እንዲሁም ዘዬ የሚያሰኛቸው በውስጣቸው የተወሰኑ ልዩነቶች መግባባትን ሙሉ በሙሉ የማያግዱ ሆነው መገኘታቸው ነው።


አንድ ሰው በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከራሱ ቋንቋ ጋር የሌሎችን ቋንቋዎች ወይም የንግግር ዓይነቶች አዳምጦ የሚመሳሰሉ መሆን አለመሆናቸውን፣ እንዲሁም የቅርበት ደረጃቸውን መናገር ይቻላል። ለምሳሌ፣ አንድ የአማርኛ ተናጋሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ትግርኛን ቢሰማ (ምንም እንኳ አንዳንድ ቃላትና አጠቃቀሞች እሱ ከሚያውቀው አማርኛ ጋር የሚመሳሰሉ መሆናቸውን መገንዘብ ቢችልም) ብዙም ጊዜ ሳይወስድ

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ትግርኛ ከአማርኛ የተለየ ቋንቋ መሆኑን መረዳት ይችላል፡፡ ባጠቃላይ አንድ የአዲስ አበባ አማርኛ ተናጋሪ በዘዬው ከጎጃም አማርኛ ልዩነት ቢኖረውም፣ ቋንቋው ግን ያው አማርኛ መሆኑን፣ አርጎብኛው እሱ ከሚያውቀው አማርኛ ቢመሳሰልም፣ የተለየ ቋንቋ መሆኑን፣ትግርኛው ደግሞ ከአማርኛው ጋር ያለው መቀራረብ ከአርጎብኛው ይልቅ የራቀ መሆኑን መግለጽ ይችላል፡፡ እንዲሁም ለምሳሌ፣ ትግርኛ ከኦሮምኛ ይልቅ፣ ኦሮምኛ ደግሞ ከእንግሊዝኛ ይልቅ ለአማርኛ የቀረቡ መሆናቸውን መናገር ይቻላል፡፡ ይህ የሚያሳየን በቋንቋዎች መካከል ዝምድና ሊኖር እንደሚችልና የዝምድና ደረጃውም ከቋንቋ ቋንቋ ሊለያይ እንደሚችል ነው፡፡

በቋንቋዎች መካከል ያለው ዝምድና እንደሰው ልጅ የዘር ሐረግ ሊታይ ይችላል፡፡ አንድ ልጅ ለወንድምና እህቱ ያለው የደም ትስስር (ዝምድና) ከአጎቱና ከአክስቱ ልጆች ይልቅ የበለጠ ነው፡፡ ለእህቱና ለወንድሙ ያለው ቅርበት በእናትና በአባት ደረጃ ሲሆን፣ ከአጎትና ከአክስቱ ልጆች ጋር ያለው ቅርበት በሁለተኛ እርከን በአያት ደረጃ ነው፡፡ እንዲሁም የቋንቋዎች ዝምድና በተለያየ እርከን ሊታይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ አርጎብኛ ለአማርኛ የወንድም ያህል፣ ትግርኛ ግን በአጎት ልጅነት ወይም ከዚያም በዘለለ ደረጃ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህን ግንዛቤ መሠረት አድርገን የሀገራችንን ቋንቋዎች ዝምድና (የዘር ሐረግ) ለማየት እንሞክራለን፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አፍሮ-እስያዊና አባይ-ሰሃራዊ ከሚባሉት ሁለት ትላልቅ ቤተሰቦች ሥር ይመደባል፡፡ ይህም ማለት በአገራችን የሚገኙት ቋንቋዎች ከነዚህ ሁለት ቀደምት አባት ቋንቋዎች የተፈጠሩ ናቸው እንደማለት ነው፡፡ አፍሮ-እስያዊ የሚባለው ትልቅ የቋንቋ ቤተሰብ ስድስት ንኡሳን ቤተሰቦች አሉት፡፡ እነዚህ ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ኦሞአዊ፣ ጥንታዊ ግብፃዊ፣ ቻዳዊና በርበር በመባል ይታወቃሉ፡፡ የእነዚህ የቋንቋ ቤተሰቦች ግንኙነት እንደሚከተለው በዛፍ ምሥል ሊቀርብ ይችላል፡፡



© MoE, FDRE, Not to be republished

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ግልጽ ማድረግ አለብን፡፡ በዛፍ ምሥሉ ላይ እንደምንመለከተው በርበር፣ ኩሻዊ፣ ኦሞአዊ ወዘተ. በሚል የተዘረዘሩት ቋንቋዎች (ወይም የቋንቋ ቤተሰቦች) ባንድ ወቅት አንድ ቋንቋ ነበሩ ማለት ነው፣ አፍሮ-እስያዊ የሚል በዛፍ ምሥሉ የተቀመጠው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ አፍሮ-እስያዊ "የሚባል" አንድ ጥንታዊ ቋንቋ በጊዜ ብዛት ወደስድስት ቋንቋዎች ተለውጧል ማለት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱን ቀደምት ቋንቋ የታሪካዊ ሥነልሳን ተመራማሪዎች አባት ቋንቋ (Proto-language) ይሉታል፡፡

በርግጥ አፍሮ-እስያዊ የሚለው ስያሜ የዚያ ጥንታዊ ቋንቋ ትክክለኛ መጠሪያ ነበር ለማለት አይደለም፡፡ ያ ቋንቋ በወቅቱ ማለትም፣ ይነገር በነበረበት ዘመን (የዛሬ አሥራ አምስት ሺህ ዓመት ገደማ) ማን ተብሎ ይጠራ እንደነበር አይታወቅም፡፡ በሁለተኛው እርከን በዛፍ ምሥሉ ላይ ኩሻዊ፣ በርበር፣ ሴማዊ ወዘተ. በሚል የቀረቡትም ቢሆን፣ በጥንት ጊዜ እንደአንድ ቋንቋ ይነገሩ ነበር ለማለት እንጂ፣ ባሁኑ ጊዜ በርካታ ቋንቋዎችን ወልደው ጠፍተዋል፡፡ ስያሜዎቹም በወቅቱ ቋንቋዎቹ ይጠሩበት የነበሩበት  አይደለም፡፡ ስለዚህ ለቋንቋዎች የወቅቱ ትክክለኛ መጠሪያ ማንነት ጊዜው ረጅም በመሆኑ ማስረጃ የለንም፡፡ ብዙውን ጊዜ የጥንታዊ አባት ቋንቋዎችን መጠሪያ ማወቅ ይከብዳል፡፡ በርግጥ የአንዳንድ የዘመናችን ቋንቋዎች ወላጅ (ምንጭ) ስለሆነው ጥንታዊ አባት ቋንቋ ስያሜ መረጃ አለን፡፡ ለምሳሌ፣ ላቲን የሚባል ጥንታዊ ቋንቋ ባሁኑ ዘመን ለሚነገሩት እንደፈረንሳይኛ፣ ጣሊያንኛ፣ ስፓንሽኛ፣ ፖርቹጋልኛ፣ እና ሩማኒያኛ ላሉት ቋንቋዎች አባት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ማለትም፣ እነዚህ ቋንቋዎች ባንድ ወቅት ላቲን የሚባል አንድ ቋንቋ ነበሩ ማለት ነው፡፡ ይህን በዚህ ትተን፣ ከላይ ወደአነሳነው አፍሮ-እስያዊ ቋንቋ እንመለስ፡፡

ከላይ በአፍሮ-እስያዊ ትልቅ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር ስድስት የሚሆኑ የቋንቋ ቤተሰቦች እንዳሉ ገልጸናል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የሴማዊ፣ የኩሻዊ እና የኦሞአዊ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ ይነገራሉ፡፡ ኦሞአዊ ቋንቋዎች በኢትዮጵያ ብቻ ሲገኙ፣ ኩሻዊ ቋንቋዎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች ይገኛሉ፡፡ አብዛኞቹ የሴማዊ ቋንቋዎች በአገራችን የሚነገሩ ሲሆን፣ ጥቂቶቹ ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅና በአንዳንድ አፍሪካ አገሮች ይነገራሉ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ከመግባታችን በፊት *ከዚህ በላይ ያነበብነውን ሃሳብ ምን ያህል ተረድተነዋል?* ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡ አስፈላጊ ከሆነም ተመልሳችሁ ጽሑፉን አንብቡና ተገቢውን ማስታወሻ ያዙ፡፡
2. ከቀረበው የምንባብ ክፍል ምን ትጠብቃላችሁ?

## ሴማዊ ቋንቋዎች

በኢትዮጵያ የሚነገሩት ሴማዊ ቋንቋዎች ሰሜን ኢትዮ-ሴማዊ እና ደቡብ ኢትዮ-ሴማዊ በሚባል በሁለት ምድቦች ይከፈላሉ፡፡ ሰሜን ኢትዮ-ሴማዊ ሦስት ቋንቋዎች አሉት፤ እነሱም ግዕዝ፣ ትግርኛና ትግረ ናቸው፡፡ ትግረ በኤርትራ የሚነገር ቋንቋ ነው፡፡ ደቡብ ኢትዮ-ሴማዊ በሁለት ምድብ በመከፈል በውስጡም በርካታ ቋንቋዎችን ይዟል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሐረሪ፣ አማርኛ፣ አርጎብኛ፣ ስልጢኛ፣ ዛይኛ፣ ሶዶ፣ ጎጎት፣ ቸሃ፣ እንደጋኝ፣ መስቃን ወዘተ. ይገኙበታል፡፡ የእነዚህ ቋንቋዎች የቅርበት ደረጃ የተለያየ በመሆኑ፣ ቋንቋዎቹ በተለያዩ እርከኖች ሊቀመጡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አማርኛና አርጎብኛ ባንድ ሲመደቡ፣ ስልጢኛ፣ ሐረሪ እና ዛይኛ በሌላ ይመደባሉ፡፡ ጎጎት፣ ሶዶና መስቃን ጉራጌ በሚል በአንድ ቡድን ሲመደቡ፣ የተቀሩት የጉራጌ ቋንቋዎች ምዕራብ ጉራጌ በሚል ይመደባሉ፡፡ በምዕራብ ጉራጌ ሥር የሚገኙ ቋንቋዎች እንደገና በንኡሳን ቡድኖች ሊፈረጁ ይችላሉ፤ ማዕከላዊ ምዕራብ ጉራጌና ዳራዊ ምዕራብ ጉራጌ በሚሉ ክፍሎች፡፡

## ኩሻዊ ቋንቋዎች

ኩሻዊ የቋንቋ ቤተሰብ በሰሜን ኩሻዊ፣ በማዕከላዊ ኩሽ፣ በምሥራቅ ኩሻዊና በደቡብ ኩሻዊ ወገን ይከፈላል፡፡ ከነዚህ አራት ንኡሳን ቤተሰቦች፣ በኢትዮጵያ የሚነገሩት ቋንቋዎች በማዕከላዊና በምሥራቅ ኩሻዊ ንኡስ ቤተሰቦች ተካትተው ይገኛሉ፡፡ ማዕከላዊ የኩሽ ቤተሰብ በአገውኛ ቋንቋዎች ሲወከል፣ በሥሩም ህምጥኛ፣ ቅማንትኛና አውንግኛ ቋንቋዎችን ይዟል፡፡ የምሥራቅ ኩሻዊ ወገንም፣ በደጋና በቆላ ከተከፈለ

በኋላ የደጋው ክፍል ቡርጂኛ፣ ጌዲዮኛ፣ ሲዳምኛ፣ ከምባትኛና ሀድይኛ ቋንቋዎችን ያካትታል፡፡ የቆላው ወገን ደግሞ በሦስት ቤተሰቦች ይከፈላል፡፡ አንደኛው ቤተሰብ አፋር-ሳሆኣዊ ሲሆን፣ አፋርኛንና ሳሆኛን ቋንቋዎችንም ያቅፋል፡፡ በሁለተኛው ቤተሰብ ውስጥም ኦሮምኛ፣ ቡሳኛ፣ ባራሬትኛ፣ ጊዶልኛ፣ ኮንሶኛ፣ ኤርቦሬኛ፣ ዳሰነችኛ፣ ገዋድኛ፣ ጎበዝኛ፣ ፃማይኛ፣ ዋሪዝኛ ይገኛሉ፡፡ በሦስተኛው ቤተሰብም ሶማልኛና ባሮሶኛ ይጠቃለላሉ፡፡ እንደኦሮምኛ፣ ሶማልኛ እና አፋርኛ ያሉ ቋንቋዎች ከአገራችን ውጭም በአጎራባች ሀገሮች የሚነገሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ኦሮምኛ ከአገራችን ውጪ በሰሜን ኬንያ፣ አፋርኛ በጅቡቲና በኤርትራ፣ ሶማልኛ በጅቡቲ፣ በሶማሊያና በኬንያ ይነገራሉ፡፡

## ኦሞኣዊ ቋንቋዎች

ኦሞኣዊ የቋንቋ ቤተሰብ፣ አንፊሎ፣ ወላይትኛ፣ ጋሞኛ፣ ሀመርኛ፤ ዲሜ፣ ማሌ፣ ኮሬ ዘይሴ፣ ጋንጁሌ፣ ዲዚ፣ ሼኮ፣ ከፊቾ፣ ናይ፣ ባስኬቶ፣ ኦይዳ፣ ወዘተ. ቋንቋዎች አቅፎ የያዘ ነው፡፡ ወላይታ፣ ኩሎ፣ ኮንታና ጋሞ በጣም ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ለመስጠት ግን ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን የንግግር ዓይነቶች ዘዬዎችም ያልናቸው ቋንቋዎች፣ በርካታውን የኦሞኣዊ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች የሚወክሉ ናቸው፡፡ እንደአንፊሎ ዓይነቶቹ ደግሞ ከመቶ ያነሰ ተናጋሪ ያላቸው በመሆናቸው በመጥፋት ላይ የሚገኙ ቋንቋዎች ይባላሉ፡፡

## ዓባይ-ሰሃራዊ ቋንቋዎች

ዓባይ-ሰሃራዊ የሚባለው ትልቅ የቋንቋ ቤተሰብ፣ ኮሞኣዊ፣ ዓባያዊ፣ ሱርማዊ፣ ወዘተ. የሚባሉ ንኡሳን ቤተሰቦች አሉት፡፡ በዚህ ትልቅ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር ኩናምኛ፣ አኙዋክኛ፣ ኑዌርኛ፣ ኮሞኛ፣ መሰንጎኛ፣ ኦፖኛ፣ ጉሙዝኛ፣ ሻቦኛ፣ በርታኛ ወዘተ. የሚባሉ ቋንቋዎች አሉ፡፡ በሀገራችን የዚህ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች ብዛት ከሌሎቹ ሦስት የቋንቋ ቤተሰቦች በጣም ያነሰ ነው፡፡ የኩሽ እና የሴም ተናጋሪዎች አብዛኛውን የሀገራችንን ህዝብ ቁጥር ሲይዙ፣ የኦሞአዊ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች ብዛት በሦስተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be reproduced

እላይ ከገለጽናቸው የቋንቋ ቤተሰቦች ውጪ ምድቡ ያልታወቀ ቋንቋ በአገራችን አለ፡፡ እሱም በራይሴ ወይም ኦኖጎታ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ቋንቋ በደቡብ ክልል የሚገኝ ሲሆን፣ ባሁኑ ጊዜ ያሉት ተናጋሪዎች ከአሥር አይበልጡም፡፡ በመሆኑም ኦኖጎታ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ የሚሞት ማለትም ጨርሶ የሚጠፋ ቋንቋ ነው፡፡ ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፈው የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ ነው፡፡ የምልክት ቋንቋ እንደማንኛውም ቋንቋ የራሱ የሆነ ውስጣዊ ሥርዓት፣ ማለትም ሰዋስው አለው፡፡ የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ ሰዋስው በወጉ የተጠና ባለመሆኑ ከሌሎች ያገራችን ቋንቋዎች ጋር ያለው ዝምድና በውል አይታወቅም፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የቃኘናቸው ቋንቋዎች በሰው ልጆች መካከል ካለው ዝምድና አንጻር ሊታይ የሚችል ዝምድና እንዳላቸውና ከዚህም አንጻር የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አፍሮ-እስያዊና ዓባይ-ሰሃራዊ ከሚባሉ ሁለት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰቦች ሥር የሚመደቡ መሆናቸውን እናጤናለን፡፡

*(ከቀድሞው የ12ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**፩.ምንባቡን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. በአገራችን የሚነገሩት ቋንቋዎች በስንት ዐበይት የቋንቋ ቤተሰቦች ሊመደቡ ይችላሉ?
2. በኢትዮጵያ ብቻ የሚነገረው የቋንቋ ቤተሰብ የትኛው ነው?
3. በኢትዮጵያ የሱዳን ጠረፍ አካባቢ የሚነገረው የቋንቋ ቤተሰብ የትኛው ነው?
4. ኦሮምኛ በየትኛው የቋንቋ ቤተሰብ ሥር የሚመደብ ቋንቋ ነው?
5. በአገራችን የሚነገሩ ቋንቋዎች በሙሉ ተለይተው ታውቀዋልን? መልሳችሁ አሉታዊ ከሆነ ለምን ይመስላችኋል?



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፪. በምንባቡ መሠረት ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጧቸው አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን ምረጡ።

1. ከአፍሮ-እስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ መካከል ስንቶቹ የቋንቋ ቤተሰቦች በኢትዮጵያ ውስጥ ይነገራሉ?
   ሀ) አምስት ለ) አራት መ) ሦስት ሠ) ስድስት
2. ከሚከተሉት የተለየ ሀሳብ የያዘው የቱ ነው?
   ሀ) ቋንቋ በጊዜና በቦታ ለውጥ ሊታይበት ይችላል፡
   ለ) በቋንቋ ጥናት እሀትማማች ቋንቋዎች እንዳሉ ሁሉ እናት ቋንቋም ይኖራል።
   መ) የቋንቋ ዝምድና በአንድ ቃልም ቢሆን ይታወቃል።
   ሠ) የሰዋስው መረጃ የቋንቋ ዝምድናን ለማወቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።
3. ከሚከተሉት ቋንቋዎች ለስልጢኛ ቋንቋ በቋንቋ ቤተሰብነት የሚመሳሰለው የቱ ነው?
   ሀ) የምኛ መ) ሐረሪኛ
   ለ) ኮንሶኛ ሠ) ከምባትኛ
4. የተወሰኑ --------- ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ ውጪ ይነገሩ እንጂ፣ የዚህ ቋንቋ ቤተሰብ አብዛኞቹ ተናጋሪዎች ኢትዮጵያውያን ናቸው።
   ሀ) የኦሞአዊ መ) የዓባይ ሰሃራዊ
   ለ) የሴም ሠ) የኩሽ
5. ከሚከተሉት ቋንቋዎች በኦሞኣዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ የማይገኘው የቱ ነው?
   ሀ) ሀመርኛ መ) ጋንጁሌ
   ለ) ጉሙዝኛ ሠ) ዘይሴኛ
6. ለኦሞኣዊ የቋንቋ ቤተሰብ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?
   ሀ) ሼኮኛ መ) ኩናምኛ
   ለ) አኝዋክኛ ሠ) ሻቦኛ

7. ከሚከተሉት ውስጥ በዓባይ ሰሃራዊ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር የሚመደበው የቱ ነው?
   - ሀ) መሰንጎኛ
   - ለ) ጋሞኛ
   - መ) ወላይትኛ
   - ሠ) ባስኬቶ
8. ከሚከተሉት አንዱ በኩሽ ቋንቋ ቤተሰብ ሥር ያለ ቋንቋ ነው።
   - ሀ) ኩናምኛ
   - ለ) ዘይሴኛ
   - መ) ጌዲዮኛ
   - ሠ) አርጎብኛ
9. ከሚከተሉት መካከል በአንድ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደቡት የትኞቹ ናቸው?
   - ሀ) ወላይትኛ፣ ሐመርኛ፣ አኝዋክኛ
   - ለ) አውንግኛ፣ ህምጥኛ፣ ቅማንትኛ
   - መ) ጋሞኛ፣ ኮንሶኛ፣ ኑዌርኛ
   - ሠ) ሶማልኛ፣ አፋርኛ አርጎብኛ

፫. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ፍች ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ከጻፋችሁ በኋላ በምንባቡ ውስጥ በሚሰጡት ፍች መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

| | |
|---|---|
| 1. አዳጋች | 6. ተሰኘ |
| 2. ስያሜ | 7. ይልቅ |
| 3. የማያወላዳ | 8. ሴም |
| 4. አቀፈ | 9. ኩሽ |
| 5. ይቆጠራሉ | 10. ዘዬ |

፬. ከላይ የቀረቡትን ቃላት ተጨማሪ ፍች ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ በምንባቡ ውስጥ ካላቸው ፍች ጋር በማነፃፀር ከምንባቡ ውጪ ባላቸው ፍች መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. በዘዬና በቋንቋ መካከል ምን አንድነትና ልዩነት እንዳለ ከመጽሐፍ ፈልጋችሁ ወይም ባለሙያ አነጋግራችሁ የምታገኙትን ሀሳብ መሠረት በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

© MoE, FDRE
Not to be republished

© MoE, FDR
Not to be rep

፪. ከአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ ጋር ይመሳሰላሉ የምትሏቸውን ሶስት የተለያዩ ቋንቋዎችን ወስዳችሁ የተመሳሰሉበትን ምክንያት በማስረጃ አስደግፋችሁ ጻፉ::

፫. በዚህ ምንባብ ውስጥ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች ውጪ የሆኑና ለኦሞአዊና ለዓባይ ሰሃራዊ የቋንቋ ቤተሰቦች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ቋንቋዎችን ከመጽሐፍ ፈልጋችሁ ወይም ባለሙያ አነጋግራችሁ ከዘረዘራችሁ በኋላ ስለቋንቋዎቹ አጭር መግለጫ በጽሑፍ አቅርቡ::

፬. ቋንቋዎች የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ጉዳዮች ባለሙያ በመጠየቅ ወይም መጽሐፍ በማንበብ ከሁለት አንቀጽ ያልበለጠ ጽሐፍ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ:: በጽሑፋችሁ ውስጥ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን መጠቀም አትርሱ::

፭. ያነባባችሁትን ምንባብ ዋና ዋና ሀሳቦች በአስተዋጽዖ መልክ በመዘርዘር አሳዩ::

፮. የሚከተሉትን በትዕዛዛቸው መሠረት ተርጉሙ::

ሀ. የሚከተሉትን የእንግሊዝኛ ዓረፍተነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉሙና ለመምህራችሁ አቅርቡ::

1. The focus of the conference was the implementation of the country’s transformation plan.
2. The following is the list of historical studies.
3. A very great deal of progress has been made in the last five years.

ለ. የሚከተሉትን የአማርኛ ዓረፍተነገሮች ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሙና ለመምህራችሁ አቅርቡ::

1. የድርሰት ዓላማ ከአንባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው::
2. አንድ ጸሐፊ ለማን እንደሚጽፍ ያውቃል::
3. በጥቅሉ አንባቢዎች ደራሲ ተኮርና አንባቢ ተኮር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ::

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ከመቅረጸ ድምፅ የሚያሰሟችሁን ንግግር ካዳመጣችሁ በኋላ ከያዛችሁት ማስታወሻ በመነሳት ስላዳመጣችሁት ጉዳይ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

፪. መምህራችሁ በመቅረጸ ድምፅ የተቀረጹ ቋንቋ ነክ ውይይቶችን በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የዞን ወይም የወረዳ የኮሙኒኬሽን ጽሕፈት ቤቶች ፈልገው ያቀርቡላችኋል:: ውይይቶቹን አዳምጣችሁ ከውይይቶቹ ያገኛችኋቸውን ፍሬ ነገሮች ለተመደባችሁበት ቡድን አቅርባችሁ ተወያዩበት::

፫. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ውስጥ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል:: ጽሑፉን በጽሞና አዳምጡ፤ አስፈላጊ ማስታወሻም ያዙ:: ከዚያም የሚከተሉትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሠረት መልሱ::

### ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ::

1. ቋንቋ መግባቢያ ነው የሚለው አገላለጽ ለቋንቋ በቂ ፍች የማይሆነው ለምንድን ነው?
2. ስለቋንቋ ምንነት በተመራማሪዎች መካከል አንድ ወጥ ስምምነት የሌለው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?
3. “ማንነታችንን እንደግለሰብም ሆነ እንደኅብረተሰብ አባል የምናገኘው” ሲል ምን ማለቱ ነው? መቼስ ነው የሚገኘው?
4. ቋንቋ ለምንድን ነው በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድረው?
5. “ኅብረተሰቡ የተቀበለውና የሚገዛበት” ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. “ቋንቋ ረቂቅ ዕውቀት ግን ደግሞ ተጨባጭ ባህሪም ነው” የሚለው የሚያመለክተው ምንን ነው?
7. “ሀሳብ በዓረፍተነገር ይገለጻል” ሲል በሌላ መንገድ ሀሳብ አይገለጽም ማለቱ ነው?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ለ) "ቋንቋ ምንድን ነው?" ከሚለው ምንባብ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ፍሬ ነገር ከያዛችሁት ማስታወሻ በማጠናቀር አንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

፬. ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች የተደረጉ ምርምሮችን ውጤቶች ከመገናኛ ብዙኃን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቡን በማስታወሻ ያዙና ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

## ክፍለ አራት፡- መናገር

፩. ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በማሰባሰብ የኢትዮ-ሴማዊና የኢትዮ-ኩሻዊ ቋንቋዎችን የተናጋሪ ብዛትና ስርጭት በሠንጠረዥ፣ በግራፍ ወይም በሌላ መንገድ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ፡፡

፪. «በአጠቃላይ በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉትን ቋንቋዎች ቁጥር ለመናገር አይቻልም፡፡» በሁለት ቡድን ተመዳድባችሁ ይህን ሀሳብ በመደገፍም ሆነ በመቃወም አጭር ንግግር አድርጉ፡፡

፫. «ዘዬ መቅረት ያለበት ጉዳይ ነው?» ስለዚህ ጉዳይ ካነበባችሁ በኋላ በቡድን ተወያዩበት፡፡

፬. የምታውቋቸውን የአገራችንን ቋንቋዎች በሙሉ ዘርዝሩና በዋና ዋና የቋንቋ ቤተሰቦች መድባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፭. «የኢትዮጵያ ቋንቋዎች» በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብና ከሌሎች ምንጮች ያገኛችኋቸውን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ መልክ ጻፉና በይዘቱ ላይ ንግግር አድርጉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሥነ ልሣን

በዚህ ክፍል የተለያዩ ሰዋስዋዊ መግለጫዎች ይቀርባሉ፡፡ መግለጫዎቹን በጽሞና አንብባችሁ ከየመግለጫዎቹ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሥሩ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍ

ከዚህ በፊት እንደተማራችሁት በመደበኛው አፃፃፍና በድምፀ ልሣናዊ አፃፃፍ መካከል ግልጽ ልዩነት አለ፡፡ መደበኛው አጻጻፍ በማንኛውም ጽሕፈት ውስጥ በምንጠቀምባቸው መደበኛ ፊደሎች የመጻፍ ሂደት ነው፤ ድምፀ ልሣናዊው ግን ለዚሁ ሲባል ከፊደሎቻችን ውስጥ በተመረጡ ፊደሎች ተናባቢውንና አናባቢውን በመለያየት ወይም በመነጣጠል የመጻፍ ሂደት ነው፡፡ ለድምፀ ልሳናዊው አጻጻፍ የተመረጡት ፊደሎች በፊደል ገበታ ላይ የሚገኘው ስድስተኛ ምድብ (ሳድስ ተብሎ የሚታወቀው) እና አናባቢዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም አጻጻፉ በእነዚህ ፊደሎች ተጽፈው የምናገኛቸውን ቃላት ወይም ሐረጋት በሚነገሩበት አኳኋን ያላቸውን ንበት ያሳያል፡፡

ለምሳሌ፣ ሀ. ***አበበ*** በድምፀ ልሳናዊ አጻጻፍ ሲጻፍ /አብብኧቦኧ/ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የሚከተሉትን እንመልከት፤

ለ. ***ለመነ*** /ልኧምኧንኧ/

ሐ. ***ክብረመንግስት*** /ክእብርኧምኧንግእስት/

ከላይ ባየናቸው ቃላት ውስጥ በፊደላቸው ብዛት አኳያ እንደቅደም ተከተላቸው ባለሶስት፣ ባለሶስት እና ባለስምንት ፊደላት ናቸው፡፡ ይሁንና ከድምፀ ልሳናቸው አኳያ ግን የመጀመሪያው ሁለት ተናባቢና ሶስት አናባቢ፣ ሁለተኛው ሶስት ተናባቢ እና ሶስት አናባቢ እንዲሁም ሶስተኛው ደግሞ ስምንት ተናባቢና አራት አናባቢ ይዟል፡፡ ስለዚህ በነዚህ ምሳሌዎች በሁለቱ አጻጻፎች መካከል ልዩነት መኖሩን መረዳት ይቻላል፡፡

© MoE, FDRE
Not to be rep

፩. የሚከተሉትን ቃላት በድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍ ጽፋችሁ በውስጣቸው ያሉትን ተናባቢዎችና አናባቢዎች ለይታችሁ በሠንጠረዡ አሳዩ::

| ተ.ቁ. | ቃል | ድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍ | የድምፀ ልሣናት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ወሰደ | | |
| 2 | አስተማረ | | |
| 3 | ተመራመረ | | |
| 4 | አለመ | | |
| 5 | መኮንን | | |
| 6 | ወቀረ | | |
| 7 | ሰረቀ | | |
| 8 | መክብብ | | |
| 9 | ደረበ | | |
| 10 | ደብተር | | |

፪. የሚከተሉትን ቃላት በመደበኛ አጻጻፍ ጻፉ::

1. /አግግኧድኧ/ ----------------------
2. /ውእርድኧት/ ----------------------
3. /ድእርስኣን/ ------------------------
4. /ዕኣይእን/ ---------------------------
5. / ግኧብርኧክኢ.ድኣን/ -----------------

፫. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ስንት የተለያዩ ተናባቢና አናባቢ ድምፀ ልሣኖች እንዳሉ አመልክቱ::

| | ተናባቢ | አናባቢ |
|---|---|---|
| 1. ወርቃፈራሁ | -------- | -------- |
| 2. አንዷለም | -------- | -------- |

| | | |
|---|---|---|
| 3. ምንዛሪ | -------- | -------- |
| 4. ሞገተ | -------- | -------- |
| 5. ሰረጎደ | -------- | -------- |

፬. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የተጓደሉትን ድምፀ ልሣኖች አሚልታችሁ ትርጉም ያላቸው ቃላት መሥርቱ:: (አንዱ ቅርጽ ከአንድ በላይ ቃላትም ሊመሠረትበት ይችላል::) ምሳሌ:- ምኧ - ኧ - -እር = መነፅር

1. /ው - - ርኧድ - / ------------------------------------
2. /ግኧ - - ኧስኧ/ ----------------------------------------
3. /ምኧ - ኧ - - ኧርኧ/ -------------------------------------
4. / - ኧምም - ርኧ/ ------ ------------------------------------
5. /- እድ - ኣስኤ/------------------------------------------

## ቀለማዊ አጻጻፍ

ቀለም ማለት በአናባቢዎች ወይም በአናባቢዎችና በተናባቢዎች ቅንጅት የሚመሠረት መዋቅር ነው:: በአጭሩ ለቀለም መዋቅር የአናባቢው ወይም የቀለም መስራቹ ድምፅ (ቀለማዊው ድምፅ) መኖር አስፈላጊ ነው:: ለምሳሌ ቡና እና ልጅ የሚሉትን ቃላት እንውሰድ:: በቃላቱ ውስጥ ያሉትን ቀለሞች ለመረዳት በቅድሚያ ቃላቱን በድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍ መፃፍ ያስፈልጋል:: ከዚያም በቃላቱ ውስጥ ባሉት አናባቢዎች ላይ ተመስርተን በቅድሚያ በስተግራ በኩል ተናባቢ መኖር አለመኖሩን እንመለከታለን፤ ካለ የቀለሙ አካል አድርገን እንወሰድዋለን፤ ከሌለ ወደቀኝ ተናባቢ ወይም ተናባቢዎች መኖራቸውን እንመለከታለን:: እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚያሻው፣ በስተቀኝ በኩል ካሉ ሊኖሩ የሚችሉት ተናባቢዎች በቋንቋው ሥርዓት መሠረት ሁለት ብቻ ነው:: ከዚያ በላይ ያሉት የሚቆጠሩት ወደሌላ

© MoE, FDR
Not to be rep

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ቀለም ነው። በዚህ ዓይነት ምሳሌዎቻችንን ከላይ በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሠረት እንመርምራቸው፤

ሀ. ቡና /ብኡንንኣ/

ለ. ልጅ /ልእጅ/

በነዚህ ቃላት ውስጥ ያሉትን ቀለሞች ለመለየት አናባቢዎቹን እንደመነሻ ወስደን በመጀመሪያ ወደግራ ቀጥሎ ደግሞ ወደ ቀኝ ሄደን ተናባቢዎች መኖር አለመኖራቸውን እናረጋግጣለን። በዚህ መሠረት በምሳሌዎቻችን ውስጥ ያሉት ቀለሞች የሚከተሉት ሆነው እናገኛቸዋለን።

ሀ. ቡና /ብኡን - ንኣ/ ሁለት ቀለሞች አሉት።

ለ. ልጅ /ልእጅ/ አንድ ቀለም አለው።

በዚህ መሠረት፣ አንድ ቃል ባለአንድ ቀለም ወይም ባለ ብዙ ቀለም ሊሆን ይችላል ማለት ነው። ቃሉ ባለ አንድ ቀለም ሲሆን ቀለሙ አንድ ሙሉ ቃል (ፍቺ ያለው ቃል) ሊሆን ሲችል፣ ቃሉ ባለብዙ ቀለም (ከአንድ በላይ ማለት ነው) ሲሆን ደግሞ ቀለሞቹ የአንድ ቃል ክፍልፋይ ይሆናሉ። በምሳሌዎቻችን መሠረት *ቡና* ባለሁለት ቀለም ሲሆን፣ **ልጅ** ደግሞ ባለአንድ ቀለም ነው ማለት ነው። በአጠቃላይ ለቀለም መኖር የአናባቢው መኖር ወሳኝ ነው። እንዲህ ዓይነቱን አወቃቀር ቀለም፣ አጻጻፉንም ቀለማዊ አጻጻፍ እንለዋለን።

**፫. ከላይ የቀረበውን መግለጫ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ቃላት የቀለም መዋቅር አመልክቱ። ያላቸውንም የቀለሞች መጠን አሳዩ።**

| | |
|---|---|
| 1. አለሙ | 6. ደብተር |
| 2. በቀለ | 7. ባትሪ |
| 3. ብር | 8. ሳር |
| 4. ሻይ | 9. ሴት |
| 5. ጠረጴዛ | 10. ድርሳን |

© MoE, FD
Not to be repr

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቤተሰቦችና ንኡሳን ቤተሰቦች ተምራችኋል፡፡ በሥነ ልሣንም ረገድ ድምፀ ልሣናዊ አፃፃፍን ተረድታችሁ በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይታችሁ የመጻፍ መሠረታዊ ችሎታ ጨብጣችኋል፡፡ የአማርኛንም የቀለም መዋቅር መሠረታዊ አወቃቀር ተረድታችሁ በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይታችሁ ማመልከትና በደረጃችሁ መተንተን ችላችኋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መዝገበ ቃላትንና አውድን በመጠቀም የቃላትን ፍች መስጠትንና ከተለያዩ መገኛኛ ብዙኃን የተላለፉ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ የተደረጉ ምርምሮችን ውጤቶች አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝን በተግባር ተለማምዳችኋል፡፡ ቀደም ሲል የተማራችሁትን የምሳሌያዊ አነጋገሮችን አጠቃቀም በማስታወስና በማጠናከር በንግግርና በጽሑፍ ተጠቅማችኋል፡፡ በመጨረሻም ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ በተለይም ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ እና ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ የመተርጎምን መሠረታዊ ዕውቀት አግኝታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በአፍሪካ ከሚነገሩት የቋንቋ ቤተሰቦች ምን ያህሉ በአገራችን ይነገራሉ?
2. በአገራችን የሚነገሩት ዐበይት የቋንቋ ቤተሰቦች ምን ምን ናቸው?
3. ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ምን ምን ተብለው ይከፈላሉ?
4. ቀለማዊ አጻጻፍ ከመደበኛው አፃፃፍ በምን ይለያል?
5. ከአፈጣጠር አኳያ ተናባቢ ድምፆች ከአናባቢዎች በምን ይለያሉ?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ሀ. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ቤተሰቦችና ንኡሳን ቤተሰቦች እናገራለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይቼ እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 3 | በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይቼ አመለክታለሁ፡፡ | | | |
| 4 | መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የቃላትን ፍች መስጠት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ከመገናኛ ብዙኃን በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ የተደረጉ ምርምሮችን ውጤቶች አዳምጬ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6 | በእንግሊዝኛ የተጻፉ ዓረፍተ ነገሮችን ወደአማርኛ እንዲሁም የአማርኛ ዓረፍተ ነገሮችን ወደእንግሊዝኛ መተርጎም ችያለሁ፡፡ | | | |

ለ. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

# ምዕራፍ ሁለት

# የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ትገልጻላችሁ፤
- የድምፀልሳናዊ አጻጻፍን ስልት ተረድታችሁ በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይታችሁ ትጽፋላችሁ፤
- የአማርኛን የቀለም መዋቅር ተረድታችሁ በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ፤
- ከስርወቃል ስሞችንና ቅጽሎችን ትመሠርታላችሁ፤
- በመዝገበ ቃላት በመታገዝ የቃላትን ቀጥተኛ ፍቺ ትገልጻላችሁ፤
- ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ትይዛላችሁ፤
- ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት የተጻፉ ጽሑፎችን አንብባችሁ ጠቃሚ ሀሳቦችን ትወስዳላችሁ፤
- የድርሰት አጻጻፍ ሥርዓትን ተከትላችሁ ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- የዓረፍተነገር ዓይነቶችንና ስልቶችን ተረድታችሁ የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ትመሠርታላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የአንድ ቋንቋ ዕድገት ከምን ከምን ጋር የሚገናኝ ይመስላችኋል?
2. አማርኛ ከየትኛው የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል?
3. በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት መሠረት የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ የትኛው ቋንቋ ነው? የሥራ ቋንቋ ስንልስ ምን ማለታችን ነው?
4. በርካታ ተናጋሪዎች ያሏቸው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የትኞቹ ናቸው?
5. "የአማርኛ አጀማመርና ዕድገት" በሚለው ምንባብ ምን ምን ጉዳዮች የሚነሱ ይመስላችኋል?

## የአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና እድገት

የሀገራችንን ቋንቋዎች ከሌሎች ቋንቋዎች በጥቅሉ የሚለዩዋቸው በርካታ ሥነልሳናዊ ባህርያት ሲኖሩ፣ ከነዚህም ባህርያት ውስጥ አብዛኞቹ የሚገኙት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በድምጽ ደረጃ ብናይ፣ እንደ ትግርኛ ባሉ የሴም ቋንቋዎች ውስጥ ከሚገኙት አራት የጉሮሮ ድምጾችና እንደኦሮምኛ ባሉ የኩሽ ቋንቋዎች ውስጥ ከሚገኘው አንድ የድድ ድምጽ በስተቀር ሌሎችን ባህርያት በሙሉ የያዘ ቋንቋ ነው፡፡ በሰዋስው ደረጃም ያለው ሁኔታ ተመሣሣይ ነው፡፡ እንደ ትግርኛ ባሉ ቋንቋዎች ውስጥ ከሚገኘውና "በግዒ" ብሎ "ዓባግዕ" ከሚለው ዓይነት የአብዢ ቁጥር ሥርዓት በስተቀር ሌሎቹን ባህርያት በሙሉ ያካተተ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቋንቋ ይልቅ፣ ከአማርኛ ቋንቋ ሥነልሳናዊ ቅርጽና ይዘት በመነሳት ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች አጠቃላይ ባህሪ ከሞላ ጎደል መናገር ይቻላል፡፡ ይህም ማለት፣ ስለሀገራችን ቋንቋዎች ሥነልሳናዊ ባህርያት፣ አማርኛ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቋንቋ የተሻለ መረጃ ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ለዚህ ታሪካዊ ምክንያት አለው፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

ታሪኩ ከቋንቋው ውልደትና እድገት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ውልደቱ እና እድገቱ ደግሞ፣ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው። ታሪካችን ባመዛኙ የወረራና የፍልሰት ታሪክ ነው ሲባል ይችላል። በድርቅና በቸነፈር ምክንያት ትውልድ አካባቢውን እየለቀቀ ወደተሻለ አካባቢ በመሄድና በዚያው በመኖር ህዝብ ከህዝብ ሲቀላቀል፣ ሲወልድና ሲዋለድ ኖሯል። ደጋው ሲራብ ቆላ ወርዶ፣ ቆላው ሲራብ ወይም በወባ ሲጠቃ ደጋ ወጥቶ ክፉ ቀን ማሳለፍና መመለስ፣ አልያም በዚያው ለምዶ መቅረት የተለመደ ነው። ለግዳይና ላደን አገር አቋርጦ፣ መልካ ተሻግሮ መሄድና በለስ እስከቀና ድረስ በሄዱበት መቆየት፣ ካልቀናም በዚያው ለምዶ መቅረት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረ ባህል ነው። እንደዚህ ያለው የህዝብ እንቅስቃሴ ተራክቦ አንዱ የታሪካችን ፈርጅ ነው።

ሌላው ፈርጅ፣ ፖለቲካዊ ቅርጽና ይዘት ያለው ነው። ይህም ከግዛትና ከእምነት ማስፋፋት ጋር የተያያዘ ሰፊ እንቅስቃሴ ነው። በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት፣ በሰላም ሳይሆን በሀይል የሚፈጸም ተግባር ነው። በዚህ ረገድ፣ መጀመሪያ ከሰሜን ወደ መሀል አገር በሴማውያን፣ በኋላም ከደቡብ ወደ ሰሜን በካማውያን (በኩሻውያን)፣ በመጨረሻም አንድ ጠንካራ ማእከላዊ መንግስት ለመፍጠር ሲባል፣ ከመሀል ሀገር ወደ ደቡብ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ጎላ ጎላ ብለው የሚጠቀሱት ናቸው።

ሰሜናውያን የሴም ወገኖች ግዛታቸውን እያስፋፉ ወደ መሀል ሀገር የመጡት፣ ልዩ ልዩ የካም (የኩሽ)፣ የኦሞና የዓባያዊ ቋንቋ በሚናገር ዘማችና ከግእዝ በመጠኑ ለየት የሚል የሴም ቋንቋ ይናገሩ በነበሩ አዝማቾች አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል። የተለያየ ቋንቋ ይናገር የነበረው ሠራዊት ቀስ በቀስ ያዝማቾቹን ሴማዊ ቋንቋ መለማመድ ይጀምራል። አጀማመሩም ቋንቋውን እንዳለ በመማር ሳይሆን፣ ከራሱ ቋንቋ ጋር እያዋሃደ፣ ማለትም እያዳቀለ በመናገር ነው። ዛሬ ታይፕ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ወስደን ተየበ፣ ተያቢ፣ ትይብ፣ ትየባ፣

ወዘተ. እያልን አማርኛ እንደምናስመስለው ሁሉ፣ ሴማውያኑ የሚናገሯቸውን ቃላትም ሰራዊቱ በዚሁ ዓይነት ከራሱ ቋንቋ ጋር እያመሳሰለና እያዳቀለ ይናገራቸው ነበር።

ይህ በቃላት ደረጃ ሲሆን፣ በመዋቅር ደረጃ ደግሞ በግስ ይጀምር የነበረውን ያዝማቾቹን ቋንቋ፣ የራሱ ቋንቋ በማስመሰል በግስ እንዲጨርስ ያደርገው ጀመር። በዚህም ምክንያት ዛሬ አማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹም ኢትዮሴማዊ ቋንቋዎች (ከግእዝ በስተቀር) እንደአረብኛ እና እንደእብራይስጥ ካሉ በግስ ከሚጀምሩ ሌሎች የሴም ቋንቋዎች ሊለዩ ችለዋል። የቃላት ቅርጹና የመዋቅሩ ስርዓት በዚህ አይነት ቀስ በቀስ እየተለወጠ የመጣው የዘማቾቹ ቋንቋ፣ ከጊዜ ብዛት ሴማዊ ባህሪውን እየተወ፣ በዚያው ልክም የኩሽና የኦሞ ቋንቋዎችን (ኩሾ-ኦሞአዊ) እየመሰለ ይመጣል። ወደአራተኛውና አምስተኛው ክፍለዘመን አካባቢም ባብዛኛው መልኩ ከጥንቱ የሴም ቋንቋ የተለየ ይሆንና ይነገርበት ከነበረው ያካባቢ ስም በመነሳት አማርኛ ተብሎ መጠራት ይጀምራል።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ያነበባችሁትን ምን ያህል ተገንዝባችኋል?
2. አንድ ቋንቋ ለምንድን ነው ባሕሪውን እየለወጠ ወይም እየተወ ሊመጣ የሚችለው?

አማርኛ የተለያዩ ቋንቋዎችን ይናገር በነበረ ዘማችና አዝማች የተፈጠረ የሠራዊት ቋንቋ ነበር ለማለት ይቻላል። መሠረታዊ መድበለ ቃላቱ ባብዛኛው ሴማዊ ሲሆኑ፣ በመጠኑ ደግሞ ኩሻዊ ናቸው። ለዚህ እንደውሻ፣ ካራ፣ ውሃ፣ ሸኮና፣ አኮሌ፣ አሬራ፣ ኮርቻ፣ ቀብድ፣ ፈረስ፣ ዱላ፣ ወዘተ. ያሉት ቃላት እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ በሙሉ ኩሻዊ ናቸው። እንደብርሌ፣ አረቄ፣ ጳጳስ፣ ዲያቆን፣ ዲያብሎስ፣ ወዘተ. ያሉት ደግሞ በሀይማኖት ሳቢያ የመጡ የግሪክ ቃላት ናቸው። እንደነዚህ ባሉ ቃላት ተጋቦት ምክንያት፣ ዛሬ ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች



© MoE, FDRE Not to be republished

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be reproduced

የሚለዩትን እንደ [ሽ፣ ች፣ ጭ] ያሉትን የላንቃና እንደ [ጽ ና ፕ] ያሉትን የከናፍር ድምጾች ሲይዝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በጥንቱ የሴም ቋንቋ ውስጥ የነበሩትንና ዛሬም ቢሆን እንደትግርኛ ባሉ ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኙትን እንደ [ሐ] እና [ዕ] ያሉትን የጉሮሮ ድምጾች ሊያጣ ችሏል፡፡ (ድምጾቹ በአማርኛ ውስጥ ባይኖሩም ፊደላቱ ግን ዛሬ እንዳሉ ልብ ይሏል፡፡)

ቃላቱ ባብዛኛው ሴማዊ የመሆናቸውን ያህል፣ ሰዋስዋዊ ስርዓቱ ደግሞ ኩሾ-ኦሞአዊ ሊሆን ችሏል፡፡ የብዙዎቹ ቅጣይ ምዕላዶች ቅርጽና ሐረግ አወቃቀሩ ስርዓት ከሴም ቋንቋዎች ይልቅ፣ እንደኦሮምኛ ላሉ የኩሽና እንደወላይትኛ ላሉ የኦሞአዊ ቋንቋዎች የሚቀርብ ነው፡፡ ለዚህ እንደ ቀበ-ኛ እና ጢነ-ኛ ያሉትን የኦሮምኛ ቃላትና በነዚሁ አምሳያ /-ኧኛ/ የሚለውን ምዕላድ እየጨመሩ የተፈጠሩትን እንደኃይለኛ፣ ጥፋተኛ ወዘተ. ያሉትን ቃላት እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ዓይነት የቃላት አመሰራረት በመሰረቱ የኩሽ እንጂ የሴም ቋንቋ አይደለም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ ዓረፍተነገርን በባለቤት ጀምሮ በግስ መጨረ ስም የሴም ሳይሆን እንደኦሮምኛና ወላይትኛ ያሉ የኩሽና የኦሞአዊ ቋንቋዎች ባህርይ ነው፡፡ በድምጹ፣ በምዕላዱና በሐረግ አወቃቀሩ ሴማዊነትን እየለቀቀ ኩሾ-ኦሞአዊነትን እያጠበቀ የመጣ ቋንቋ ነው፡፡ ሴማዊነቱን ካዝማቹ፣ ኩሾ-ኦማዊነቱን ደግሞ ከዘማቹ ሠራዊትና ሠራዊቱ ከተንቀሳቀሰበት ህዝብ ይዞ የወጣ ቅይጥ ቋንቋ ነው ሊባል ይችላል፡፡ የሠራዊት ቋንቋ በመሆኑም ከሠራዊቱ ጋር መዝመት የጀመረው በዚያን ጊዜ ነው ለማለትም ይቻላል፡፡

በአክሱምም ሆነ በተከታዩ የዛጉዌ ዘመን የቤተመንግሥቱ ቋንቋ ግእዝ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በተለይ በዛጉዌ ዘመን፣ ቤተመንግሥቱ እንደ ጥንቱ ግእዝን ሲጠቀም፣ ሠራዊቱና ህዝቡ አማርኛን ከአገውኛ ጋር በሻሚያ፣ ማለትም ጎን ለጎን ይጠቀም ነበር፡፡ በሂደቱም አማርኛ ከልሳነሠራዊትነት

ወደ ልሳነንጉሥነት ሊሸጋገር እንደቻለ ይነገራል፡፡ ይኸውም በንጉሥ ላሊበላ ዘመን ሲሆን፣ ምክንያቱ ደግሞ አማርኛ ተናጋሪ የነበረውን ሠራዊት ድጋፍ ላለማጣት እንደሆነ የሚገልጽ አፈታሪክ አለ፡፡

ይህ ባንድ በኩል የሚሰጥ አስተያየት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቋንቋው በርግጥ ልሳነንጉሥ የሆነው የዛጉዬ ዘመን አክትሞ ሥልጣን ከላስታ ወደሸዋ ሲሻገርና የሰሎሞናውያኑ ስርወመንግሥት እንደገና በ1272 ሲጀመር እንደሆነ የሚጠቅስ ጽሑፋዊ ማስረጃ አለ፡፡ ይህም በአፄ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ነው፡፡

በላሊበላም ይሁን በይኩኖ አምላክ ዘመን ቋንቋው ልሳነንጉሥ ይባል እንጅ፣ እንደግእዝ ልሳነጽሑፍ አልነበረም፡፡ ለዚህ የበቃው በ14ኛ ክፍለዘመን እንደሆነ የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለጽሑፍ የበቃውም የግእዝን ፊደል በመውረስና በማሻሻል ነው፡፡ ከኩሽ ቋንቋ ላገኛቸው ድምጾች ምልክት የሆኑትንና ዛሬ አንዳንድ ጊዜ አረቤ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ዲቃላ እየተባሉ የሚጠሩትን እንደ [ሽ፣ ጭ፣ ወዘተ.] ያሉትን ሲፈጥር፣ የግዕዝን የጉሮሮ ድምጾች ይወክሉ የነበሩት ፊደሎች ደግሞ እንዳለ ሊወስዳቸው ችሏል፡፡ እነዚህና ዛሬ ትርፍ የሚባሉት ሌሎች ፊደሎችም [አ፣ ዐ፣ ፀ፣ ጸ፣ ሐ፣ ሀ፣ ኀ፣ ሰ፣ ሠ]፣ አማርኛ ከግዕዝ ሳይመርጥ በጅምላ በመውሰዱ ምክንያት የገቡና አገልግሎት ላይ ያሉ ናቸው፡፡

ልሳነንጉሥ ብሎም ልሳነጽሑፍ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ፣ በትረመንግሥቱ የትም ይሂድ የት፣ ዙፋኑ ላይ ማንም ይቀመጥ ማን፣ ቋንቋው የህዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የመንግስትም ቋንቋ እንደሆነ ሊቀጥል ችሏል፡፡ በኋላም ዘመናዊ ትምህርት ሲስፋፋ መጀመሪያ የትምህርት ቀጥሎ በተወሰነ ደረጃ የማስተማሪያም ቋንቋ ሊሆንና የበለጠ ሊታወቅና ሊስፋፋ በቅቷል፡፡ ስለዚህም ዛሬ ከማንኛውም ሌላ ያገራችን ቋንቋ የበለጠ ስፋት ያለው ክልል ሊያዳርስና የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ዜጎችን ሊያነጋግር ችሏል፡፡



© MoE, FDRE
Not to be republished

በመልክዓ ምድራዊ ስርጭት ብቻ ሳይሆን፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸው አማርኛ በሥነልሣናዊ ቅርጽና ይዘቱም አገራዊ (ሕብረ ብሄራዊ) ባህሪ ያለው ቋንቋ ነው፡፡ ሴማዊ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች የበለጠ ኩሾ-ኦማዊ በመሆኑ የሁሉንም የቋንቋ ዘርፎች ባህሪያት አካቶ ሊይዝ ችሏል፡፡

*(ከባየ ይማም 1987፤ የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍ የተወሰደ፡፡)*

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ ልደት ወይም መነገር የጀመረው በዚህ ጊዜ ነው ማለት ይቻላል? ለምን?
2. "የአገራችንን ቋንቋዎች ከሌሎች ቋንቋዎች ከሚለዩዋቸው ሥነልሳናዊ ባሕርያት አብዛኞቹ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ይገኛሉ፤" የተባለው ለምንድን ነው?
3. ከአማርኛ በመነሳት ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች አጠቃላይ ባሕርያት መናገር አዳጋች ነው? ለምን?
4. የአማርኛ ውልደቱና ዕድገቱ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው፤ ለምን?
5. በአክሱምም ሆነ በዛጉዌ ዘመን የቤተ መንግሥት ቋንቋ የነበረው አማርኛ ቋንቋ ነው ማለት ይቻላል? ለምን?
6. አማርኛ ለጽሑፍ የበቃው በየትኛው ክፍለ ዘመን ነው? ለጽሑፍ የበቃውስ እንዴት ነው?
7. አማርኛ ምንም ሳይለውጥ ያሉትን ድምፆች (ፊደሎች) ሙሉ ለሙሉ የወሰደው ከየትኛው ቋንቋ ነው?
8. አማርኛን አገራዊ (ሕብረ ብሔራዊ) ባሕርይ ያለው ቋንቋ ያሰኙት ዋና ዋና ባሕርያት ምን ምን ናቸው?



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**፫. የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ወይም ስህተት የሆነውን "ሀሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በአጭሩ በጽሑፍ ግለጹ::**

1. በአማርኛ ውስጥ የሚገኙት በርካታ ሥነልሳናዊ ባሕርያት በሌሎች ቋንቋዎች ውስጥ አይታዩም::
2. ታሪካችን በአመዛኙ የወረራና ፍልሰት ታሪክ ነው::
3. ከግዕዝ በመጠኑ ለየት ያለ የሴም ቋንቋ ይናገሩ የነበሩት ዘማቾቹ ናቸው::
4. በግስ ይጀምር የነበረው ቋንቋ የአዝማቾቹ ቋንቋ ነው::
5. እብራይስጥና አረብኛ መዋቅራቸው ከአሁኑ አማርኛ መዋቅር ጋር አንድ ዓይነት ነው::
6. እንደ ብርሌ፣ ዲያቆን፣ ኮርማ፣ ቀብድ የመሳሰሉት የአማርኛ ቃላት የተገኙት ከኩሽ ቋንቋዎች ነው::
7. የአማርኛ ቋንቋ ቃላት በአብዛኛው ኩሻዊ ሲሆኑ፣ የሰዋስው ሥርዓቱ ደግሞ ሴማዊ ነው::
8. አማርኛ ለጽሕፈት የበቃው በላሊበላና በይኩኖ አምላክ ዘመን ነው::

**፲. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::**

1. ከላይ ካነበባችሁት ምንባብ ተነስታችሁ ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ምን ምን ጉዳዮችን በመጥቀስ መደምደም ትችላላችሁ? ዋና ዋና የመደምደሚያ ሀሳቦቻችሁን ዘርዝሩ::
2. ስለአማርኛ አጀማመርና ዕድገት ዋና ዋና ታሪካዊ ሁነቶችን በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::

**፬. ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ቀርበዋል:: ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ በያዙት ፍች ላይ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተነጋገራችሁ በኋላ በየግላችሁ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው::**

1. ተቆራኝ
2. ፍልሰት
3. ተራክቦ
4. ቸነፈር
5. ሲጠቃ
6. ሻሚያ
7. ግዳይ
8. ቀና
9. ፈርጅ
10. የሚጠቅስ

፫. ከዚህ በላይ የቀረቡትን ቃላት ፍች ከመዝገበ ቃላት ከፈለጋችሁ በኋላ፣ በምንባቡ ውስጥ ካላቸው ፍች በምን እንደሚለዩ በቡድን ተነጋገሩባቸው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መጻፍ

### ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ አባባሎች ተሰጥተዋል፡፡ አባባሎቹን እንደገና በራሳችሁ አባባል ጻፏቸው፡፡
   ሀ) አማርኛ ከማንኛውም ሌላ የአገራችን ቋንቋ የተሻለ መረጃ ይሰጣል፡፡
   ለ) በዚያው ለምዶ መቅረት የተለመደ ነው፡፡
   መ) ሰዋስዋዊ ሥርዓቱ ኩሾ-ኦሞኣዊ ነው፡፡
   ሠ) በሥነልሳናዊ ቅርጹና በይዘቱ ሕብረ ብሔራዊ ባህርይ ያለው ቋንቋ ነው፡፡
2. “የአማርኛ ቋንቋ ፖለቲካዊ ፈርጅ ከግዛትና እምነት ማስፋፋት ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴ ነው፤” የሚለውን ዓረፍተ ነገር መንደርደሪያ በማድረግ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
3. ስለአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ ልደትና እድገት ከሰው ጠይቃችሁ ወይም ከመጽሐፍ አንብባችሁ ከሁለት አንቀጽ ያልበለጠ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡
4. “የአማርኛ የሐረግ አወቃቀር ሥርዓት ከሴም ቋንቋዎች ይልቅ ለኩሽና ለኦሞኣዊ ቋንቋዎች የሚቀርብ ነው፤” የተባለበትን ምክንያት ማስረጃ በማስደገፍ አንድ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡

### ፪. በሚከተሉት ፈሊጦች ፍቻቸውን የሚያሣዩ አረፍተ ነገሮች ጻፉ

| | |
|---|---|
| 1. ጥጋቡ በረደ | 5. ነገር ቀመመ |
| 2. ቆርጦ ሄደ | 6. እግሩ ቀለለ |
| 3. አይኑ ቀላ | 7. ሆዱ ሻከረ |
| 4. ልቡ ቀረ | 8. የጥጃ ቀንዳም |



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ድርሰት ስትጽፉ ልታስታውሷቸው የሚገቡ መርሆች

ድርሰት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ (ጭብጥ) ላይ የሚጻፍ የጽሑፍ ዓይነት ነው፡፡ ድርሰት ለመጻፍ ሲፈለግ ጸሐፊው በቅድሚያ ማወቅ ወይም መረዳት ያለበት በርካታ ፍሬ ነገሮች ወይም የድርሰት መርሆች አሉ፡፡ መርሆቹም በቅድመጽሕፈት ተግባራትና በጽሕፈት ተግባራት ይከፈላሉ፡፡

1. ቅድመ ጽሕፈት ተግባራት

*ሀ. ድርሰት የመጻፍ ዓላማ፣* ድርሰት ለመጻፍ የሚነሳ ሰው ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ፣ የሚጽፍበትን ዓላማ ጠንቅቆ መረዳት ነው፡፡ የጽሑፉ ወይም የድርሰቱ ዓይነት እንደሚለያይ ሁሉ፣ ዓላማውም ይለያያል፡፡ ስለዚህ ድርሰት የሚጻፍበትን ዓላማ በቅድሚያ መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡

*ለ. ርዕስ መምረጥ፣* አንድ ድርሰት የሚጻፍበት ርዕሰ ጉዳይ ወይም ጭብጥ በቅድሚያ ራሱን ጸሐፊውን ሊያረካው፣ ሊስበውና ሊያስደስተው ይገባል፡፡ ስለዚህ ተስማሚ ርዕስ መምረጥ የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ እርግጥ ነው ሁልጊዜ ይኼ እውነት ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ጸሐፊው ተገድዶ የሚጽፍበት ሁኔታና ጊዜ ሊኖር ይችላልና ነው፡፡ ያም ቢሆን ግን ጸሐፊውን በሚስበው መልኩ የተሰጠውን ርዕስ ማደራጀት የጸሐፊው ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡

*ሐ. ርዕስን ማጥበብ (መወሰን)፣* የሚጻፍበት ርዕስ የሚጻፍበትን ዓላማ የሚያሟላ ወይም ግብ የሚመታ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ልኩን፣ ወሰኑን ወዘተ. የሚመጥን መሆን ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም የሚጻፈው ድርሰት በጊዜ፣ በቦታ፣ በቃላት መጠን፣ ወዘተ. የሚወሰን ስለሚሆን ለዚህ ሁሉ በሚስማማ መልኩ ርዕስን ማጥበብ ወይም መወሰን ተገቢ ሥራ ነው፡፡

*መ. መረጃ ማፈላለግ፣* ከላይ የተገለጹት ከተከወኑ፣ ቀጣዩ ሥራ በተመረጠው ርዕስ ዙሪያ፣ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን መፈለግና ማሰባሰብ ነው፡፡ ከዚያም በመልክ በመልካቸው ማደራጀትና ሥርዓት ማስያዝ ቀጣዩ ሥራ ነው፡፡

*ሠ. አስተዋጽኦ/ቢጋር መንደፍ፣* ቢጋር የሚለው ቃል ዋናውን ጽሑፍ ወይም ድርሰት በጽሑፍ ከማስፈር በፊት፣ አጠቃላይ የጽሑፉን አካሄድ የሚያሳየውን ዝርዝር ዕቅድ ወይም ንድፍ ይመለከታል፡፡ ይህ ከሆነ ድርሰቱ ከመጻፉ በፊት በድርሰቱ ውስጥ መካተት ያለባቸውን ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች በቢጋር መልክ ማዘጋጀት ለድርሰቱ ውጤታማነት አስፈላጊ ደረጃ ነው፡፡

*ረ. ተደራሲና ዐውድ፣* የድርሰት ዓላማ ድርሰቱ ወይም ጽሑፉ ታላሚ ከሚያደርገው አንባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ይህም ማለት ጸሀፊው ለእነማን እንደሚጽፍ፣ በቅድሚያ ያውቃል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ጸሐፊው እንደሚጽፍላቸው ተደራስያን ከቋንቋ መረጣ ጀምሮ ሌሎችንም መርሆች መረዳትና መወሰን ይጠበቅበታል፡፡

### 2. የጽሕፈት ተግባር

*ሀ. ረቂቅ መጻፍ፣* በአንድ ርዕስ ጉዳይ ላይ በርካታ ሀሳቦች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ ሀሳቦቹ ስላሉ ብቻ ሁሉንም እንዳሉ፣ እንደወረዱ መጻፍ አይቻልም፤መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከላይ የተመለከተው ቢጋር ሀሳቦችን ለመምረጥና ለማደራጀት ጠቃሚ ነው፡፡ ስለሆነም በቢጋራችን ላይ ተመሥርተን ረቂቁን መጻፍ ተገቢ ነው፡፡ የረቂቅ ጽሑፍ ዋነኛ ግቡ የመጨረሻው ድርሰት ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊውን ማስተካከያና እርማት ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በተለያዩ ስልቶች ረቂቃችንን መጻፍ ይጠበቅብናል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ለ. **የመጨረሻ ረቂቅ፣** የአንድ ድርሰት ረቂቅ ተዘጋጅቶ ካበቃ በኋላ በልዩ ልዩ መንገዶች የማጣራት ተግባራት ይከናወናሉ:: ከእነዚህ ተግባራት ውስጥ አንዱ በራሱ በጸሐፊው የሚደረገው የማረጋገጫና የማጣሪያ ተደጋጋሚ ንባብ ነው:: በዚህ ሂደት በጽሑፉ ውስጥ በተካተቱት ዋና ዋና ነጥቦችና ዝርዝሮች ላይ ተገቢ ትኩረት በማድረግ በደንብ ያልተገለጸ ወይም ያልተብራራ ሀሳብ ካለ አስፈላጊው ማስተካከያ ይደረጋል:: ያላግባብ የገቡ ሀሳቦችም ካሉ እንዲወገዱ ይደረጋል:: የፊደላት፣ የቃላት፣ የዓረፍተነገሮች ወዘተ. ግድፈትም እንዳይኖር ሙሉ ጥንቃቄ የሚደረገው በዚሁ ሂደት ነው::

*(ደረጀ ገብሬ፣1996:: ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ:: አዲስአበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት:: ከሚለው መጽሐፍ ከገጽ89-128 ከተጠቀሰው የመጻሐፉ ክፍል ተሻሽሎ የተወሰደ::)*

ሮ. **ቀጥሎ ደግሞ ባለፉት የክፍል ደረጃዎች በተማራችሁት መሠረት አንድ አጠር ያለ ወጥ ድርሰት ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ::**

በቅድሚያ ግን:-

- ድርሰት የምትጽፉበትን ርዕስ ከራሳችሁ ፈልጉና አሳዩ፤
- ርዕሳችሁ በመምህራችሁ ተቀባይነት ሲያገኝም (ተቀባይነት ካላገኘ እንደገና ሌላ ርዕስ ፈልጋችሁ ማቅረብ ይኖርባችኋል) አስተዋጽኦ ንደፉ፤
- ከዚያም ከሦስት መቶ ባልበለጡ ቃላት አጭር ድርሰት ጻፉ፤ ስትጽፉም ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በድርሰታችሁ ውስጥ ተጠቀሙ፤
- የክፍል ጓደኞቻችሁ ድርሰታችሁን አንብበው አስተያየት እንዲሰጧችሁ አድርጉ፤ በተሰጣችሁ አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ የመጨረሻውን ጽሁፍ ለመምህራችሁ አስረክቡ::



© MoE, FDRE, Not to be reproduced

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሚተላለፉ ድራማዎችን ተከታትላችሁ በማስታወሻ ያዙና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፪. በኢትዮጵያ ሬዲዮ ወይም በማንኛውም ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች የሚተላለፉ ልቦለዳዊ ትረካዎች አዳምጣችሁ የተረዳችኋቸውን ፍሬ ነገሮች በማስታወሻ አስፍሩና አጭር ንግግር ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

፫. በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በ"ከወጣቶች ዓለም" የሚቀርብ ሥነ ጽሑፋዊ ዝግጅትን (ቅንጫቢም ሊሆን ይችላል) አዳምጡና የዝግጅቱን ፍሬ ነገር በአጭሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ፡፡

፬. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ውስጥ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን በጽሞና አዳምጡ፤ አስፈላጊ ማስታወሻም ያዙ፡፡ ከዚያም የሚከተሉትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች መልሱ፡፡

**ሀ) የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የቋንቋ ዘፈቀዳዊነት እንዴት ይገለጻል?ተናገሩ፡፡
2. ቅርጹን ይዞ ወይም ተመልክቶ መልዕክቱን ወይም የሚወክለውን ነገር ለመገመት የማይቻለው ለምንድን ነው? ምሳሌ እየጠቀሳችሁ ተናገሩ፡፡
3. የሁለትዮሽነት ባህርይ ከዘፈቀዳዊነት ባህርይ በምን ይለያል?
4. ተነጣይነትና ተፈጣሪነት የሚሉት ስያሜዎች ምንን ያመለክታሉ?
5. የተፈጣሪነት ባህሪ ከድንበር ዘለልነት ባህሪ ይለያል? እንዴት?
6. የሰው ልጅ ቀደም ሲል ያልሰማውን ወይም ያልተናገረውን ዓረፍተነገር በአዲስ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ መፍጠር መቻሉ የምን ምልክት ነው?
7. "ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው፤" የሚለውን "ቋንቋ ሥርዓታዊ ነው፤" ከሚለው ጋር እያነፃፀራችሁ ተናገሩ፡፡
8. የሰው ልጅ ቋንቋ ማነቃቂያ የማይፈልገው ለምንድን ነው?
9. የንቦች ዳንስ ከየትኛው የቋንቋ ባህርይ ጋር ይመሳሰላል? ለምን?
10. "ቋንቋ ባህላዊ የውርርስ ባህርይ አለው" ሲል ምን ማለቱ ነው?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ለ) "የቋንቋ ባህርይ" የሚለው ምንባብ ሲነበብላችሁ የያዛችሁትን ማስታወሻ ለመምህራችሁ ካሳያችሁ በኋላ ያገኛችሁትን ፍሬ ነገር መነሻ በማድረግ አንድ አጭር ጽሑፍ ጽፉችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አራት፡- መናገር

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትዕዛዛቸው መሠረት መልሱ፡፡**

1. "ከአማርኛ በመነሳት ስለሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አጠቃላይ ባሕርይ ከሞላ ጎደል መናገር ይቻላል፡፡" ከምንባቡ ማስረጃ በመያዝ ይህን ሐሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ፡፡
2. የኅብረተሰብ መቀላቀል እንዴት የቋንቋዎችን መቀላቀል እንደሚያመጣ በቡድን ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ውጤት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ፡፡
3. ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በራሳቸው ቋንቋ መጠቀማቸው ያለውን ጠቀሜታ በቡድን ተነጋገሩበት፡፡
4. "አማርኛ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓቱ ኩሾ-ኦሞኣዊ ሊሆን ችሏል፤" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በአጭሩ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አስረዱ፡፡
5. አማርኛ በመልክዓ ምድራዊ ስርጭት ብቻ ሳይሆን በሥነልሳናዊ ቅርጽና ይዘት አገራዊ (ሕብረ ብሔራዊ) ባሕሪ ያለው ቋንቋ ሆኗል፤ ይህንን ሀሳብ ተወያዩበት፡፡

**፪. ቀጥሎ የተለያዩ የመከራከሪያ ሀሳቦች ተሰጥተዋል፡፡ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሁለት ቡድን ከተከፋፈላችሁ በኋላ አንዱን ሀሳብ መርጣችሁ ተከራከሩ፡፡ በምትከራከሩበትም ጊዜ ከግል አስተያየት ይልቅ በማስረጃና በእውነት ላይ መመሥረትን አትዘንጉ፡፡**

ሀ. የኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ ግዴታ መሆን አለበት/የለበትም፡፡

ለ. አሁን የሚታየው የወጣት ሴት ልጆች አለባበስ "በባህላችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረነው" የሚል አስተያየት የሚሰጡ ወገኖች፣ "የሴት ልጆችን አለባበስ በተመለከተ መመሪያ መውጣት አለበት" ይላሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ደግፋችሁ ወይም ተቃውማችሁ ተከራከሩ፡፡

© MoE, FD
Not to be rep

## ክፍል አምስት:- ሥነልሣን

፩. የሚከተሉትን ቃሳት በድምፀልሣናዊ አፃፃፍ ጻፉ፤ በተፃፉበት ሁኔታ በውስጣቸው የሚገኙትንም ተናባቢዎች ብዛት አመልክቱ::

1. አስኳል--------------------
2. ብላቴና--------------------
3. ወንፊት--------------------
4. መንገደኛ -----------------
5. ለበለበ --------------------
6. አልጋ -------------------
7. ግርሻ -------------------
8. ለገሰ ---------------------
9. አመልካች --------------
10. ማነቆ --------------------

፪. በምዕራፍ አንድ በተማራችሁት መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ::

1. የሚከተሉትን ቃላት በድምፀልሣናዊ አጻጻፍ ከጻፋችሁ በኋላ በውስጣቸው የሚገኙትን ቀለሞች ለይታችሁ በጽሑፍ አመልክቱ::

| ተ.ቁ. | ቃላት | ድምጸልሳናዊ አጻጻፍ | የቀለሞች ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ብራና | | |
| 2 | ወርቅ | | |
| 3 | ሥራፊት | | |
| 4 | እንቁላል | | |
| 5 | ሰርጎገብ | | |

2. የሚከተሉትን ቃላት በጽሞና መርምራችሁ በእያንዳንዱ ቃል ውስጥ የሚገኙትን ቀለሞች መጠን ወይም ብዛት በቃላቱ ትይዩ ጻፉ::
   ሀ) ምንጣፍ
   ለ) መንኮራኩር

© MoE, FD
Not to be rep

መ) ሰልፈኛ

ሠ) ላሊበላ

ረ) አዝማቾች

፫. ቀጥሎ ንውሳን ጥንዶች ተሰጥተዋል፡፡ በእነዚህ ንውሳን ጥንዶች ውስጥ የትርጉም ልዩነት እንዲመጣ ያደረጉትን ድምጸ ልሳናት ለይታችሁ አመልክቱ፡፡ የንውስ ጥንድን ምንነትና አገልግሎት ቀጥሎ ከቀረበው መግለጫ ተረዱ፡፡

## የንኡስ ጥንድ ምንነትና አገልግሎት

ንኡስ ጥንድ ማለት፣ በሁሉም ነገር ተመሳሳይ ሆነው በአንድ ድምፅ ብቻ የሚለያዩ ቃላት ጥንድ ጥንድ ሆነው የሚቀርቡበት ነው፡፡ ይህም ንኡስ ጥንድ በቋንቋው ውስጥ ትርጉም ለዪ የሆኑትን ድምጸ ልሣኖች ለይቶ ለመረዳትና በዚያ ቋንቋ ውስጥ ምን ያህል ድምፆች እንዳሉ ለመወስን ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፣ በላ እና በሳ የሚሉትን ቃላት ወስደን እንመልከት፤ በቅድሚያ በድምፀ ልሣናዊ አጻጻፍ እንጻፍ፤ /ብኧልልኣ/ እና /ብኧስስኣ/ ይሆናሉ፡፡ በነዚህ ቃላት ያለው ልዩነት የተፈጠረው በ/ል/ እና በ /ስ/ ድምፀ ልሣኖች አማካይነት ነው፡፡ ስለዚህ ጥንዶቹን ንዑስ ጥንድ እንላቸዋለን፡፡ ከዚህም ምሳሌ ተነስተን እነዚህ ሁለት ድምፆች (/ስ/ እና /ል/) የአማርኛ ድምፀ ልሣኖች ናቸው ማለት እንችላለን፤ ምክንያቱም የትርጉም ልዩነት አምጥተዋልና፡፡

1. አረሰ
   አረደ
2. መጠቀ
   መጠነ
3. ገመሰ
   ገመደ
4. ለኮሰ
   ለወሰ

| | |
|---|---|
| 5. ከመረ<br>ደመረ | 6. ደፈረ<br>ደፈነ |
| 7. ጋቢ<br>ገቢ | 8. ቀና<br>ቁና |
| 9. ባት<br>ቤት | 10. ወርቅ<br>ወርድ |

፬. ከላይ በሠራችሁት መሠረት የተለያዩ ድምፀልሣኖችን ትርጉም ለዩ መሆናቸውን ለማመልከት አስር አስር ንዑሳን ጥንዶች በየግላችሁ ጻፉ፡፡

፭. ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት እንደየትዕዛዛቸው ከሥርወ ቃላቱ ስሞችንና ቅጽሎችን መሥርቱ፡፡

**ሥርወቃል** ማለት የአንድ ቃል ሥር ወይም ያን ቃል ያስገኙ ተናባቢዎች፣ አናባቢ በመካከላቸው ሳይገባ፣ ባላቸው ቅደም ተከተል መሠረት የተዋቀሩበት ቅርጽ ማለት ነው፡፡ ቃሉን ባስገኙት ተናባቢዎች መካከል አናባቢ ከገባ፣ ሥርነቱ ይቀርና አምድ (stem) ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት ***በለጠ*** የሚለው ግስ ሥርወቃል /ብ-ል-ጥ/ ነው ማለት ነው፡፡ በተናባቢዎቹ መካከል አናባቢ ቢገባ ግን፣ ለምሳሌ /ብኧልልኧጥ-/ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የግስ አምድ ነው፤ አምድነቱም ፍጽም (የተፈጸመ፣ የተደረገ) አምድ ነው፡፡

***ምሳሌ፡-*** 1. /ብ-ል-ጥ/ ከሚለው ስርወቃል ***ብልጠት፣*** /ው-ፍ-ር/ ከሚለው ደግሞ ***ውፍረት*** የሚል ስም ይመሰረታል፡፡

1. በምሳሌ 1 መሠረት ቀጥሎ ከተሰጡት ስርወቃሎች ስም መስርቱ፡፡
   ሀ) /ቅ-ብ-ጥ/ ------------------
   ለ) /ድ-ፍ-ር/ --------------------
   መ) /ው-ር-ድ/ --------------------



© MoE, FDRE Not to be reproduced

ሠ) /ድ-ር-ቅ/ ---------------------

ረ) /ፍ-ጥ-ን/ ----------------------

***ምሳሌ፡-*** 2. /ል-ብ-ስ/ ከሚለው ስርወ ቃል ***ልብስ*** የሚለው ስም ሲመሠረት፣ /ክ-ብ-ር/ ከሚለው ደግሞ ***ክብር*** ይመሰረታል፡፡

2. በምሳሌ 2 መሠረት ስም መስርቱ፡፡

ሀ) /ግ-ን-ብ/ -----------------------

ለ) /ቅ-ው-ር-ጥ/ --------------------

መ) /ም-ር-ት/ ---------------------

ሠ) /ብ-ር-ዝ/ ----------------------

ረ) /ዝ-ው-ር/ ----------------------

***ምሳሌ፡-*** 3. /ብ-ል-ጥ/ ከሚለው ስርወቃል ***ብልጥ*** የሚል ቅጽል ይመሠረታል፡፡

3. በምሳሌ 3 መሠረት ቅጽል መሥርቱ፡፡

ሀ) /ድ-ር-ስ/ ----------------------

ለ) /ቅ-ር-ብ/ ----------------------

መ) /ም-ር-ጥ/ --------------------

ሠ) /ግ-ው-ር-ድ/ ------------------

ረ) /ብ-ር-ድ/ -----------------------

***ምሳሌ፡-*** 4. /ጭ-ክ-ን/ ከሚለው ስርወቃል ***ጨካኒ= ጨካኝ*** የሚል ቅጽል ይመሠረታል፡፡

4. በምሳሌ 4 መሠረት ከሚከተሉት ስርወቃሎች ቅጽል መሥርቱ፡፡

ሀ) /ር-ው-ጥ/ -----------------------------------

ለ) /ድ-ፍ-ር/ ------------------------------------

መ) /ን-ፍ-ቅ/ -----------------------------------

ሠ) /ጥ-ቅ-ም/ -----------------------------------

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDR
Not to be rep

## የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች

ዓረፍተነገር የሐረጎች ሥርዓታዊ ግንኙነት የሚያስገኘው ከፍተኛ መዋቅር ነው፡፡ ዓረፍተነገርን የሚያስገኙት መሠረታዊ ተዋቃሪዎች ስማዊ ሐረጉና ግሳዊ ሐረጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ተዋቃሪዎች በሁሉም ረገድ ስምሙ ሆነው መገኘት፣ ለዓረፍተነገሩ ሰዋስዋዊነት መሠረታዊ ናቸው፡፡ እነዚህ ሐረጎች በየውስጣቸው የገቡት ሐረጎች ተራ ከሆኑ፣ ዓረፍተነገሩም ተራ ይሆናል፤ ሐረጎቹ ግን ውስብስብ ከሆኑ፣ ማለትም በውስጣቸው ሌላ ዓረፍተነገር ካለ ዓረፍተነገሩ ውስብስብ ይሆናል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንውሰድ፤

1. ረጅሙ መምህር ዛሬ ወደ ውጪ ሄደ፡፡
   ስማዊ ሐረግ= ***ረጅሙ መምህር***
   ግሳዊ ሐረግ = ***ዛሬ ወደ ውጪ ሄደ፡፡***
2. አልማዝ ጎበዝ ተማሪ ነች፡፡
   ስማዊ ሐረግ= ***አልማዝ***
   ግሳዊ ሐረግ = ***ጎበዝ ተማሪ ነች፡፡***
   በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የገቡት ስማዊ ሐረጎችና ግሳዊ ሐረጎች ተራ በመሆናቸው፣ ዓረፍተነገሮቹም ተራ ዓረፍተነገሮች ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በሌላ በኩል የዓረፍተነገሮቹ መሥራቾች ውስብስብ ቢሆኑ ኖሮ፣ የሚከተለውን ዓይነት ይሆኑ ነበር፡፡
3. ወደ ውጪ የሄደው መምህር ለዘመዶቹ ደብዳቤ ላከ፡፡
   ስማዊ ሐረግ= ***ወደ ውጪ የሄደው መምህር***
   ግሳዊ ሐረግ = ***ለዘመዶቹ ደብዳቤ ላከ፡፡***
4. የአለሙ ወንድም ወደ ክፍል ሲሄድ አምስት ብር አገኘ፡፡
   ስማዊ ሐረግ= ***የአለሙ ወንድም***
   ግሳዊ ሐረግ = ***ወደ ክፍል ሲሄድ አምስት ብር አገኘ፡፡***

በምሳሌ 3 እና 4 ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጎች ተራ ሐረጎች ሳይሆኑ፣ ዓረፍተነገሮች (ጥገኛ) ናቸው፡፡ ጥገኛ ዓረፍተነገሮች ናቸው የተባሉት፣ ግሶቻቸው ዓረፍተነገር መጨረስ የማይችሉ

(ወይም የማያስሩ) ዓረፍተነገሮች ናቸው፡፡ በነዚህም ጥገኛ ዓረፍተነገሮች መኖር ዓረፍተነገሮቹ ውስብስብ ዓረፍተነገሮች ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በአጠቃላይ በዓረፍተነገሩ ውስጥ እንደሚገኙት ሐረጎች ተራነትና ውስብስብነት ዓረፍተነገሩም ተራ ወይም ውስብስብ ይሆናል፡፡

፩. ከላይ በቀረበው መግለጫ መሠረት *የአማርኛ አጀማመርና ዕድገት* ከሚለው ምንባብ ውስጥ አሥር ተራና አሥር ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች መርጣችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
፪. በመግለጫው መሠረት ከራሳችሁ አሥር የተለያዩ ተራ ዓረፍተነገሮች ጻፉ፡፡
፫. በተመሳሳይ ሁኔታ ከራሳችሁ አሥር የተለያዩ ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ፡፡

## የዓረፍተ ነገር ስልቶች

ዓረፍተነገሮች በተነገሩበት ስልት መሠረት የተለያዩ ተግባራት ይኖሯቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ሐተታዊ ወይም አታች፣ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ፣ አንዳንዶቹ መጠይቃዊ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ትዕዛዛዊ ይሆናሉ፡፡

1. **ሐተታዊ ዓረፍተነገር** ስለአንድ ድርጊት ወይም ሁነት አዎንታ ዊም ሆነ አሉታዊ አስተያየት ወይም ሀሳብ የሚገልጽ የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ ለየብቻ እንመልከታቸው፤

ሀ. **አዎንታዊ ዓረፍተነገር** ስለአንድ ድርጊት ወይም ሁነት ወይም ክስተት የሚገልጽ፣ የሚያትት ዓረፍተነገር ነው፡፡

***ምሳሌ***

1. ረጅሙ መምህር ዛሬ ወደውጪ ሄደ፡፡
2. አልማዝ ጎበዝ ተማሪ ነች፡፡

እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች እንደቅደም ተከተላቸው ስለረጅሙ መምህር ወደውጪ መሄድና ስለአልማዝ ጎበዝ ተማሪ መሆን የሚገልጹ በመሆናቸው ሐተታዊ፣ የተገለጹበት መንገድ ደግሞ አዎንታዊ ነው፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ለ. **አሉታዊ ዓረፍተነገር** የአዎንታዊ ዓረፍተነገር ተቃራኒ የሆነ የዓረፍተነገር ስልት ነው። በሌላ አገላለጽ በአዎንታዊ መንገድ የቀረበን ሀሳብ የሚያፈርስ ወይም የሚቃረን ዓረፍተነገር ነው።

***ምሳሌ***

3. ረጅሙ መምህር ወደውጪ አልሄደም።
4. አልማዝ ኀበዝ ተማሪ አይደለችም።

ከምሳሌዎቹ መመልከት እንደሚቻለው እነዚህ ዓረፍተነገሮች ከላይ በምሳሌ 1 እና 2 የተገለጹትን ሐሳቦች አሌ የሚሉ ወይም የሚያፈርሱ ናቸው። በዚህም ምክንያት አሉታዊ ዓረፍተነገር ተብለዋል። አሉታዊ ዓረፍተ ነገር በአሉታዊ ምዕላድ አማካይነት የሚመሠረት ነው። መነሻውም ከላይ እንደተመለከትነው አዎንታዊ ዓረፍተነገር ነው። የአሉታዊነቱም መንስዔ አል- የሚለው ምዕላድ ሲሆን፣ የሚገኘውም በግሱ መነሻ ላይ ነው።

2. **መጠይቃዊ ዓረፍተነገር** ስለአንድ ጉዳይ ወይም ስለተፈጸመ ድርጊት ወይም ሁነት ወዘተ. ጥያቄ የሚያቀርብ ዓረፍተነገር ነው። በመሆኑም ያልታወቀን ነገር ለማወቅ ወይም የታወቀን ጉዳይ ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄያዊ ዓረፍተነገር ነው። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንውሰድ፤

***ምሳሌ*** 5. ዓለሙ ምን በላ?
6. ዓለሙ ለምን መጣ?

እነዚህ ሁለት ዓረፍተነገሮች መጠይቃዊ ናቸው። መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር ለመመሥረት፣ ብዙ ጊዜ መጠይቃዊ ቃላትን (ለምን፣ምን፣ መቼ፣ የት ወዘተ.) እንጠቀማለን። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ግን እነዚህ መጠይቃዊ ቃላት ሳይኖሩም ዓረፍተ ነገሩ መጠይቃዊ ይሆናል።

***ምሳሌ*** 7. አለሙ ወደ ክፍል ሄደ?

ስለዚህ ለመጠይቃዊነት ስልት የመጠየቂያ ቃላት ቢኖሩም፣ ለጥያቄያዊ ዓረፍተነገር ዋናው አስፈላጊ ነገር መጠይቃዊ የድምፅ ቅላፄ ወይም ቃና ነው።

3. **ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር** አንዳች ነገር እንዲከወን ወይም እንዲደረግ የሚያስገድድ የዓረፍተነገር ስልት ነው፡፡ ይህ ዓረፍተነገር ሁለት ዓይነት አቀራረብ አለው፤ የመጀመሪያው ቀጥተኛ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ኢቀጥተኛ ወይም ኢርቱዕ ነው፡፡ ቀጥተኛው ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር የሚነገረው ድርጊቱን እንዲፈጽም ለሚፈለገውና በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ለተገለጸው ወይም ለተወከለው አካል ነው፡፡

***ምሳሌ***

8. (እናንተ) ወደ ክፍል ግቡ!
9. (አንተ) መጽሐፉን አምጣ!

ምሳሌዎቹ እንደሚያሳዩት የሚነገረው ሰው ወይም አካል ትዕዛዙን ፈጻሚው ነው፡፡ በቅንፎቹ ውስጥ እንደተጠቀመው የተወከለው በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ነው፡፡ ይሁንና ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገሮች ሁሉ እንደምሳሌ 8 እና 9 ቀጥተኛ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ኢርቱዕ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገርም ሊኖር ይችላል፡፡ ለማስረጃ የሚከተለውን እንመልከት፤

***ምሳሌ***

10. አለሙ መጽሐፉን ያምጣ!

በዚህ ጊዜ ትዕዛዙ በቀጥታ ለፈጻሚው ሰው ወይም አካል የሚነገር ሳይሆን፣ ትዕዛዙ የሚተላለፈው በሦስተኛ ወገን አማካይነት ነው፡፡ አንቀጹም ወይም ስልቱም የሚጠቀመው መጠይቃዊ የሆነውን የግስ ቅርጽ እንደሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ፈቃድን ለመጠየቅ የምንጠቀምበትን ***አለሙ መጽሐፍ ያምጣ?*** ዓይነት የግስ ቅርጽ የያዘ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለቀጥተኛውም ሆነ ለኢርቱዑ ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር ልክ እንደመጠይቃዊ ዓረፍተነገር የድምፅ ቅላፄ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

**፲፩. ከላይ የቀረበውን መግለጫ በጽሞና በማንበብ ለሐተታዊ፣ ለመጠይቃዊ፣ ለትዕዛዛዊና ለአሉታዊ አንቀጾች ወይም ስልቶች አሥር አሥር ዓረፍተነገሮች በየግላችሁ መሥርቱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ውድ ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ከቀረበላችሁ ምንባብ ተረድታችኋል፡፡ በሥነልሣን ረገድም ባለፈው ምዕራፍ የጀመርነውን ድምፀልሣናዊ አፃፃፍ በተጠናከረ ሁኔታ ተረድታችሁ፣ በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይታችሁ መጻፍ እንደቻላችሁ ይታመናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ የአማርኛን የቀለም መዋቅር ተገንዝባችሁ በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይታችሁ መጻፍ በሚገባ ተለማምዳችኋል፡፡ ከዚያም፣ ከስርወቃል ስሞችንና ቅጽሎችን መመሥረት ተለማምዳችኋል፡፡ የዓረፍተነገር ዓይነቶችን ተረድታችሁ የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ከመመሥረታችሁም ሌላ፣ በዓረፍተነገር ዓይነቶችና በዓረፍተነገር ስልቶች መካከል ያለውን ልዩነት ተረድታችኋል፡፡ በተግባርም ዓረፍተነገሮችን በመመሥረት አሳይታችኋል፡፡

በሌላ በኩልም መዝገበ ቃላትንና አውድን በመጠቀም፣ የቃላትን ፍቺ መፈለግ በተግባር ከመለማመዳችሁም በተጨማሪ፣ ከተለያዩ መገኛኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ የመያዝን ልምድ አዳብራችኋል፡፡ ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት የተጻፉ ጽሑፎችን አንብባችሁ ጠቃሚ ሀሳቦችን ወስዳችኋል፡፡ ቀጥላችሁም፣ የድርሰት አጻጻፍ ሥርዓትን ተከትላችሁ አንድ ድርሰት ጽፋችኋል፤ በጻፋችሁትም ድርሰት ውስጥ በአግባቡ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ተጠቅማችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስለአማርኛ አጀማመርና ዕድገት በአጭሩ ተናገሩ፡፡
2. የአማርኛን የቀለም መዋቅር አምስት ቃላት ከራሳችሁ በመስጠት አብራሩ፡፡
3. ከሥርወቃል ስሞችና ቅጽሎች እንዴት እንደሚመሠረቱ በምሳሌ አብራሩ፡፡
4. በዓረፍተነገር ዓይነቶችና ስልቶች (አንቀጾች) መካከል ያለውን ልዩነት በአጭሩ ምሳሌ በመስጠት አብራሩ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለአማርኛ ቋንቋ አጀማመርና ዕድገት ተረድቻለሁ:: | | | |
| 2 | ድምፀ ልሣናዊ አፃፃፍን ተረድቼ በቃላት ውስጥ የሚገኙ አናባቢዎችንና ተናባቢዎችን ለያይቼ እጽፋለሁ:: | | | |
| 3 | የአማርኛን የቀለም መዋቅር ተረድቼ በቃላት ውስጥ የሚገኙ ቀለሞችን ለይቼ አመለክታለሁ:: | | | |
| 4 | መዝገበ ቃላትንና አወድን በመጠቀም የቃላትን ፍች መስጠት እችላለሁ:: | | | |
| 5 | ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች አዳምጬ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ እችላለሁ:: | | | |
| 6 | የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችንና ስልቶችን ተረድቼ የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን መመሥረት ችያለሁ:: | | | |
| 7 | ድርሰት መጻፍ ችያለሁ:: | | | |
| 8 | ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በሥርዓቱ ውይይት ማድረግ ችያለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ::

© MoE, FDRE Not to be reproduced

# ምዕራፍ ሦስት

# ሒስ

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:-**

- የሒስን ምንነት በቃልና በጽሑፍ ትገልጻላችሁ፤
- ተገቢውን ሥርዓት ተከትላችሁ በልዩ ልዩ ርእስ ጉዳዮች ላይ ትከራከራላችሁ፤
- ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን አዳምጣችሁ ትረዳላችሁ፤
- ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በሒሳዊ የአነባበብ ሥልት አንብባችሁ ትገመግማላችሁ፤
- ሒሳዊ አስተያየት የያዘ አስረጅ ድርሰት ትጽፋላችሁ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፤
- አጠቃላይ እውነታ እና የግል አስተያየት የያዙ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ፤
- ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች ታስተካክላላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በፊት ያነበባችሁት ወይም ያዳመጣችሁት ሥነጽሑፋዊ ሒስ አለን? ካለ በምን ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነበር?
2. የአንድ ሐያሲ ተግባር ምንድን ነው ብላችሁ ትገምታላችሁ?
3. በአንድ ሀገር ውስጥ የሥነጽሑፍ ሐያሲ የሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስሏችኋል?
4. አንድ ልቦለድ አንብባችሁ ስትጨርሱ በጠንካራና ደካማ ጎኖቹ ላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተወያይታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ጠንካራ እና ምን ደካማ ጎኖችን አነሳችሁ?

## የሥነጽሑፍ ሒስ ምንነትና የሐያሲው አስፈላጊነት

በእንግሊዝኛው አጠራር "ክሪቲክ" በመባል የሚታወቀው ሐሳብ ግብሩንም ገባሪውንም ያመለክታል። በአማርኛ ግን ሒስ የግብሩ፣ ሐያሲ ደግሞ የገባሪው መጠሪያ ሆኖ ያገለግላል። ግብሩ ግምገማ፣ ግምት፣ ፍርድ፤ ገባሪው ደግሞ ገምጋሚ፣ ገማች፣ ፈራጅ ማለት ነው።

በተለይ ሥነጽሑፋዊ ሒስ በዋናነት በአንድ የፈጠራ ሥራ ላይ የሚሰነዘር ሚዛናዊ አስተያየት ነው። ማለትም፣ ያን የፈጠራ ሥራ መፈከርን፣ መተንተንን እና መገምገምን የሚያካትት ተግባር ነው። ፍከራው፣ በፈጠራ ሥራው ውስጥ የሚገኙት ቃላትና አገላለጾች የያዙትን አውዳዊ እንዲሁም አንድምታዊ ፍች አንጥሮ ማውጣትን እና በድምሩ ሊባል የተፈለገውን ነገር መለየትን የሚመለከተው ቀዳሚ ተግባር ነው። ትንተና፣ በፍከራው ደረጃ የተገኘውን ዓቢይ ሐሳብ ማስረጃዎች እየጠቀሱ በዝርዝር ማብራራት ማለት ነው። ግምገማ ደግሞ፣ የፈጠራ ሥራውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለይቶ በማውጣት፣ ጠንካራ ጎኖቹን "ይበል" ብሎ ደካማ ጎኖቹ የሚቃኑበትን መንገድ ማመላከት ነው፤ ይህም የፈጠራ ሥራውን ደረጃ ለመወሰን የሚያስችል ምዘና ነው ማለት ይቻላል።



© MoE, FDRE Not to be reproduced

ይህ የፍከራ፣ የትንተና እና የግምገማ ተግባር ደግሞ የሚከናወንባቸው የራሱ የአሠራር ደረጃዎች እና ዘዴዎች አሉት፡፡ ሳይንሳዊና ኪናዊ የአሒያሒያስ ዘዴዎችን ተከትሎ የሚከናወን ሥነጽሑፋዊ ሒስ፣ ለደራሲው ብቻ ሳይሆን ለአንባቢያንም ከፍ ያለ ጥቅም ያስገኛል፡፡ ደራሲው የፈጠራ ሥራውን ብቃትና ጉድለት ለይቶ አከያየኑን የሚያሻሽልበትን ልምድና መመሪያ ያገኛል፡፡ አንባቢው ደግሞ በንባቡ ያልተገነዘባቸውን ጸናና ጉዳዮች በተብራራ ሁኔታ የሚረዳበት እድል ያገኛል፡፡ ይህም በድምሩ ለአጠቃላይ ሥነጽሑፉ እድገት ከፍ ያለ አስተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡

በተለምዷዊ አመዳደብ÷ ሥነጽሑፋዊ ሒስ በሁለት ይከፈላል፡፡ የመጀመሪያው ተራ ሒስ የሚባለው ነው፡፡ ተራ ሒስ አንድን የፈጠራ ሥራ በጎ ወይም መጥፎ ብሎ ከመፈረጅ ባሻገር፣ በጎ እና መጥፎ ያሰኙትን ብቃትና ጉድለቶች ለማሳየት የማይሞክር የሒስ ዓይነት ነው፡፡ በማስረጃ ላይ ስለማይመሠረትና ከስሜታዊነት የጸዳ ስለማይሆንም አሳማኝነት ይጎድለዋል፤ ተቀባይነትም አይኖረውም፡፡

ሁለተኛው የሒስ ዓይነት ምሁራዊ ሒስ የሚባለው ነው፡፡ ይህኛው÷ ስሙ እንደሚያመለክተው÷ በእውቀት ላይ የሚመሠረት የሒስ ዓይነት ነው፡፡ ሐያሲው ከምንም ነገር አስቀድሞ ስለሥነጽሑፍ፣ ስለሒስ እና ስለመሔሻ ዘዴዎች በቂ እውቀት ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ የሚሔሰውን የሥነጽሑፍ ሥራ በሚገባ ያጠናል፡፡ ሥራውን ሲፈክር፣ ሲተነትንና ሲገመግምም በሥነጽሑፍ እውቀቱና በጥናቱ ውጤት ላይ ተመሥርቶ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በስሜታዊነት የተመራ መደምደሚያ በመስጠት ፋንታ ከሚሔሰው ሥራ ውስጥ ማስረጃዎችን በመጥቀስ ማሳመኛ ያቀርባል፡፡ ስለዚህም፣ ተቀባይነቱ የጎላ ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምሁር ሐያሲም ሚዛናዊ ሐያሲ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ለመሆኑ ደራሲ የሆነ ሁሉ ሐያሲ መሆን ይችላልን? ሶቅራጥስ የተባለው ጥንታዊ የግሪክ ፈላስፋ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ሞክሯል፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

በሶቅራጥስ አስተሳሰብ÷ ሀብተ ቅኔ፣ ሀብተ ድርሰት የተሰጠው፤ መንፈሰ ፈጠራ ያደረበት ሰው፣ የድርሰቱ ፍሬ ነገር የሚገለጽለትና ያንኑም በቃላት መሣሪያነት የሚገልጸው አብዛኛውን ጊዜ በተመስጦ ሁኔታ ላይ ሳለ ነው፡፡ የደራሲዎችና የሐያስያን ግብራቸው ተደጋጋፊ ቢሆንም፣ ስጦታቸው እየቅል መሆኑንም አብራርቶ አስረድቷል፡፡ ይህም ሲባል አብዛኛውን ለመናገር ነው እንጂ ደራሲም፣ ባለቅኔም፣ ሐያሲም፤ ሦስቱንም አጣምረው ለመሆን የቻሉ ጥቂቶች አልነበሩም፤ አሁንም የሉም ለማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ታላቁን መስኮባዊ ሌዎ ቶልስቶይን፣ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ እንግሊዛዊውን ቤርናርድ ሾን ማስታወስ ይበቃል፡፡

የሥነጽሑፍ ሐያስያን አስፈላጊ የሚሆኑባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሥነጽሑፍ ሐያስያን በማኅበራዊ ኑሮ አስፈላጊ ሆነው የሚገኙባቸው ልዩ ልዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ ልናስተውለው የሚገባን÷ ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ዋጋቸው የማይቀንስ መጻሕፍት መኖራቸውን ነው፡፡ እነዚህን መጻሕፍት÷ ያለፈው ትውልድ ያከበራቸውና የወደዳቸው በጊዜው በነገሠው ሐሳብና አስተያየት፣ በተፈጠረው የኑሮ ችግር፣ በዘመኑ የታሪክ ዝንባሌ መሠረትነት ነበር፡፡ ተከታዩ ትውልድ ግን እነዚህን ዘለዓለማዊ ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት የሚያነባቸው በራሱ የኑሮ ችግር፣ በገዛ ዘመኑ መንፈስ ሓሳብና አስተያየት መሠረት መሆኑ ስለማይቀር፣ ከመጻሕፍቱ የሚያገኘውም ትምህርት፣ ምሳሌና ተግሣፅ በዚያው መጠን የተለየ መሆን አለበት፡፡ መጻሕፍቱም ጠቃሚነታቸው ሳይጓደል፣ ከትውልድ ወደትውልድ በመተላለፋቸው ታላቅነታቸው ጸድቆ ይኖራል፡፡ ስለዚህ፣ ያለፉት ትውልዶች በየጊዜያቸው ያፈሩትን ታላላቅ ድርሰትና ቅኔ ለአሁኑ ትውልድ የሚያስተዋውቀውና የሚተረጉምለት፣ የሚያመዛዝንለትና የሚገምትለት የሥነጽሑፍ ሐያሲ አስፈላጊ ነው፡፡

በተጨማሪም፣ ማንኛውም ጸሐፊ (ልብ ወለድ ደራሲ ወይም ባለቅኔ) ቢሆን ትክክለኛ ቦታውና እውነተኛ ዋጋው የሚታወቀው፣ በጊዜው ካሉት

© MoE, FDRE Not to be republished

ከቢጤዎቹ ጋር ብቻ ሳይሆን ካለፉት አንጋፋ ደራሲዎች ጋር ሲመዛዘን፣ ሲነጻጸርና ሲወዳደር ነው፡፡ ስለዚህ፣ ይህንኑ ሥራዬ ብሎ የያዘ ስጦታ ያለው ሐያሲ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህም ሌላ÷ የሰው ልጅ ሐሳብና አስተያየት ከዘመናት ጋር የሚለዋወጥ ነው፡፡ ባንዱ ዘመን መልካምና ትክክለኛ ነው የተባለው አስተያየት÷ በቀደመው ወይም በሚከተለው ዘመን ከስሕተት ይቆጠር ይሆናል፡፡ ይህንንም በሥነጽሑፍ (በጥበበ ቃላት) ረገድ በሚገባ ለማጣራትና ለአሁኑ ትውልድ ለማስረዳት ደንበኛ ሐያሲ ያስፈልጋል፡፡

የምናነበው ልብ ወለድ ጽሑፍ ሊሰብከንና ግብራችንን ሊለውጠው ይችላል፡፡ ብዙ መጻሕፍትን ያላነበቡ ሰዎችና ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች÷ መጽሐፍ ባነበቡ ቁጥር የደራሲው መንፈስ እየነገሠባቸው በየደራሲው ሐሳብ መመራት ግድ ይሆንባቸዋል፡፡ አንድ ጊዜ አንዱ ደራሲ በአእምሯቸው ላይ ይነግሣል፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ደራሲ ያይልባቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ደራሲዎቹ ባልበሰለው አንባቢ አእምሮ ውስጥ እርስ በራሳቸው መጣላት፣ ውጊያና ጦርነት ይጀምራሉ፡፡ የአንባቢውም አእምሮ ይበጠበጣል፡፡ ይህ አንባቢ፣ በአእምሮ ረገድ ራሱን ለመቻል የሚበቃውና ለየደራሲው ሐሳብ ከመገዛት ነፃ የሚወጣው በሰፊው በማንበብ ብቻ ነው፡፡ በሰፊው ማንበብ ማለት ደግሞ፣ የሚረባውንም የማይረባውንም በጭፍኑ ማግበስበስ ስላልሆነ መነበብ የሚገባቸውን ደህና ደህናዎቹን መጻሕፍት እየመረጠ ለአንባቢዎች የሚያመለክት የሥነጽሑፍ ሐያሲ ያስፈልጋል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. በእስከአሁኑ ንባባችሁ ጽሑፉ የተጻፈበት ዓላማ ምን እንደሆነ አወቃችሁ? ለዚህ ማስረጃችሁ ምንድን ነው?
2. የሥነጽሑፍ ሐያሲ አስፈላጊ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው ተብለው ተገልጸዋል?
3. በእስከአሁኑ ንባባችሁ ስለምን ምን ዝርዝር ጉዳዮች ተገነዘባችሁ? በቀሪው የጽሑፉ ክፍልስ ስለምን ለመረዳት ትሻላችሁ?



© MoE, FDRE, Not to be reproduced

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

የሥነጽሑፍ ሐያሲ የሚሰጠው ጥቅም ከዚህ በላይ ባሉት መስመሮች ተገልጿል፡፡ ሐያስያን የሚያስፈልጉባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች እነዚሁ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ አንዳንድ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ስለሐያሲ ተግባር ያቀረቧቸው አስተያየቶች ይህንኑ ሐሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ የጥቂቶቹን አስተያየት እንጥቀስ፡፡ ቲ.ኤስ. ኤልየት እንደሚለው፥ “የደንበኛው ሐያሲ ተግባር የልብ ወለድና የቅኔን ድርሰቶች መፍታት፣ መተርጎም፣ ማብራራት፣ ስለነሱም በሕዝብ ዘንድ የተሳሳተ አስተያየት ቢኖር ማረም ነው፡፡” ማቲዎስ አርኖልድ እንደጻፈው ደግሞ፥ “የደንበኛው ሐያሲ ተግባሩ በየሀገሩና በየዘመኑ ከተጻፈው ሁሉ ብልጫ ያለውን፣ በጎኛውን እየፈለገ ሲያገኘው ይህንኑ ለአንባቢዎች ማመልከት ነው፡፡” በሌዎ ቶልስቶይ አስተሳሰብ፥ “የደንበኛው ሐያሲ ተግባሩ ከመጥፎው፣ ከብላሹ፣ ከብልሹው የድርሰትና የጽሕፈት ባሕር ደገኛውን፣ በጎኛውን፣ ደህነኛውን ፈልጎ ማግኘት፤ ካለፈውና ከአሁኑ ብልጫ ያለውን መርጦ አቅርቦ ለሁሉ ማሳየት ነው፡፡”

ሐያሲ ይህን ከፍተኛ ተግባሩን የሚያከናውንበት ዘዴው ጤነኛ ሰው የሚጠይቀውን ተገቢ የሆነውን ጥያቄ መጠየቅ ነው፤ ማለትም ሐያሲ፥ “ደራሲው ድርሰቱን ሲጽፍ ሲነሳ ምን ለመግለጽ አስቦ ነበር? ሲገልጸው ያሰበው ነገር ተገቢ ነው ወይ? ደራሲው ድርሰቱን በመጻፉ በልቡ ያለውን ለመፈጸም ችሏል ወይ?” የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ይመራመራል፡፡ ለጥያቄዎቹም መልስ የሚያገኝላቸው፣ የሚመረምረውን ልብ ወለድ ድርሰት የታሪኩን አወራረድ፤ ታሪካቸው በድርሰቱ የተጻፈውን ሰዎች የጠባያቸውን፣ የባሕሪያቸውን፣ የሁኔታቸውን መስማማት ወይም መፋለስ በማመዛዘን፤ ደግሞም ከድርሰቱ ውስጥ አልፎ አልፎ ጥቂት መስመሮች መርጦ በጥብቅ በመመርመርና የደራሲውን የአእምሮ ኃይል በመገመት ነው፡፡

ደንበኛው ሐያሲ የመጣለትን ሐሳብ ሁሉ እንዲያው እንደመጣ ሳያገላብጥ፣ ሳያወጣና ሳያወርድ፣ እንዲሁም ሳያውል ሳያሳድር አይቀበልም፡፡ አስተያየቱም በመውደድ ወይም በጥላቻ ስሜት ላይ

አይመሠረትም። የወዳጆቹን መጻሕፍት አመስግኖ የጠላቶቹን ሳይነቅፍ፣ በትክክለኛነት ይፈርዳል። ደንበኛው ሐያሲ ቢያመሰግንም፣ ቢነቅፍም ጽሑፉን፣ ቢፈርድም በጽሑፉ ነው እንጂ በጻፈው ሰው አይደለም። (ማለት ደራሲው በያም ጊዜ ቢበላ፣ አግብቶ ቢፈታ፣ ወይም በሌብነት ቢያዝ መንፈሳዊ ተግሣፁን ከአምላኩ፣ ሥጋዊ ቅጣቱን አግባብ ካላቸው ባለሥልጣኖች ይቀበል እንደሆን እንጂ ድርሰቱ በወንጀሉ መሠረት ሊገመትበት አይገባም፤ አይቻልምም።) እንዲህ ያለው ሐያሲ፣ እውነተኛነት ከረቂቅ ስሜት ጋር አለው ማለት ነው። ሐያሲ ወገን ሳይለይ በገዛ እግሩ ራሱን ችሎ ሲቆም ሳይገዛ፣ ራሱን ሳይሸጥ፣ ደራሲዎች ጊዜና ጉልበታቸውን ጠቃሚና ቋሚ ለሆነ ሥራ እንዲያውሉት፣ አንባቢዎች ምርጡን ከምራጩ፣ ስንዴውን ከእንክርዳዱ ለይተው እንዲያውቁትና በእውቀታቸውም እንዲጠቀሙበት ከፍ ያለ እርዳታ ሊያደርግና ዋጋው በቀላሉ የማይገመት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

*(መንግሥቱ ለማ (1949 ዓ.ም.)፡፡ "የጥበበ ቃላት ክሪቲክ ፕሮብሌም በኢትዮጵያ" ከሚለው ጽሑፋቸው በመጠኑ ተሻሽሎና ታክሎበት የተወሰደ፡፡)*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ - አንብቦ መረዳት

፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።

1. በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ላይ ሚዛናዊ አስተያየት የሚያቀርብ ሰው በአማርኛ ምን ተብሎ ይጠራል?
2. በተለምዷዊው አገላለጽ ሥነጽሑፋዊ ሒስ ምንድን ነው? ምን ምን ጉዳዮችንስ ያካትታል?
3. በሥነጽሑፋዊ ሒስ ተግባር ውስጥ ፍከራ የምንለው ምን ዓይነቱን ተግባር ነው?

4. በተራ ሒስ እና በምሁራዊ ሒስ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
5. የደራሲነት ተሰጥዖ ያለው ሰው ስሜቱንና ሀሳቡን በቋንቋ ለመግለጽ፣ ማለትም መልካም ድርሰት ለመጻፍ ምን ያስፈልገዋል?
6. መስኮባዊው ሌዎ ቶልስቶይ እና እንግሊዛዊው ቤርናርድ ሾ በምሳሌነት የተጠቀሱት ስለምን ጉዳይ ለማስረዳት ዓላማ ነው?
7. ትውልድ ሁሉ ዘላለማዊ ዋጋ ያላቸውን መጻሕፍት የሚያከብራቸውና የሚወዳቸው ምንን መነሻ አድርጎ ነው?
8. ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ሀሳብ ሳይሆን፣ የሚያነቧቸው መጻሕፍት በሚይዙት ሀሳብ የሚመሩት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
9. እውነተኛነት ከረቂቅ ስሜት ጋር አለው የሚባለው ሐያሲ ምን ዓይነት ሐያሲ ነው?
10. አንድ ሐያሲ በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ላይ ሚዛናዊ ትችት ለማቅረብ ሲነሳ፣ የደራሲውን ሰብእና ከግምት ውስጥ ማስገባት የማይኖርበት ለምንድን ነው?
11. ሐቀኛና በራሱ የሚተማመን ሐያሲ ዋጋው በቀላሉ የማይገመት አገልግሎት የሚሰጠው ለማን ነው?
12. አንድ ሐያሲ አንድን የፈጠራ ሥራ በሚገመግምበት ጊዜ ለሚያነሳቸው ፈርጀ ብዙ ጥያቄዎች ተጨባጭ መልሶችን ያገኝ ዘንድ ምን ማድረግ አለበት?
13. ሦስት የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ስለሐያሲ ተግባር ያቀረቧቸው አስተያየቶች በምንባቡ ውስጥ ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚህን አስተያየቶች አንድ የሚያደርጋቸው መሠረታዊ የጋራ ጉዳይ ምንድን ነው?

**፪. ምንባቡን መሠረት አድርጋችሁ የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ትክክል ከሆኑ “እውነት”፤ ስህተት ከሆኑ ደግሞ “ሐሰት” በማለት እየለያችሁ ተናገሩ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡**

1. ከሥነጽሑፋዊ ሒስ ተግባር ዋናው ተጠቃሚ ሐያሲው ራሱ ነው፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

© MoE, FD
Not to be rep

2. ጽሑፉ ስለሥነጽሑፋዊ ሒስ ምንነትና ስለሐያሲ አስፈላጊነት የሚገልጽ ቢሆንም፣ በአብዛኛው ስለሐያሲ አስፈላጊነት ለማስረዳት የታለመ ነው፡፡
3. "ትውልድ አልፎ ትውልድ ሲተካ ዋጋቸው የማይቀንስ" የተባሉት መጻሕፍት ደራሲም ሐያሲም በሆኑ ሰዎች የተጻፉ ናቸው፡፡
4. ዘመን የማይሽራቸውን መጻሕፍት ተከታታይ ትውልዶች ሁሉ የሚያከብሯቸውና የሚወዷቸው በየዘመኑ ያለው መንፈስ፣ ሐሳብና አስተያት አንድ ዓይነት ስለሚሆን ነው፡፡
5. የሥነጽሑፍ ሐያሲ አንዱ ተግባር፣ በአለፉት ትውልዶችና በአሁኑ ትውልድ የሥነጽሑፍ ሥራዎች መካከል ድልድይ መሆን ነው፡፡
6. የአንድን ደራሲ ታላቅነት ለማወቅ ያን ደራሲ በእሱ ዘመን ካሉ ሌሎች ደራሲዎች ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ካለፉ አንጋፋ ደራሲዎች ጋር ማወዳደርና ማነጻጸር ያስፈልጋል፡፡
7. በአንድ የሥነጽሑፍ ሥራ ውስጥ የሚገኝ አስተያየት በአንድ ትውልድ መልካም እና ትክክለኛ ሊባል ቢችልም÷ በሌላ ትውልድ ደግሞ ከስሕተት ሊቆጠር ስለሚችል ለይተው የሚያስረዱ ሐያስያን ያስፈልጋሉ፡፡
8. ብዙ መጻሕፍትን አነበብንም አላነበብንም ልቦለድ ድርሰት ሊሰብከንና አስተሳሰባችንን ሊለውጠው ይችላል፡፡
9. ሦስቱ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ስለሐያሲ ተግባር ከአቀረቧቸው አስተያየቶች መካከል፣ የማቲዎስ አርኖልድ እና የሌዎ ቶልስቶይ አስተያየቶች የበለጠ የሚመሳሰሉት፣ የሐያሲ ዋና ተግባር አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ ድርሰቶችን ለይቶ ማመልከት መሆኑን ስለሚገልጹ ነው፡፡
10. ሐያሲ ከሚገመግመው ድርሰት ውስጥ ጥቂት መስመሮችን መርጦ በጥብቅ መመርመር ያለበት የደራሲውን የአእምሮ ኃይል ለመገመት እንጂ፣ ስለታሪኩ አወራረድ ለሚያነሳቸው ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት አይደለም፡፡

፫. ከምንባቡ በተወሰዱት በሚከተሉት ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት የያዙትን አውዳዊ ፍች ከገለጻችሁ በኋላ ተመሳሳይ ፈልጉላቸው፡፡

1. “ክሪቲክ” በመባል የሚታወቀው ሐሳብ <u>ግብሩንም</u> <u>ገባሪውንም</u> ያመለክታል፡፡
2. <u>ሀብተ ቅኔ</u>፣ <u>ሀብተ ድርሰት</u> የተሰጠው፤ መንፈሰ ፈጠራ ያደረበት ሰው የድርሰቱ ፍሬ ነገር የሚገለጽለት …
3. ያንኑም በቃላት መሣሪያነት የሚገልጸው አብዛኛውን ጊዜ <u>በተመሥጦ</u> ሁኔታ ላይ ሳለ መሆኑን ሶቅራጥስ ተገንዝቧል፡፡
4. የደራሲዎችና የሐያስያን ግብራቸው ተደጋጋፊ ቢሆንም ስጦታቸው <u>እየቅል</u> መሆኑንም አብራርቶ አስረድቷል፡፡
5. ከመጻሕፍቱ የሚያገኘውም ትምህርት፣ ምሳሌና <u>ተግሣፅ</u> በዚያው መጠን የተለየ መሆን አለበት፡፡
6. ይኸንንም በሥነጽሑፍ (በጥበበ ቃላት) <u>ረገድ</u> በሚገባ ለማጣራትና ለአሁኑ ትውልድ ለማስረዳት ደንበኛ ሐያሲ ያስፈልጋል፡፡
7. መጻሕፍቱም ጠቃሚነታቸው ሳይጓደል ከትውልድ ወደትውልድ በመተላለፋቸው ታላቅነታቸው <u>ጸድቆ</u> ይኖራል፡፡
8. <u>ራእይ</u> እንደሚታየው ሰው ናቸው፡፡
9. <u>በጎኛው</u>ን እየፈለገ ሲያገኘው ይህንኑ ለአንባቢዎች ማመልከት ነው፡፡
10. የሁኔታቸውን መስማማት ወይም <u>መፋለስ</u> በማመዛዘን

፬. በምንባቡ ውስጥ የተነሱት ዓበይት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? በየተራ እያነሳችሁ ተወያዩባቸው፡፡

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. ከምንባቡ የተወሰዱት የሚከተሉት ጥንድ ወይም ሦሉስ ቃላት እንዲሁም ሐረጋት ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ከገለጻችሁ በኋላ ልዩነታቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ፡፡



© MoE FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE
Not to be reproduced



| | |
|---|---|
| 1. ግምገማ፣ ግምት | 7. መጥፎ፣ ብላሽ፣ ብልሹ |
| 2. ፈራጅ፣ ተቺ | 8. ደገኛ፣ በጎኛ፣ ደህነኛ |
| 3. ደራሲ፣ ባለቅኔ | 9. ጠባይ፣ ባሕርይ |
| 4. ሐሳብ፣ አስተያየት | 10. ሀብተ ድርሰት፣ ስጦታ |
| 5. ሥነጽሑፍ፣ ጥበበ ቃላት | |
| 6. መፍታት፣ መተርጎም፣ ማብራራት | |

**፪. ከዚህ ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዳቸው በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ እያብራራችሁ ጻፉ፡፡**

1. የሰው ልጅ ሐሳብና አስተያየት ከዘመናት ጋር የሚለዋወጥ ነው፡፡
2. የምናነበው ልብ ወለድ ጽሑፍ ሊሰብከንና ግብራችንን ሊለውጠው ይችላል፡፡
3. ሐያሲ፣ ወገን ሳይለይ በገዛ እግሩ ራሱን ችሎ ሲቆም ሳይገዛ፣ ራሱን ሳይሸጥ ለደራሲዎች...እና ለአንባቢዎች...ከፍ ያለ እርዳታ ሊያደርግና ዋጋው በቀላሉ የማይገመት አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል፡፡

**ሐሳብን በራስ አባባል መግለፅ**

አንድን ሐሳብ ወይም አስተያየት በራሳችሁ አባባል ለመግለጽ በምትነሱበት ጊዜ የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ሞክሩ፡፡

- ረጃጅም ዓረፍተነገሮች የያዙትን ሐሳብ በአጫጭር ዓረፍተነገሮች መግለጽ፤ አጫጭሮቹን ዓረፍተነገሮች ደግሞ ማዋሃድ፤
- ዓረፍተነገር ለሚይዘው ሐሳብ ግልጽነት ሲባል፣ ቃላትንና ሐረጋትን ከቦታ ወደቦታ በማንቀሳቀስ አቀማመጣቸውን ማቀያየር፤
- ቃላትን ተመሳሳይ ፍች ባላቸው ሌሎች ቃላት መተካት፤
- በራስ አባባል የተገለጸው ሐሳብ ወይም አስተያየት ከዋናው ጽሑፍ የተለየ መልእክት እንዳይኖረው መጠንቀቅ፡፡

፫. በሐያሲ እና በዳኛ መካከል ሊኖር የሚገባውን የምግባር መመሳሰል መሠረት በማድረግ፣ ቢያንስ ሦስት አንቀጾች የሚኖሩት አስረጅ ድርሰት ጽፋችሁ አቅርቡ።

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ውስጥ ሁለት ጊዜ የሚያነቡላችሁን ከአንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ የግል የህይወት ታሪክ የተወሰደ ቅንጭብ ጽሑፍ በጽሞና አዳምጣችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የባለታሪኩ ሙሉ ስም ማን ነው?
2. የተወለዱበት ቀን፣ ወር እና ዓመት መቼ ነው?
3. የወላጆቻቸው ሙሉ ስም ማን እና ማን ይባላል?
4. የወላጆቻቸው የትውልድ ቦታስ የት ነው?
5. ባለታሪኩ የልደት ዘመናቸውን ሲነግሩን የጠቀሱት የመረጃ ምንጭ አለ። ይህ የመረጃ ምንጭ ምንድን ነው? ለምንስ የተጠቀሰ ይመስላችኋል?
6. ባለታሪኩ በተወለዱበት ጊዜ አባታቸው የሚኖሩት የት ነበር? ለምን?
7. እናታቸው ከአባታቸው ተለይተው ባለታሪኩ ወደተወለዱበት ቦታ እንዲሄዱ የተደረገበት ምክንያት ምን ነበር?
8. ከቀረበው ቅንጭብ ታሪክ ስለባለታሪኩ ምን ተረዳችሁ?

፪. በመምህራችሁ የታዘዙ ሁለት ተማሪዎች በኢትዮጵያ ሬዲዮ ብሔራዊ አገልግሎት የሚነበበውን የምሽት ዜና፣ ማስታወሻ እየያዙ ካዳመጡ በኋላ ዜናውን አሳጥረው በቃል ያቀርቡላችኋል። ተማሪዎቹ የሚያቀርቡትን ዜና በጽሞና ካዳመጣችሁ በኋላ፣ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ ተገቢ ምላሽ ስጡ።

1. እያንዳንዳቸው ካቀረቡት ዜና ምን ምን ጉዳይ አዳመጣችሁ?
2. ሁለቱ ተማሪዎች ያቀረቡትን ዜና ስታዳምጡ፣ ምን የአቀራረብና የይዘት ልዩነት አስተዋላችሁ?

© MoE, FDRE Not to be republished

፫. በመምህራችሁ የተመደቡ አሥር ተማሪዎች የሚመሠርቱት ቡድን ከልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ በማሰባሰብ ስለታዋቂዋ ሯጭ ስለደራርቱ ቱሉ የስኬት ጉዞ ያዘጋጁትን አጭር ጽሑፍ የቡድኑ ተወካዮች ያነቡላችኋል፡፡ ጽሑፉ ሲነበብ በሚገባ አዳምጣችሁ የቡድኑ አባላት ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ፡፡

## ክፍል አራት፡- መናገር

፩. ደራሲ ሁሉ ሐያሲ መሆን ይችላል ትላላችሁ? ለምን? ተወያዩበት፡፡

**በውይይት ጊዜ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች**

በውይይታችሁ ወቅት የሚከተሉትን ጉዳዮች ልብ በሉ!

- በተማሪነታችሁ ጥያቄዎችን የማንሳት እና አስተያየት የማቅረብ መብት እንዳላችሁ አትዘንጉ፡፡
- በጽሞና አዳምጡ፡፡
- ሌሎች እንዲሰሟችሁ አድርጋችሁ ተናገሩ፡፡
- የምታቀርቡት ሐሳብ በማስረጃ የተደገፈ ይሁን፡፡
- የሌሎችን ሐሳብ አታጣጥሉ፤ ስትነቅፉም በማስረጃ አስደግፋችሁ መሆን ይገባዋል፡፡
- የራሳችሁ ሐሳብ ብቻ ተቀባይነት እንዲያገኝ በመሻት በሌሎች ላይ ጫና አታሳድሩ፡፡

፪. ደራሲ ሁሉ ይብዛም ይነስ የሐያሲነት ሚና ይጫወታል፤ ምክንያቱም በፈጠራ ሥራው ውስጥ ሒስ አለ፡፡ ሐያሲ ሁሉ ከሞላ ጎደል የደራሲነት ድርሻ አለው፤ ምክንያቱም በሚያቀርበው ሒስ ውስጥ ፈጠራ አለ፡፡ ይህ አባባል እውነትነት አለው ትላላችሁ? ተወያዩበት፡፡

፫. የላቀ የፈጠራ ተሰጥዖ የሚጠይቀው ደራሲነት ነው ወይስ ሐያሲነት? ፍላጎታችሁን መሠረት በማድረግ መምህራችሁ በሁለት ቡድን ይመድቧችሁና ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተማራችኋቸውን የክርክር አቀራረብ ደንቦች በመከተል ማሳመኛ እያቀረባችሁ ተከራከሩ፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**በክርክር ጊዜ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች**

በክርክር ወቅት የሚከተሉትን ጉዳዮች ልብ በሉ!

- የመከራከሪያ ሐሳቦቻችሁን በወጉ አደራጁ።
- የመከራከሪያ ሐሳቦቻችሁን በቅደም ተከተል በመዘርዘር አቅርቡ።
- የመከራከሪያ ሐሳቦቻችሁ በማስረጃ (በምሳሌዎች፣ማገናዘቢያዎች፣ በአሃዛዊ መረጃዎች) የተደገፉ ይሁኑ።
- የተከራካሪን ወገን ሐሳብ በማስረጃ ውድቅ ለማድረግ ሞክሩ፤
- ለተከራካሪ ወገን ጥያቄዎች በአክብሮት ተገቢ መልስ ስጡ።

፬. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች "አጠቃሳይ እውነታ" ወይም "የግል አስተያየት" በማለት ከለያችሁ በኋላ፣ ምክንያት እያቀረባችሁ ተወያዩባቸው።

1. የሥነጽሑፍ ሐያሲ ለአንድ ሀገር ሥነጽሑፍ እድገት እጅግ አስፈላጊ ነው።
2. በሀገራችን መንግሥቱ ለማን የሚወዳደር ሐያሲ የለም።
3. ደራሲነትም ሆነ ባለቅኔነት ተሰጥዖን ይጠይቃሉ።
4. በቋንቋ ችሎታ ከልቦለድ ደራሲዎች ይልቅ ገጣሚዎች ይበልጣሉ።
5. ችሎታው ቢለያይም፣ ማንኛውም ጤነኛ ሰው የትኛውንም ቋንቋ ሊለምድ ይችላል።
6. "የልጅ አመሳሶ የለውም" እንደሚባለው ሁሉ፣ በመሠረቱ የቋንቋ ትንሽ እና ትልቅ የለውም።
7. ልቦለድ ከማንበብ ይልቅ፣ ድራማ መመልከት ያስደስታል።
8. ***የልምሻት*** ከተባለው የሐዲስ ዓለማየሁ ልቦለድ ይልቅ፣ ***ፍቅር እስከ መቃብር*** የተባለው ልቦለዳቸው ታሪክ ይማርካል።
9. ከበደ ሚካኤል፣ መንግሥቱ ለማ እና ፀጋዬ ገብረመድኅን ገጣሚም ጸሐፌ ተውኔትም ናቸው።
10. በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት 12ኛው የክፍል ደረጃ ተማሪዎችን ለከፍተኛ ትምህርት የሚያዘጋጅ ትምህርት የሚሰጥበት ነው።

## ክፍል አምስት:- ሥነልሳን

፩. ጽሑፎችን በማንበብም ሆነ ሰዎችን በመጠየቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተውሶ ቃላት:-

1. ከየትኛው ቋንቋ እንደተገኙ ግለጹ፡፡
2. ስያሜዎቹ ከመገኛው ቋንቋ በውሰት ሲወሰዱ፣ ምን ምን ዓይነት ሥነልሳናዊ ለውጦች እንደተደረጉ በማንሳት ተወያዩባቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ሃይማኖት | 6. መኪና | 11. ሻይ | 16. አውቶቡስ |
| 2. ሱቅ | 7. መሐንዲስ | 12. አናናስ | 17. ቢሮ |
| 3. ሸሚዝ | 8. ባርኔጣ | 13. ኮረንቲ | 18. ፕሬዚደንት |
| 4. ጠረጴዛ | 9. ሽንኬሎ | 14. ኮርኒስ | 19. ፋብሪካ |
| 5. ሰዓት | 10. ትሪ | 15. ራዲዮ | 20. ፓርላማ |

፪. የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ናቸው፡፡ ሰዋስዋዊ ስህተታቸው ምን እንደሆነ (የቁጥር፣ የፆታ፣ የጊዜ፣ የባለቤትና ግሥ አለመስማማት፣ የተሳቢ እና የገስ አለመጣጣም፣ የሐረግ አለመዛመድ፣ ወዘተ. በማለት) እየገለጻችሁ ዓረፍተነገሮቹን እንደገና አቃንታችሁ ጻፏቸው፡፡

1. በዓባይ ወንዝ ላይ ለሚሠራው ታላቁ የህዳሴ ግድብ የገንዘብ ድጋፍ ያደረጉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ብዙ ናቸው፡፡
2. ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ልማት ያስመዘገበችው አመርቂ ውጤት በበለጸጉት ሀገሮች መንግሥታት ተመሰገነች፡፡
3. ግብጽ ባለፉት አምስት ወራት የሚገጥሟትን ችግሮች መለስ ብላ ለመመርመርና የልማት እቅዶችን ለመንደፍ አሁን ፋታ አግኝታለች፡፡
4. የሀገር መሪው ወገኖቻቸውን በመጨፍጨፋቸውና ሥልጣን ስላልለቀቁ በሠላም ወዳድ ሕዝቦች እና መንግሥታት ተወግዘዋል፡፡

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

5. አዲስ አበባ ከተማችን ከአፍሪካ አንደኛ ጽዱ ከተማ እንድትሆን ሁላችንም ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግለት ይገባል፡፡
6. ድርጅታችን የሚያስመጣቸውን ሁሉንም ሸቀጦች አንድም ሳያስቀር ሸጦታል፡፡
7. ኅብረተሰቡ ጥፋተኞችን በማጋለጥ ከፖሊስ ጎን እንዲቆምና ትብብር ለማድረግ ተጠየቁ፡፡
8. በስንፍና ቁጭ ብለው ሰው ከማማት የተገኘውን ሁሉ እየሠራችሁ ከድህነት መላቀቅ ሳይሻላቸው አይቀሩም፡፡
9. አማርኛን የሚማሩ የውጭ ሀገር ሰዎች የቋንቋው ሰዋስው ስለሚከብዳቸው አማርኛ አስቸጋሪ ቋንቋ መሆኗን ይናገራሉ፡፡
10. ደራሲ እና ሐያሲ ተጨባጭ መረጃ በሌለው ተገቢ ያልሆኑ ጉዳይ ላይ የሚነታረኩ ከሆነ ውዝግባቸው ለሥነጽሑፉ እድገት የሚያበረ ክቱት አስተዋጽዖ አይኖርም፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሥነጽሑፍ

፩. በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሱት የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች መካከል ሁለቱ ስለሐያሲ ተግባር ሲያስረዱ፣ በየዘመኑ ከተጻፈው ሁሉ ብልጫ ያለውንና ጥሩ የሚባለውን የሥነጽሑፍ ሥራ ለአንባብያን ማመልከት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለመሆኑ ብልጫ ያለውንና ጥሩ የሆነውን ለመምረጥ የሚያስችል ተጨባጭ መመዘኛ አለን? ካለ ምንድን ነው ትላላችሁ? ተወያዩበት፡፡

፪. በምንባቡ ውስጥ፣ ከመጨረሻው አንቀጽ ቀደም ብሎ በሚገኘው አንቀጽ ውስጥ፣ ደንበኛ ሐያሲ አንድን ልቦለድ ድርሰት ለመተቸት ሲነሳ ሊጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎችና ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ተዘርዝረዋል፡፡ የሚከተለው ቅንጫቢ ጽሑፍ በየትኛው ጉዳይ ላይ ያተኮረ ትችት እንደያዘ ለይታችሁ ተናገሩና በሒሳዊ አስተያየቱ ተገቢነት ላይ ተወያዩበት፡፡

ደራሲ በአሉ ግርማ በሁሉም ልቦለዶቹ ውስጥ ህይወት ያላቸው፣ ሰው መሆናቸው በግልጽ የሚታይ፣ ከአንባቢ አእምሮ የማይጠፉ ሴት

© MoE, FDRE Not to be republished

ገጸባህርያትን ቀርጿል፡፡ እነዚህ በእውኑ አለም የሚያጋጥሙ አይነት ሴቶች ደምቀው የሚታዩና የሆነ ሳቢ ሀይል ያላቸው ናቸው፡፡ የበአሉ ሴቶች ከመናገራቸው በፊት እንባቸው የሚቀድም፣ በረባ ባልረባው የሚነፋረቁ ድኩማን አይደሉም፡፡ አንገታቸውን ደፍተው በወንዶች ስር የሚንከላወሱ ከልታማዎችም አይደሉም፡፡ ለማንኛውም ድርጊት የወንዶችን ትእዛዝ፣ የወንዶችን ቀዳሚነት የሚጠብቁ የራሳቸው አቋም የሌላቸው ሆነው አልተቀረጹም፡፡ የሱ ሴቶች አንገታቸውን ቀና አድርገው የሚሄዱ፣ ጮክ ብለው የሚናገሩ፣ ወንዶችን የሚጋፈጡና ያፈተታቸውን የሚሰሩ ብርቱዎች ናቸው፤ ነገረስራቸው ሁሉ ድብን ያለ፡፡ ሲያጠምዱ ሲይዙ፣ ሲወዱ ሲጠሉ፣ ሲያባልቱ ሲያመሩ፣ ሲሰጡ ሲቀበሉ፣ አጠንክረው ነው፡፡ ጥብቅ አድርገው፡፡ …

"ማንም ወንድ ሉሊትን ተራምዷት ሊሄድ አይችልም" (***ከአድማስ ባሻገር***፣ 41) በማለት ኩሩነቷን ያሳየችው ሉሊት ታደሰ፣ "ከኔ እርካታ የሚያገኝ ወንድ የለም፤ እኔ ለወንዶች ምን ጊዜም የውሃ ጥም ነኝ" (***የቀይ ኮከብ ጥሪ***፣ 38) ብላ ለወንድ ደንታ ቢስነቷን ያሳወቀችው ሂሩት ጉልላት፣ "እንዲህ እንደቀለድክብኝ አትቀርም፡፡ እኔም ተራዬን እቀልድብሃለሁ…እኔ ለባብሼና አጊጬ ብወጣ ሽህ አስከትላለሁ፡፡ ደሞ ላዲሳባ ወንድ" (***ደራሲው***፣ 17) እያለች ማንነቷን ለማሳወቅ የምትጥረው ጽጌ ሀይለማርያም፣ "ያባቴን ፈቃድ ለመፈጸም ለመስዋእትነት እንደበግ አልጎተትም" (***ሀዲስ***፣ 170) በሚል መራር ቃል የቆየውን ልማድ እምትቃወመው አይናለም ተካ፣ "ወንድ ቀንድ አስበቅላለሁ" (***ኦሮማይ***፣ 236)… "በወንዶች መጫወት ደስ ይለኛል" (358) በማለት ፍላጎቷን በግልጽ እምትናገረው ፊያሜታ ጊላይ፣ አምስቱም 'ሀይለኛ' ሴቶች ናቸው፡፡

የሀይለኝነታቸው ምንጭ ከተቀረጹበት የህይወት ቅንብብ፣ ከገቡባቸው ሁነቶችና ከሰብእናቸው የሚነሳና ከወንዶቹ ጋር ከሚፈጥሩት ግንኙነትና ለወንዶች ካላቸው አመለካከት በትይዩ ያለ ነው፡፡ አምስቱም ወንዶችን የመሳብ መግነጢሳዊ ሀይል አላቸው፡፡ አበራን፣ ደርቤንና ተፈራን፣

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

ሲራክን፣ ሀዲስን፣ ጸጋዬን በየፊናቸው ማርከው እንደየሁኔታው በስራቸው አድርገዋል። የፈለጉትን የማግኘትና ለግባቸው በቁርጥ ውሳኔ የመኀዝ ሀይል አላቸው። አምስቱም ወንዶችን የማገዝ፣ ከገጠማቸው ችግር ለመውጣት እንዲችሉ የመርዳት ሀይል ተሰጥቷቸዋል። ከአላማቸው ፍንክች ያለማለትም ብርታት አላቸው።

*(ዘሪሁን አስፋው፣ "የበአሉ ግርማ ሴቶች አምስት ሀይለኞች"፣* ጥር 1986፣ ገጽ 20-21)

**፫. የሚከተለው ቅንጫቢ ጽሑፍ ሐያስያንን ከምግባር አንጻር በሁለት ከፍሎ ይገልጻቸዋል። ይህ አገላለጽ፣ ምሁራዊ ሒስ እና ተራ ሒስ በመባል ከሚታወቀው የሒስ አመዳደብ ጋር ያለውን ግንኙነት መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት።**

በየትም አገር አንዱ የሠራውን ሥራ አይተው የሚያመዛዝኑና ለሥራው ተገቢ ነው የሚሉትን ፍርድ የሚሰጡ ሰዎች ነበሩ። አሁንም አሉ። የነዚህ ዓይነቶቹ ሥራ በሁለት መንገድ የተከፈለ ነው። አንዳንዶቹ በአንድ ሥራ ላይ ያዩትን መልካም ነገርና ጉድለት አመዛዝነው ለመልካሙ የድጋፍና የምስጋና አስተያየት የሚሰጡ፣ ለጎደለው ማሻሻያና ማቃኛ ምክር የሚያቀርቡ ናቸው። እነሱም አሻሻይ ተቺዎች ይባላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ለዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የአንድን ሰው ስምና ሥራ ቢቻል ጨርሶ ለማጥፋት፣ አለዚያ ለማጉደፍ ሚዛንና ፍርድ በሌለው ሁኔታ በሚችሉት የቋንቋ አገላለጽ ሁሉ ነቀፋና ጥላቻ የሚያወርዱ ናቸው። እነሱም አፍራሽ ተቺዎች ይባላሉ።

(አቤ ጉበኛ (1961 ዓ.ም)። *የሐሜት ሱሰኞች፥* ገጽ 11)

**፬. በኢትዮጵያ ሬዲዮ ብሔራዊ አገልግሎት የሚቀርብን አንድ አጭር ትረካ በጽሞና አዳምጣችሁ፣ በመረጣችሁት አንድ ጉዳይ ላይ በማተኮር ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ሒሳዊ አስተያየት አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።**

**፭. ከዚህ በታች የቀረበው ንግግር በሀዲስ አለማየሁ *ፍቅር እስከ መቃብር* ውስጥ ከሚገኙት ዋና ገጸባህርያት አንዱ የሆነው የካሣ ዳምጤ (ጉዱ ካሣ) ንግግር ነው። የንግገሩ መልዕክት ምንድን ነው?**



© MoE, FDRE Not to be republished

“የማህበራችን አቋዋም የተሰራበት ስራት ልማዱ፣ ወጉ፣ ህጉ እንደህይወታዊ ስራተ ማህበር ሳይሆን ህይወት እንደሌለው የድንጋይ ካብ አንዱ ባንዱ ላይ ተደራርቦ የላይኛው የታችኛውን ተጭኖ የታችኛው የላይኛውን ተሸክሞ እንዲኖር ሆኖ የተሰራ በመሆኑ፣ ከጊዜ ብዛት የታችኛው ማፈንገጡ ስለማይቀርና ይህ ሲሆን ህንጻው በሙሉ እንዳይፈርስ እንደገና ተሻሽሎ ሰውን ከድንጋይ በተሻለ መልክ የሚያሳይ የህያዋን አቋዋመ ማህበር እንዲሰራ ያስፈልጋል፡፡ የዛሬው ስራተ ማህበራችን ሲሰራ በዚያን ጊዜ ለነበረው ማህበር እንዲህ ሆኖ መሠራቱ ጠቃሚ ኖሮ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለዛሬው ማህበር ጠቃሚ አለመሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የሆነ ሆኖ ማናቸውም ሥራት ማህበሩ ለዚያው ለማህበራዊ ኑሮው እንዲያገለግለው ሰው የሰራው ሲሆን፣ ማህበሩን ባሪያ አድርጎ እንዲገዛው መሆኑ ጣኦት በፈጣሪ ቦታ እንደማስቀመጥና እንደማምለክ ነው፡፡”

*(ሀዲስ አለማየሁ (1958 ዓ.ም.)፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር፣ ገጽ 122)*

**የሥነጽሑፋዊ ሒስ ምንነትና አስፈላጊነት ተጨማሪ ማብራሪያ**

ለራኔ ዌሌክ ስነጽሁፋዊ ሒስ የተወሰኑ ደራስያንን ስራዎች ተመልክቶ ጥንካሬና ድክመታቸውን በመለየት ዳኝነት መስጠት ብቻ አይደለም፡፡ ስለስነጽሁፍ ቲዎሪና መርሆች፣ ስለስነጽሁፍ ባህሪይ፣ ስለአፈጣጠር ምስጢሩ፣ ስለተግባሩ፣ ስለሚያስከትላቸው ውጤቶች፣ ከሌሎች ሰዋዊ ተግባራት ጋር ስለአለው ግንኙነት፣ ስለአይነቶቹ፣ ስለአጻጻፍ ዘዴዎቹ፣ ስለአመጣጡና ስለታሪኩ የሚሰነዘሩትን አስተሳሰቦች ሁሉ ያቅፋል፡፡… “ስነጽሁፋዊ ሒስ የስነጽሁፍን ታሪክ ማውሳትና የስነጽሁፍ ዘሮችን በአይነት በአይነት መመደብንና መግለጽን ይጨምራል፡፡ ስነጽሁፍ ምንድን ነው? ለምንስ ይጻፋል? ከሌሎች ሰዋዊ ጉዳዮች ጋርስ እንዴት ይዛመዳል? የሚሉ አጠቃላይ ጥያቄዎችን የሚይዝ ነው፡፡” በሌላ በኩል ደግሞ “የኪነጥበብ ስራዎችን መተንተን፣ ማጥናት መመዘን እንዲሁም ስራዎቹ የሚመዘኑባቸውን ኪነጥበባዊ መለኪያዎች፣ ዘዴዎችና መርሆች ማውጣት ነው” ተብሏል፡፡ …

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ስነጽሁፋዊ ሂስ ለደራሲው፣ ለአንባቢው፣ በአጠቃላይ ለስነጽሁፉ ያለው አስፈላጊነትና የሚሰጠው አገልግሎት የላቀ ነው፡፡ በአንድ ደራሲ ስራ ላይ የሚደረግ ስነጽሁፋዊ ሂስ የስራውን ድክመትና ጥንካሬ የሚያሳይ በመሆኑ፣ ደራሲው ጠንካራ ገጽታዎቹን በማወቅ በተከታይ ስራው ይበልጥ እንዲጠቀምባቸው፣ ደካማ ገጽታዎቹን ደግሞ በመተው የማሻሻያ ነጥቦችን እንዲፈልግ ያግዘዋል፡፡ የሂስ ቀዳሚው ተግባር ስራውን መርምሮ ፍርድ መስጠት በመሆኑ ደራሲው ያለበትን ደረጃ ሊያውቅ የሚችልበት አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በኪነጥበባዊ ተግባሩ ደረጃውን ተገንዝቦ ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚያውቅበትና የደራሲነት ብቁነቱን የሚያረጋግጥበት ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡ …

ስነጽሁፋዊ ሂስ ለደራሲው ብቻ ሳይሆን ለአንባቢውም ከፍ ያለ አስፈላጊነት አለው፡፡ ከስነጽሁፋዊ ሂስ መሰረታዊ ተግባራት አንዱ ስራውን ኪነጥበባዊ በሆነ መልክ መተንተን በመሆኑ፣ ስራው ሲተነተን ለአንባብያን ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ሀያሲው የሚሰጠው ትንታኔ የተደበቀውን የማውጣት፣ አሻሚውን የመለየት፣ የረቀቀውን የማቅለል እንዲሁም የተምሳሌቱን ትርጓሜ የመፍታት ተግባር ስለሚፈጽም አንባቢው ስራውን ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ ሊረዳው ይችላል፡፡ በዚህ አይነት የደራሲውን አላማም ሆነ የስራውን ይዘት ይበልጥ የመግለጽና የማብራራት አገልግሎት የሚሰጥ በመሆኑ ስነጽሑፋዊ ሂስ አስፈላጊነቱ ከፍ ያለ መሆኑ እውቅ ነው፡፡ …

(ዘሪሁን አስፋው (1992 ዓ.ም) ፡፡*የስነጽሁፍ መሰረታውያን*፣ ገጽ 353 እና 357)

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ሥነጽሑፋዊ ሒስ በዋናነት በፈጠራ ሥራዎች ላይ ሚዛናዊ ፍርድ መስጠት ስለመሆኑ ተረድታችኋል፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ የሥነጽሑፍ ሐያሲ መኖር አስፈላጊ ስለሚሆንባቸው ምክንያቶችም ተገንዝባችኋል፡፡ ዋና ዋና የሚባሉት የሥነጽሑፍ ሐያሲ ተግባራት፣ የሥነጽሑፍ ሥራን መርምሮ በጥንካሬና ድክመቱ ላይ ሚዛናዊ አስተያየት ማቅረብ፣ ከተጻፈው ሁሉ የተሻለው የትኛው እንደሆነ ለይቶ ማመልከት፣ እንዲሁም በደራሲውና በአንባቢው መካከል ድልድይ ሆኖ ማገልገል መሆናቸውንም አውቃችኋል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ ደራሲም ሐያሲም ሆነው የተገኙ አንዳንድ ሰዎች ቢኖሩም፣ ደራሲ ሁሉ የግድ ሐያሲ መሆን ስላለመቻሉ ተረድታችኋል፡፡ አንድን የሥነጽሑፍ ሥራ ስንተች የደራሲውን ማንነት መመዘኛ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን ልብ ብላችኋል፡፡ አንድ ሐያሲ አንድን የሥነጽሑፍ ሥራ ለመተቸት ሲነሳ ሊጠይቃቸው ስለሚገቡ መሠረታዊ ጥያቄዎች በቂ ግንዛቤ አግኝታችኋል፡፡ በተጨማሪም ከሥነልሳን እውቀት አንጻር አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች ስለተዋሳቸው ቃላት፣ እንዲሁም ስለሰዋስዋዊ ስህተት ዓይነቶችና ስህተቶቹን ስለማቃኛ መንገዶች አውቃችሁ በቂ ልምምድ አድርጋችኋል፡፡ አጠቃላይ እውነታንና የግል አስተያየትን የያዙ አገላለጾችን ልዩነት ተረድታችኋል፡፡ የቃላትን አውዳዊ ፍች መግለጽ ችላችኋል፡፡ በክርክር ጊዜ መደረግ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎችም አውቃችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሥነጽሑፋዊ ሒስ ምንድን ነው?
2. በአንድ ሀገር ውስጥ የሥነጽሑፍ ሐያሲ አስፈላጊ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
3. ዓበይት የሚባሉት የሥነጽሑፍ ሐያሲ ተግባራት ምንድን ናቸው?
4. አንድ የሥነጽሑፍ ሐያሲ አንድን የፈጠራ ሥራ ለመተቸት ሲነሳ ሊጠይቃቸው የሚገቡ ጥያቄዎች የትኞቹ ናቸው?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሒስን ምንነት በቃልና በጽሑፍ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በሚሰጡኝ ርዕሶች ላይ ሥርዓት ባለው መንገድ እከራከራለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን አዳምጬ እረዳለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በሒሳዊ የአነባበብ ሥልት አንብቤ እገመግማለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ሒሳዊ አስተያየት የያዘ አስረጅ ድርሰት እጽፋለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | አጠቃላይ እውነታ እና የግል አስተያየት የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን ለይቼ አሳያለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች አስተካክዬ እጽፋለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

# ምዕራፍ አራት

# ሥነጽሑፍ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:-**

- የሥነጽሑፍን ምንነት በቃልና በጽሑፍ ትገልጻላችሁ፤
- ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን፣ በተለይም ቃለ ተውኔትን፣ አዳምጣችሁ ትረዳላችሁ፤
- ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በሒሳዊ የአነባበብ ሥልት አንብባችሁ ትገመግማላችሁ፤
- የኢልቦለድን እንዲሁም የልቦለድን ምንነትና ባህርይ ትገልጻላችሁ፤
- በልቦለድና በኢልቦለድ ድርሰት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ታስረዳላችሁ፤
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ለይታችሁ ትገልጻላችሁ፤
- ለቃላት አውዳዊ ፍች ትሰጣላችሁ፤
- የተለያዩ ሀሳቦችን በራሳችሁ አባባል አብራርታችሁ ትገልጻላችሁ፤
- አጭር ልቦለድ ትጽፋላችሁ።

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ልቦለድ ጽሑፍ ከኢ-ልቦለድ ጽሑፍ ጋር በምን ይመሳሰላል? በምንስ ይለያል?
2. ያላችሁበት የክፍል ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ብሔራዊ ፈተና የምትወስዱበት የክፍል ደረጃ ነው። ፈተናውን ከወሰዳችሁ በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ስለመግባት ወይም አለመግባት አስባችሁ ታውቃላችሁ?
3. ወላጆቻችሁ፣ ዘመዶቻችሁ ወይም ጓደኞቻችሁ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚያስገባ ውጤት ካመጣችሁ እንደሚሸልሟችሁ ቃል ገብተውላችሁ ያውቃሉን? ቃል ተገብቶላችሁ ከሆነ ከፈተናው ጋር በተያያዘ ያሳደረባችሁ ስሜት ምንድን ነው?
4. እጅግ የሚያስደስት አንድ ነገር አጋጥሟችሁ በደመነፍስ ስትጮሁ ያዩ ወላጆቻችሁ ድንገት ጩኸታችሁን ከእብደት ጋር አያይዘውት ቢያስሯችሁ ምን ታደርጋላችሁ?

### "አልወደቅሁም!"
### (አጭር ልቦለድ)

### ክፍል አንድ

በብዙ ምክንያቶች ሰዎች "እንቅልፍ አጣን" ሲሉ ይሰማል። በርሱም ሳይደርስበት አልቀረም። ነገር ግን ሰኔ 29 ቀን ለ30 አጥቢያ ሌሊት የደረሰበት የተለየ ነበር። እቅጩን ለመናገር በዓይኑ እንቅልፍ አልዞረም። ከአንሶላዎቹ መካከል ሲትኮነኮን፣ ሲትመከመክ አደረ። ማን? አያሌው ይልማ። ለምን? የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና ውጤት ከነገዩቱ ፀሐይ ጋር ስለሚወጣ ነበር። የማታውን የራዲዮ ጥያቄና መልስ ሰምቷል። ባይሰማም ከሚሰሙት ጋር ነበር። የተስፋውና የምኞቱ መፈጸሚያ እንደተተረበ ተሰምቶታል። አዎን፣ ሲያልፍ ቤተዘመድ ሁሉ እንደሚሸልመው በተገባለት ቃል ያውቃል። መውደቅ በሐሳብ ብቻ እንደ እንዝርት ነዘረው።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

አያሌው የሚኖረው ከታላቅ ወንድሙ ከአቶ ተስፋዬ ጋር ነው፡፡ ተስፋዬ ነፍስ የሆነች መኪና አለችው፤ ቤቱም የዘነጠ ነው፡፡ አባቱ አቶ ይልማ ዳኛ ናቸው፡፡ ያን ሌሊት÷ "ስታልፍ የምገዛልህን አታውቀውም!" የሚለው የአቶ ይልማ ድፍን ቃልኪዳን የአያሌውን መኝታ ቤት ግድግዳ ሲደበድብ አደረ፡፡ አያሌው በክፍል ፈተና ዘወትር መልካም ውጤት ያገኝ ነበር፡፡ "እግዜር ያውቃል" ብሎ ከአሳቡ ለማምለጥ ሞከረ፡፡ ግን ፍርሃት፣ ይሉኝታ፣ የመውደቅ ወዮልኝ፣ ችኮላ፣… በሕሊናው መሰላል ተክለው ይወጡበት፣ ይወርዱበት ጀመር፡፡

አይነጋ የለም ነጋ፤ ወፎቹ ተንጫጩ፤ የኀዘን ይሁን የደስታ ግን አይታወቅም፡፡ ፀሐይቱም ልታበስር ወይም ልታረዳ በቶሎ እንደምትፈነጥቅ ተሰማው፡፡ ማለዳ ተነስቶ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደ፡፡ በስተምሥራቅ ዞረና ትንንሽ ጠጠሮችን ሰብስቦ፣ ጠጠሮቹን ከመሬት አስጣጥቶ፣ ሱሪውን ከጉልበቱ በላይ ከፍ አድርጎ ተንበረከከባቸው፡፡ ከዚያም የሚያውቃቸውን የጻድቃን ስሞች እየጠራ ጸለየ፡፡

"… ፈተና ባልፍ የሎተሪ ትኬት እገዛና አስር ሺህ ሲደርሰኝ ሦስት ሺህ ለማርያም፤ ሦስት ሺህ ለሚካኤል፤ ሦስት ሺህ ለገብርኤል …..." ይህን ዝግ ብሎ ቢያሰላው ዘጠኝ ሺህ ደረሰ፤ አንድ ሺህ ቀረ፡፡ "…አንድ ሺህ ለጊዮርጊስ…" አለ፡፡ ነገር ግን ጊዮርጊስ አሳነስከኝ ብሎ የሚጥለው መሰለውና ጨነቀው፡፡ "… ግዴለም ወዳጄ ጊዮርጊስ ላንተ ለብቻህ አንድ ትኬት ገዝቼ አሥር ሺህ አግኝቼ ሁሉንም ትወስዳለህ …" አለ፡፡

ከረጅም ጊዜ ጸሎት በኋላ መሬት ሳመና ተነሣ፡፡ ያሳዝናል፤ ከጉልበቱ ደም ይንጠበጠባል፡፡ ጠጠሮቹ ግማሽ ግማሽ ሳንቲም ከገላው ገብተው ኖሮ መራመድ ተሳነው፡፡ ሆኖም ደስ አለው፡፡ ወትሮ፣ ሰዎች ከጸሎት ጋር የደም መስዋዕት ያቀርቡ አልነበረምን? እግዜርስ ደሙን እያዘራ ሲለምነው ይጥለዋልን? መውደቅ በስሜት ብቻ ዘገነነው፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be reproduced

ከጸሎት ሲመለስ ያ ጉልበቱ ቆጠቆጠው። የኤሌክትሪክ ምሰሶ ተደግፎ ቆሞ ሳለ አንድ ነገር አስተዋለ - ጀንበር። ጀንበር የሚቀኑባት ናት፤ ሁልጊዜ ፈገግታ አይለያትም። ሌሊት ይመጣባታል፤ ጨለማ ይውጣታል፤ ደመና ይጐርሳታል። ግን ታሸንፋለች። ይህ እንኳ አልደነቀውም። ብቻ ጀንበር የምትደነቀው በፈገግታዋ ነው። በውድቅትም በትንሣኤም ሁል ጊዜ ፈገግታ አላት። ምንኛ የምታስቀና ናት?

“ድምፅ አለ!” አለና አንድ ጋዜጣ ሻጭ ከአሳብ ስጥመት አወጣው። ገዛ። ዓይኑን ጠራረገና አነበበ። አዎን መቶ ሃያ አምስት ብቻ አለፈ። ከእሳት እንደገባ ጅማት ኩምትር አለ። አንጀቱ ተሸማቀቀ፤ የልቡም ትርታ ቆመ። ቅልጥሙ ራደ፤ መንፈሱ ተሸበረ፤ ልቡም ፈራ። አንድ መቶ ሃያ አምስት ብቻ! ይህ ቁጥር አያሌውን ይጨምራልን? አዲስ ዓላማን ለአዲስ ግብ ሲጀምር፣ ለጥብጣብ መቁረጫ ያዘጋጀው የወርቅ መቀስ ከእጁ ላይ ሲቀልጥ ተሰማው። ተስፋውንም በብረት ምሳር መቁረጥ እንዳለበት ተረዳ። አንድ መቶ ሃያ አምስት ብቻ! ይህ አያሌውን አይደብልም፤ ይደብል ይሆን?

ከዚህ ቁጥር ልግባ በማለቱ ራሱን ነቀፈው። “ተስፋ የለኝም?” አለ። ለመጀመሪያ ጊዜ በሙሉ ልብ ሞትን ተመኘ። አንድ መቶ ... እነ ጋሼ፣ እነአባባ፣ እነእማማ፣ እነእቴሜቴ፣ እነእትዬ፣ እነእንትናዬ ምን ይሉ ይሆን? ከሕያዋን ዓይን ለመሰወር አንዲት ፉካ እንኳ አጣ? “ሞት አንድ ክፋት ቢኖረው ሲጠሩት አለመምጣቱ ነው” አለ።

ተኮናንቦ ከአንድ ቡና ቤት ገብቶ ስልክ ለመደወል ጠየቀ። “አሥር ሣንቲም ትከፍላለህ” አለችው÷ ኮረዳዋ። ከፈለ፤ ግን መደወል አልቻለም። አሳቡ ወደ ት/ቤቱ ዲሬክተር ነበር። ግን ወድቀሀል ቢሉትስ? ደግሞ ለመውደቁ ጥርጥር የለውም። ውርደት! ከኮረዳዪቱ ፊት ቢ... “መጣሁ ቆይ!” አለና ሔደ።



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

አያሌው በተፈጥሮው ጨካኝ አልነበረም። ግን ሕያዋን ለጥቂት ጊዜ ከሕልውና መዝግብ ተደምስሰው ውጤቱን ከሰማ በኋላ ነፍስ እንዲዘሩ ተመኘ። ወዲያው ደግሞ ምኞቱ ከንቱ መሆኑን ተረዳ። አንድ መቶ ሃያ አምስት! "ግራም ነፈሰ ቀኝ አላልፍም! ውጤት ሰማሁ አልሰማሁ ምን ይለያል?" አለ።

ከቤቱ ሔደና ነጠላውን አስቀመጠ። የተስፋዬ ሚስት መንበረ ከጓዳ ብቅ ስትል አየችው።

"እንደምን ሆንክ?" አለችው።
"ማ? እ ... እ ... እእኔ?"
"አሞሀል እንዴ አያሌው፣ ምነው ነጭህ ወጣ?"
"አ... አዎን አሞኛል...ደኅና ነኝ ... ራሴን ትንሽ አሞኛል...ደኅና ነኝ። በ...በ...በጣም" አለና ከመኝታ ቤቱ ገብቶ በሩን ዘግቶ ተኛ።

"እይ ወድቋል!" አለች መንበረ። አያሌውም ከወስጥ ሆኖ ሰማት። አረረ፤ መሔጃም አጣ። እንደሞተ ሰው ከአልጋው ላይ ዝርር እንዳለ አሸለበው። ሲነቃ ሰዓቱ አምስት ሰዓት ተኩል ሆኗል። ቶሎ ተነሣና ጠጉሩን አበጣጥሮ ወጣ።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አያሌውን እጅግ ያስጨነቀውና እረፍት የነሳው ችግር ምንድን ነው?
2. ለአያሌው ጭንቀት መባባስ ምክንያት የሆነው ዓቢይ ጉዳይ ምንድን ነው?
3. እስከአሁን ባነበባችሁት የታሪኩ ክፍል አያሌው የተጋጨው ከማን ጋር ነው?
4. በእስካሁኑ ንባባችሁ የታሪኩ ዋና ገጸባህሪያ ማን ሆኖ አገኛችሁት?

"ናሳምር!" አለ፥ ሊስትሮ። አያሌው ከመንገዱ ዳር ቆሞ ጫማውን አስወለወለ። ካለቀ በኋላ ጫማውን አቀርቅሮ ተመለከተው። ያች ታምረኛ ጀንበር አሁንም ከጫማው ውስጥ ገብታ ትስቃለች። ጫማው ያምራል። በርግጥም የተማሪ ጫማ አልነበረም። በሠላሳ አራት ብር የተገዛ የጣሊያን ሥራ ነበር። የሚሄደው መውደቁን ሊሰማ ነው። ታዲያ የጫማው ሽቅርቅርነት ምን ይባላል? ያስፈርድበት፣ ዳንኪረኛ ያሰኘው የለምን?

"ሊስትሮ! ሊስትሮ!" አለ።

"አቤት! አለን! አቤት!" እያሉ አምስት ሊስትሮዎች መጡ።

"ይህን ጫማ ማበላሸት የሚችል ማነው?" አለ። ሊስትሮዎቹ ተያዩና "ስክሯል" እየተባባሉ ሄዱ። በሰሞኑ ከበድ ያለ ዝናብ ባለመኖሩ ጭቃ እንኳን ማግኘት ቀላል አልነበረም። ቢሆንም ወደወንዝ ወርዶ ጭቃ ስላገኘ ቀባውና የጫማውን ጸዳል አበረደው። የተማሪ ጫማም አስመሰለው። ሳያውቀው የክፍል ጓደኞቹን አበበን፤ ተክሉን፤ ደምመላሽንና ዳዊትን አገኛቸው። ስሜቱን ለመደበቅ ቆረጠ።

"እንዴት ሆናችሁ?"አለ አያሌው።

"ሁላችንም ውሀ ጠጣን!" አለ ተክሉ። ሁሉም ሳቁ።

"ም .... ም .... ምን?"

"ጨረቃ ነካን እባክህ፤ አንተስ?" አለ ዳዊት።

"ገ ...ገና ልሔድ ነው። ለመሆኑ ስንት ልጅ አለፈ?"

"አይታወቅም። ዲሬክተሩ ያንተን ውጤት ብቻ ስለሚነግሩህ የሌላውን አታውቅም" አለ ዳዊት።

አያሌው ተለያቸው። ሆኖም ያንዱ ውድቀት የሌላው መዘባበቻ እንዳይሆን ያንዱን ሌላው አለማወቁ አስደሰተው። ዲሬክተሩን በልቡ አመሰገናቸው። ሆኖም ሔዶ መጠየቅ ፈራና መላ መታ። ከአንድ ከታላቅ ቡና ቤት ገብቶ ስልክ ደወለ።



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

“እኔ የአያሌው አባት ይልማ ነኝ፤ እባክዎን የልጄን ውጤት ሊነግሩኝ ይችላሉ?” አለ አያሌው በጕረነነ ድምጥ፡፡

“የለም ጌታዬ ልጁ ከዚህ ካልመጣ አንናገርም” አሉ ዲሬክተሩ፡፡

“አሀ! ገባኝ፤ ብቻ ልጄ በሒሳብ ደካማ ይመስለኛል፤ ማለፍ አለማለፉን እባክዎ ይንገሩኝ?” አለ፡፡

“ብቻ በስልክ እንኳ አይነገርም ነበር፤ ግን በሒሳብ…አዎን…ቆይ… በሒሳብ አልፏል፤ ሲ አግኝቷል፡፡”

“እግዜር ይስጥልኝ!” አለ አያሌው፡፡

በኃይል ተነፈሰና ፈገግ አለ፡፡

ግን ወዲያው ግንባሩን አኮማትሮ “አንድ መቶ ሃያ አምስት ብቻ” አለ፡፡ የተስፋው ቀንበጥ ሲቀጭ ታየው፡፡ ላብ አሰመጠው፡፡ ‘እነ አባባ፤ እነጋሼ …ምን ይሉኝ ይሆን?’ ወንበር ፈልጎ ቁጭ አለ፡፡ ሐሳብም ጭልል ወዳለ በረሃ ወሰደው፡፡

“ምን ይምጣ ጌታዬ?” የሚል መረዋ ድምጥ አነቃው፡፡ ባለድምጧ የቡና ቤት አስተናጋጅ ወይዘሮ ነበረች፡፡ ደነገጠ፡፡ ቡና ቤት መግባቱ ለስልክ እንጂ ለመብላት ለመጠጣት አለመሆኑ ታወሰው፡፡ ምላሱ ተሳሰረ፡፡

“ት… ት… ትትትኩስ ሻይ?” አላት፡፡

“ምነው በጠሐይ አያቃጥሎትም?” አለችው፡፡

“በ … በ … በረዶ ጨምሪበት!”

“ምን? ቡና በወተት ማለቶ ነው? ኡ- ኡቴ እርሶስ ተራቅቀዋል፡፡ ስንት ላምጣ?”

አያሌው ግራ ቀኙን ተመለከተ፡፡

“ብ … ብቻዬን ነኝ ዋ!” አለ፡፡

“እ … እ … ምን? አዎን እ … እሺ ሁለት ይሁን!” አለ፡፡ ልታመጣ ሔደች፡፡ አያሌው የመውደቅ ስሜት ሆድዕቃውን አራሰው፡፡ መንፈሱ ታወከ፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

"አንድ መቶ ሃያ አምስት" አለ፡፡

"ሔጀ ልስማ አልስማ" በሚለው ርዕስ ነገር ሁለት ተቃራኒዎች ይሟገቱበት ጀመር፡፡ አንዱ ወገን "ይለይልህ ጠይቅ!" ቢለውም ሌላው ወገን "ለይቶልሃል ከመቶ ሃያ አምስት ቁጥር የለህም" ይላል፡፡

ሁለት ስኒ ቡና በወተት መጣለት፡፡ ኮረዳዋ እየሳቀች ከጉኑ ወንበር ስባ ተቀመጠች፡፡ እርር አለ፡፡ ባለፈ የቡና ቤቱን ሰው ሁሉ በጋበዘም ነበር፡፡ ተሰማው፤ አያልፍም፤ ግን ወድቀሃል አልተባለም፡፡ አምሳ ሳንቲም አወጣና ከጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ከቡናው ሳይቀምስ እየተንገዳገደ ወጣ፡፡ በታክሲም ተሳፍሮ ወደ ት/ቤቱ ነጉደ፡፡ አንኳኳና ቢገባ ዋናውን ሳይሆን ምክትል ዲሬክተሩን አገኛቸው፡፡

"የፈተና ውጤት ለመስማት ነበር!" አለ፡፡

"ፈተና ስትገባ የያዝከውን መታወቂያ ወረቀት ይዘሃል?" አሉት፡፡

"አልያዝኩም!"

"ያለመታወቂያ ካርድ አትንገር ብለውኛል ዲሬክተሩ፤ አዝናለሁ" አሉት፡፡ ጠረጴዛውን በሁለት እጁ አነቀና እንባ ባቀረረ ዓይን እያስተዋለ "ስለገብርኤል፤ ስለማርያም፤ እንዲያው ባርባራቱ ታቦት ማለፍ አለማለፌን አይተው ይንገሩኝ!" አላቸው፡፡

ምክትል ዲሬክተሩ አዘኑለት፡፡ ስለታዘዙ ነው እንጂ፤ አያሌውነቱን ያውቃሉ፡፡ ወረቀት አገላበጡና ትክ ብለው አዩት፡፡

"በጠቅላላው ፈተና ... "

"ወደቅሁ አለፍሁ?" አለ በችኮላ፡፡

"አትንጦልጦል እኮ! በፈተናው..."

"እ! እ! ታዲያስ?" አለ በመንገብገብ፡፡

"አልፈሀል፤ ግን ... "

ሰማይና ምድር ተገላበጡበት፡፡ ከቶ ደስታም እንደሀዘን እንዲያ ያብረከርካልን? ያሰቡት ሲፈጸም ያሳብዳልን? ሁለት የእንባ ዘለላዎች በጉንጩ ላይ ኮለል ብለው ተሽቀለቀሉ፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

"ግን" አሉ÷ ምክትል ዲሬክተሩ ንግግራቸውን በመቀጠል:: "በያንዳንዱ ትምህርት ምን እንዳገኘህ ለማወቅ የመታወቂያ ወረቀትህን አሁን፣ አምን ለሰባት አምስት ጉዳይ ነው ትደርሳለህ ቶሎ ሄደህ አምጣ::"

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

፩. ከዚህ ቀጥሎ እስከአሁን ያነበባችሁትን የአጭር ልቦለዱን ታሪክ መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: የታሪኩን ዓውድ መሠረት በማድረግ ለጥያቄዎቹ ተገቢ የቃል መልስ ስጡ::

1. አያሌው ይልማ የሚኖረው ከማን ጋር ነበር?
2. አያሌው እንቅልፍ በዓይኑ ሳይዞር ያደረው በምን ምክንያት ነበር?
3. አያሌው ጀንበርን የሚቀናባትና የሚያደንቃት በምኗ ነው?
4. ከአንድ ቡና ቤት ገብቶ ስልክ ለመደወል ከጠየቀ በኋላ ለመደወል ያልቻለው በምን ምክንያት ነበር?
5. አያሌው ስለፈተና ውጤቱ እያሰበ እንዲጨነቅና የኀሊና ሙግት ውስጥ እንዲገባ ያደረጉት ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ምንና ምን ናቸው?

፪. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን አውዳዊ ፍች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከገለጻችሁ በኋላ ተመሳሳይ ፈልጉላቸው::

1. ...ነገር ግን ሰኔ 29 ቀን ለ30 <u>አጥቢያ</u> ሌሊት የደረሰበት የተለየ ነበር::
2. ...<u>እቅጩን</u> ለመናገር በዓይኑ እንቅልፍ አልዞረም::
3. ...ከአንሶላዎቹ መካከል <u>ሲትኮነኮን</u>፣ <u>ሲትመከመክ</u> አደረ::
4. ...መውደቅ በስሜት ብቻ <u>ዘገነነው</u>::
5. ...ከጸሎት ሲመለስ ያ ጉልበቱ <u>ቆጠቆጠው</u>::

© MoE, FDRE Not to be reproduced

6. ...<u>ለጥብጣብ</u> መቁረጫ ያዘጋጀው የወርቅ መቀስ ከእጁ ላይ ሲቀልጥ ተሰማው፡፡
7. ...ከሕያዋን ዓይን ለመሰወር አንዲት <u>ፉካ</u> እንኳ አጣ፡፡
8. ...ሆኖም ያንዱ ውድቀት የሌላው <u>መዘባበቻ</u> እንዳይሆን ያንዱን ሌላው አለማወቁ አስደሰተው፡፡
9. ...ጭቃ ስላገኘ ቀባውና የጫማውን <u>ጸዳል</u> አበረደው፡፡

## "አልወደቅሁም!"
## (አጭር ልቦለድ)

### ክፍል ሁለት

አያሌው ሌባ ሻይ እንደቀመሰ ሰው ከዳይሬክተሩ ቢሮ እየከነፈ ወጣ፡፡ ታክሲ አጣ፡፡ ቢያገኝም እስኪወጣና እስኪገባ የሚመሽ መሰለውና በእግሩ መረተተ፡፡ ያካባቢው ሰው ጉድ እስኪለው ድረስ በረረ፡፡ ከቤቱ ሲደርስ ያጥሩ መዝጊያ ተዘግቶ አገኘው፡፡ ሁለቴ በርግጫ አዳሸቀውና ሰበረው፡፡ ተስፋዬና መንበረ በመስኮት ደንግጠው አስተዋሉት፡፡ የቤቱን መዝጊያ በርግዶ ዘለለና ከመኝታ ቤቱ ገብቶ መታወቂያ ወረቀቱን ይፈልግ ጀመር፡፡ አይ የሚፈልጉት ነገር? ሲቸኩሉ እንደዚያ ዕቃ ይጠፋልን? መጽሐፍና ደብተር አገላብጦ ሲያጣበት ሲወረውር፤ ሲያጣበት ሲወረውር... ወለሉ በመጽሐፍ፣ በወረቀትና በደብተር ተሸፈነ፡፡ ኪሱን በመዳበስ እንዲሁ ሱሪውን፣ ኮቱን፣ ሸሚዙን ከወለሉ አነጠፈው፡፡ እንዲያ እንዲያ ሲል አገኘውና በመጣበት አኳኋን መታወቂያውን ይዞ እየተገላተመ ወጣ፡፡

ተስፋዬና መንበረ ክው ብለው ቆሙ፡፡ የመንበረ ግን ለብቻው ነበር፡፡ "ፈተና መውደቅ እንዲህ ያሳብዳል እንዴ?" አለ ተስፋዬ፡፡ "ምነው አያሳብድ! በየነጋው ትወድቅና ትወድቅና! ትለዋለህ ያላንተ ጠላት የለውም!" አለች መንበረ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be republished

"ማ?" አለ ተስፋዬ፡፡

"ማ ባዩ ነዋ!" አለች ጥርሷን ነክሳ፡፡

በጥፊ ጋጋት፤ በካልቾ ደገማት፡፡ የምላስ ኃይል ስለነበራት ስድብ አከናነበችው፡፡ ተናደደና ስኒውን ከነእግሩ አንስቶ ቢወረውረው ግንባሯን መታት፡፡ ከጥፊውም መራረቀላትና ገብቶ ከመኝታው ላይ ፎጣ ተከናንቦ ጋደም አለ፡፡ በአስር ደቂቃ ውስጥ መንበረ ልብሷን በሻንጣ አጭቃ ወደ እናቷ ቤት ሄደች፡፡ አያሌው እየከነፈ ተመለሰ፡፡ "ጋሼ! ጋሼ!" እያለ እየተምታታ ወደ ተስፋዬ መኝታ ቤት ሲያመራ፤ ወንበር አደናቀፈውና ወደቀ፡፡ ጠጠር የበላው ጉልበቱ ነዘረው፡፡ ተሥፋዬ ተናደደና ሁለት ጊዜ በጥፊ አጮኸው፡፡ "ምነው?!" አለ አያሌው በድካም፡፡ "ዝም በል!" አለውና ማጅራቱን አንቆ ከመኝታ ቤቱ አስገብቶ ከውጪ ቆለፈበት፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. አያሌውን ምን ዓይነት ምግባር ያለው ገጸባህሪ ሆኖ አገኛችሁት?
2. መንበረ እና ተሥፋዬ የተጋጩት በምንድን ነው?
3. አያሌው በጭንቀትና በችኮላ ምን ምን ያልተለመዱ ተግባራትን ፈጸመ?
4. ከዚህ በኋላ አያሌው ምን የሚያደርግ ይመስላችኋል? የታሪኩስ መጨረሻ ምን ይሆናል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

አያሌው መናገር ተሳነው፡፡ ነገሩ ሁሉ አዲስ ሆነበት፡፡ በመመስገን ፈንታ ጥፊ ለምን እንደተሰጠው አልገባህ አለው፡፡ አዎን፤ መስኮቱም በሩም ዝግ ነው፡፡ ተስፋዬ ኤሌክትሪኩን ስላቆመው (ባልቦላውን ስለነቀለው) መብራት አልነበረም፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቶ ይልማ የልጃቸውን ውጤት ለመስማት መጡ፡፡ አያሌው ግራ ገባው፡፡ ቢያዳምጥ ሠራተኛቸው አበራሽ እየተንፈቀፈቀች ስታለቅስ ሰማት፡፡

"ጋሼ አብዷል መሰለኝ" አለች። ሆዱ ባዶ ስለነበረ አቅም አነሰው። በተለይ የአባቱ መምጣት በቤተሰቡ ላይ የደረሰ አደጋ ለመኖሩ ምስክር ሆነው። ሆዱ ተንቦጫቦጨ፤ እንዳይጠይቅ ተቆልፎበታል። ወዲያው መላ መታ። ከመኝታ ቤቱ ኮርኒስ ላይ ወደቆርቆሮ መውጫ የጣራ መስኮት መኖሩን አስታወሰ። ወንበር ቀጣጠለና በኮርኒሱ ጣራ ወጥቶ በልቡ እየተሳበ፣ በቆርቆሮ ማገር እየተንጠላጠለ፣ የካርቶኑን ኮርኒስ እየረገጠ ከሳሎኑ (አባቱና ወንድሙ ከሚንሾካሾኩበት) ደረሰ። ሹክሹክታውን ከላይ ሆኖ አዳመጠ።

"አያሌው እውነት ወደቀ?!" አሉ አቶ ይልማ።

"አዎን ወደቀ" አለ ተስፋዬ።

"ድራሹን ያጥፋው! ዘር አሰዳቢ! በቃው እንግዲህ የትም ይድረስ።"

"አልበቃም፤ ገና ጉድ አለ።"

" የምን ጉድ?"

"ንዴት አሳብዶት የሚሠራውን አያውቅም! በጭራሽ አንጉል ሆኗል! አሁን ጉድጓድ እንዳይገባ እመኝታ ቤት ውስጥ ዘጋሁበት ..."

አያሌው ከላይ ሆኖ ድንግጥ አለ። አጥንቱ እንደሰም ቀለጠ። አካሉ ራደ። አብደሀል የተባለ አላበድኩም ብሎ ለመከራከር ይችላልን? ሞተሀል ተብሎ መቃብሩ የተማሰ፣ ልጡ የተራሰ ሰው አልሞትሁም ለማለት አቅምና ጊዜ ይፈልጋል። አብደሀል መባል አሳበደው። የያዘውን ለቀቀው። ይኸን ጊዜ ያረፈበት የኮርኒስ ካርቶን ቃ! ቃ! ቃቃቃ! አለና ይዞት ወረደ። ደመነፍሱን ተፍጨርጭሮ አንድ አግዳሚ ማገር አንቆ ተንጠለጠለ። ቤቱ ተተራመሰ። ቶሎ ብለው አወረዱትና እንገቱን ይደባብሱ ጀመር። ፈጥነውም ከሐኪም ቤት ወሰዱት። ሐኪሙም የእንቅልፍ መርፌ ወጋውና ከአንድ ብቸኛ ክፍል አስተኛው። ረኃብ፣ ድንጋጤ፤ ደስታ፤ ንዴት! ... ስላዋከቡት መናገር እጅግ አወከው።

በማግሥቱ ረኃብ በጧት ቀሰቀሰው። ዓይኑን ገለጥ ቢያደርግ ቤተሰቡ ተሰብስቦ ሲያለቅስ አየ። ዓይኑን ለመጠራረግ ፈለገ። ግን እጁ አልነቃነቅ

ስላለው ፍላጎቱን ሰረዘው፡፡ አዎን፤ አልተሳሳተም፤ ያለቅሳሉ፡፡ ልቡ ስንጥቅ አለ፡፡ ከቶ ማን ሞቶ ይሆን? ለመንቀሳቀስ ፈለገ፤ ግን አቃተው፤ እግሩን ለመሰብሰብ ሞከረ፤ ግን ከበደው፡፡ ሲገላበጥ ወደደ፤ ግን ደበተው፡፡ ዓይኑን ብቻ ሲያንከራትት ተስፋዬ ቀረብ አለው፡፡ "እኔ ማነኝ?" አለ ተስፋዬ፡፡

አያሌው ተገረመና ቁጭ ለማለት ሁለቱን እጁን ጐትቶ ትከሻውን እንደመስበቅ አለ፡፡

አይ የሰው ልጅ ጣጣ? አይ የሕይወት ትርኪምርኪ? አወይ አለመግባባት? ታወቀው፤ ተሰማው፡፡ እጅና እግሩ ተወጣጥረው ከአልጋው ብረት ጋር ተከርችመው ታስረዋል፡፡ አብደሀል መባሉ ተሰማውና በንዴት ጥርሱን አፋጨ፡፡ የወደቀ መስሏቸው ይሆን? አዎን፤ በአማርኛ ሲ፤ በእንግሊዝኛ ቢ፤ በታሪክ ሲ፤ በሒሳብ ሲ፤ በባዮሎጂ ሲ፤ በጂኦግራፊ ቢ አግኝቷል፡፡ በትክክል አልፏል፡፡

"ፍታኝ!" አለ፡፡ እንደመፍታት ቤተዘመዱ ይላቀሳል፡፡ በዚህ ጊዜ ዶክተሩ ገባና ሁለቱን ጣቱን ቀሰረ፡፡
"ይህ ስንት ነው?" አለው÷ አያሌውን፡፡ አያሌው በሒሳብ የኮሌጁን መግቢያ ፈተና እንኳ ማለፉን ማን በነገራቸው! እንግዲህ እንዴት ብሎ ማስረዳት ይቻላል? ሰዎች እብድ የሚሉትን ሁሉ ለአንድ ደቂቃ እንኳ በሙሉ ልብ እንዲሰሙ ማን በመከራቸው?
"ፍታኝ!" አለ አያሌው በንዴት፤
"የት ትሔዳለህ?" አለው ሐኪሙ፡፡
"ፈተና ስላለፍሁ የምስክር ወረቀቴን ዛሬ ነው የማገኝ!"
ሐኪሙ ወደተሥፋዬ እያመለከተ "ይኸ ማነው?" አለው፡፡ አያሌው በገነ፡፡ ደህና ነበር፡፡ አእምሮው በትክክል ይሠራል፡፡ እንዴት እብድ ይባላል?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

እርር አለ፡፡ ሠራተኞች ጠይብ፣ የምር ተናጋሪዎች እብድ የሚባሉበት ዓለም ምንኛ ጎደሎ ነው?

“ኸረ ስለእውነት አምላክ ፍቱኝ!” አለ፡፡ በእውነትም ድምጹ በሀዘን መንደ የተመታ ነበር፡፡ ዶክተሩ ዝቅ አለና፡-

“ተሻለህ?” አለው፡፡

“መቼ ታመምኩ?!” አለ፡፡

“ታዲያ ለምን ትናንትና ከጣሪያ ለመሰቀልና ለመታነቅ ሞከርክ?” አለ

“ማ? እ …እኔ? መቼ? ልታነቅ? አብደሀል እንዴ!” መናገር አቃተው፤ እውነትን መናገር እንደአቀበት መንገድ ያውካልን? መናገሩንስ በተናገረ፤ ግን ማን ይሰማል? አንዴ ዕብድ ተብሎ የለምን?

ሐኪሙ ወደ ሰዎቹ ፊቱን መልሶ “በደንብ አልተሻለውም፤ ነገሩ ፈተና ስለወደቀ የአእምሮ መቃወስ ይመስላል፡፡ ነገ አማኑኤል ሆስፒታል ቢሄድ አይከፋም” አለ፡፡

“ፈተና አልወደቅሁም!” አለ አያሌው፡፡

“ዝም በል አትለፍልፍ!” አለ ሐኪሙ፡፡

“አልወደቅሁም! አልወደቅሁም! አልወደቅሁም! አልወደቅሁም! አልወደቅሁም! አልወደቅሁም! አልወደቅሁም!…” እያለ በከፍተኛ ጩኸት ሐኪም ቤቱን ነቀነቀው፡፡ ሌሎች ሐኪሞች ፈጥነው መጡ፡፡

“ ምንድን ነው?! ምን በሽታ ነው?!” አለ አንዱ፤

“ እብደት!” አለ የበፊቱ ሐኪም፡፡

“ የእንቅልፍ መርፌ እንዲሰጠው!” አለ ሌላው፡፡

“ ልቡን ያደክመዋል!” ሲል ተቃወመ የበፊቱ ሐኪም፡፡

“አዎን እውነት ነው” አለ÷ አንድ ሌላ ሐኪም፤ “ብቻ በጩኸቱ እንዳ ንረበሽ እንጨት እናጉርሰው፡፡”

“አልወደቅሁም! አልወደቅሁም!…” አገሩን አደባለቀው፡፡ ብቻ ወዲያው አንድ ሰንሰለት ከአልጋው ብረት ጋር ቋጠሩና ከሰንሰለቱ ጋር የተያየዘ የእንጨት ኳስ አጐረሱት፡፡

"ኡዱኩም! ኡዱኩም! ኡዱኩም!..." እያለ በደከመ ድምፅ አቤቱታውን ቀጠለ። ሐኪሙ ቤተዘመድ እንዲወጣ አዘዘ። እነሱም እያለቀሱ "ሳይማሩ ቢቀርሳ!" እያሉ ወጡ። የአያሌው ጓደኞች የምስክር ወረቀታቸውን ሲቀበሉ እርሱ ከሐኪም ቤት አፉ ተለጉሞ፣ እጅ እግሩ ታስሮ መዋል ግድ ሆነበት።

"አዱኩም! አዱኩም! ..." አለ። ግን ማንም ሰሚ አልነበረም። ዓይኑ ክፍሉን ሲማትር አንድ ነገር አስተዋለ። ያች ጀንበር አሁንም እግሯን በመስኮት በመዘርጋት ትስቃለች። አወይ ዘወትር ፈገግታ! አወይ ዘወትር ደስታ! አናደደችው። አሁን ምን የሚያስቅ ነገር ከክፍሉ ውስጥ አለ?

"አዱኩም! አዱኩም!" አለ ለጀንበሯ። ዝም አለችው። አዎን፤ እናንተም ሔዳችሁ ጆሮአችሁን ከመዝጊያው ላይ ለጠፍ አድርጋችሁ ብታዳምጡ ይህን ቃል ትሰማላችሁ። ትርጉም ላታገኙበት ትችላላችሁ።

"አዱኩም! አዱኩም! አዱኩም!"

(ፍቅረማርያም ይፍሩ (1957 ዓ.ም)፡፡ *አዲስ ዘመን* ፡፡)

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፦ አንብቦ መረዳት

**፩. ከዚህ ቀጥሎ የአጭር ልቦለዱን ታሪክ መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የታሪኩን ዓውድ መሠረት በማድረግ ለጥያቄዎቹ ተገቢ የቃል መልስ ስጡ።**

1. ከቤተሰቡ አባላት መካከል አያሌውን አብዷል ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠራጠረው ማን ነው?
2. በመንበረ አስተሳሰብ አያሌውን ለእብደት ያበቃው ምንድን ነው?
3. የቤተሰቡም ሆነ የኅብረተሰቡ አባላት አሞታል ብለው እንዲጠራጠሩት ያደረጉ ስንት ያልተለመዱ የአያሌው አድራጎቶችንና ንግግሮችን እናገኛለን? በዝርዝር አስረዱ።



© MoE, FDRE Not to be republished

4. አያሌው ቡና ቤት ገብቶ ሻይ ሲያዝ በደመነፍስ "በ … በ … በረዶ ጨምሪበት!" ባላት ጊዜ አስተናጋጇ የሰጠችው ያልተጠበቀ መልስ ስለቋንቋ መሠረታዊ ባህርይና ስለንግግር ዐውድ ምን የሚያስገነዝበው ነገር አለ? ተወያዩበት፡፡
5. አያሌው ሐኪም ቤት በገባበት ጊዜ ሐኪሙ አያሌውን አንድ ጥያቄ ከጠየቀ በኋላ "በደንብ አልተሻለውም፤ ነገሩ ፈተና ስለወደቀ የአእምሮ መቃወስ ይመስላል፡፡ ነገ አማኑኤል ሆስፒታል ቢሄድ አይከፋም" በማለት ላመጡት ቤተሰቦቹ ሲናገር እንሰማዋለን፡፡ ይህ የሐኪሙ አነጋገር ደራሲው ስለዚያ ዘመን የህክምና ባለሞያዎች ሊያስተላልፈው የፈለገው ምን መልእክት መኖሩን ይጠቁማል?

**፪. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ዐውዳዊ ፍች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከገለጻችሁ በኋላ ተመሳሳይ ፈልጉላቸው፡፡**

1. <u>ሌባ ሻይ</u> እንደቀመሰ ሰው እየከነፈ ወጣ፡፡
2. እስኪወጣና እስኪገባ የሚመሽ መሰለውና በእግሩ <u>መረተተ</u>፡፡
3. ሁለቴ በርግጫ <u>አዳሸቀውና</u> ሰበረው፡፡
4. በመጣበት አኳኋን መታወቂያውን ይዞ <u>እየተገላተመ</u> ወጣ፡፡
5. ሊገላበጥ ወደደ፤ ግን <u>ደበተው</u>፡፡
6. በእውነትም ድምጹ በሀዘን <u>መንደ</u> የተመታ ነበር፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

፫. ያነበባችሁትን አጭር ልቦለድ አጠቃላይ ታሪክ እና መዋቅር በሚከተለው መንገድ አሳዩ፡፡

የልቦለዱ ርእስ፡-

መቼት፡-
ገጸባሕርያት፡-
ዋና ገጸባህርያት፡-
ንዑሳን ገጸባህርያት፡-

ዋና ገጸባህርይው ሊደርስበት ያሰበው ግብ፡-

ያጋጠመው ችግር፡-

ከችግሩ ለመውጣት ያደረገው የመጀመሪያ ሙከራ፡-

የሙከራው ውጤት፡-

ሁለተኛ ሙከራ፡-

የሙከራው ውጤት፡-

ሦስተኛ ሙከራ፡-

የሙከራው ውጤት፡-

የመጨረሻ መፍትሄ፡-

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

አንድ ቃል ብዙ ዓይነት ፍች እና የፍችም ማዕረግ ሊኖረው ይችላል፡፡ የአንድ ቃል ፍች በብዙ ስልት ሊጠብ፣ ሊሰፋ፣ ሊሻሻልና ሊወሰን ይችላል፡፡ አንድ ቃል መደበኛ ፍች ይኖረዋል፡፡ ለማጥበቡም ሆነ ለማስፋቱ፣ ለማሻሻሉም ሆነ ለመወሰኑ መሠረት የሚሆነው ያ የቃሉ መደበኛ ፍች ነው፡፡ የአንድ ቃል መደበኛ ፍች በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡

ሀ) የቃሉ ጥሬ ወይም ዝርው ፍች፡- እንግሊዝኛ ይህን ዓይነቱን ፍች "ሊትራል ሚኒንግ" ወይም "ዲኖቴሽን" ይለዋል፡፡ እኔ <u>እማሬ</u> ብዬዋለሁ፡፡

ለ) የቃሉ የምስጢር ወይም የዘይቤ ፍች፡- እንግሊዝኛ ይህን ዓይነቱን ፍች በብዙ ሥም ይጠራዋል፡፡ መደበኛው ግን "ኮኖቴሽን" ነው፡፡ ይህን ደግሞ <u>ፍካሬ</u> ብዬዋለሁ፡፡ ጉዳዩን በአንዲት ምሳሌ ማገናዘብ ይቻላል፡፡

በአማርኛ ***እባብ*** የሚል ቃል አለ፡፡ አለቃ ደስታ ተክለወልድ ባዘጋጁት ***ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*** ቃሉ የተፈታው እንደሚከተለው ነው፡፡

1. አንድስ ቅጤ፣ ጉሚት ገና እፍኝት፣ እግር አልባ መሬት በል በምድር የሚሳብ የሚጎተት የሚሰልክ፣ በደረቱ የሚሄድ፣ የሚዘል፣ የሚወረወር መርዘኛ አውሬ፡፡

2. ክፉ ተንኮለኛ ሰው፣ ነገረ መርዝ፡፡

በቁጥር "1" የተጠቀሰው የቃሉ እማሬ ሲሆን፣ በቁጥር "2" የተጠቀሰው ደግሞ የቃሉ ፍካሬ መሆኑ ነው፡፡ "እንደ እባብ ብልህ፣ እንደ እርግብ የዋህ ሁኑ" የሚለውም ምክር የተመሠረተው እባብ እና እርግብ ከተባሉት ቃላት ፍካሬ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት እርግብ እና እባብ በተለይ በጥንካሬ ተቃራኒ ናቸው፡፡ ይህን ሁለቱን ዓይነት ፍች<u> እማሬውንና ፍካሬውን አጠቃለን የመዝገበ ቃላት ፍች ልንለው እንችላለን</u>፡፡ ሕዝባዊ ነው፡፡ እንግዲህ በፍች በኩል ቃላት ለአንድ የኪነት ደራሲ በደምሳሳው በሁለት ዓይነት መንገድ፣ በሁለት ማዕረግ ያገለግሉታል ማለት ነው፡፡

ቃላት ሊጠቡ፣ ሊሰፉ፣ ሊሻሻሉ በአንድ ቃል ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡ በዚሁ ልክ አንድ ደራሲ የየቃሉን መደበኛ ፍች እንደተፈላጊነቱ መወሰን ይችላል፡፡

እዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ፡፡ የአንድ ቃል የእማሬም ሆነ የፍካሬ ፍችው ሕዝባዊ ነው ተብሏል፡፡ ምን ማለት ነው? ቋንቋውን የሚሠራበት ሕዝብ (ምሁሩንም አጠቃሎ) የቃሉን ሁለት ዓይነት ፍች ያውቀዋል፤ ይሠራበታል ማለት ነው፡፡

(ይህ አባባል በየቀበሌው፣ [በየክልሉ] የሚሠራበትን ልዩ ልዩ የአነጋገር ፈሊጥ አይመለከትም፡፡) ይህ ሕዝባዊ የሚሆነው የመዝገበ ቃላት ፍች የደራሲው የግል ሀብት አይደለም፡፡ ቋንቋውን የሚሠራበት ሰው ሁሉ ሀብት ነው፡፡ ደራሲውም ለጽሑፉ መነሻ የሚያደርገው የየቃሉን ሕዝባዊ ፍች ነው፡፡ <u>ይሁን እንጂ እሱ ደግሞ በኪነት ስጦታው አማካይነት የሚያበረክተው ፍች አለ፡፡</u> በዚሁ ልክ የሚሠራበትን ቃል ሕዝባዊ ፍችውን ሊያበለጽገው ይችላል፡፡ የግሉ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ለእኛም የሚያካፍለው የግሉ ካደረገው በኋላ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ስልት የሚገኘውን ፍች ግላዊ ፍች፣ ፍካሬውንም ግላዊ ፍካሬ እንበለው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ፍች በተለየ የሚሠሩበት ገጣሚዎች፣ ባለስለምኖችና ባለቅኔዎች ናቸው፡፡ የልብ ወለድ ጸሐፊዎችም አይብዛ እንጂ ይሠሩበታል፡፡

(ዮሐንስ አድማሱ (1966 ዓ.ም)፡፡ "ቃላትና የኪነት ጽሑፍ"፡፡ *አዲስ ዘመን ጋዜጣ፡፡* ተቀንጭቦ የተወሰደ)

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. ከዚህ ቀጥሎ ከአጭር ልቦለዱ የተወሰዱ ዓረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዳቸው በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ የያዙትን ሐሳብ በራሳችሁ አገላለጽ እያብራራችሁ ለእያንዳንዳቸው ባለአንድ አንቀጽ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡

1. ሕያዋን ለጥቂት ጊዜ ከሕልውና መዝገብ ተደምስሰው ውጤቱን ከሰማ በኋላ ነፍስ እንዲዘሩ ተመኘ፡፡




© MoE FDRE Not to be reproduced

2. የተስፋውና የምኞቱ መፈጸሚያ እንደተተረበ ተሰምቶታል፡፡
3. ሠራተኞች ጠይብ፤ የምር ተናጋሪዎች እብድ የሚባሉበት ዓለም ምንኛ ጎደሎ ነው?

፩. የልቦለዱን ታሪክ ከሦስት መቶ ባልበለጡ ቃላት አሳጥራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፪. ደራሲው በአጭር ልቦለዱ ውስጥ ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልእክት የሚያስረዳ ባለሁለት አንቀጽ ሒሳዊ ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፫. ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች የተማራችሁትን መነሻ በማድረግ፣ በልቦለድ እና በኢልቦለድ ድርሰቶች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ አሳዩ፡፡ ከዚያም በስዕላዊ መግለጫው የቀረቡትን ነጥቦች መሠረት አድርጋችሁ ልቦለድን እና ኢልቦለድን የሚያወዳድርና የሚያነጻጽር አንድ ድርሰት ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡




፬. ከዚህ በታች የቀረበው ጽሑፍ ከአንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ የግል የህይወት ታሪክ ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው፡፡ ይህን ድርሰት በሦስተኛ መደብ አንጻር ከተተረከ ልቦለድ ድርሰት እንዴት ለይቶ ማወቅ ይቻላል? ቀደም ሲል ባዘጋጃችሁት ጽሑፍ መመዘኛነት ገምግሙትና አስተያየታችሁን በጽሑፍ አስፍራችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

አንድ ቀን ወደዚያ ተማሪ ቤት ሄጄ ዋልሁና ለምሳ ተመለስሁ፡፡ ምሳ ከበላሁ በኋላም ወደ ተማሪ ቤት እንደምሄድ ዓይነት ከቤት ወጣሁና ሽቅብ ወደመስቀለሶስ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ከኋላዬ የሚይዘኝ ሰው የተከተለኝ እየመሰለኝ በየጊዜው እገላመጥ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን ዳገት ወጥቼ ዳኖት ከሚባለው ቀጣና ደረስሁ፡፡ ይኸውም የነመምሬ አብቴና የነአቶ ላቀው መንደር ነው፡፡ የመንደሩ ሰው እንዳያየኝ የሚጥሹን ቅጠል ከለላ እያደረግሁ ሁለተኛውን ዳገት ተያያዝኩት፡፡ በዚያ በገረረ የፀሐይ ሙቀት ስለተዳከምኩ አለከልክ ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ለመመለስ ተስፋ አልነበረኝምና ማረፊያ ከሚባለው ከላይኛው ቀጣና አፋፍ ደረስሁ፡፡ ይህ ስፍራ መንገደኞች ብርቱውን ዳገት ጨርሰው የሚያርፉበት ቦታ ነው፡፡ እኔም እዚያ ስደርስ ከፀሐይ ሙቀት እንዲጋርደኝ የትልቁን ቋጥኝ ጥላ ተገን አድርጌ ተጋደምሁ፡፡ አንድ ሰዓት ያህል እዚያ ተኝቼ እፎይ ካልሁ በኋላ የቀረኝን መንገድ ቀስ በቀስ ተጉዤ ማታ ለዓይን ሲይዝ መስቀለሶስ ከእናቴ ቤት ገባሁ፡፡

(መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (2002 ዓ.ም)፡፡ *ትዝታዬ፣ ገጽ* 26)

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

**፩. በኢትዮጵያ ሬዲዮ ብሔራዊ አገልግሎት የመዝናኛ ፕሮግራም የሚቀርብን አንድ የሬዲዮ ድራማ ክፍል በሚገባ አዳምጣችሁ የድራማውን መንፈስ እና መልእክት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላችሁ አስረዱ፡፡**

**፪. መምህራችሁ በመምህሩ መምሪያ የቀረበውን አንድ አጭር ተረት ሲተርኩላችሁ በጽሞና አዳምጡና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ተረቱ ስንት ገጸባህርያት አሉት?
2. የገጸባህርያቱ ስም ማን ማን ይባላል?
3. ታሪኩ የተፈጸመው መቼ እና የት ነው?
4. የተረቱ መልእክት ምንድን ነው?
5. የተረቱን መልእክት የሚገልጽ አንድ ምሳሌያዊ አነጋገር ፈልጋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be republished

## ክፍል አራት:- መናገር

፩. በቡድን ተከፋፍላችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና የደረሳችሁበትን በተወካያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::

1. አያሌው የማለፊያ ውጤት ባያመጣ ኖሮ የታሪኩ አካሔድ ምን ይሆን ነበር?
2. አያሌው ከእስር ቢፈታ የታሪኩ መጨረሻ ምን ይሆን ይመስላችኋል?

፪. በዚህ ምዕራፍ ሥር የቀረበው አጭር ልቦለድ ደራሲ፣ በዓለም ላይ የምንኖር ሰዎች ልማዳዊ አኗኗራችን በጭፍኑ ስለሚመራን ምንም ልብ ብለን ሳንመለከት የምንደርስበት መደምደሚያ ብዙ ሰዎችን ለእብደት ያጋልጣል ለማለት የፈለገ ይመስላል:: በዚህ ሐሳብ ትስማማላችሁን? በቃል አስረዱ::

፫. አያሌው ይልማ እብድ ተብሎ ለመታሰር የበቃው በራሱ መንቀዥቀዥ ነው እንጂ፣ ቤተዘመድ ሽልማት ለመግዛት ቃል መግባቱ ባስከተለው ጭንቀት ምክንያት አይደለም:: ይህን ሐሳብ ለሁለት ተከፍላችሁ ተከራከሩበት::

፬. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በሚከተለው ሰንጠረዥ ካመለከታችሁ በኋላ በተዘረዘሩት ነጥቦች ላይ በመመሥረት ስለአንድነትና ልዩነታቸው ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ማብራሪያ ስጡ::

| | አጭር ልቦለድ | ረጅም ልቦለድ |
|---|---|---|
| መለያ ባህርያት | | |
| የጋራ ባህርያት | | |

፭. አያሌው ከሌሎች ሰዎች ጋር ካደረጋቸው ንግግሮች መካከል አንዱን መርጣችሁ በማጥናት በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ተውኑት::

## ክፍል አምስት:- ሥነልሳን

፩. በምንባቡ ውስጥ "መረተተ"፣ "መንዶ"፣ "ተገላተመ" የመሳሰሉ አሁን በመደበኛው ቋንቋ ውስጥ ብዙም የማይሠራባቸው ብሉይ (አሮጌ) ቃላት ይገኛሉ:: እነዚህ ቃላት ከቋንቋ መወለድ፣ ማደግ እና መሞት ጋር ያላቸውን ዝምድና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::

© MoE, FDRE — Not to be reproduced

፪. ከብሉይ ቃላት በተጨማሪ፣ "እየተንፈቀፈቀች"ን እና "ቀጠቀጠው"ን የመሳሰሉ በመደበኛው አማርኛ ሳይሆን በአንድ አካባቢ ብቻ የሚያገለግሉ ዘዬ ቃላት በምንባቡ ውስጥ አሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ቀበልኛ (ዘዬ) ቃላት የሚፈጠሩት እንዴት ነው? ተወያዩበት፡፡

፫. በግዕዙ የአበዛዝ ሥርዓት መሠረት የቀረቡትን የሚከተሉትን ስሞች ነጠላ ቁጥር ከገለጻችሁ በኋላ፣ የብዙ ብዙ ሆነዋል የምትሏቸውን ስሞች እንደገና በተገቢው መንገድ አብዝታችሁ ጻፉ፡፡

*ምሳሌ፡- መጻሕፍቶች - መጽሐፍ - መጻሕፍት*

*ምሁራን - ምሁር*

| | |
|---|---|
| 1. አእማድ | 6. ድርሳናት |
| 2. አእዋፋት | 7. አብያተመጻሕፍት |
| 3. አረጋውያን | 8. ሊቃነመናብርት |
| 4. ምእመናን | 9. አብያተክርስቲያናቶች |
| 5. መምህራኖች | 10. ሊቃነጠበብቶች |

## ክፍል ስድስት፡- ሥነጽሑፍ

፩. የሚከተሉት አገላለፆች ከአጭር ልቦለዱ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በእያንዳንዳቸው ውስጥ የሚገኘው ዘይቤ ምን እንደሆነ ከገለጻችሁ በኋላ ዘይቤው ለአገላለጹ ለዛና ኃይል ያበረከተውን አስተዋጽዖ በቃል አስረዱ፡፡

1. መውደቅ በአሳብ ብቻ እንደእንዝርት ነዘረው፡፡
2. ተስፋዬ ነፍስ የሆነች መኪና አለችው፤
3. የአቶ ይልማ ድፍን ቃልኪዳን የአያሌውን መኝታ ቤት ግድግዳ ሲደበድብ አደረ፡፡
4. ፍርሐት፣ ይሉኝታ፣ የመውደቅ ወዮልኝ፣ ችኮላ፣... በሕሊናው መሰላል ተክለው ይወጡበት፣ ይወርዱበት ጀመር፡፡
5. ከእሳት እንደገባ ጅማት ኩምትር አለ፡፡
6. ተስፋውንም በብረት ምሳር መቁረጥ እንዳለበት ተረዳ፡፡
7. "ሞት አንድ ክፋት ቢኖረው ሲጠሩት አለመምጣቱ ነው፡፡"

8. ያች ታምረኛ ጀንበር አሁንም ከጫማው ውስጥ ገብታ ትስቃለች፡፡
9. አጥንቱ እንደሰም ቀለጠ፡፡

፪. በአጭር ልቦለዱ ውስጥ የሚገኙት ዐበይት ገጸባህርያት አስተሳሰብና ድርጊት ተአማኒ ነውን? ከገጸባህርያት አቀራረጽ መርሆች አኳያ ጥንካሬና ድክመታቸውን የሚገመግም ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

፫. ባነበባችሁት ልቦለድ ውስጥ ዘመኑንና ቦታውን(መቼት) ሊጠቁሙ የሚችሉትን የገጸባህርያቱን አነጋገሮች፣ አድራጎቶች፣ ቁሳቁስ እና የግብይይት አጋጣሚዎች እየዘረዘራችሁ ተወያዩባቸው፡፡

***ምሳሌ፡-*** *ሁለት ስኒ ቡና በወተት መጣለት፡፡ ኮረዳዋ እየሳቀች ከጐኑ ወንበር ስባ ተቀመጠች፡፡ … አምሳ ሳንቲም አወጣና ከጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ከቡናው ሳይቀምስ እየተንገዳገደ ወጣ፡፡*

፬. በልቦለዱ ውስጥ በሰው እና በሰው፣ እንዲሁም በሰውና በገዛ ኅሊናው መካከል የተፈጠረ ግጭት ያጋጥመናል፡፡ በተስፋዬ እና በባለቤቱ መካከል ለተፈጠረውና መንበረ በተስፋዬ ድብደባ ምክንያት ሻንጣዋን ይዛ ወደቤተሰቦቿ እንድትሄድ ሳደረጋት ግጭት የቀረበው መንስኤ ግጭት አሳማኝ ነው ትላላችሁ? ከግጭት ባህርያት አንጻር ጠንካራና ደካማ ጎኑን እየገመገማችሁ ተወያዩበት፡፡

**የግጭት ባህርያት**

*ለልቦለድ የጀርባ አጥንት የሆነው ግጭት እንዲፈጠር ሁለቱ ተጻራሪ ኃይላት እግጭት ውስጥ ገብተው ድርጊቶችን ይፈጽሙ ዘንድ በውል የሚታይ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም ዓላማ መኖር አለበት፡፡ ይህ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም ዓላማ **መንስኤ ግጭት** ይባላል፡፡ መንስኤ ግጭቱ የሚታመን፣ ግጭቱን ለመቆስቆስ ብቃት ያለውና በሰዎች ገጠመኝ ሊከሰት የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡*

© MoE, FDRE Not to be reprinted

ሌላው የግጭት ባህርይ በሁለት ተጻራሪ ኃይላት መካከል የሚኖረውን ግጭት የሚመለከት ነው፡፡ አቀንቃኙም ሆነ ተቀናቃኙ ገጸባህርያት በመንስኤ ግጭቱ የተነሳ ተገደው እግጭት ውስጥ ከገቡ በኋላ ለመሸናነፍ ወይም አላማን ለማሳካት ሲታገሉ መታየት አለባቸው፡፡ ይህን በሁለቱ መካከል የሚደረግ ትግል **ፍልሚያ** እንለዋለን፡፡ በዚህ ሂደት ሁለቱም ወገኖች ሲፋለሙና ሲፍጨረጨሩ ታሪኩ ልብ እየሰቀለ “የትኛው ያሸንፍ ይሆን? ወይስ የየትኛው አላማ እግቡ ይደርስ ይሆን?” እያስባለ ይጓዛል፡፡ በሁለቱ መካከል የሚደረገው ፍልሚያ እየተባባሰና እየከረረ ይሄድና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ይንራል፡፡ ይህ የግጭቱ ከፍተኛ የንረት ደረጃ **ጡዘት** የሚባለው ነው፡፡ ከዚህ በኋላ የከረረው እየላላ፣ የታሰረው እየተፈታ፣ የተቆለፈው እየተከፈተ በመሄድ ግጭቱ አንድ ዓይነት መፍትሄ፣ ውጤት ወይም መደምደሚያ ያገኛል፡፡ ይህ የግጭቱ መቋጫ **ልቀት** ይባላል፡፡ በግጭቱ መቋጫ በገጸባህርያቱ ላይ አንድ ዓይነት ለውጥ ይከሰታል፡፡

ገጸባህርያቱ እግጭቱ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት በነበሩበት ሁኔታ አይቆዩም፡፡ እግጭት ውስጥ የሚገቡት ተጻራሪ ኃይላት ተመጣጣኝ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ተመጣጣኝ ይሁኑ ሲባል በገቡበት ሁኔታ ውስጥ አንድን ዓላማ እግብ ለማድረስ ያላቸው ፍላጎት፣ በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወሰን ያላቸው አግባብ፣ በአጠቃላይ በመካከላቸው ያለው የተቀናቃኝነት ደረጃ ተቀራራቢነት ይኑረው ማለት ነው፡፡ በመካከላቸው በጣም የሰፋ ልዩነት ወይም መበላለጥ ካለ ገና ከመነሻው የኃይል አለመመጣጠን አለ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ያለ አለመመጣጠን ካለ፣ ለግጭቱ መነሻ ለሆነው ጉዳይ ያላቸው ፍላጎት፣ አመለካከት፣ አቋምና ዓላማ በእጅጉ ከተራራቀ ፍጭቱ ወይም ትግሉ እሚያጓጓ፣ እሚጥም ለመሆን አቅም ያንሰዋል፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

የልቦለድ ግጭት በሰዎች ገጠመኝ ሊከሰት የሚችልና የሚታመን መሆን ይኖርበታል። በእውኑ ዓለም ሊያጋጥም የሚችል ዓይነት ከሆነ ታሪኩም ተአማኒነት ይኖረዋል።

(ዘሪሁን አስፋው (1992 ዓ.ም)። የስነጽሁፍ መሰረታውያን። አ.አ.፣ ንግድ ማ.ቤት። ገጽ 173 — 175። ከመጠነኛ ለውጥ ጋር ተቀንጭቦ የተወሰደ)

፫. ያነበባችሁት አጭር ልቦለድ ከአርባ ሰባት ዓመት በፊት የተጻፈ ቢሆንም፣ አሁንም ግን የአንባቢን ስሜት የመያዝ አቅም አለው። ይህን አቅም የፈጠረለት ምኑ ይመስላችኋል?

፬. ባነበባችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ ጀንበር ቢያንስ ሦስት ቦታ ተደጋግማ ተገልጻለች። ለመሆኑ ጀንበር የምን ተምሳሌት ሆና የቀረበች ይመስላችኋል?

፭. ልቦለድ ድርሰት÷ የተጻፈበት ዘመን መስተዋት ነው ይባላል። ስለተጻፈበት ዘመን ኅብረተሰብ የአኗኗር ሥርዓት፣ አስተሳሰብና በአጠቃላይም ባህል ምን መረጃ እና እውቀት አገኛችሁበት? የዚያ ዘመኑ አኗኗርና አስተሳሰብ አሁን ካላችሁበት ዘመን አኗኗርና አስተሳሰብ ጋር በምን ይመሳሰላል? በምን ዓበይት ጉዳዮችስ ይለያል? ተራ በተራ ሀሳብ አቅርቡ።

፮. “ፈተና” በሚል ርዕስ አንድ አጭር ልቦለድ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡና የተሻለ ነው ተብሎ በመምህራችሁ ሲመረጥላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ስለሥነጽሑፍ ምንነት መሠረታዊ ግንዛቤ አግኝታችኋል። በኢ-ልቦለድ እና ልቦለድ ድርሰቶች መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት ለይታችሁ አውቃችኋል። በአጭር ልቦለድ እና በረጅም ልቦለድ መካከል ስላለ አንድነትና ልዩነትም ተረድታችኋል። አንድ አጭር ልቦለድም ጽፋችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ስለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች፣ እንዲሁም ስለቃላት አውዳዊ ፍች በቂ እውቀት አግኝታችኋል። ካነበባችሁት አጭር ልቦለድ የተወሰዱ ዓረፍተነገሮችን በራሳችሁ አባባል አብራርታችሁ ገልጻችኋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. “አልወደቅሁም!” በሚል ርዕስ የቀረበው አጭር ልቦለድ ዋና መልእክት ምንድን ነው?
2. አንድ ጽሑፍ ሥነጽሑፋዊ ነው የሚባለው ምን ሲሆን ነው?
3. በኢልቦለድ እና በልቦለድ ድርሰቶች መካከል ያለው ልዩነትና ተመሳሳይነት ምንድን ነው?
4. አጭር ልቦለድ እና ረጅም ልቦለድ ምን የጋራ ባህርያት አሏቸው?
5. የቃላት ፍካሬያዊ ፍች ከእማሬያዊ ፍቻቸው በምን ይለያል?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥነጽሑፍን ምንነት በቃልና በጽሑፍ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በተለይም ቃለ ተውኔትን አዳምጬ የተረዳሁትን እገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በሒሳዊ የአነባበብ ሥልት አንብቤ እገመግማለሁ፡፡ | | | |
| 4 | የኢ-ልቦለድን እና የልቦለድን ምንነት እንዲሁም ባህርያት ማስረዳት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | በልቦለድና በኢልቦለድ ድርሰት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት አብራራለሁ፡፡ | | | |
| 6 | የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ለይቼ መግለጽ፤ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | የተለያዩ ሃሳቦችን በራሴ አባባል አብራርቼ እገልጻለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺያቸውን እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 9 | አጭር ልቦለድ እጽፋለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስከትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

# ምዕራፍ አምስት

# ሰብዓዊነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ።
- በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ታስተካክላላችሁ።
- ወቅታዊና ማህበራዊ የሆኑ ጉዳዮችን አዳምጣችሁ የራሳችሁን አስተያየት ትሰጣላችሁ።
- የአንድን ሐሳብ ዋና ዋና ነጥቦች በንግግር ታቀርባላችሁ።
- በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ጭውውት ታደርጋላችሁ፤
- በቃለመጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ በንግግራችሁና በጽሑፋችሁ ትጠቀማላችሁ።
- የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻችሁን በማስታወሻ ትይዛላችሁ።
- የተለያዩ ጽሑፎችን ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ትተረጉማላችሁ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be republished

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሰብዓዊነት ምንድነው? እንዴትስ ይገለጻል?
2. ሰብዓዊ ድርጅቶች የበጎ አድራጎት አገልገሎትና ድጋፍ የሚያደርጉት ለማንና ለምን ይመስላችኋል?
3. ሰብአዊ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች እንዴት ያሉ ናቸው?
4. በአካባቢያችሁ ሰብአዊ አገልግሎት ስለሚያከናውኑ ድርጅቶች የምታውቁትን ተናገሩ፡፡

## ሰብዓዊነት

ሰብዓዊነት በሰብዓዊ ፍጡራን ህሊና ውስጥ የሚፈጠር የለጋስነት፣ የርህራሄና የአዘኔታ ምግባረ ሠናይ ባህርይ ነው፡፡ በዚህ ባህርይ ምክንያት የሚደረገው መነሳሳት በአንድ አካባቢ ብቻ ሳይወሰን፣ ጠባብ ወገንተኝነት ሳይኖርበት በየትኛውም ዓለም ለሰዎችና ለእንስሳት የሚፈጸም በጎ ተግባር ነው፡፡

ይህ የሰብዓዊነት ባህርይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስበቀስ በሰዎች አእምሮ ውስጥ እየሰረፀ፣ እያደገ፣ ደጋፊዎችንም እያገኘ የመጣ፤ ለተጐዱ፣ ግፍ ለተፈጸመባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጾታ፣ ብሔር፣ ሃይማኖትና ዘር ሳይለይ ያለአንዳች መድልዎ ድጋፍና ርዳታ የማድረግ በጎ ምግባር ነው፡፡ ሰብዓዊነት ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር ያለአንዳች ውዴታና ጥላቻ ሁሉን በእኩል ዓይን የሚያይና የሚቀበል ነው፡፡ የሴቶችን በወንዶች መጨቆን ይቃወማል፡፡ ለሴቶች መብት መከበር እውቅና ይሰጣል፡፡ ሰብዓዊነት በሰዎችና በእንስሳት ላይ የሚፈጸመውን የግፍ ድርጊት ሁሉ ይቃወማል፡፡ በተለይ ለአእምሮ ህሙማን ተገቢው እንክብካቤ ይደረግላቸው ዘንድ ያበረታታል፡፡ በየአገሩ የቀይ መስቀል ርዳታ ድርጅት መቋቋምንና ሰብዓዊ ተግባራቱን ይደግፋል፡፡ በመንግሥታት በተቋቋሙ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የሕግ እስረኞች ላይ የሚፈጸሙ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች እንዲሻሻሉ ይታገላል፡፡

በአገራችን ውስጥ ሰብዓዊነትን የሚያራምዱ በርካታ ድርጅቶች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- አበበች ጉበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር፣
- ሰላም የህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት፣
- የአረጋውያን መርጃ ድርጅት፣
- የጐዳና ተዳዳሪ እናቶችና ህፃናት መርጃ ድርጅት፣
- ሜሪጆይ የልማትና ተራድኦ ድርጅት፣
- ሰዎች ለሰዎች ድርጅት ወዘተ.

በአገራችን አገልግሎት ከሚሰጡ ሰብዓዊ ድርጅቶች መካከል “አበበች ጉበና የህፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር” የተባለውን ድርጅት ወስደን የተቋቋመበትን ዓላማና የፈጸማቸውን ጉልህ ተግባራት የድርጅቱ መስራች የሆኑትን የወ/ሮ አበበች ጉበናን ታሪክ መነሻ በማድረግ እስኪ እንመልከት፡፡

አበበች ጉበና ከአባታቸው ከአቶ ጉፋ ሄዩ ከእናታቸው ከወ/ሮ ወሰኔ ብሩ በቀድሞው ሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ ልዩ ስሙ ሸበል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተወለዱ። ጊዜው የኢጣሊያ ፋሺስት ኢትዮጵያን የወረረበት ዘመን ነበርና በተወለዱ በወራቸው አባታቸው በጠላት እጅ ተገደሉ። እናታቸው በባለቤታቸው ዕረፍት ምክንያት መሪር ሐዘን ተሰምቷቸው ልጃቸውን አበበች ጉበናን ለወላጆቻቸው ትተው ወደ ሌላ ሥፍራ ሄዱ። የአበበች ጉበና አያቶች በሚቱ ልጃቸው ምትክ ስለሚያይዋቸው በቅንጦትና በቅምጥል አሳደጓቸው። እድሜያቸው አሥራ አንድ ዓመት ሲሆን እናታቸው ወ/ሮ ወሰኔ፣ አበበችን ከአያቶቻቸው ነጥለው ወደሚኖሩበት አካባቢ ወስደው ብዙም ሳይቆዩ ዳሯቸው።

ወ/ሮ አበበች ተገድደው ያገቡትን ባልም ሆነ የመሠረቱትን ትዳር ባለመፍቀዳቸው በየጊዜው ወደእናታቸው ቤት ይሸሹ ነበር። እናት ደግሞ እየገሰጹ ወደባለቤታቸው ይመልሷቸው ነበር፡፡ ከጥቂት ሳምንታት

© MoE, FDRE Not to be republished

በኋላ ወ/ሮ ወሰኔ ድል ያለ ድግስ ይደግሱና የልጃቸውን ባልና ቤተሰቦች መልስ ይጠራሉ፤ እነሱም ይመጣሉ። ወ/ሮ አበበች ግን የግብዣው፣ የጨዋታውና የጭፈራው ሁኔታ ምንም ሳይጥማቸው እስከ እኩለ ሌሊት ቆይተውና አዘናግተው ከቤት በመውጣት እኩበት ደረባ ወይም ክምር ስር አደሩ። ጉህ ሳይቀድ እግራቸው ወደ መራቸው ተጉዘው ከሶስት ቀናት ተኩል በኋላ በሰዎች ድጋፍና እርዳታ አዲስ አበባ ደረሱ። ይሁን እንጂ አዲስ አበባ ዘመድ አዝማድ አልነበራቸውም። መሄጃ ስላልነበራቸው ከአራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት የእሳት አደጋ መከላከያ ግንብ ሥር ኩርምት ብለው ሳለ አቶ አሥራት የተባሉ ትልቅ ሰው በዚያ በኩል በአጀብ ሲያልፉ አይተዋቸው በማነጋገር ወደቤታቸው ወስደዋቸው በዚያ ይኖሩ ጀመር። ቤተሰቡንም እያገለገሉ ትምህርት እንዲማሩም ተፈቅዶላቸው ነበር።

ወ/ሮ አበበች እንደዋዛ የጀመሩት ትምህርት ተሳክቶላቸው በአንድ እህልና ቡና ላኪ ድርጅት ውስጥ በጥራት ተቆጣጣሪነት ተቀጥረው ሠርተዋል። ትዳራቸውን በፈቃዳቸው ከፈቱ ከሃያ ዓመታት በኋላ አቶ ከበደ ኮስትሬ የተባሉ በእድሜ የሚበልጧቸውን ሰው አግብተው በትዳር ኖረዋል። ወ/ሮ አበበች አቶ ከበደን ሲያገቡ አምስቱንም የአቶ ከበደን ልጆች እንደልጆቻቸው ተቀብለው፣ «ልጆቼ አይደሉም» ሳይሉ ተንከባክበው፣ መክረውና ገስፀው ለከፍተኛ ማዕረግና ለትዳርም ያበቋቸው ወ/ሮ አበበች እንደሆኑ ዛሬም ይመሰክራሉ። ወ/ሮ አበበች ግን የአብራካቸው ክፋይ የሆነ አንድም ልጅ የላቸውም።

ወ/ሮ አበበች አጠር ያሉ የቀይ ዳማ ሲሆኑ ደግነት፣ መንፈሳዊነት፣ ሩህሩህነትና አዛኝነት ከፊታቸው ላይ ይነበባል። በተለይ ትህትናቸው ከልብ ነው፤ የተቀባባ አይደለም፤ አጋጣሚን አይቶ የሚወይብ፣ አጋጣሚን አይቶ የሚፈካ ተለዋዋጭ ትህትና አይደለም። የወ/ሮዋ ትህትናና መንፈሳዊነት በውስጣቸው ሥር የሰደደ እውነት ነው። የወ/ሮ

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

አበበችን የሕይወት አቅጣጫ የለወጠው የወሎ ጉዟቸው ነበር፡፡ መስከረም 14 ቀን 1972 ዓ.ም. ግሸን ማርያምን ሊያነግሱ ወደ ወሎ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ያ ዘመን ደግሞ በአገራችን ድርቅ መጥቶ በሕዝብ ላይ መዓት ያወረደበት፣ ድርቅ ክንዱን አፈርጥሞ ሕይወት ያለውን ሁሉ የደቆሰበት ዘመን ነበር፡፡ ወ/ሮ አበበች ከግሸን ማርያም መልስ ደሴን አይዋት፡፡ ያይዋት፣ ያስተዋሏት ደሴ ግን የጠወለገች ነበረች፡፡ ሰው በመኖርና ባለመኖር፣ ሰመመን ውስጥ ያለ ሕፃን፣ ወይም ሽማግሌ ወይም አሮጊት፣ የተጨነቁ ጐልማሶች፣ ሲቃ የሚተናነቃቸው እናቶች፣ በዋይታ ላይ ያሉ ሕፃናት፣ ኧረ ስንቱ! ብቻ ወ/ሮ አበበች ደሴን ያገኙዋት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ነበር፡፡

መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደግሸን የተጓዙት ወ/ሮ ባዩትና ባስተዋሉት ነገር መንፈሳቸው ተነክቶ ያላሰቡትንና ፈጽሞ ያላለሙትን ነገር ለመከወን ቁርጥ ውሳኔ አደረጉ፡፡ የሙት እናቷን ጡት እየጠባች ያገኟትን ህፃን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ሰብዓዊነት ምንድነው?
2. ወ/ሮ አበበች ጉበና የት ተወለዱ?
3. ወ/ሮ አበበች ወደ ወሎ የሄዱት ለምንድነው?
4. ወ/ሮ አበበች ደሴን ያገኟት በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው?
5. ቀሪው የምንባቡ ክፍል ምን ሊሆን ይችላል?

»

ወ/ሮ አበበች ከደሴ ወደአዲስ አበባ ይዘው የተመለሱት ቤተልሔምን ብቻ አልነበረም ሌሎች ልጆችም ነበሩ፤ አንጀታቸው አልችል ብሎ፣ ሰብዓዊነት አሸንፎአቸው፡፡ ወደቤት ሲመለሱ ግን ከቤተሰቦቻቸውና ከባለቤታቸው የጠበቃቸው አቀባበል ለየት ያለ ነበር፡፡ ከባለቤታቸው ጋር ተጣሉ፤

© MoE, FDRE Not to be republished

እነዚህን በሞት መንጋጋ ውስጥ ሊለወሱ ጥቂት የቀራቸውን ሕፃናት ሕይወት ይዘው በመምጣታቸው እንደእብድ ታዩ፡፡ ግጭቱ እጅግ የከረረ ነበር፡፡ ከቤተሰቦቻቸውና ከሞቀ ትዳራቸው ጋር አብሮ ለመዝለቅ አንድ አማራጭ ብቻ ነበራቸው፡፡ ይኸውም ያመጧቸውን ልጆች ማባረርና መጣል፣ የግጭቱ፣ የጠቡም ምክንያት እነርሱ ናቸውና፡፡ ወይዘሮዋ ግን በተቃራኒው ወሰኑ፡፡ ከትዳራቸውና ከዘመዶቻቸው ይልቅ ዘመድ አልባ፣ ወላጅ አልባና ምንም ደጋፊ የሌላቸውን ልጆች መረጡ፡፡ ቅሌን ጨርቄን ሳይሉ ቀደም ሲል ዶሮ ያረቡበት የነበረ የቆርቆሮ ማዕድ ቤት ውስጥ ሃያ አንድ ልጆችን ይዘው ገቡ፡፡

በዚህም ምክንያት “ጭንቅላቷ ተነክቷል በሚል ባለቤቴም ቤተሰቡም በሙሉ ጠሉኝ” ይላሉ ወ/ሮ አበበች፡፡ የሃያ አንድ ህፃናትን ጉሮሮ ለመድፈን፣ የሃያ አንድ ሕፃናትን እርቃን ለመሸፈን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ያውጠነጥኑ ጀመር፡፡ በመጀመሪያ የነበራቸውን ልዩ ልዩ የወርቅ ጌጣጌጦች ሸጡ፡፡ በገንዘቡ እህል ሸምተው አስፈጭተው እንጀራ እየጋገሩ መሸጡን ተያያዙት፡፡ ቆሎ እየቆሉ፣ ዳቦ እየጋገሩ በመሸጥ በሚገኘው ትርፍ ልጆቻቸውን እየመገቡ፣ እርቃናቸውንም ይሸፍኑ ጀመር፡፡ ይህ የምግብ ዝግጅት በአሁኑ ጊዜም እንደተጨማሪ ገቢ ማስገኛ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ በዶሮ ቤት ውስጥ ሲኖሩ መኝታቸው መደብ ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ግን በሣር ፍራሽ ተለውጧል፡፡ ወ/ሮ አበበች ቆሎ፣ ጠላ፣ ጠጅ፣ እንጀራ በመሸጥና ሕፃናቱን በመንከባከብ ተስፋ ሳይቆርጡ ለስድስት ዓመታት በቆራጥነት ከቆዩ በኋላ ጥረታቸውን ያዩ ግለሰቦች፣ ለሀገር ለወገን በሚል ሁኔታ ጥረታቸውን የተመለከቱ መንግሥታዊ፣ ሕዝባዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም እጆቻቸውን መዘርጋት ሲጀምሩ፣ እሳቸውም ሰብዓዊ ተግባሮቻቸውንና ድርጅታቸውን ማጠናከር ቀጠሉ፡፡

ድርጅታቸውም በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት” ብሩህ ተስፋ የሕፃናት መንደርና ት/ቤት” በሚል በአገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት

(መያድ) ስም ተመዝግቦ ቆይቷል፡፡ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ደግሞ ስያሜውን በመለወጥ «የአበበች ጐበና ወላጅ አልባ ሕፃናት ማሳደጊያና ት/ቤት» ተባለ፡፡ በጥቂት ሕፃናት የተጀመረው ሰብዓዊ ተግባር በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ አድጎና ተመንድጎ በብዙ ማህበረሰባዊ ዕድገትና ልማት ውስጥ ተስፋፍቶ ማህበረሰቡን ለለውጥና ለእድገት በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት የድርጅቱ መጠሪያ “አበበች ጐበና የሕፃናት እንክብካቤና ልማት ማህበር” በመባል ይታወቃል፡፡



ክብርት ዶ/ር አበበች ጐበና

ድርጅቱ ላለፉት ሠላሳ ዓመታት የተሠማራባቸው የሥራ መስኮች:-

1. **የሕፃናት እንክብካቤ፣ ድጋፍና ጥበቃ:-** ለ120 ሕፃናት በአዳሪነት፣ ለ12,000 ወላጅ አልባና ደጋፊ ለሌላቸው ሕፃናት በየዓመቱ ድጋፍ በመስጠት ይንከባከባል፡፡ ለ472 ችግረኞች ጥበቃ፣ ድጋፍና መሠረታዊ ፍላጎትን የማሟላት ተግባር ያከናውናል፡፡ ሌላው በአገር ውስጥና በውጪ ቤተሰብ የማፈላለግ፣ ከቤተሰብ ጋር የማገናኘት በህፃናት መብት ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር ተግባርን ያከናውናል::



© MoE, FDRE Not to be republished

2. **በጤና መስክ፡-** ክሊኒኮችና ሆስፒታሎች እየሠራ ለሕዝብ ጥቅም አውሏል፡፡ በኤች አይ ቪ/ኤድስ ወላጆቻቸው ለሞቱባቸው ለ522 ወንዶችና ለ260 ሴቶች ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡ ኤድስን ለመከላከል እንዲቻል 850,000 ኮንዶሞችን አሠራጭቷል፡፡ ለ65,000 ህፃናት ተመጣጣኝ ምግብ በየዕለቱ ያቀርባል፡፡ የሕፃናትን ሞት ለመቀነስና ምጣኔ ሕዝብ ሥራ ላይ ይውል ዘንድ ለ600,000 ሕዝብ ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
3. **በትምህርት መስክ፡-** ድርጅቱ አፀደ ሕፃናት፣ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን እየሠራ ለትምህርት መስፋፋት ጉልህ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ መደበኛ ላልሆነና ለጐልማሶች ትምህርትም ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ አጫጭር የሙያና የቴክኒክ ሥልጠናዎችን እያካሄደ ይገኛል፡፡
4. **የተቀናጁ ሕፃናት ተኮር የከተማ ልማት ሥራዎች፡-** በዚህ ረገድ ከተከናወኑት አካባቢን ማልማትና ማሻሻል፣ ሴቶችን በተለያዩ ሁኔታዎች መደገፍና ራስ ማስቻል፣ ግንዛቤ በሁሉም መስክ ማስረጽ፣ የአካበቢን ንጽህና መጠበቅ ወዘተ. ይገኙበታል፡፡
5. **በገጠር የተቀነባበረ የማህበረሰብ ዕድገት መርሐግብር፡-** ድርጅቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የወተት ላሞች እርባታና ስርጭት፣ ክብት ማድለብ፣ የአትክልት ልማት፣ የጐጆ ኢንዱስትሪ፣ የደን ተከላ፣ የመስኖ ሥራ፣ የእርሻ ምርት ውጤት የማሳደግ፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እያከናወነ ይገኛል፡፡

እነዚህን ጠቃሚ ተግባራት በትክክል ለመከወን ድርጅቱ የአፈጻጸም ስልት ቀይሶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይኸውም፤

- ማህበረሰብን፣ የመንግሥት አካላትን፣ አጋር ድርጅቶችንና ባለ ድርሻ አካላትን በማሳተፍ፣
- ሥልጠናዎችንና የአገር ውስጥ አቅም ግንባታ በማመቻቸት፣
- ሥርዓተ ፆታ ላይ በመሥራት፣

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

- ሕፃናት ተኮር ሥራዎች ላይ ትኩረት በመስጠት፣
- ቅንጅታዊና የትስስር ሂደት በመፍጠር የማህበረሰቡን ወግና ልማድ በማክበር ውጤታማ ሥራዎችን ለመሥራት ድርጅቱ ባለው ሃይል በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። የድርጅቱ እንቅስቀሴ የሚደገፈው ከውስጥ ገቢና ከውጪ ከሚገኝ እርዳታ ነው። ለዚሁ ዓመት የታቀዱ ሥራዎች የተመደበው በጀት ሃያ ሚሊዮን ብር መሆኑ ታውቋል።

የድርጅቱን ሥራ የሚያከናውኑ ሠራተኞች ብዛት 237 ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ 117ቱ ሴቶች ናቸው፡፡

## ሽልማት

ወ/ሮ አበበች ጎበና ለሀገርና ለወገን ላበረከቱት የላቀ አስተዋጽኦ የጂማ ዩኒቨርሲቲ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል። ክብርት ዶ/ር አበበች ጎበና ዛሬም ድርጅቱን በዋና ሥራ አስኪያጅነት እየመሩ ናቸው። ድርጅቱ ላለፉት 30 ዓመታት ለሕዝብ ለሰጠው ቅን አገልግሎት ከተለያዩ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ መንግሥታዊ እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በርካታ ዋንጫዎችንና የምስክር ወረቀቶችን ተሸልሟል፡፡

ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና ከሁሉም የላቀ ትርጉምና ስሜት የሚሰጣቸው ልጆቻቸው በአካልና በአእምሮ ጎልምሰው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰው ማየት ነው።

ምንጭ
- አበበች ጎበና የሕፃናት ክብካቤና ልማት ድርጅት 27ኛ ዓመት መጽሔት 1999
- Abebech Gobena Yehetoanat Kebekabens Limat Mahimber. (Overview) 2011
- Abebech Gobena – Mother of Many-(leaflet)

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. በምንባቡ ውስጥ ሰብዓዊነት የተባለው እሳቤ የተገለፀው እንዴት ነው? አብራሩ፡፡
2. ሰብዓዊነት "በሰዎችና በእንስሳት ላይ የሚፈጸሙ የጭካኔ ድርጊቶችን ይቃወማል" ተብሏል፡፡ ይህ ሐሳብ ምን ማለት ነው? በምሳሌ እያስደገፋችሁ አስረዱ፡፡
3. ሰብዓዊ ድርጅቶች የበጎ አድራጎት አገልግሎትና የልማት ድጋፍ የሚሰጡት ለማን ነው?
4. "አበበች ጐበና የህፃናት ክብካቤና ልማት ማህበር" የተባለው ድርጅት የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?
5. ከምንባቡ በዋናነት የምንረዳው ስለምንድን ነው? በማስረጃ እያስደገፋችሁ አስረዱ፡፡

**፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በምንባቡ መሠረት ይበልጥ የሚስማማውን ምረጡ፡፡**

1. ሰብዓዊነት ምን ዓይነት ባህርይ ነው?
   ሀ. በተፈጥሮ የሚገኝ
   ለ. በልምድ የሚገኝ
   ሐ. በትምህርት የሚገኝ
   መ. በሁሉም መንገዶች የሚገኝ
2. ከሚከተሉት ውስጥ ሰብዓዊነት በዓለማችን አስፈላጊ የሚሆንበት መሠረታዊ ምክንያት የትኛው ነው?
   ሀ. በርካታ ህዝቦች ችግረኞች መሆናቸው
   ለ. በበርካታ ህዝቦች ላይ የሚደርሰው ግፍና በደል
   ሐ. በርካታ ሕዝቦች ተጨቁነው መኖራቸው
   መ. ሁሉም



© MoE, FDRE Not to be reproduced

3. ለወ/ሮ አበበች ጉበና 1972 ዓ.ም. የሕይወታቸው ጉልህ ዘመን የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
   ሀ. ከሥራ ስለተባረሩ
   ለ. ወላጃቸው ስላረፉ
   ሐ. የሰብዓዊነት ባህርይ ስለተቀረፀባቸው
   መ. ሁሉም
4. ወ/ሮ አበበች ሁለቱን ሕፃናት ይዘው ወደአዲስ አበባ ሲመለሱ የገጠማቸው ሁኔታ
   ሀ. አስደንጋጭ
   ለ. አሳዛኝ
   ሐ. አስደሳች
   መ. ሀ እና ለ
5. በዚህ ምንባብ ውስጥ የተጠቀሰው ሰብዓዊ ድርጅት በየትኛው ይካተታል?
   ሀ. በመንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት
   ለ. በውጭ ድርጅት
   ሐ. በመንግስታዊ ድርጅት
   መ. በመንግስት የንግድ ድርጅት

ë. የሚከተሉት ቃላት እና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች በጽሑፍ አብራሩ፡፡

1. ሰብዓዊ
2. ግብረሰናይ
3. በጎ ምግባር
4. መርሐግብር
5. ሥነ ምግባር
6. መድልዎ
7. መሠረታዊ ፍላጎት
8. መስረጽ
9. ባህርይ
10. ጠባይ



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፬. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር መስርቱ።

| | |
|---|---|
| 1. ለጋስ | 5. መለከፍ |
| 2. ርህራሄ | 6. አቅርቦት |
| 3. ማደጎ | 7. ተሞክሮ |
| 4. አበረታች | 8. ድጎማ |

፭. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።

| | |
|---|---|
| 1. ምርት | 6. ተዘነጋ |
| 2. ተጠናቀቀ | 7. በርካታ |
| 3. ድህነት | 8. አምራች |
| 4. መቅረፍ | 9. ህሙማን |
| 5. ጉልህ | 10. ጠባብ ወገንተኝነት |

፮. በምድብ "ሀ" ሥር ለሚገኙት ቃላት ተመሳሳይ ይሆናሉ የተባሉ ቃላት በምድብ "ለ" ሥር ተዘርዝረዋል። ደበልጥ የሚስማማውን እየመረጣችሁ አዛምዱ።


| ሀ | ለ |
|---|---|
| ------1. ተራክቦ | ሀ. አንባቢያን |
| ------2. ደምሳሳ | ለ. ዝምታ |
| ------3. ተደራስያን | ሐ. ግንኙነት |
| ------4. መርሕ | መ. ጠቅላላ |
| ------5. አርምሞ | ሠ. መመሪያ |
| ------6. ብስና | ረ. ልምድ |
| ------7. መናፍቅ | ሰ. ግሳት |
| ------8. ረኸጥ | ሸ. ቸር |
| ------9. ነጠፈ | ቀ. ተጠራጣሪ |
| ------10. ገጠመኝ | በ. ንቁ |
| | ተ. ደረቀ |
| | ቸ.ብርታት |
| | ኀ. ሰነፍ |

፫. በምድብ “ሀ” ሥር ለሚገኙት ቃላት ተቃራኒ ይሆናሉ የተባሉ ቃላት በምድብ “ለ” ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይበልጥ የሚስማማውን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ------1. አባሪ | ሀ. ነጠላ |
| ------2. ዘለገ | ለ. ገለልተኛ |
| ------3. እኩሌታ | ሐ. ቀዘቀዘ |
| ------4. ቡልኮ | መ. ዳበረ |
| ------5. ቆረቆዘ | ሠ. ልም |
| ------6. ግርድፍ | ረ. ሙሉ |
| ------7. ደነገገ | ሰ. አጠረ |
| ------8. ባዝራ | ሸ. ቸረ |
| ------9. ነፈገ | ቀ. ድንጉላ |
| ------10. ነፈረ | በ. ቀዘቀዘ |
| | ተ. አፈረሰ |

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

በኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ህፃናት መርጃ በ__________ ዓ.ም. ጠቅላላ የገቢ አርዕስት በመቶኛ




ምንጭ፣ የልብ ህሙማን ሕፃናት ድርጅት ከ1990-1994

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ምስል ላይ ተመሥርታችሁ በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ከበጎ አድራጊዎች በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተሰበሰበውን ገቢ የሚገልጽ አንድ አጭር ጹሑፍ አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. ከበጎ አድራጊዎች በጥሬ ገንዘብ ከተገኘው እና ከገቢ ማስገኛ የትኛው በምን ያህል ያንሳል? በማነፃፀር አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
3. ከበጎ አድራጊዎች በዓይነት የተገኘው እርዳታ ምን ምንን ሊይዝ እንደሚችል በመገመት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

፪. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ የሚገኝን አንድ መያድ (መንግሥታዊ ያልሆነ በጎ አድራጊ ድርጅት) በመጐብኘት ስለዓላማውና ዝርዝር ተግባሮቹ ቃለ መጠይቆችን በማቅረብና ከቃለመጠይቁ የተገኙ መረጃዎችን በሥርዓት በማደራጀት ከ500 ቃላት ባልበለጠ አንድ ጽሑፍ አዘጋጁ፡፡

**መረጃ ለማሰባሰብም፡-**

ሀ) በቡድን ሆናችሁ መረጃ ሊያሰባስቡ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አውጡ፤

ለ) ቃለመጠይቅ ለምታደርጉለት ድርጅት ወይም ግለሰብ ደብዳቤ ጻፉ፤

ሐ) በቃለ መጠይቁ ወቅት የቃለመጠይቁን ዓላማ የሚያስረዳ፣ አባላቱን የሚያስተዋውቅና ቃለመጠይቁን የሚያቀርብ የቡድን አባል መድቡ፤

መ) ቃለመጠይቁ እየቀረበ ምላሽ ሲሰጥ ማስታወሻ የሚይዝ የቡድን አባል መድቡ፤

ሠ) የተገኙትን መረጃዎች በቡድን አጠናቅራችሁና በጹሑፍ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ፡፡

፫. ስለሰብአዊነት ቃለመጠይቅ አዘጋጅታችሁ ልምድ ላላቸው ሰዎች በማቅረብና ይህን ጉዳይ የሚያብራሩ መጻሕፍትን በተጨማሪ በማንበብ ከሁለቱም ያገኛችኋቸውን ሐሳቦች አጠናቅራችሁ ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::

፬. ቀደም ሲል ከቀረበው ምንባብ በመነሣት በዶ/ር አበበች ጐበና ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎችን "የአበበች ጐበና እውነታዎች" በሚል በዓመተ ምህረት ቀደም ተከተል ዘርዝራችሁ ፃፉ::

*ምሳሌ፡-*

የአበበች ጐበና እውነታዎች

- አበበች ጐበና በ1928 ዓ.ም. ተወለዱ.

፭. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደየትዕዛዛቸው ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ ወይም ከአማርኛ ወደእንግሊዝኛ ተርጉሙ::

**ሀ. የሚከተሉትን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ዓረፍተ ነገሮችን ወደአማርኛ ተርጉማችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ::**

1. Ethiopia shares many things with the rest of the world.
2. It has its own cultural linguistic and historic identity.
3. A very special difference is that Ethiopia uses the Julian Calendar.
4. The Julian Calendar consist of thirteen months of which twelve months have thirty days and one month of five/six in a leap year.

**ለ. የሚከተለውን ጽሑፍ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሙ::**

1. ወ/ሮ አበበች ጎበና በሰላሌ አውራጃ ተወለዱ::
2. ጊዜው ፋሽሽት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን የወረረበት ጊዜ ነበር::
3. ወ/ሮ አበበች ጎበና የተዳሩትም በዚሁ ዘመን ነበር::



© MoE, FDRE Not to be reproduced

፮. የሚከተሉትን በዕለት ማስታወሻ አወሳሰድ ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ባለፈው ሳምንት በየዕለቱ ያከናወናችኋቸውን ትምህርታዊ ተግባራት አስታውሳችሁ በጽሑፍ አስፍሩና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. በሚቀጥሉት ሦስት ቀናት ውስጥ የሚያጋጥሟችሁን ነገሮች በዕለት ማስታወሻ መዝግቡና ለመምህራችሁ አቅርቡ፤ ከዚያም በሚሰጧችሁ አስተያየት መሠረት አሻሽላችሁ ጻፉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ

መምህራችሁ ከመምህር መምሪያ ውስጥ አንድ በመገናኛ ብዙሃን የተሳሰፈ ሳይንስ ነክ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ የሚቀርብላችሁን ጽሑፍ በጽሞና አዳምጡና መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የዓለማችን የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ መሄዱ በተለያዩ አቅጣጫዎች አሳሳቢ መሆኑ እየተነገረ ነው፡፡ እስኪ አሳሳቢ የምትሏቸውን አንዳንድ ጉዳዮች ዘርዝሩና በእያንዳንዱ ላይ ተወያይታችሁ መፍትሔ ይሆናሉ የምትሏቸውን ሐሳቦች አቅርቡ፡፡
2. በላቦራቶሪ ውስጥ ሊመረት ስለታሰበው ሥጋ አዳምጣችኋል፡፡ በቅርቡ ተመርቶ ገበያ ላይ ቢቀርብ ለመጠቀም በሰዎች ዘንድ ሊመጣ የሚችለው ሥነልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ ተወያዩ፡፡
3. ካዳመጣችሁት ጽሑፍ አንጻር ሳይንቲስቶች ሌላ ምን ነገር በላብራቶሪ አዘጋጅተው ሊያቀርቡልን ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?
4. ሰዎች ምርጫ ቢሰጣቸው በላብራቶሪ ከተገኘው ሥጋና በተፈጥሯዊ ሁኔታ ከተገኘው ሥጋ የቱን የሚመርጡ ይመስላችኋል? ለምን?
5. ተመራማሪዎቹ፣ በላብራቶሪ ተዘጋጅቶ በሚቀርበው ሥጋ የተዘጋጀ ውን በርገር መጀመሪያ የሚቀምስ ሰው እንፈልጋለን ያሉት ለምንድን ነው? ስለተመራመሩበት ጉዳይ እርግጠኞች አይደሉም ማለት ነው? አብራሩ፡፡

© MoE, FDR[E] Not to be rep[roduced]

## ክፍል አራት:- መናገር

### ፩. ከዚህ ቀጥሎ በተሰጡት ርዕሶች ላይ በቂ ዝግጅት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ።

1. በአካባቢያችሁ ካሉ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች መካከል ስለአንዱ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ፣ ድርጅቱ በሰብዓዊ አገልግሎት ለመሣተፍ ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች መነሻ በማድረግ ለክፍላችሁ ንግግር አድርጉ።
2. በአካባቢያችሁ ስለሚገኝ አንድ የሰብአዊ አገልግሎት ድርጅት መረጃ ሰብስባችሁ፣ ስላከናወናቸውና ወደፊት ሊያከናውን ስላቀዳቸው ተግባራት፣ ስኬቱንና ችግሮቹን በመጥቀስ ንግግር አድርጉ።

### ፪. ከዚህ ቀጥሎ በተሰጡት መመሪያዎች መሠረት ተግባራቱን ፈጽሙ።

1. በአንድ ሰብኣዊ ድርጅት ሥራ አስኪያጅና በአንዲት እርዳታ ፈላጊ ሴት መካከል የተደረገውን ጭውውት ከየቡድናችሁ ሁለቱን ባሕርያት ወክለው የሚጨዋወቱ ተማሪዎች ምረጡና ጭውውቱን ተከታተሉ። ከጭውውቱ ግርጌ የሚገኙትን ሁለት ጥያቄዎችም በቃል አብራሩ።

2. ጭውውቱን እንደምሳሌ በመውሰድ ከራሳችሁ ገጠመኝ አጭር የጭውውት ጸሑፍ አዘጋጅታችሁ ለቡድናችሁ አቅርቡና ተወዳደሩ። በቡድናችሁ በጋራ የተመረጠውንም ጭውውት ለጠቅላላው ክፍል አቅርቡ።

<u>**የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅና የእርዳታ ፈላጊ ሴት ጭውውት**</u>

| | |
|---|---|
| እርዳታ ፈላጊ ሴት:- | (የሥራ አስኪያጁን ቢሮ አንኳኩተው በመግባት) “ጤና ይስጥልኝ፤ እንደምን አደሩ?” |
| ሥራ አስኪያጅ:- | “ጤና ይስጥልኝ፤ ምን ልታዘዝ?” |
| እርዳታ ፈላጊ ሴት:- | “ባለቤቴ በሞት ከተለየኝ ሦስት ዓመት ሆኖታል። ሁለት የሙት ልጆችን ይዤ ያለረዳት በማሳደግ ላይ ነኝ። ይሁንና ኑሮን ልቋቋም አልቻልኩም፤ |

| | |
|---|---|
| | አቃተኝ፤ ታከተኝ፤ በልተን ከምናድርበት ምግብ ሳናገኝ የምንውልበት ቀን ብዙ ነው፡፡ ስለዚህ አባክዎ ድርጅትዎ ልጆቼን ተረክቦ እንዲያሳድግ ልኝ ወይም ደግሞ እኔው ጋ ሆነው እንዲረዳልኝ ለማመልከት ነው የመጣሁት፡፡" |
| ሥራ አስኪያጅ፡- | "እውነት ነው፤ከዚህ በፊት ብዙ እርዳታ እንሰጥ ነበር፡፡ አሁን አንቺ እንዳልሽው የኑሮው ሁኔታ እርዳታ ሰጪዎችንም እጃቸውን እያሳጠረብን ስለሄደ፣ በአሁኑ ጊዜ ጥያቄሽን ለመቀበል እንቸገ ራለን፡፡" |
| እርዳታ ፈላጊ ሴት፡- | "ጌታዬ! እባክዎ ጌታዬ! እኔ'ኮ የምገባበት ጠፍቶኝ ነው ወደርስዎ የመጣሁት፤ እባክዎ አይጨክኑ ብኝ፡፡" (በጣም እያነቡ) |
| ሥራ አስኪያጅ፡- | "አይ! እንግዲህ ያለውን ሁኔታ ነገርኩሽ፡፡ እኔ ምንም ሳደርግልሽ አልችልም'ኮ ነው የምልሽ!" (ቆጣ ብሎ) |
| እርዳታ ፈላጊ ሴት፡- | "ኧረ እባክዎ? ጌታዬ ይርዱኝ! እባክዎ ይርዱኝ!" |
| ሥራ አስኪያጅ፡- | "ነገርኩሽ'ኮ አሁን ምንም ሳደርግልሽ አልችልም፡፡ እስቲ ምናልባት እድሉ ካለ በሚቀጥለው ሳምንት ነይ!" |
| እርዳታ ፈላጊ ሴት፡- | እሺ ጌታዬ፣ አመሰግናለሁ፡፡ |

1. በጭውውቱ ላይ ምን አስተያየት አላችሁ?
2. ከጭውውቱ የተረዳችሁትን ነገር በአጭሩ በቃል ግለጹ፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

## ክፍል አምስት:- ሥነ ልሣን

በሚከተለው አጭር አንቀጽ ውስጥ የሚታዩትን ሰዋስዋዊ ስህተቶች የምን የምን ስህተቶች እንደሆኑ ከገለጻችሁ በኋላ ስህተቶቹን አርማችሁ አንቀጹን እንደገና ጻፉ፡፡

በጠቅላላው በኢትዮጵያ ከሚገኘው የውሃ አካል በብዙ ሺህ ቶን የሚገመት ዓሣ ይገኛል ተብሎ ይነገር ነበር፡፡ ይህ አባባል በአሁኑ ጊዜ እውነት መሆኑ አጠራጣሪ ሆነ፡፡ ለምሳሌ የዝዋይ ሐይቅ ዓሣ አልባ ከሆነ ሰንብተዋል፡፡ ከሀዋሳ ከጫሞና ከአባያ ሐይቆች በገፍ ከሚመረተው ዓሣዎች ውስጥ ተፈላጊና ውድ የሆኑት ነጭ ዓሣ ወይም ናይል ፐርች ለዘር ላይተርፍ እየጠፉ ነው፡፡ በሌላ ሐይቆች የሚገኘው ዓሣዎችም አደጋ እያንዣበበት ነው፡፡ የዝዋይ ዓሣ አስጋሪዎችና ነጋዴ ወደአቢያታ፣ ላንጋኖ ሀዋሳና አርባ ምንጭ እየወረደ ነው፡፡ አሁንም የጥፋት መረባቸውን አንግቦ አይሱዙ መኪናቸውን አስጠግተው ባለቤት የሌለውን ዓሣ ማጥመዱንና ለገበያ ማቅረቡ ይዘወተራል፡፡ እዚህ የሚገኘውን ዓሣ ለዘር ሳያስቀር ለሌላ የጥፋት ተልዕኮ ተጓዥ መሆናቸውን እንዳይነቃ ከአካባቢው አንዳንድ ዓሣ አጥማጆችና ነጋዴዎች ጋር ተመሳጥረው ለዳግም ጥፋት ዘምቷል፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የቀረበላችሁን ጽሑፍ አንብባችሁ በመረዳት፣ በተለያዩ ሰብዓዊ ተግባራት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ድርጅቶችንና የሚሰጧቸውን ግልጋሎት መግለጽ ችላችኋል፡፡ የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች በትክክል የማዛመድን፣ በአንቀጽ ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ለይታችሁ የማስተካከልንና በወቅታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያዳመጣችሁትን ጽሑፍ ስለአቀራረቡ፣ ስለሳቢነቱ፣ መልዕክቱ በተገቢው ሁኔታ ስለመተላለፉ አስተያየት የመስጠትን ክሂል አዳብራችኋል፡፡ ባዘጋጃችኋቸው ጽሑፎች ዋና ዋና ነጥቦች ዙሪያ ንግግር የማቅረብንና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ጭውውት የማካሄድን ጥበብ አውቃችኋል፡፡ ከቃለመጠይቅ የሰበሰባችኋቸውን መረጃዎች በሥርዓት አደራጅታችሁ በጽሑፍም በንግግርም ማቅረብ እንደምትችሉ ተገንዝባችኋል፡፡ የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኛችሁን በማስታወሻ የመያዝን ችሎታ ተለማምዳችኋል፡፡ በአንቀጽ መልክ የቀረበውን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ ጽሑፍ ወደምታውቁት ቋንቋ አስተካክላችሁ የመተርጎም ልምድ አዳብራችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሰብዓዊነት ባህርያት እንዴት ያሉት ናቸው?
2. የቃላት ሀብታችንን ማበልጸግ በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ከሰዎች ጋር ለመግባባት ያለው ጠቃሚነት ምንድን ነው?
3. ስለዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻችሁ የምትወስዷቸው ማስታወሻዎች ጠቀሜታ ምንድን ነው?
4. በቃለመጠይቅና በመጠይቅ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
5. በጭውውትና በውይይት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
6. አንድን ጽሑፍ ከምንጩ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ለመተርጎም መደረግ ያለበት ዋና ጥንቃቄ ምንድን ነው?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ሀ. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የማነበውን ጽሑፍ መረዳት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2 | የቃላትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ በትክክል አዛምዳለሁ፡፡ | | | |
| 3 | የአንቀጽን ሰዋሰዋዊ ስህተቶች ለይቼ አስተካክላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በወቅታዊና በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ባዳመጥኩት ዙሪያ ስለአቀራረቡ፣ ስለሳቢነቱ፣ መልዕክት በተገቢው ሁኔታ ስለመተላለፉ አስተያየት እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ባዘጋጀሁት ጽሑፍ ዋና ዋና ነጥቦች ዙሪያ ንግግር አቀርባለሁ፡፡ | | | |
| 6 | በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ክፍል ውስጥ በሚቀርብ ጭውውት በስርአት እካፈላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | በቃለመጠይቅ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በሥርዓት አደራጅቼ በጽሑፍና በንግግር አቀርባለሁ፡፡ | | | |
| 8 | የዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኜን በማስታወሻ መያዝ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 9 | የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች ከአማርኛ ወደእንግሊዘኛ፣ ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ መተርጎም ችያለሁ፡፡ | | | |

ለ. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDR
Not to be repr

# ምዕራፍ ስድስት

# ጥናታዊ ጽሑፍ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ለቃላት ቀጥተኛ ፍች ትሰጣላችሁ፤
- ሥርዓተ ነጥቦችን፣ በተለይም ማለበሚያን (አስተሪክስን) በአግባቡ ትጠቀማላችሁ፤
- በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች አጠቃላይ እውነታንና የግል አስተያየትን ትለያላችሁ፤
- ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ውጤቶችን  አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ጽፋችሁ ታነባላችሁ፤
- ምርምር ለማካሄድ የሚረዱ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን ተረድታችሁ ጥናታዊ ጽሑፍ ታዘጋጃላችሁ፤
- ለጥናታዊ ጽሑፍ ሥራዎቻችሁ መጻሕፍትንና የተለያዩ ሰንጠረዦችን በማንበብ፣ እንዲሁም ቃለመጠይቅ በማቅረብ መረጃዎችን ትሰበስባላችሁ፤
- ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሀሳቦች በራስ አባባልና በጭምቃሳብ ትገልጻላችሁ፤
- የመረጃ ምንጮችን አጠቃቀስ ተረድታችሁ በጥናታዊ ሥራዎቻችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ሳይንሳዊ ግኝት ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ምርምር (ጥናት) ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ጠቀሜታውስ?
3. ለጥናታዊ ፅሁፍ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ?
4. ስለምርምር ምንነትና አገልግሎት የምታውቁትን ከዘረዘራችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ከምታገኙት ሃሳብ ጋር አነፃፅሩ፡፡

## የጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት

በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ መጥቀው አንቱ የተባሉት አገሮች ለዚህ የበቁት ለምርምር ሥራ ከፍተኛ ዋጋ በመስጠታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሀገሮች ከፍተኛ ገንዘብ፣ ብዙ ጊዜና በርካታ ለምርምር ተፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይመድባሉ፡፡ ለተመራማሪዎች ሙያዊ ነጻነት በመስጠት የተገኙትንም የምርምር ውጤቶች በሚገባ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም የእነሱን ሕይወትና አኗኗር ከመለወጥ አልፈው፣ የእኛንና የመሰሎቻችንን አኗኗር፣ ባህልና ልምድ እየተጫኑ ባንወድም በግድ እየለወጡት ይገኛሉ፡፡ ታዲያ የዚህ ሁሉ ለውጥ መንስዔው ምርምር ከሆነ፣ «ምርምር ምንድን ነው?» ብለን መጠየቃችን አይቀርም፡፡ ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት አድርጎ ማኅበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ትምህርታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት ወይም በተለያዩ መስኮች አዳዲስ ትውረትን (ንድፈ ሀሳብን) ለማፍለቅ በሰዎች ወይም በሌሎች ማናቸውም ነገሮች ላይ የሚካሄድ ጥናት ነው፡፡ ምርምር ሳይንሳዊ ዘዴን መሠረት ያደርጋል ሲባል፣ ልክ እንደ ሌሎቹ የእውቀት መስኮች ህግን፣ ደንብንና ሥርዓትን ተከትሎ በተላውጦዎች (ቫሪያብልስ) መካከል የሚኖርን ግንኙነት ለመፈተሽ፣ የተከሰተን ችግር ለመፍታት ወይም የጎደለ እውቀትን ለማሟላት የሚከወን ሂደት ነው ማለት ነው፡፡



© MoE, FDRE
Not to be republished

በመሆኑም ተመራማሪው ሊያከናውናቸው የሚፈልጋቸውን ተግባራት ደረጃ በደረጃ ያቅዳቸዋል፤ ይተገብራቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ሂደቱ የምርምርን ሳይንሳዊ ባህሪ የሚያሳይ ነው፡፡

አንድ ምርምር (ጥናት) ሂደት በመሆኑ ተመራማሪው ሊከተላቸው የሚገቡ ደረጃዎችና ቅደም ተከተሎች አሉ፡፡ እነዚህም ቅደም ተከተሎች ርዕስ መምረጥ፣ ስለርዕሱ በቂ ግንዘቤ መጨበጥ፣ የጥናቱን ሂደት በቅድሚያ ማቀድ፣ መረጃ ማሰባበሰብና መተንተን እና ጥናታዊ ጽሑፉን ማዘጋጀት ናቸው፡፡ ቀጥለን በአጫጭሩ እንመልከታቸው፡፡

**ርዕስ መምረጥ፡-** በጥናታዊ ጽሑፍ ዝግጅት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር የጥናታዊ ጽሑፉን ርዕስ መምረጥና መወሰን ነው፡፡ በርዕስ መረጣውም ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች፣ ጥናቱን ለማካሄድ ያለን አቅም፣ ጊዜ፣ ገንዘብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህን በቅድሚያ መወሰን ወደፊት በሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከወዲሁ ለመፍታት ያስችላል፡፡ ርዕሱ ከተመረጠ በኋላ ይዘቱን ወሰኖ (ርዕሱን አጥብቦ) በማያሻማ መንገድ በግልጽ ማስፈር ተገቢ ነው፡፡

**ስለርዕሱ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ፡-** የጥናት ርዕሱ ተመርጦና በግልጽ ተጽፎ ከቀረበ በኋላ ተከታዩ ሥራ በተመረጠው ርዕስ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ነው፡፡ ይህም የተመረጠውን ርዕስ በሚመለከት ቀደም ሲል የተጻፉ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ መጣጥፎች፣ ጋዜጦች ወዘተ. መኖራቸውን ማረጋገጥና እነዚህንም በማንበብ በርዕሱ ላይ በቂ ሃሳብ ማግኘት ተገቢ መሆኑን ያመለከታል፡፡ ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎች በበቂ ከሌሉ፣ ጥናቱን ለማካሄድ የሚያግድ ነገር ባይኖርም፣ የሥራው ሂደት ከባድና አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለሆነም አጥኚው

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

በቤተመጻሕፍት ብቻ ሳይወሰን፣ መረጃ ሊገኝባቸው ከሚችሉ ቦታዎች (ለምሳሌ ከቤተመዛግብት) እና ከግለሰቦች ጭምር ማሰባሰብ ይጠበቅበታል፡፡

**የጥናቱን ሂደት በቅድሚያ ማቀድ፡-** ሊካሄድ የታሰበው ጥናት ግቡን ሊመታ የሚችለው በቅድሚያ የጥናቱ አካሄድ ምን መምሰል እንዳለበት በንድፍ መልክ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ እንደሆነ ነው፡፡ መቀመጥ ብቻ አይደለም፤ አጥኚው እየተመላለሰ የሚከተለውና እንዳስፈላጊነቱም በሂደት የሚያስተካክለው የጥናት ዕቅድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱ በምን ዘዴ መካሄድ እንዳለበለትና የጥናቱ መረጃዎችም በእንዴት ዓይነት መንገድ መሰብሰብና መተንተን እንዳለባቸው የሚወሰነው በዚሁ ደረጃ ነው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

**እዚህ ላይ ንባባችሁን ገታ አድርጉና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. እስካሁን ያነበባችሁት ቀደም ሲል ስለምርምር ካቀረባችሁት ሃሳብ ጋር ይስማማል?
2. እስካሁን ካነበባችሁትና ከምታውቁት በመነሳት የቻላችሁትን ያህል ስለጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት በአጫጭሩ ጥቀሱ፡፡
3. ከቀሪው የምንባቡ ክፍል ምን ትጠብቃላችሁ?

**መረጃዎች መሰብሰብና መተንተን፡-** የጥናቱ መረጃዎች የሚሰበሰቡት ለጥናቱ በተመረጠው/ጡት መንገድ/ዶች ነው፡፡ በመሆኑም መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ ወዘተ. ሊሰበሰቡ እንደሚችሉ ልብ ማለት ተገቢ ነው፡፡ ተገቢውን መረጃም ለማዘጋጀት በቅድሚያ እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በጥንቃቄ ሊዘጋጁ፣ እንዳስፈላጊነቱም በባለሙያ ሊገመገሙና አስተያየት ሊሰጥባቸው

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

ይችላል፡፡ መሣሪያዎቹ በጥንቃቄ ከተዘጋጁ በኋላ መረጃዎችን ከተገቢዎቹ የመረጃ ምንጮች መሰብበሰብና በመልክ በመልኩ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚያም በንባብ ከተገኘው ሀሳብ ጋር እያዛመዱ መረጃዎችን መተንተን ቀጣይ ሥራ ነው፡፡ በትንተና ሂደቱም እንዳስፈላጊነቱ ሠንጠረዦች፣ ምሥሎች፣ ግራፎች ወዘተ. በመጠቀም የጥናቱን ውጤት አጉልቶ ማሳየት ተገቢ ነው፡፡

**ጥናታዊ ዘገባውን ጽፎ ማዘጋጀትና ማቅረብ፡-** መረጃዎች በአግባቡ ተሰብስበው ከተነተኑ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ማጠቃለያና አስተያየት ማዘጋጀትና የጥናቱን ዘገባ የመጨረሻ መልክ አስይዞ መጻፍ ነው፡፡

የጥናቱ ዘገባ ሲዘጋጅ፣ ጽሑፉ በተለያዩ መሠረታዊ ክፍሎች ተከፋፍሎ መቅረብ አለበት፡፡ የጥናታዊ ዘገባ መሠረታዊ ክፍሎችም መግቢያ፣ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (ወይም ክለሳ ድርሳን)፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ትንተና እና የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት የሚሉት ናቸው፡፡ የጥናቱ መግቢያ የዘገባው የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን፣ ስለጥናቱ አጠቃላይ የሆነ መንደርደሪያ ሀሳብ፣ ጥናቱን ለማካሄድ ሳላነሳሱ ምክንያቶች (ወይም ችግሮች)፣ ስለጥናቱ ዓላማ ወይም ጥናቱ ስለሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ እንዲሁም የጥናቱ መካሄድ ስለሚያስገኘው ጥቅም ይገለጽበታል፡፡ ከዚህ የሚቀጥለው ደግሞ የተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት (ክለሳ ድርሳን) ነው፡፡ ይህ ምዕራፍ (ክፍል) በጥናቱ ርዕሰጉዳይ ላይ ቀደም ብለው የተሠሩ ሥራዎች ከተለያዩ ምንጮች ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች፣ ከጋዜጦች፣ ከሰዎች፣ ከተቋማት ወዘተ. የሚጠናቀሩበትና የሚደራጁበት ክፍል ነው፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ (ክፍል) የሚቀርበው ደግሞ፣ የጥናቱ ዘዴ ተብሎ የሚታወቀውና ጥናቱ ስለሚከተለው ዘዴ፣ ስለመረጃ ምንጮች፣ ስለመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ የጥናቱ ትንተና ስለሚከተለው ዘዴ (ስልት) ወዘተ. የሚገለጸው ምዕራፍ ነው፡፡ ከዘዴው ቀጥሎ የሚመጣው



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

ምዕራፍ (ክፍል) የመረጃ ትንተና ነው፡፡ ይህ ክፍል በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሥርዓቱና በአግባቡ በምዕራፍ ሦስት በተጠቀመው ዘዴ የሚተነተኑበትና የሚዳራጁበት ክፍል ነው፡፡ ከትንተናው የሚቀጥለው ክፍል የጥናቱ የመጨረሻ ምዕራፍ የሆነው የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ነው፡፡ ይህ ክፍል ከስያሜው እንደምንረዳው ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ጥናቱ የሚጠቃለልበትና ተመራማሪው መደረግ (መሆን) ስላለበት ነገር አስተያየት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡ ከዚያም በመጨረሻ ዋቢ ጽሑፎችን በፊደል ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ ማያያዝ አንዱ የጥናታዊ ዘገባ የማይቀር ተግባር ነው፡፡ ከዚያ በኋላ እንዳስፈላጊነቱም የተለያዩ አባሪዎች (ካሉ) ሊያያዙ ይችላሉ፡፡

(ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998)፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር*፤ እና ከአለም እሸቱ፡፡ 1994፡፡ *መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ፡፡ ከተባሉት መጻሕፍት የተወሰደ፡፡)*

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡**

1. የአደጉት አገሮች አሁን የደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሱት ምን በማድረጋቸው ነው?
2. የምርምር ውጤቶች በሥራ ላይ መዋላቸው የኅብረተሰብን አኗኗር ይረዳል? እንዴት?
3. ምርምር አንድ ወጥ ብያኔ አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
4. ምርምር በመሠረቱ የሚካሄደው ለምንድን ነው?
5. ምርምር ሳይንስ ነው የተባለበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
6. *“ምርመር ሂደት ነው”* የተባለው ለምን ይመስላችኋል?
7. ምርምር የግል አስተያየት ነፀብራቅ መሆን የለበትም፤ ለምን?
8. የምርምር ደረጃዎች ምን ምን ናቸው?
9. ለጥናት መካሄድ የግድ መኖር ያለበት ነገር ምንድን ነው?
10. አንድ የጥናታዊ ጽሑፍ መሠረታዊ ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

፪. የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አውዳዊ ፍች በቃል ተናገሩ፤ ከዚያም ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ ያሏቸውን ፍችዎች በሙሉ ጻፉና ለመምህራችሁ ኣሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መጨበጥ | 6. መፍታት |
| 2. የበቁት | 7. ተላውጦዎች |
| 3. መሰብሰብ | 8. መወሰን |
| 4. መተንተን | 9. ተከሰተ |
| 5. መስክ | 10. ማደራጀት |

፫. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውሰጥ ባላቸው ፍች መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፡፡

| | |
|---|---|
| 1. መጠይቅ | 6. የሚያግድ |
| 2. ሂደት | 7. የሚከወን |
| 3. ናሙና | 8. ግንዛቤ |
| 4. መቀመጥ | 9. ማቀድ |
| 5. ምንጭ | 10. ተገቢ |

## ክፍል ሁለት፡- መጻፍ

፩. ከሚከተሉት ጽሁፎች ውስጥ የግል አስተያየት የሆኑትንና ያልሆኑትን ሀሳቦች ለይታችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. እነዚህ ምሁራን ይህን አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል ሲገልጹት አባቶች ልጆቻቸውን የመንከባከብና ስሜታቸውንም ልክ እንደ እናቶች ከልጆቻቸው ጋር ማቆራኘት የጀመሩበት ነው ይሉታል፡፡ በፍሪስትንበርግ (1993) አባባል የዛሬ አባቶች የመኪና ጎማ የመቀየርን ያህል የሽንት ጨርቅንም መቀየር የሚችሉ ሥልጡኖች ናቸው፡፡

*(ካለፈው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የተወሰደ)*

2. አንዳንድ ምርምሮች (ኬቲ 1996፣ ጄፎርድስ 1989) መንከባከብ የግድ አካላዊ ተሳትፎን እንደማይፈልግ፣ አካላዊ ተሳትፎ ደግሞ የግድ ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን ለሌላ ዓላማም ሊውል እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ (ኢሺ ኩንትዝ 1993፣ ዴይ እና ሚኪ1986) ምንም እንኳ አባቶች እንደእናቶች ቤተሰብ ውስጥ በአካል ተገኝተው ልጆችን ባይንከባከቡም፣ በሀሳብና በስሜት ከቤት የማይለዩ መሆናቸውን በመገንዘብ አባቶች የራሳቸው የሆነ የመንከባከቢያ ዘዴ አላቸውና የእነሱን ባሕሪ ከእናቶች የመንከ ባከቢያ ዘዴ ጋር በማነፃፀር "ተንከባካቢ ናቸው" ወይም "አይደሉም" ብለን መፈረጅ "ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ነው" ይላሉ፡፡

*(ካለፈው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጸሐፍ የተወሰደ)*

3. በተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ በተለያዩ ደረጃዎችና ጊዜዎች የተከናወኑት ጥናቶች የሚያስገነዝቡት፣ የንባብ ትምህርትና ልምምድ በየትምህርት ቤቶቹ የሚከናወን ቢሆንም፣ በተማሪዎቹ ላይ ግን ተፈላጊው ችሎታ ወይም ክሂል አለመታየቱን ነው፡፡ "...ተማሪዎች በደረጃቸው የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመገንዘብ ችሎታቸው ዝቅተኛ እንደሆነና የመማሪያ ቋንቋው የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብም የሚፈለገውን የንባብ ክሂል ለማዳበር ብቃት እንደሌለው..." (ወንደአጥር፣ 1993 ገጽ 54) ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

*(ደረጀ ገብሬ፣ 2009፡፡ "የንባብ ልምድ ቅኝት በአዲስ አበባ"፡፡ Etiopian Journal of Education. Vol. XXIX No 2, pp 69-102.*

**፪. በዚሁ ክፍል በተራ ቁጥር ፩/1 የቀረበው አንቀጽ በውስጡ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አልያዘም፡፡ እናንተ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ተጠቅማችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡**



© MoE, FDRE Not to be reproduced

፫. በጥናታዊ ጽሑፍ ረገድ ቀዳሚው ነገር ምርምር የሚካሄድበትን ርዕስ መምረጥ ነው:: የምንመርጠውም ርዕስ ከአቅማችን ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት::

በዚህ መርህ መሠረት ከሚከተሉት አጠቃላይ ርእሰ ጉዳዩች መርጣችሁ ሁለት ሁለት ጥናት ልታካሂዱባቸው የምትችሉባቸውን የምርምር ርእሶች አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ:: በሚሰጧችሁም አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ::

**አጠቃላይ ርዕሰ ጉዳዮች:-**

- ወጣትነትና ኤች አይ ቪ ኤድስ
- የተማሪዎች የጥናት ጊዜ ምርጫ
- የሴትና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

፬. በጥናት ሥራ ሂደት ከርዕስ መረጣው ቀጥሎ የሚመጣው ተግባር በርዕሱ ዙሪያ ከዚህ ቀደም የተሠሩ ሥራዎችን ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔት፣ ከጋዜጦች ወዘተ. በመፈለግና በማንበብ በቀጥታ ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሀሳቦች በአግባቡ መሰብሰብና ማደራጀት ነው:: በመሆኑም ከላይ በመረጣችሁትና ከመምህራችሁ ጋር በተስማማችሁበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ከቤተመጻሕፍት ፈልጋችሁና ዕውቀቱና ልምዱ ያላቸውን ሰዎች ጠይቃችሁ ለጥናታችሁ የሚሆን ተዛማጅ ጽሑፍ አዘጋጁና ለመምህራችሁም አቅርቡ::

፭. ጥናቱን ለማካሄድ የምትከተሉትን ቅደም ተከተልና ዘዴ የተለያዩ የምርምር መጽሐፎችን በማንበብ ወይም ዕውቀቱ ያላቸውን መምህራን በመጠየቅ በቅደም ተከተል ነድፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ:: በሚሰጧችሁ አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ በማቅረብ በሚሰጡ አስተያቶች መሠረት አስተካክሉና ጻፉ::



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

፩. በጥናታዊ ጽሑፍ አዘገጃጀት ሂደት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በርካታ ናቸው። እነዚህ መሣሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ከምርምር መጻሕፍት በማንበብ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ፣ ለእናንተ ምርምር የሚስማማችሁ የትኛው እንደሆነ በመወሰን ለመምህራችሁ አቅርቡ፤ በሚሰጧችሁ ምክር መሠረት ከአስተካከላችሁ በኋላ መሣሪያዎቹን በጥንቃቄ አዘጋጁ።

፪. በመረጣችሁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ተገቢውን መረጃ ሰብስቡ፤ መረጃዎቻችሁንም በተገቢው መንገድ አደራጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፤ የሚሰጧችሁን አስተያየቶች ተቀብላችሁ አስተካክሉ።

፫. ከላይ ደረጃ በደረጃ የሠራችኋቸውን (ከርዕስ መረጣ እስከመረጃ መሰብሰብ ድረስ ያሉትን) ሥራዎች አንድ ላይ በሥርዓት አደራጁና አንድ ወጥ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጁ፤ ለዝግጅቱም መነሻ ይሆናችሁ ዘንድ፣ በምዕራፉ መጨረሻ ከማጠቃለያው በፊት አንድ ናሙና ጥናት ቀርቦላችኋል። ናሙና ጥናቱ ከዋቢዎች በስተቀር ሌሎቹን የጥናት አካላት ይዟል። በዚሁ ናሙና መሠረት ጥናታችሁን ካዘጋጃችሁ በኋላ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

፬. ከሚከተሉት የማለበሚያ (የአስተሪክስ) አጠቃቀሞች ምን ተረዳላችሁ? የተረዳችሁትን ጻፉና በክፍል ውስጥ ከጓደኞቻችሁና ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩበት። በመጨረሻም ከአንድ ማጠቃለያ ላይ ድረሱና በማስታወሻችሁ ያዙ።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

## ማለበሚያ (አስተሪክስ)

ሥርዓተ ነጥቦች በጽሑፍ ቋንቋ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንደላቸው ባለፉት የክፍል ደረጃዎች መማራችሁን ታስታውሳላችሁ። ዛሬ ደግሞ ማለበሚያን (አስተሪክስን) ትማራላችሁ። ማለበሚያ (አስተሪክስ) በአንድ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ በአንድ ጉዳይ ላይ ከጥናቱ ገለጻ ውጪ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ የበለጠ ማብራሪያ ለሚፈልግ አንባቢ የት ሄዶ መመልከት እንዳለበት ለመጠቆም ሲፈለግ፣ የጥቅስን መገኛ ቦታ ለማመልከት ሲፈለግ፣ አዳዲስ ወይም እንግዳ ቃላትን በበለጠ ዝርዝር ማስተዋወቅ ተገቢ ሲሆን፣ ወዘተ. ከግርጌ ማስታወሻው ጋር የምናጣቅስበት የነጥብ ዓይነት ነው። አተገባበሩም በዋናው የጥናት አካል ውስጥ በተፈላጊው ቦታ ላይ የማለበሚያ ምልክት (*) ወይም የሚጠቆመው ነገር ተከታታይነት ያለው ከሆነ ደግሞ ቁጥሮችን $^{1, 2 \ldots}$ እንጠቀማለን። እነዚህ ምልክቶች ግን፣ በግርጌ ማስታወሻውም ላይ በተመሳሳይ እንደሚጠቆሙ ልብ ማለት ያስፈልጋል። የሚከተለው ለማለበሚያ ምሳሌ ይሆን ዘንድ የቀረበ ነው።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDR
Not to be rep

## የንባብ ልምድ ቅኝት-በአዲስ አበባ

ደረጀ ገብሬ*

"---አብዛኞቹ አስተያየቶች መነሻቸው በቂ ጥናት ሳይሆን ነሲባዊ አስተሳሰብ፣ ግምታዊ ምደባ፣ ከፊል ምርምራዊ ማጠቃለያ ናቸው ማለት ያስኬዳል። አስተያየቶቹም የሚቀርቡት ልዩ ልዩ ልምድ፣ እውቀትና ሙያ ካላቸው ግለሰቦች ወይም እንደቡድን በሚታሰቡ አካሎች ጭምር ነው።[1] በተለይ..."

(The *Ethiopian Journal of Education* No 2 December 2009. p 69 ከሚለው የተወሰደ።)

*(ይህ ማለበሚያው በተሠጠበት ገጽ ግርጌ ይቀመጣል)*

* በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ትምህርት መምህር

[1] ደረጀ ደስታ 1986 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ግንቦት 21 ቀን በ54ኛ ዓመት ቁ. 220ኛ እትሙ ዕለተ ሰንበት በገጽ 2 መጽሐፍ ያልያዘ ትውልድ በሚል ርዕስ የወቅቱን የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ኃላፊዎችን አነጋግሮ ነበር፤

© MoE, FDR
Not to be rep

## የማስታወሻ አወሳሰድና የሀሳብ መዋሻ መንገዶች

ቀጥተኛ ጥቅስ፣ ግለገለፃና ጭምቃሳብ በጥናታዊ ጽሑፍ ዝግጅት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋነኞቹ የሀሳብ መዋሻ መንገዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሀሳብ መዋሻ መንገዶች የየራሳቸው ባሕርያት ስላሏቸው በአጠቃቀም ረገድ የተለያዩ መንገዶችን ይከተላሉ፡፡ በመሆኑም ለአጠቃቀም ይረዳን ዘንድ እነዚህን የሀሳብ መዋሻ መንገዶች አጠር አጠር ባለ ሁኔታ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

### 1. ቀጥተኛ ጥቅስ

ቀጥተኛ ጥቅስ ምንጩን በሚገባ ጠቅሰን የምንወስደው ወይም የምንዋሰው የሌላ ሰው ሀሳብ ወይም አገላለጽ ነው፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ በምርምር ጽሑፍ ውስጥ ሲሰፍር ከምንጩ በተገኘበት አኳኋን ቃል በቃል ይሰፍራል እንጂ በራስ አባባል ተገልጾና ተስፋፍቶ አይቀርብም፡፡ በራስ አባባል ከተገለጸ ቀጥተኛ ጥቅስ መሆኑ ይቀራልና ጥንቃቄ ይፈለጋል፡፡ ቀጥተኛ ጥቅስ በቀጥታ የተወሰደ ሀሳብ እንደመሆኑ መጠን፣ በጥናታዊ ሥራው ውስጥ ሲሰፍር እንደርዝማኔው አቀማመጡ የተለያየ ነው፡፡ አጭር ጥቅስ ሲሆን በትእምርተ ጥቅስ ተለይቶ ይቀመጣል፤ ረዥም ጥቅስ ሲሆን ደግሞ ከግራና ከቀኝ ገባ ገባ ተብሎ ይጻፋል፡፡ በዚህ ጊዜ ትእምርተጥቅስ አስፈላጊ አይደለም፡፡

**የቀጥተኛ ጥቅስ ምሳሌ፣**

ትምህርት ተኮር ጉባዔዎች ወይም ውይይቶች የሚከናወኑባቸው መድረኮች ሲዘጋጁ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የንባብ ነገር ከተነሳ ኢትዮጵያውያን የንባብ ባህላችን አልዳበረም የሚል ማጠቃለያ ሲሰጥ መስማት ልማድ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል አያልነህ፣ *"ግልጽና ዕውቅ በሆኑ አያሌ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ለረጂም ጊዜ ቀጭጮ ቆይቷል፡፡ ህዝቡም በማይምነት መጋረጃ ውስጥ ተሸፍኖ የቆየ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የንባብ ባሕሉ አልዳበረም" (አያልነህ 1985፣ ገጽ 2)* ሲል ይገልጻል፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

## 2. ግስገለፃ

በአንድ ጥናት ውስጥ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመውሰድ በግለገለፃ ማስፈር የተለመደ አሠራር ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ዘጋቢው የደራሲውን ሀሳብ ሳይለቅ በራሱ ቋንቋና በራሱ ስልት የማቅረብ መብት አለው፡፡ ግለገለፃ ከምንጩ የተወሰደውን ሀሳብ በሌላ መንገድ እንደገና የመፍጠር ያህል ነው፡፡ በግለገለፃ ሀሳብን ማስፈር ይቻል ዘንድ ከዚህ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር አስፈላጊ ነው፡፡

ሀ. አንድ ተመራማሪ ወይም አጥኚ በግለገለፃ ሊያሰፈር የሚፈልገውን የሌላ ተመራማሪ ሐሳብ በሚገባ መረዳትና የጸሐፊውንም ዓላማና ፍላጎት በትክክል መጨበጥ ይኖርበታል፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ትኩረት በተመላበት ሁኔታ ጥናቱን በቅድሚያ ማንበብ ተገቢ ነው፡፡

ለ. አንድን ቃል በሌላ ቃል ተክቶ ማቅረብ ወይም የቃላትን ቅደም ተከተል ማለዋወጥ ብቻውን ግለገለፃ ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በአገላለጹ ላይ ቋንቋችንና ግላዊ ስልታችን ጎልቶ መታየት አለበት፤ ማለትም ሐሳቡ እንጂ ቋንቋውና የአገላለጽ መንገዳችን የራሳችን መሆን አለበት ማለት ነው፡፡ ለዚህም በተደጋጋሚ መለማመድ ወይም ሙከራ ማድረግ በጣም ይጠቅማል፡፡

ሐ. አንድ ሀሳብ በግለገለፃ ሲሰፍር የሐሳቡ ባለቤት ስምና የሕትመት ዘመኑ እንዳስፈላጊነቱም ሐሳቡ የተወሰደበት ገጽ ወይም የተወሰደባቸው ገጾች በቅንፍ ውስጥ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

**ምሳሌ፣ ከባየ ይማም (1987፡ 1) *የአማርኛ ሰዋስው የተወሰደ፣***

"ቁዋንቁዋ ሁለት የተያያዙ ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡፡ አንደኛው፣ ሀሳብን ማስተላለፍ ሲሆን፣ ሁለተኛውና የዚሁ ነፀብራቅ የሆነው ደግሞ ማንነትን ማመልከት ወይም ማሳወቅ ነው፡፡"

**የምሳሌው ሀሳብ በግለገለፃ ሲሰፍር እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፤**

ባየ ይማም (1987) ***የአማርኛ ሰዋስው*** በተሰኘው መጽሐፉ እንደገለጸው ዋና ዋናዎቹ የቋንቋ አገልግሎቶች በሁለት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ። አንደኛው አገልግሎቱ መልዕክት ከአንዱ ሰው ወደሌላ ሰው ማስተላለፊያነቱ ነው። ሁለተኛው ደግሞ፣ ከመጀመሪያው አገልግሎት የሚመነጭና የማንነት መገለጫነቱ ማለትም ስለአንድ ሰው ወይም ስለአንድ ማኅበረሰብ ማንነት ፍንጭ መስጠት የመቻሉ ጉዳይ ነው። እነዚህ ሁለት አገልግሎቶች ግን ተነጣጥለው የሚታዩ አይደለም።

**3. ጭምቃሳብ**

በምርምር ሥራ ውስጥ ከተለያዩ ምንጮች ሀሳብ ለመዋስ ወይም ለማሰባሰብ አንዱ መንገድ ጭምቃሳብ ነው። ጭምቃሳብ የአንድን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ በራሳችን አገላለጽ አሳጥረን የምናቀርብበት መንገድ ነው። ከዚህ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ግለገለፃ የሌሎችን ሀሳብ በራስ ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት መንገድ እንደሆነ ተረድተናል። ጭምቃሳብ ግን የጽሑፉን ሙሉ ሀሳብ በሌላ ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት ብቻ አይደለም። ጭምቃሳብ የጽሑፉን ፍሬ ሀሳብ አሳጥረን በራሳችን ቋንቋና አገላለጽ የምናቀርብበት መንገድ ነው። ምንም እንኳ አሳጥረን በራሳችን ቋንቋ ብንጽፍም በቅንፋዊ ማስታወሻ ውስጥ የሚሰፍሩትን ነጥቦች ግን መዘንጋት አይኖርብንም። አንድን ጽሑፍ ጨምቆ የተዋጣ ጭምቃሳብ ለመጻፍ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

**ሀ. በጥንቃቄ ማንበብ**

ጥንቃቄ የተሞላበት ንባብ፣ ለጥሩ ጭምቃሳብ መሠረት ነው። በመሆኑም የአንድን ምርምር ወይም ጥናት ዋና ሀሳብ በትክክል ለመጨበጥ እንዲቻል ደግሞ ማንበብ ያስፈልጋል። እንግዳ ቃልም ሲያጋጥምም፣ በመዝገበ ቃላት እየታገዙ ማንበብ የጥንቃቄው አንድ ገጽታ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ የጥናቱ ዋና ሀሳብ በትክክል ለመጨበጥ አስፈላጊ ነገር ነው።



© MoE, FDRE Not to be reproduced

**ለ. በምልክት መጠቀም**

ጥናታዊ ጽሑፉ በሚነበብበት ጊዜ፣ አጫጭር ማስታወሻ ከመውሰድ ጎን ለጎን ፍሬ ፍሬ ሀሳቡን እየለዩ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ከስር በርሳስ ማስመር ወይም በሌላ አማራጭ እያመለከቱ ማለፍ (ይህ የሚደረገው ጽሁፉ የራሳችን ንብረት የሆነ እንደሆነ ነው እንጂ የጋራ መጠቀሚያ ከሆነ ግን አንድም በርሳስ ያሰመርነውን ሙልጭ አድርገን ማጥፋት፣ አለበለዚያም ደግሞ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይገባናል) ፍሬ ሀሳቡን ለመጨበጥና ተደግሞ በሚነበብበት ጊዜ የት የት አካባቢ ላይ በይበልጥ ማተኮር እንደሚገባ ለመጠቆም ይረዳል፡፡

**መ. ዋና ሀሳቡን ለይቶ በራስ አገላለጽ ማስፈር**

በጥንቃቄ አንብበን ፍሬ ፍሬ ሀሳቡን ከለየን በኋላ፣ ተከታዩ ተግባር የጥናታዊ ጽሑፉን ማዕከላዊ ወይም ዋና ሀሳብ በራሳችን አገላለጽ ማስፈር ይሆናል፡፡

(ከቀድሞው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ናሙና ጥናት

**በልጅ አስተዳደግ ውስጥ አባታዊ ተሳትፎ ያለው ሚና፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች እይታ**

### 1. ዳራ (መግቢያ)

በልጅ አስተዳደግ ውስጥ አባታዊ ተሳትፎ ያለውን ሚና መመርመር የተጀመረው በቅርቡ አይደለም፡፡ ይህንን በሚመለከት ከ1950ዎቹ ጀምሮ እነቦልቤ (1952)፣ ኢንጊሲሽ (1954)፣ በመቀጠልም በ1960ዎቹና በ1970ዎቹ እነናሽ (1965)፣ ኮቴል ቻክ (1976)፣ ፔድርስን (1996) የመሳሰሉት ምሁራን በስፋት ያተኮሩበትና አሁን ድረስም

© MoE, FDRE Not to be rep

የተመራማሪዎችን ዓይን እየሳበ የሚገኝ፣ ሰፊ የጥናት መስክ ነው፡፡ በ1950ዎቹ የተደረጉት ምርምሮች አባቶች እንደሁለተኛ ወላጆች የሚታዩና ለልጆቻቸውም ራቅ ያለ ስሜት ያላቸው መሆኑን ሲያሳዩ፣ የ1960ዎቹና የ1970ዎቹ ጥናቶች ደግሞ ያባትነት ሚና ካለፈው ለውጥ እያሳየ መምጣቱን ገልፀዋል፡፡ በዚህ ረገድ አንዳንድ አባቶች፣ ለቤተሰብ ገቢ ከማስገኘትም አልፈው፣ በቤት ውስጥ ሥራም መሳተፍ መጀመራቸውን እነዚህ ጥናቶች አመልክተዋል፡፡ ይህ ለውጥ በ1980ዎቹና በ1990ዎቹ ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ፣ ይህንን ለውጥ መነሻ አድርገው የቤተሰብ ጉዳይ ተመራማሪዎች፣ "አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል" እየተፈጠረ መምጣቱን ይገልፃሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ፍሬስ ትንበርግ (1988)፣ ላሮሳ (1988)፣ ኘሌክ (1983)፣ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን ይህንኑ አዲስ ዓይነት የአባትነት ባህል ሲገልፁት፣ "አባቶች ልጆቻቸውን የመንከባከብና ስሜታቸውንም ልክ እንደናቶች ከልጆቻቸው ጋር በብቃት ማቆራኘት የጀመሩበት ነው" ይሉታል፡፡ በፍሪስ ትንበርግ (1993) አባባል "የዛሬ አባቶች የመኪና ጎማ የመቀየርን ያህል የሽንት ጨርቅም መቀየር የሚችሉ ሥልጡኖች ናቸው፡፡"

ሆኖም ግን ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተደረጉትን እነዚህን ምርምሮች ስናጤን፣ ሶስት መሠረታዊ ችግሮች እናይባቸዋለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሁሉም ምርምሮች ትኩረት ያደረጉት የአባትነት ፀጋ በደረሳቸው ወንዶች ላይ ብቻ ነው፡፡ መሠረታዊው ግንዛቤያቸውም አባትነት የሚጀምረው፣ ግለሰቡ ወላጅ አባት ሲሆን ብቻ እንደሆነ አድርጎ ከመገመት የመነጨ ይመስላል፡፡ አባትነት ግን የሚጀምረው ወላጅ ከመሆን ረዥም ዓመታት በፊት ነው፡፡ እንዲያውም ገና ከልጅነት ጊዜያችን ጀምሮ በጨዋታ ሂደት የአባትነትን ሚና እንጫወታለን፡፡ ወላጆች ከመሆናችን በፊት ወደአባትነት የሚያስገቡንን ክህሎት፣ ልምዶች፣ ፍላጎቶችና ባህሪያት እንማራለን፡፡ በተለይ የጉርምስና ዘመናችን የወንድነትን ባህሪና ስብዕና የምንመሠርትበት ወቅት እንደመሆኑ መጠን፣ የአባትነትንም ስብእና በስፋት እናዳብራለን፡፡ ታዲያ

© MoE, FDRE Not to be repro

በዚህ የአባትነት መጀመሪያ ወቅት፣ “ባለ ተስፋ አባቶች” ማለትም ለአካለ መጠን የደረሱት ጎረምሶች ልጅ በማሳደግ ረገድ “የአባትነትን ሚናን እንዴት ይመለከቱታል?” ለሚለው ጥያቄ እስከአሁን ከተደረጉት ምርምሮች ምንም ፍንጭ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ሁለተኛም ያለፉት ምርምሮች ችግር፣ ሁሉም የተደረጉት በአደጉ አገሮች በሚገኙ አባቶች ላይ ብቻ ከመሆኑ ይመነጫል፡፡ በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች የሚገኙ አባቶች ባህርይ ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ የሁለቱ አገሮች አባቶች በሁለት እጅግ የተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸውና የአባትነት ባህሪያቸውም ልክ እንደየባህላቸው የሚለያይ በመሆኑ፣ ካደጉት አገሮች ልምድ ተነስተን በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ስለሚገኙ አባቶች አስተያየት መስጠቱ የተደረሰበትን መደምደሚያ ስህተት ያደርገዋል፡፡ የአደጉት አገሮች ባህል “እኔነት” የተንሰራፋበት ሲሆን፣ በማደግ ላይ የሚገኙ የአፍሪካና የእሲያ አገሮች ባህል ደግሞ “እኛነት” በስፋት የሚታይበት ነው፡፡ እኛነት መተባበርን፣ መደጋገፍን፣ መረዳዳትን፣ አብሮ መኖርን የሚያጠቃልል ስለሆነ፣ የአባትነት ሚናም በዚህኛው ባህል ሲታይ፣ “እኔነት” ከበዛበት ካደጉት አገሮች ባህል የተለየ ሊሆን ይችላል፡፡ “እንዴት ይለያል?” ለሚለው ጥያቄ ግን፣ አሁንም ቀደም ካሉት ምርምሮች የምናገኘው ምላሽ የለም፡፡

ሦስተኛውና ዋነኛው ችግር፣ “የአባትነትን ተሳትፎ” ከመተርጎምና ከመረዳት ጋር ተያይዞ የመነጨ ይመስላል፡፡ ካለፉት ምርምሮች የምንረዳው “የአባትነት ተሳትፎ” አንድ ገፅታ ብቻ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው የጥንቶቹ ምርምሮች፣ አባቶችን “በልጅ አስተዳደግ ረገድ ተሳትፎ የማያደርጉ፣ በርቀት የሚገኙ” ብለው ሲኮንኑ፣ የአሁኖቹ ደግሞ “የለም አባቶች ተለውጠዋል፤ ልክ እንደእናቶች በቅርበት ልጆቻቸውን መንከባከብ ጀምረዋል” ብለው ሲያወድሱ የሚታዩት፡፡ ልዩነቱ መኮነንና ማወደስ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ይዘታቸው አንድ ነው፡፡ ሁሉም የሚሉት፣ መንከባከብ ማለት በአካል ለልጆች ቅርብ ሆኖ ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ ችግራቸውን ማድመጥና እርዳታ ማድረግ

© MoE, FD
Not to be rep

ነው። ይህ ምናልባት አግባብነት ያለው እንክብካቤ ነው ሊባል ይችላል። ግን አባቶች የተለየ የመንከባከብ ትርጉም ቢኖራቸውስ? ወይም ደግሞ ሕፃናትን መንከባከብ ከዚህ በተለየ መንገድ ሊገለፅ ይገባዋል ብለው የሚያምኑ ቢሆንስ? እንዲያውም በአካል ከልጆቻቸው ጋር በቅርበት መገኘት ህፃናትን “አጉል” ነገር ማስተማር ስለሆነ፣ ከልጆች ራቅ ብሎ ልጆች “ራስን መቻል”፣ “ጥንካሬን” “በራስ መተማመንን”፣ ወዘተ. እንዲያውቁ መርዳት፣ “ሳይንከባከቡ መንከባከብ” አይደለምን ብለው ቢያምኑስ? ለምሳሌ በአንድ ወቅት አንድ አባት “ለምንድን ነው ልጅህን አቅፈህ ስትስመው የማትታየው” ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ፣ “ልጄ እንዲለምደኝ አልፈልግም፤ ሲያጣኝ እንዲሳቀቅብኝ ስለማልፈልግ” በማለት የእሱ አባት በሞተ ጊዜ እሱ ምን ያህል ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ተሰምቶት እንደነበር ተናግሯል።

በተጨማሪም አንዳንድ ምርምሮች (ኬቲ 1996፣ ጀፎርድስ 1989) መንከባከብ የግድ አካላዊ ተሳትፎን እንደማይፈልግ፣ አካላዊ ተሳትፎ ደግሞ የግድ ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለሌላ ዓላማም ሲውል እንደሚችል ያስረዳሉ። ሌሎች ደግሞ (ኢሺ ኩንትዝ 1993፣ ዱይ እና ሚኪ 1986) ምንም እንኳን አባቶች እንደእናቶች ቤተሰብ ውስጥ በአካል ተገኝተው ልጆችን ባይንከባከቡም፣ በሀሳብና በስሜት ከቤት የማይለዩ መሆናቸውን በመገንዘብ፣ አባቶች የራሳቸው የሆነ የመንከባከቢያ ዘዴ አላቸውና የእነሱን ባህሪ ከእናቶች የመንከባከቢያ ዘዴ ጋር በማነፃፀር፣ “ተንከባካቢ ናቸው” ወይም “አይደሉም” ብለን መፈረጅ “ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ” ነው ይላሉ።

እንግዲህ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ነው፣ ለአባትነት እየተዘጋጁ ያሉትንና በማደግ ላይ ባለ አገር ባህል ውስጥ የሚገኙት የኢትዮጵያ ወጣቶች “አባትነት ምንድን ነው ይላሉ? አባትነትንስ እንዴት ይገልፁታል? የሚሉትን ጉዳዮች ለማጥናት የተነሳነው።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**2. የጥናቱ አላማ**

ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሪ ጥያቄዎች በማንሳት የኢትዮጵያን ወጣቶች የአባትነት ግንዛቤ ይመረምራል፡፡

1ኛ. "የአባቶችን የልጅ አስተዳደግ ተሳትፎ" በተመለከተ የኢትዮጵያ ወጣቶች ግንዛቤ ቀጥተኛ እንክብካቤ የማድረግን ሚና ብቻ ያሳያል? ወይስ ቀጥተኛ ያልሆነ እንክብካቤ መኖሩንም ይጠቁማል?

2ኛ. የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ ያባቶችንስ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? ልጆችን ለመንከባከብ ብቻ ነው ይላሉ? ወይስ ቀጥተኛ ተሳትፏቸው ልጆችን ከመንከባከብ ባሻገር ለወንድነት ተግባር ማስፈፀሚያ ሊሆንም ይችላል ይላሉ?

3ኛ. በተሳትፎ ወቅት የአባቶችን ሚና እንዴት ይመለከቱታል? አባቶች ከአድራጊነት ይልቅ ልጆች ድርጊቶችን እንዲያደርጉ ምን የመገንባት ሚና ነው የሚጫወቱት ይላሉ?

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት አላማ፣ አባትነት በኢትዮጵያ ምን ይመስላል? በተለይ የኢትዮጵያ ወጣቶች በዚህ ረገድ ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ አሰባስቦ በመፈተሽ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

**3. የጥናቱ ዘዴ**

**3.1. ናሙና**

554 ያላገቡ ጎረምሳ (እድሜያቸው ከ14 እስከ 19 የሆኑና ዕድሜያቸው በአማካይ 16 የሆነ) ተማሪዎች (ከ9ኛ እስከ 12ኛ ያሉ) በአዲስ አበባ ከሚገኙ ሶስት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በነሲብ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው በናሙናነት ተወስደዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 55% ያህሉ ወንዶች ሲሆኑ፣ የተቀሩት 45% ያህሉ ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

### 3.2 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያ

መረጃ ለማሰባሰብ የጽሑፍ መጠይቅ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ መጠይቁም አራት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡ ክፍል አንድ፣ የልጅ እንክብካቤ ተግባራትን ይዘረዝራል፡፡ ክፍል ሁለት ደግሞ ልጅን ራስ የማስቻል ተግባራትን ይዘረዝራል፡፡ ክፍል ሦስት፣ ልጅን ስለወንድ ፆታ የማስተማርን እንቅስቃሴዎች ይዘረዝራል፡፡ ክፍል አራት ደግሞ ሥነሥርዓትን ለማስተማር ስለሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና እርምጃዎች ይዘረዝራል፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አምስት አምስት ተግባራት ሲዘረዘሩ፣ በአጠቃላይ የአባትን ተሳትፎ ያመለክታሉ የተባሉ 20 ተግባራት ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ መላሾችም እያንዳንዱን ተግባር ካነበቡ በኋላ፣

1ኛ. አባቶች ምን ያህል ተግባሩን (ልጆች መንከባከቡን) ራሳቸው ያከናውናሉ? ለሚሉት ከ1 እስከ 5 በሚደርሱ ነጥቦች ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ (1 ዝቅተኛውን ሲያመለክት፣ 5 ከፍተኛውን ያመለ ክታል፡፡)

2ኛ. አባቶች ምን ያህል ራሳቸው ተግባሩን (ልጆች መንከባከቡን) ከማከናወን ይልቅ እናቶች እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ? ለሚሉ ትም እንዲሁ ከ1 እስከ 5 ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ (1 ዝቅተኛውን ሲያመለክት፣ 5 ከፍተኛውን ያመለክታል፡፡)

በዚህ መልክ የተገኘው ምላሽ ተሰባስቦ እየተጠናቀረ እንዲተነተን ተደርጓል፡፡

### 3. የጥናቱ ግኝት

ከፍ ሲል ተግባራዊ በተደረጉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃዎች ተሰብስበው ሲተነተኑም የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት አንኳር የሆኑትን የዚህን ጥናት ግኝቶች ብቻ ከዚህ በታች እንመልከት፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

1ኛ. በናሙናነት የተወሰዱት የኢትዮጵያ ወጣቶች የሰጡት ምላሽ እንደሚያሳየው የአባትነት ተሳትፎ፣

- ቀጥተኛ ብቻ ሳይሆን ተዘዋዋሪ መልክም አለው፤ ማለትም፣ ልጆችን እንደእናቶች በቀጥታ መንከባከብ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ ራቅ ብሎ የመንከባከብ ሁኔታ እንደሚያሳዩ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡
- በአድራጊነት ብቻ ሳይሆን፣ ልጆችም ድርጊቶችን እንዲያከናውኑ ከማስቻልም አኳያ ሊታይ ይችላል፡፡ ይህም ለልጆች የሚፈልጉትን በቀጥታ በማድረግ ላይ የሚመሰረት ሳይሆን፣ ልጆች ድርጊቶችን በራሳቸው ማከናወን ይችሉ ዘንድ አቅም በመገንባት ላይ የሚያነጣጥር ነው፡፡
- ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለወንድነት ፍላጎት ማስፈፀሚያ የሚውል ነው፡፡ በዚህም መሠረት መረጃዎቹ ባሕሉ ለወንድ ከሚሰጠው ቦታ የመነጨ፣ መቆጣጠርን፣ ማዘዝንና የመሳሰሉትን የወንድነት ባህሪያት ለማስተማር ሊውል እንደሚችል ገልፀዋል፡፡

2ኛ. ከላይ በተጠቀሱት የአባቶች ተሳትፎዎች መካከል ከፍተኛ ግንኙነት አለ፡፡ ከፍተኛ የሆነ ቀጥተኛ ተሳትፎ የሚያደርጉ፣ ከፍተኛ የሆነ ተዘዋዋሪ ተሳትፎም አላቸው፡፡ በአድራጊነት ሚና የሚሰማሩ አባቶች፣ ልጆች አድራጊዎች እንዲሆኑም ያደርጋሉ፤ ለመንከባከብ የሚሳተፉት ለወንድነት ፍላጎት ተግባርም ይሰተፋሉ፡፡

3ኛ. ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ግንኙነት ቢኖርም፣ በመካከላቸው ከፍተኛ የሆነ ልዩነትም ታይቷል፡፡ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማለት ተዘዋዋሪ ተሳትፎ ማለት አይደለም፤ በአድራጊነት መሳተፍ ማለት ልጆች እንዲያደርጉ መርዳት ማለት አይደለም፤ ልጆችን ለመንከባከብ መሳተፍ ማለት ለወንድነት ፍላጎት ሲባል መሳተፍ ማለት አይደለም፡፡

## 4. ማጠቃለያ

ከጥናቱ ግኝት መረዳት የሚቻለው፣ እንደኢትዮጵያ ባሉና በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ያሉ ወጣቶች ለአባትነት ያላቸው እይታ ብዙ ገፅታ

© MoE, FD
Not to be rep

ያለው መሆኑን፣ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ ማለት ልክ እናቶች እንደሚንከባከቡት ዓይነት መንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለወንድነት ፍላጎት ማስፈፀሚያ ሊሆን የሚችል መሆኑንና (ለምሳሌ መቆጣጠር፣ ማዘዝ፣ የወንድነት ባህሪን ማስተማር ወዘተ.) ቀጥተኛ ተሳትፎ ያለማድረግ ማለት ያለመንከባከብ ያለመሆኑን ነው፡፡ ይህ በተለይ እንክብካቤን አስመልክቶ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ በርቀት ሆኖ የልጆችን ሁኔታ መከታተል መንከባከብ ነው ብለው አባቶች ሊያምኑ የሚችሉ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ምናልባት በአካል ከልጅ ጋር የማይታየው ግለሰብ ልጁን አይንከባከብም ቢባልም፣ እሱ ግን የሚያውቀው ያለመንከባከቡን ሳይሆን፣ ይልቁንም የበለጠ እየተንከባከበ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ ይህን ዓይነት አመለካከት አባቶች ልጆቻቸውን በመቅረብ ማሳለፍ የሚያስፈልጋቸውን ጊዜና ማጥፋት ያለባቸውን ጉልበት ላለማጥፋት የፈጠሩት የብልጣብልጥነት ዘዴ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ ወይም ወደልጆች መቅረቡ "የሴትነትን ሥራ" ማከናወን መስሎም ስለሚታያቸው፣ ከዚህ ለመሸሽ ሳያውቁት የፈጠሩት የመከላከያ ዘዴ ልንለውም እንችላለን፡፡ ምናልባትም አባቶች የበለጠ እንዳይቀየሩና ሴቶች ወደአደባባይ በወጡ ቁጥር እነሱም በተራቸው ወደቤት ውስጥ ዘልቆ የመግባትን የባህርይ ለውጥ እንዳያመጡ ያደረገው ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማንኛውም ወንዶችን መረዳት ካስፈለገ አሁን ካላቸው አተያይ ጋር (ያላቸው አተያይ የተሳሳተም ሊሆን ይችላል) ልንረዳቸው ይገባል፡፡ የለውጥ መጀመሪያው ችግርን ማወቁ ነውና፡፡

(ምንጭ፡- በላይ ተፈራ፣ 1993፡፡ "በልጅ አስተዳደግ አባታዊ ተሳትፎ፤የኢትዮጵያ ወጣቶች እይታ፡፡" ያልታተመ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡)

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. በኢትዮጵያ ሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ከሚተላለፉ የምርምር ውጤት ዘገባዎች (ለምሳሌ በሳይንስ፣ በጤና፣ በትምህርት ...) አንዱን መርጣችሁ አዳምጡና የጥናቶቹን ውጤቶች በአጭሩ በማስታወሻችሁ ጻፉ፤ ከዚያም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::

፪. በምርምር ዘገባዎቹ መሠረት ለምርምሮቹ መካሄድ ሰበብ የሆኑት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ፣ ምርምሮቹ የተካሄዱባቸው አጠቃላይ ደረጃዎች ምን እንደሚመስሉ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ ከላይ ካነበባችሁት የምርምርን አዘገጃጀት የሚመለከት ምንባብ ጽንሰ ሀሳብ ጋር በማስተያየት ያላችሁን አስተያየት በአጭሩ ተናገሩ::

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE
Not to be reprinted

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስለምርምር የቀረበላችሁን ምንባብ አንብባችሁ የተረዳችሁትን ሀሳብ በቃልና በጽሑፍ ገልጻችኋል፡፡ በጽሑፋችሁም ውስጥ ሥርዓተ ነጥቦችን በተለይም ማለበሚያን (አስተሪክስን) በአግባቡ ተጠቅማችኋል፡፡ ከዚያም በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች ውስጥ ዕውነታንና የግል አስተያትን መለየትን በተግባር አሳይታችኋል፡፡ መዝገበ ቃላትንና ዓውድንም በመጠቀም የቃላትን ፍቺዎች መስጠትና በዓረፍተነገርም ውስጥ መጠቀም ችላችኋል፡፡ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችንና የምርምር ውጤቶችን አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ ይዛችኋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ ምርምር ለመሥራት የሚረዱ የአሠራር ቅደም ተከተሎችን፣ ለጥናታዊ ጽሑፍ ሥራዎቻችሁ ከመጻሕፍት፣ ከተለያዩ ሰንጠረዦችና ከቃለ መጠይቆች የመረጃዎችን አሰባሰብ፣ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኛችኋቸውን ሀሳቦች በግለገለጻና በጭምቃሳብ መግለጽን፣ የመረጃ ምንጮችን አጠቃቀስ በመረዳት በጥናታዊ ሥራዎቻችሁ ውስጥ መጠቀምን በተግባር ተለማምዳችኋል፤ በደረጃችሁም አንድ ወጥ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅታችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ጥናታዊ ጽሑፍ ከሌላው ጽሑፍ በምን ይለያል?
2. ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሠራ ምን ምን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው?
3. የጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዋና ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አንብቤ የተረዳሁትን ሀሳብ በቃልና በጽሑፍ መግለጽ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ሥርዓተ ነጥቦችን በተለይም ማለበሚያን በአግባቡ መጠቀም ችያለሁ፡፡ በጽሑፍ ከሚቀርቡ ሥራዎች ውስጥ ዕውነታንና የግል አስተያየትን መለየት እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የቃላትን ቀጥተኛ ፍች መስጠት ችያለሁ፤ | | | |
| 4 | ከተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ሳይንሳዊ ግኝቶችና የምርምር ውጤቶች አዳምጬ ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ መያዝ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | የጥናታዊ ጽሑፍ ቅደም ተከተሎችን ተረድቼ ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጃለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ከመጻሕፍት፣ ከተለያዩ ሰንጠረዦች፣ ከቃለመጠይቆች ወዘተ. መረጃ መሰብሰብ እችላለሁ፤ | | | |
| 7 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ያገኟቸውን መረጃዎች በግለገለጻና በጥምቃሳብ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 8 | በአጠቃላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ማዘጋጀት ችያለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# ሥነግጥም

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- የሥነግጥምን ምንነት በቃልና በጽሑፍ ታስረዳላችሁ፤
- በግጥም ውስጥ ቃላት የሚኖራቸውን እማሬያዊም ሆነ ፍካሬያዊ ፍች ለይታችሁ ታሳያላችሁ፤
- በድምጾች መጥበቅና መላላት ምክንያት የሚፈጠሩ የፍች ለውጦችን ለይታችሁ ታስረዳላችሁ፤
- ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ፤
- የልዩ ልዩ ግጥሞችን መልእክት በራሳችሁ አገላለጽ በቃልና በጽሑፍ ታስረዳላችሁ፤
- የዘይቤዎችን ምንነት ታብራራላችሁ፤
- ከግጥም ውስጥ የዘይቤ ዓይነቶችን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፤
- የቅኔዎችን ምስጢር ፈትታችሁ ታሳያላችሁ፤
- አጭር ግጥም ትጽፋላችሁ።

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ግጥም ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘሮች የበለጠ ስሜታችንን የማማለል አቅም የሚኖረው ለምን ይመስላችኋል? በምክንያት የተደገፈ ማብራሪያ ስጡ፡፡
2. በተረትና በአፋዊ ግጥም ውስጥ ጊዜ፣ ሰማይ፣ ምድር፣ ዛፍ የመሳሰሉና ሰው ያልሆኑ ረቂቅና ግዑዝ ነገሮች እንደሰው አፍ አውጥተው ሲያወሩ ስትሰሙ ምን ስሜት ይፈጠርባችኋል? ምን የሚባለው የዘይቤ ዓይነትስ ትዝ ይላችኋል? ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑ ምሳሌዎችን አቅርቡ፡፡
3. ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም ርዕስ ስታነቡ ከግዑዝና ረቂቅ ነገሮች ንግግር ጋር የተያያዘ ምን ሐሳብ መጣላችሁ?
4. ከግጥሙ ርዕስ በመነሳት ግጥሙ ስለምን ሊናገር እንደፈለገ ገምቱ፡፡

### ዓለምና ጊዜ

እኔማ አቶ ጊዜ ከጥንት ዠምሬ፣
ለፍጥረት ታዛቢ ሆኜ በመኖሬ፤
እጅግ በረዘመው በራቀው  መንገዴ፣
ቸኩዬ በፍጥነት ሳልፍ እንደልማዴ፤
መቼም አይቀርና አይቶ መመልከት፣
ትልቅ ግቢ አይቼ ባለብዙ ቤት፤
ከደጅ ሲተራመስ ሰዉ ከቤት ተርፎ፣
ይመስል ነበረ ንብ ያለበት ቀፎ፡፡
ያጥሮቹ አሠራር የግቢውም መድመቅ፣
የቤቶቹም ብዛት በጣም የሚደነቅ፤
እንደዚህ ግቢውን ሠርቶ ያሳመረ፣

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

ማን ይሆን? አልኩና ከዚህ የሰፈረ፤
ደንቆኝ ስመለከት በጣም ተገርሜ፣
ሰው አገኘሁና አልኩት በል ወንድሜ፤
የዚህ የውብ ግቢ ባለቤቱ ማነው?
ያባት ያያቱ ርስት ያንድ ከበርቴ ነው፤
ርስቱም ዘላለም አለ ሳይነካ፣
ብሎ መለሰልኝ ኮርቶ እየተመካ።

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ፣
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ።
ከዚያ ካጥር ግቢ ከዚያ ሁሉ ቤት፣
ከቁመቱ ርዝመት ከጎኑ ስፋት፣
አንድ ድንጋይ እንኳ ጠፍቶ ምልክት፤
ያ ያየሁት ሁሉ እንዳልነበር ሆኖ፣
ከግቢው ቦታ ላይ አየሁ ትልቅ መስኖ።
የለመለመበት አንድ ትልቅ ጨፌ፣
ተመለከትሁና ልሄድ ስል አልፌ፤
አንድ ትልቅ ዛፍ ሥር ተጠግቶ ጥላ፣
አንድ እረኛ አገኘሁ ከብቶች ሣር ሲያበላ።
እንደዚህ ያለ ሣር የበቀለበት፣
ከመቼ ወዲህ ነው? ብዬ ጠየቅሁት።
እሱም ቁጭ እንዳለ ቀና ብሎ አይቶኝ፣
ዘላለም ለከብቶች ግጦሽ የሚገኝ፤
ከዚሁ መስኖ ነው ሲል መለሰልኝ።

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ፣
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ።
መስኖውም ጠፋና ጨፌነቱ ቀርቶ፣
ከመስኩ ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ፤



© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

የቤቱ መበርከት የመንገዱ ማማር፣
የከተማው ጥዳት የግንቡም አሠራር፤
የሕዝቡ አበዛዝ የገበያው መድመቅ፣
ታይቶ እማይጠገብ እጅግ የሚደነቅ፤
ያማረች ከተማ የጥበብ መዝገብ፣
ጠንተው የቆሙባት ዐዋጅና ደንብ፤
ውበቷን አድንቄ ስመለከታት፣
እድሜው የጠና ሰው አግኝቼ ድንገት፣
መች ነው የተሠራች? ብዬ ጠየቅሁት::
እሱም መለሰልኝ በጣቱ አመልክቶ፣
ይች ትልቅ ከተማ ከጥንትም አንሥቶ፤
መልኳ እየታደሰ ውበቷ እያበራ፣
ይኖራል ዘለዓለም ሥልጣኗ እንደ ኰራ::

ብዙ ትውልድ አልፎ ለትውልድ ደርሼ፣
ደግሞ በዚያው መንገድ መጣሁ ተመልሼ::
ከዚያች ከከተማ ጠፍቶ ምልክት፣
አየሁ ከዚያ ቦታ ጫካ በቅሎበት::
ሲተራመሱበት ቍብ፣ ነብር፣ አንበሳ፣
በያይነቱ አውሬ አእዋፍ እንስሳ፤
ሁሉም በየቋንቋው ድምጹን እያሰማ፣
ለጫካው ሲሰጡት የሚያስፈራ ግርማ፤
የዛፉ አበዛዝ ያውሬው መበርከት፣
እጅግ አስደናቂ ሆኖ አገኘሁት::
ደኑን ተመልክቼ እያየሁ ስሄድ፣
አገኘሁ ያገር ሰው ድንገት በመንገድ::
ዛፍ እንጨቱ በቅሎ ጫካው የደመቀው፣
ከመቼ ወዲህ ነው? ብዬ ብጠይቀው፤

© MoE, FDR
Not to be repu

ትክ ብሎ እያየ ጫካ ጫካውን፣
እንዲህ መለሰልኝ እሱም ተራውን፤
ይህን መጠየቅህ እንግዳ ነህ ለካ፣
ጥድ የሚበቅልበት ግራርና ወርካ፤
ጥንቱንም ደን ነው የዘላለም ጫካ።

አንዱ ስፍራ ሲለቅ አንዱ እየተተካ፣
ሁሉም ርስቴ ነች እያለ ሲመካ፤
ሞኝነት አድሮብን ሳናስበው እኛ፣
ዓለም ሰፈር ሆና ሕዝቡ መንገደኛ፤
ትውልድ ፈሳሽ ውሃ መሬቷም ቻረት፣
መሆኑን ዘንግቶ ይህ ሁሉ ፍጥረት፤
ስትመለከቱት በሰልፍ ተጉዞ፣
ሁሉም በየተራው ያልፋል ተያይዞ።

(ከበደ ሚካኤል (1994 ዓ.ም.) *የቅኔ ውበት።* አ.አ.፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።)

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. ግጥማዊ ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።**

1. አቶ ጊዜ በዓለም ላይ የኖረው ምን ሲያደርግ ነው?
2. ጊዜ፣ በረዘመው መንገዱ በፍጥነት ሲያልፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋጠመው ምንድን ነው?
3. “ይመስል ነበረ ንብ ያለበት ቀፎ” የተባለው ምንድን ነው?
4. አቶ ጊዜ በመንገዱ ያጋጠመው ባለብዙ ቤት ግቢ የማን ሆኖ ተገኘ?
5. በግጥሙ መጨረሻ አካባቢ “መሆኑን ዘንግቶ ይህ ሁሉ ፍጥረት” የሚል ስንኝ አለ። ፍጥረት ሁሉ የዘነጋው ምኑን ነው?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

6. አቶ ጊዜ በየትውልዱ ሲመላለስ፣ በአንድ ስፍራ ላይ ያጋጠሙት አካባቢያዊ ለውጦች ስንት ዓይነት ናቸው? በዝርዝር ግለጹ።
7. በዕድሜው ጠና ያለ ሰው አግኝቶ የጠየቀውስ ያ ስፍራ ምን ሆኖ ስላየ ነበር?
8. አቶ ጊዜ ስለዚያ ስፍራ ከጠየቃቸው ሰዎች መካከል የሥራ ድርሻው የተገለጸው የትኛው ነው? ሥራውስ ምንድን ነው?
9. ስላጋጠሙት ልዩ ልዩ አካባቢያዊ ለውጦች አቶ ጊዜ ላነሳቸው ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህርይ ምንድን ነው?
10. የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

፪. የሚከተሉት ስንኞች በምንባብነት ከቀረበው ግጥም ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። በየስንኞቹ ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት የያዙትን ዐውዳዊ ፍች ከገለጻችሁ በኋላ ተመሳሳይ ቃል ፈልጉላቸው።

1. ለፍጥረት ታዛቢ ሆኜ በመኖሬ
2. ያባት ያያቱ ርስት ያንድ ከበርቴ ነው
3. ርስቱም ዘላለም አለ ሳይነካ
4. ብሎ መለሰልኝ ኮርቶ እየተመካ
5. የለመለመበት አንድ ትልቅ ጨፌ
6. ዘላለም ለከብቶች ግጦሽ የሚገኝ
7. ከመስኩ ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ
8. ጠንተው የቆሙባት ዐዋጅና ደንብ
9. ለጫካው ሲሰጡት የሚያስፈራ ግርማ
10. ትውልድ ፈሳሽ ውሃ መሬቷም ቕረት

፫. የሚከተሉት ቃላት በግጥሙ ውስጥ ጠብቀው ወይም ሳልተው መነበባቸውን ለይታችሁ ከተናገራችሁ በኋላ፣ በግጥሙ ውስጥ ከሚነበቡበት በተቃራኒ ሲነበቡ በሚኖራቸው ፍች ዓረፍተነገር መስርቱባቸው፡፡

1. ትልቅ ግቢ አይቼ ባለብዙ ቤት
2. ይመስል ነበረ ንብ ያለበት ቀፎ፡፡
3. ሰው አገኘሁና አልኩት በል ወንድሜ
4. ያባት ያያቱ ርስት ያንድ ከበርቴ ነው
5. ርስቱም ዘላለም አለ ሳይነካ
6. አንድ እረኛ አገኘሁ ከብቶች ሣር ሲያበላ፡፡
7. እንደዚህ ያለ ሣር የበቀለበት
8. እሱም ቁጭ እንዳለ ቀና ብሎ አይቶኝ
9. ይች ትልቅ ከተማ ከጥንትም አንሥቶ
10. በያይነቱ አውሬ አእዋፍ እንስሳ፤

፬. እላይ ከቀረበው ግጥም በተወሰዱት በሚከተሉት ስንኞች ውስጥ በተሰመረባቸው ተመሳሳይ/ተወራራሽ ቃላት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ከገለጻችሁ በኋላ፣ ገጣሚው ለምን ዓላማ እንደተገለገሉባቸው አስረዱ፡፡

## ማስታወሻ

ገጣሚዎች ለሚገልጹት ሐሳብ አጽንዖት ለመስጠት ወይም ከቃላቱ ጠባብ የፍች ልዩነት አንዳች መልእክት ለማስገኘት ወይም ምጣኔውን ለመጠበቅና ዜማ ለመፍጠር ሲሉ ተቀራራቢ ፍች ያላቸውን ተመሳሳይ ቃላት፣ አንዳንድ ጊዜም አንድ ዓይነት ፍች ያላቸውን ተወራራሽ ቃላት አንድ ላይ በማሰለፍ ግጥም ይገጥማሉ፡፡

1. እጅግ በረዘመው በራቀው መንገዴ
2. ቸኩዬ በፍጥነት ሳልፍ እንደልማዴ
3. መቼም አይቀርና አይቶ መመልከት



© MoE, FDRE Not to be rep

4. ደንቆኝ ስመለከት በጣም ተገርሜ
5. ብሎ መለሰልኝ ኰርቶ እየተመካ
6. መስኖውም ጠፉና ጨፌነቱ ቀርቶ
   ከመስኩ ቦታ ላይ ከተማ ተሠርቶ
7. ጠንተው የቆሙባት ዐዋጅና ደንብ
8. መልኳ እየታደሰ ውበቷ እያበራ
9. በያይነቱ አውሬ አዕዋፍ እንስሳ፤
10. ጥንቱንም ደን ነው የዘላለም ጫካ፡፡

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. የሚከተሉት ስንኞች በምንባብነት ከቀረበው ግጥም የተወሰዱ ናቸው፡፡ ስንኞቹ የያዙትን ሐሳብ በራሳችሁ ዝርው አገላለጽ አስፋፍታችሁ ጻፉ፡፡

1. እኔማ አቶ ጊዜ ከጥንት ዠምሬ
   ለፍጥረት ታዛቢ ሆኜ በመኖሬ
2. ያማረች ከተማ የጥበብ መዝገብ
   ጠንተው የቆሙባት ዐዋጅና ደንብ
3. መልኳ እየደመቀ ውበቷ እያበራ
   ይኖራል ዘለዓለም ሥልጣኗ እንደኰራ፡፡
4. አንዱ ስፍራ ሲለቅ አንዱ እየተተካ
   ሁሉም ርስቴ ነች እያለ ሲመካ
   ሞኝነት አድሮብን ሳናስበው እኛ
   ዓለም ሰፈር ሆና ሕዝቡ መንገደኛ
   ትውልድ ፈሳሽ ውሃ መሬቷም ቸረት
   መሆኑን ዘንግቶ ይህ ሁሉ ፍጥረት
   ስትመለከቱት በሰልፍ ተጉዞ
   ሁሉም በየተራው ያልፋል ተያይዞ፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep

፪. የሚከተለውን ግጥም መልእክት የሚያብራራ አንድ የተሚሳ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

**አንሽና ወዳቂ**

ተዘርሮ አየሁት
ቀርቤ አነሳሁት
እሱ ግን ተከፋ
ቅስሙ ተሰበረ
አብሬው ባልወድቅ
ሳይፅናና ቀረ፡፡

(በእውቀቱ ስዩም (1995 ዓ.ም)፡፡ *ኗሪ አልባ ጎጆዎች፣* ገጽ 10)

፫. ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን ግጥም ደጋግማችሁ ካነበባችሁ በኋላ ወደስድ (ዝርው) ጽሑፍ ለውጣችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

**ተበላችሁ**

‘የበላና የተማረ ወድቆ አይወድቅም
በርታ ተማር’ ብላችሁ
ያሳደጋችሁት ልጃችሁ
የብሂሉን ልክነት አረጋግጦ
ተምሮ ተምሮ ስልጣኑን ጨብጦ
‘ውለታ ይመልሳል፣ ሕዝብ ያገለግላል’
ብላችሁ እናንተ ምላሽ ስትጠብቁ
እውቀቱን መች አጣት አጅሬ ጥንቁቁ
ዞሮ የናንተኑ ሀብታችሁን ግጦ
  የቀረውን ሸጦ
ቅርጥፍ አርጎ በላ የሀገር አደራ
ብላችሁት የለ አይወድቅም የበላ፡፡

(ሜሮን ጌትነት (1999 ዓ.ም.)፡፡ *ዙረት፣* ገጽ 36)

፬. ከዚህ በላይ የቀረበውን ግጥም መልእክት በአንድ ዓረፍተነገር ግለጹ፡፡

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

፩. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ አንድ ጊዜ ብቻ የሚያነቡላችሁን አንድ ግጥም በጽሞና አዳምጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ::

1. በግጥሙ ውስጥ አያቶች፣ አባቶች፣ ልጆች የተባሉት እነማን ናቸው?
2. አያቶች ምን ሲያደርጉ ኖሩ?
3. አባቶች ምን አድርገው አለፉ?
4. ልጆች ምን ማድረግን መረጡ?
5. የግጥሙ ዋና መልእክት ምንድን ነው?
6. በግጥሙ ውስጥ በተደጋጋሚ የተገለጸው ጎጆ ምንን ወክሎ የገባ ነው?

፪. በመምህራችሁ የታዘዙ ሁለት ተማሪዎች በየተራ የሚያቀርቡላችሁን አፋዊ ግጥሞች በጽሞና አዳምጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ::

1. ግጥሞቹ የያዙት ሐሳብ ምንድን ነው? ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ::
2. በእያንዳንዳቸው ውስጥ የሚገኘው የዘይቤ ዓይነት ምን እንደሆነ ግለጹ::

፫. በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚተላለፉ ግጥሞችን አዳምጣችሁ የግጥሞቹን መልእክት እና ስለግጥሞቹ ያላችሁን አስተያየት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ::

## ክፍል አራት:- መናገር

፩. በምንባብነት የቀረበው ግጥም ያሳደረባችሁን ስሜት አጠር አድርጋችሁ በቃል አስረዱ::

© MoE, FDRE, Not to be republished

፪. በመምህራችሁ አስተናባሪነት እንደየፍላጎታችሁ በሁለት ቡድን ተመዳደባችሁ፣ ስለግጥም ባህሪና አፈጣጠር ከተሰነዘሩት ከሚከተሉት ሁለት ሐሳቦች መካከል አንዱን መርጣችሁ በመደገፍ በሥነሥርዓት ተከራከሩ፡፡

1. ግጥም ከልቦለድ የበለጠ አንባቢን ይስባል፡፡
2. ግጥም መጻፍ፥ ማንኛውም ሰው ሊሞክረው የሚችል ቀላል ተግባር ነው፡፡

## ክፍል አምስት:- ሥነልሳን

፩. በምሳሌው መሠረት ከሚከተሉት ግሶች ውልድ ስም (በቀድሞ አጠራሩ ጥሬ ዘር) አውጡ፡፡

**ምሳሌ:-** 'ካደ' ከሚለው 'ክህደት'፣ 'ጋለበ' ከሚለው ደግሞ 'ግልቢያ' ይመሠረታል፡፡

| | |
|---|---|
| 1. ባለገ | 6. መሰከረ |
| 2. ገመተ | 7. ኀበጠ |
| 3. ገረጣ | 8. ኀለመሰ |
| 4. ገነዘ | 9. ቀረደደ |
| 5. ዘረዘረ | 10. መነተፈ |

፪. ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው ናቸው፡፡ ሰዋስዋዊ ስህተቱ የምን እንደሆነ ከተናገራችሁ በኋላ ዓረፍተነገሮቹን አቃንታችሁ እንደገና ጻፏቸው፡፡

1. ለተማሪዎች ከሚያስፈልጋቸው ነገሮች አንዱ ንጽህናው የተጠበቀ የመማሪያ ክፍል ነው፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት መስፋፋት ለሕብረተሰቡ የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው፡፡
3. ትዳር ለመመሥረት መጠናናት አያስፈልግም የሚል ሁሉ ለራሳቸው ሳያውቁ ሌላውን የሚመክሩ ናቸው፡፡



© MoE, FDRE Not to be reprinted

4. መምህራን ለግድቡ ማሠሪያ ያዋጡትን የገንዘብ ድጋፍ ቦንድ እንዲገዛበት ተወሰነ።
5. የጥላሁን ገሠሠ እና የማይክል ጃክሰን ተከታትሎ መሞት በሙዚቃው ዘርፍ ላይ ትልቅ ጉዳት እንደሚያስከትሉ የታወቀ ነው።
6. ፀሐይን ከጨረቃ የበለጠች ጠቃሚ የሚያደርጋት ፀሐይ የራሱን ብርሃን የሚፈጥር መሆኗ ነው።
7. የሀገራችን ሯጮች ብዙ ልምምድ ስለሚያደርጉና ራሳቸውን ከአጉል ሱስ በመጠበቃቸው ሁልጊዜ ውጤታማ ይሆናሉ።
8. ደራስያን የሚፈጥሯት ኪነት ለሕብረተሰቡ ትልቅ ጥቅም እንደሚሰጥ ማንም አይክድም።
9. ቋንቋን በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አማካይነት መማር የሚኖራቸው ጥቅም ተወዳዳሪ የለውም።
10. የሚቀጥለው ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ከዘንድሮው ፈተና ከብዶ እንደነበር መገመት ይቻላል።

## ክፍል ስድስት:- ሥነጽሑፍ

፩. “ዓለምና ጊዜ” በተባለው ግጥም ውስጥ ሁለት ስንኞች ተደጋግመው ተጽፈዋል።

ሀ) እነዚህ ስንኞች የትኞቹ ናቸው?
ለ) በግጥሙ ውስጥ ያላቸው አገልግሎትስ ምንድን ነው?
ሐ) በዘፈን ግጥም እንደዚህ ለሚደጋገሙ አውራ ስንኞች የሚሰጠው ስም ምን ይባላል?

፪. “ዓለምና ጊዜ” የተባለው ግጥም ሰውኛ ዘይቤን እንዴት ተገልግሎበታል? ምን ማስረጃ አላችሁ?

፫. በአንዳንድ ሐያስያን አገላለጽ “ሥነግጥም የህይወት ሒስ ነው” ይባላል። “ዓለምና ጊዜ” የተሰኘው ግጥም “ሥነግጥም የህይወት ሒስ ነው” የሚለውን አባባል የሚያረጋግጥ ይመስላችኋል? ያረጋግጣል የምትሉ ከሆነ ህይወታችንን እንዴት እንደሚተች አስረዱ።



© MoE, FDRE, Not to be republished

© MoE, FDR
Not to be rep

## ሥነግጥም

ሥነግጥም፣ በደምሳሳ አገላለጽ፣ የግጥም አጻጻፍ ጥበብ ማለት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ግጥምን እውን ለማድረግ የሚኖረውን ሥንክናዊ የአበጃጀት ተግባርና የግጥምን ምልዐተ ተፈጥሮ የሚያካትት የሥነጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡ ሥነግጥም የጥበቡ መጠሪያ ነው፡፡

ግጥም ደግሞ የጥበቡ ውጤት መጠሪያ ነው፡፡ ማለትም በስንኞች የሚመጠን፣ ምትና ዜማ ያለው፣ ቤት የሚመታ፣ በዚህም ከስድ ጽሑፍ የሚለይ፣ መልእክትን ለዛ፣ እምቅነትና ክረት ባለው መልክ ለመግለጽ ወይም ለማስተላለፍ የሚያስችል ኪናዊ የሐሳብና የስሜት መግለጫ ነው፡፡ ከስድ ጽሑፍ በተለየ ዓይን የሚታይበትና የሚመረጥበትም ምክንያት፣ ገጣሚው ደበበ ሰይፉ እንዳለው፣ "አንዳች ስሜትንና ሐሳብን፣ ማለትም ትርጉም አዘል ሰብአዊ ገጠመኝን ክረትና ኃይል፣ ፍላትና ቅርበት ባለው መንገድ የመግለጽና የማስተላለፍ" ብርቱ አቅም ያለው መሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ "ግጥም" እና "ሥነግጥም" የሚሉትን እሳቤዎች ማምታታት አይገባም፡፡ ብዙ ሰዎች ግን ይህን ልዩነት በጽሞና መርምረው የተረዱት አይመስሉም፡፡ መድረክ ላይ ወጥተው አንድ ግጥም ሊያነቡ ሲዘጋጁ "አንድ ሥነግጥም ላነብላችሁ ነው" ማለት ይቀናቸዋል፡፡ ይሄ የተሳሳተ መሆኑን ለማስረገጥ በባህላችን በስፋት የሚታወቅ አንድ ሞያ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ "ሽመና" በልዩ ልዩ የጥበቡ መሣሪያዎች መገልገልን የሚጠይቅና የተወሰኑ የክንውን ደረጃዎች ያሉት ሞያ ነው፡፡ በዚህ ሞያ ባለቤቶች የሚመረተው ጥሬ ነገር ሸማ ይባላል፡፡ ታዲያ "ሸማ ሠራሁ፣ ሸማ ለበስኩ" እንጂ "ሸመና ሠራሁ፣ ሸመና ለበስኩ" እንደማይባል ሁሉ "ግጥም ጻፍኩ፣ ግጥም አነበብኩ" እንጂ "ሥነግጥም ጻፍኩ፣ ሥነግጥም አነበብኩ" ማለት እንደማይገባ መረዳት ያሻል፡፡

ግጥም ራሱን የቻለ አንድ ሥነጽሑፋዊ ቅርጽ ነው፡፡ ማለትም ገጣሚ ሰሎሞን ዴሬሳ እንዳለው፣ "ግጥም ቅርጽ አለው፤ እንደእብነበረድ የሚዳሰስም ባይሆን፡፡ ባጭሩ የስንኞች መገናኘት፣ የድምጽ ስልት፣ አወራረድ፣ ከቃላቱ የሚፍለቀለቁት ሥዕሎች አመጣጥ፣ ወረቀት ላይ ታትሞ የሚታየው የየግጥሙ ጠቅላላ ቅርጽ፣ የመስመሮች እጥረት የሚያስከትለው ጥድፊያ ወይንም ተጎታችነት፤ የስሜት፣ የሐሳብና የዜማ መወሳሰብ፣…" ሁሉ አንድ ቅርጽ ነው፡፡ ይህን ቅርጽ የሚፈጥረው ወይም ግጥምን እንደአንድ ራሱን የቻለ ሥንክናዊ ቅርጽ በምልዐት የሚያስገኘው በፈጠራ ሥራነቱ የሚኖሩት የተለያዩ አላባውያኑ እና ባህርያቱ የጠበቀ ጽምረት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተወሳው ደግሞ ግጥምን ከሌሎች ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተለየ የሚያደርጉት ምጣኔውና ምቱ ናቸው፡፡

ምትና ምጣኔ እጅግ የጠበቀ ትስስር ያላቸው የግጥም አላባዎች ናቸው፡፡ በሥነግጥም ምት የምንለው፣ እንደልብ ትርታ ተደጋግመው በሚሰሙና በአንድ ትንፋሽ በሚነበቡ የቃላት ስብስቦች መሀል ያለውን የተወሰነ የጊዜ መጠን መጠበቂያ ስልት ነው፡፡ የግጥም ምት የሚመነጨው ሌሎቹ የምልዐቱ ማስገኛ ክፍሎች ከሚኖራቸው ምጣኔ ነው፡፡ ስለዚህ ምጣኔ በተፈጥሯዊ ቅንብርና በሥርዓታዊ ትስስር ግጥምን ህልው የሚያደርጉት ልዩ ልዩ ምልዐት ማስገኛ አላባዎች መጠን የሚወሰንበት ልኬታ ነው፡፡ እነዚህ አላባዎች ስንኝ፣ ሐረግ፣ ቤት፣ ቤት መምቻ፣ ቤት መድፊያ፣ ቀለም፣ ምት፣ ምጣኔ፣ ዜማ፣ አርኬ፣ እና አንጓ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

(ብርሃኑ ገበየሁ (1999 ዓ.ም.)፡፡ *የአማርኛ ሥነግጥም*፡)

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፬. የሚከተለው ግጥም በተምሳሌት ዘይቤ የተጻፈ ነው፡፡ ግጥሙን ደጋግማችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ ምን በምን ተወክሉ እንደቀረበ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡ ለምትገልጹት ውክልና ከግጥሙ ውስጥ የተወሰደ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋችኋል፡፡

**ብቻ መገኘትሽ**

እንደናፋቂ ህጻን እናቱን እንዳየ
በደስታ ሐዘን እንደተሰቃየ፣
እንባውን እንዲያዘንብ ለሐሴቱ መቅድም
ዐይንሽን ባየሁኝ እንባዬን ባፈስም፤
ወይም
ታውሮ እንደኖረ እንደአንድ ጎበዝ
በድንገት ብልጭታ እንዲደነዝዝ
በጨለማ ቤቱ አንቺ ጮራይቱ
ዘው በማለትሽ ቢጠፉኝ ብልሃቱ፤
እንባውም ይደርቃል
ብልሃቱም ይገኛል፤
የወጣሽው ፀሐይ ጽልመቱ ሲሸሸ
        ብቻ መገኘትሽ
        ብቻ መኖርሽ፡፡

(ደበበ ሰይፉ (1980 ዓ.ም.)፡፡ *የብርሃን ፍቅር፡፡* አ.አ.፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ገጽ 61፡፡)

፭. በሚከተለው የግጥም ቅንጫቢ ውስጥ የሚገኙት ስንኞች በምጸት ዘይቤ የተጻፉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ስንኞቹን በእርጋታ አንብባችሁ ምጸትነቱ እምኑ ላይ እንደሆነ አስረዱ፡፡

ሰው ለምን ያማዋል?
ባህል አፍራሽ ብሎ ይህን ጆሊ ጆኒ

ቅጠል በልቶ እሚውል
ዕፅ አሽቶ እሚያድር እሱ እንደሁ መናኒ
አባ ሆይ ተብዬ
ልከበር አላለ አልተመጻደቀ
'ስምዓኒ' እያለ
ጧት ማታ በስግደት ቅስሙ እየደቀቀ
ወገቡ እያለቀ።

(ደበበ ሰይፉ (1980 ዓ.ም)። *የብርሃን ፍቅር።* አ.አ.፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ ገጽ 92።)

፮. በሚከተለው የግጥም ቅንጫቢ ውስጥ ያሉት ስንኞች ደግሞ ጠቃሽ (ንቡር ጠቃሽ) ዘይቤ የሚገኝባቸው ናቸው። ስንኞቹን በጽሞና አንብቡና ምን ምንን ከምን ከምን እንደጠቀሱ በመግለጽ የመጥቀሱን ፋይዳ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

ምክንያቱን ይሻል ለሚታየው ሁሉ፤
እንዲያው፤ ለግብር ይውጣ፤ ለወጉ ላመሉ።

ሶቅራጥስ አፍላጦን ሙሴና ዳዊት፤
ያለም ፈላስፋዎች ያለም ነብያት፤
የትናንቶቹና የትናንቱ በስቲያ
የዚያ የዚህ ወዲያ . . . ወዲያ . . . ወዲያ፤ ወዲያ!
ልቤ ተስፋን ቆርጧል እናንተን አይቼ።
ግና ሁሉ ሲሞት ልብ ይሞታል መቼ?

ስሕተት ነው መሰለኝ ሰበቡን መሻት
"ለምንድነው" ማለት "ለምን ምክንያት"
ለምንድነው አንበል?
"ለ"ን እንግደፋት?

(መንግሥቱ ለማ (1952 ዓ.ም.)። *የግጥም ጉባዔ።* አ.አ.፣ ብ.ሰ.ማ/ቤት፣ ገጽ 11-12።)

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FD
Not to be rep

## ጠቃሽ ዘይቤ

ከዚህ ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች አነጻጻሪ፣ ለዋጭ፣ ግነት፣ ሰውኛ፣ ተምሳሌት፣ ምጸት፣ አያዎ ስለመሳሰሉ የዘይቤ ዓይነቶች ተምራችኋል፡፡ አሁን ደግሞ ስለጠቃሽ ዘይቤ የሚከተለውን አጭር ማብራሪያ አንብባችሁ ለመረዳት ሞክሩ፡፡

በሥነጽሁፍ ወይም በታሪክ ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን፣ ሁነቶችን ወይም ነገሮችን፣ የሚጠራ፣ የሚያነሳ ወይም የሚጠቅስ የዘይቤ ዓይነት ነው፡፡ ጠቃሽ በቃላት የዝምድና አካሄድ ፍችን የማሸጋገር ስልት ነው፤ አንድ ቃል ከዘወትሩ ፍችው በተለየ ሁኔታ የሚያስታውሰው አንድ ሐሳብ፣ ድርጊት ወይም ታሪክ፡፡ በሌላ አባባል፣ ጠቃሽ ቃላት ከቀጥተኛና መደበኛ ፍቻቸው በስተጀርባ አዝለውት የሚኖሩት የታሪክና የባህል ቅሪት (ክምችት) ነው፡፡ ገጣምያን ጠቃሽ ዘይቤን መልክአምድራዊ አካባቢና ከተወሰነ የዘመን ድንበር ለማዘለል፣ በሌላ ቃልም ሁለንተናዊ ፍች ለመሻት ነው፡፡ ጠቃሽ ዘይቤ አቀራረቡ ኢርቱዕ ሲሆን፣ ገጣሚውና አንባቢው ስለተጠቃሹ ነገር በጋራ የሚያውቁት ነገር እንዳለ በመገመት የሚደረግ የንግግር ስልት ነው፡፡

ታሪክ ጠቃሽ በታሪክ ሰነዶችና በቃል ታሪክ የታወቁ ሰብእናዎችን፣ ድርጊቶችንና ቦታዎችን፣ በርዕሰ ጉዳይነት ሳይሆን ስለአንድ ሌላ ጉዳይ ጣልቃ አስገብቶ በማምጣት፣ ሐሳብን የማግዘፍ፣ የማስፋትና ከታሪክ የማዛመድ ብልሀት ነው፡፡...

ሥነጽሁፍ ጠቃሽ እንደታሪካዊ ሁነቶች ሁሉ ገጣሚው ሐሳቡን ለማግዘፍ በታላላቅና ታዋቂ ደራስያን ሥራዎች፣ በተረት ወይም በአፈታሪክ የሚገኙ ገጸባህርያትን፣ ድርጊቶችንና ትዕይንቶችን ሊያጣቅስ ይችላል፡፡...

ቅዱሳት መጻሕፍት፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቅዱስ ቁርዓን እንዲሁም ሌሎቹ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የሚመሩባቸው መጻሕፍት፣ ከሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ፋይዳቸው በተጨማሪ ታላላቅ የእውቀት ምንጮች መሆናቸው የተረጋገጠ እውነት ነው፡፡ እያንዳንዳቸውም አማኞቻቸው እንደ ህይወት መመሪያ የሚከተሏቸው፣ በታላቅ አክብሮት የሚመለከቷቸው ሰብዕናዎች የሚገኙባቸው ሁነቶችና ትረካዎች አሏቸው፡፡ ... መጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሽ [ከእንደነዚህ ዓይነት ቅዱሳት መጻሕፍትና ከሃይማኖታዊ ጽሑፎች] ሰዎችን፣ ሁኔታዎችን፣ ድርጊቶችን፣ ትረካዎችን፣ አባባሎችን፣ ወዘተ. የሚጠቅስ ዘይቤ ነው፡፡

(ብርሃኑ ገበየሁ (1999 ዓ.ም)፡፡ *የአማርኛ ሥነግጥም፡፡ ገጽ* 138-145)

**፯. የሚከተሉትን ቅኔዎች ሕብረቃል ከለያችሁ በኋላ ቀጥተኛ ፍቻቸውን (ሰሙን) እና ምስጢራዊ ፍቻቸውን (ወርቁን) ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. ሸማማ ሁል ጊዜ እለብስ የለም ወይ፣
   ብርቅ መስሎ ታየኝ ጥበብ ለብሰው ባይ፡፡
2. አጠገቤ ሆኖ ሲጠይቀኝ ወሬ፣
   አላቅም ብዬ ነው አለመናገሬ፡፡
3. ዘንፋላ ፀጉሯን ሳይ ወንድሟ ቢያየኝ፣
   ላጫት ላጫት አልኩት የምለው ጠፍቶኝ፡፡
4. አሞራ አይደለሁ ሳቢሳ፣
   ላባይ ለጣና የምሳሳ፤
   ከባሕሩ ቆሜ ቢያየኝ፣
   እኔን ደሴት አለኝ፡፡
5. ማነው ይህን መጽሐፍ ሳያትም የቀረ፣
   መምህሩስ የሚሉት አትሙት ነበረ፡፡
6. ሰው ሁሉ አብዝቶ ይጠጣል በጣም
   እኔስ ምንም ብሆን ከልኬ አላልፍም፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

7. መቼ ነው ኮረንቲ ሐኪም የሆነው፣
   የያንዳንዱን ሰው ደም የሚመጥነው፡፡
8. ሚስቴ በያይነቱ ቁርሴን ስትሰጠኝ፣
   ቅንጨዋ ናት ለኔ የምትጥመኝ፡፡
9. የሠራውን ሠርቶ አበጀሁ ቢላችሁ፣
   ይህን ባለ ጊዜ ምን ትሉታላችሁ፡፡
10. መስተዋት አልገዛ እጄ ባዶ ነው፣
    በሰው መስተዋት ነው ፊቴን የማየው፡፡

፫. በዚህ ምእራፍ ውስጥ ካየናቸው የዘይቤ ዓይነቶች መካከል አንዱ ወይም ሁለቱ የሚገኙበት አጭር ግጥም ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩና የተሻለ ነው ተብሎ ሲመረጥላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡



© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ስለሥነግጥም ምንነትና ባህርያት አውቃችኋል፡፡ ስለዘይቤ ምንነትና ዓይነቶች፣ እንዲሁም ዘይቤ በሥነግጥም ውስጥ ስላለው ሚና ተረድታችኋል፡፡ ግጥምን ወደስድ ጽሑፍ ለውጦ ስለመጻፍ እና የግጥምን መልእክት በራስ አባባል ስለመግለጽ አውቃችሁ በቂ ልምምድ አድርጋችኋል፡፡ በመጥበቅና በመላላት የፍች ልዩነት የሚያመጡ ቃላትን ባህርይ አውቃችኋል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ የግጥሞችን መልእክት በራሳችሁ አባባል ገልጻችኋል፡፡ አጭር ግጥም ጽፋችኋል፡፡ ስለቅኔ አፈታት ብልሃቶች ተረድታችሁም ቅኔ አፈታትን ተለማምዳችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሥነግጥም ከሌሎች የሥነጽሑፍ ዘሮች የበለጠ ስሜታችንን የሚስበው በምን ምክንያት ነው?
2. ዘይቤ በሥነግጥም ውስጥ ምን ዓይነት አገልግሎት ይሰጣል?
3. ሦስቱ የጠቃሽ ዘይቤ ዓይነቶች ልዩነት ምንድን ነው?
3. በመጥበቅና በመላላት የፍች ለውጥ የሚያመጡ ቃላት ከአማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድን ነው?
4. ከምዕራፉ ምን አዲስ እውቀት ገበያችሁ?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል:: በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ::

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥነግጥምን ምንነት በቃልና በጽሑፍ ማስረዳት እችላለሁ:: | | | |
| 2 | በግጥም ውስጥ ቃላት የሚኖራቸውን ዐውዳዊ ፍች ለይቼ አሳያለሁ:: | | | |
| 3 | በድምፆች መጥበቅና መላላት ምክንያት የሚፈጠሩ የፍች ለውጦችን ለይቼ አስረዳለሁ:: | | | |
| 4 | ከመገናኛ ብዙሃን ልዩ ልዩ የሥነጽሑፍ ሥራዎችን አዳምጬ እረዳለሁ:: | | | |
| 5 | የልዩ ልዩ ግጥሞችን መልእክት በራሴ አገላለጽ በቃልና በጽሑፍ አስረዳለሁ:: | | | |
| 6 | የዘይቤዎችን ምንነት አብራራለሁ:: | | | |
| 7 | ከግጥም ውስጥ የዘይቤ ዓይነቶችን ለይቼ ማውጣት እችላለሁ:: | | | |
| 8 | የቅኔዎችን ምስጢር ፈትቼ አሳያለሁ:: | | | |
| 9 | አጭር ግጥም እጽፋለሁ:: | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደግማችሁ ከልሱ::



© MoE, FDRE
Not to be republished

# ምዕራፍ ስምንት

## ውሳኔ ላይ መድረስ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ:-**

- ለቃላት ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፤
- ወቅታዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመገናኛ ብዙሃን ታዳምጣላችሁ፤
- ሥርዓትን ተከትላችሁ ትከራከራላችሁ፤
- መመሪያዎችን ተከትላችሁ ልዩ ልዩ ተግባራትን ታከናውናላችሁ፤
- ከቃለመጠይቅና ከሠንጠረዥ የምታገኙትን ሐሳብ አደራጅታችሁ ጽሑፍ ታዘጋጃላችሁ፤
- ከምታዳምጡትና ከምታነቡት ጽሑፍ ማስታወሻ መውሰድ ትችላላችሁ፤

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ውሳኔ ስለሚያስፈልገው አንድ ብርቱ ጉዳይ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምን ምን ነገሮች ታሳቢ መሆን ይኖርባቸዋል?
2. በአስተማማኝ ማስረጃ ላይ በመመሥረት በእርግጠኛነት የሚወሰኑ ውሳኔዎች ምን ዓይነት ባህርይ ያላቸው ይመስሏችኋል? በይሆናል የምንወስነውስ ውሳኔ?
3. በግል የሚወሰን ውሳኔና ሰዎች ተሰብስበው በጋራ የሚወስኑት ውሳኔ በምን ይለያያል?
4. ዲሞክራሲያዊ ውይይት ተገቢ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?

## ውሳኔ ላይ መድረስ

ሰው አየር፣ ምግብ፣ ውሃ ወዘተ. ያስፈልጉታል። እነዚህን ማጣት የረሀብ፣ የጥማት ወይም የሌላ ዓይነት ፍላጎት ግፊት ይፈጥራል። ይህን የመሰለው ግፊት በመጨረሻ ፍላጎትን ወደውሳኔ ያሸጋግራል። ግፊት እርካታን ይፈልጋል። ይህን የመሰለው ውስጣዊ ግፊት በተለይ በመጀመሪያው የሕፃንነት እድሜ ክልል ወቅት እጅግ አይሎ የሚታይ ቢሆንም፣ እድሜ በገፋ መጠን በሌሎች አእምሮአዊ ኃይሎች እየተገራ ይሄዳል። የታየው ሁሉ በግድም በውድም ይኑረኝ የሚለው ሐሳብ እየተዳከመ ይመጣል።

የሦስት ወይም የአራት ዓመት ሕፃን ጉረቤት ለሚኖር ጓደኛው የተገዛለትን ዓይነት አሻንጉሊት ቤተሰቦቹ እንዲገዙለት ወዲያው ይወስንና ቤተሰቦቹን ይወተውት ይሆናል። ዳሩ ግን እድሜው እየገፋ በሄደ መጠን ውስጣዊ ግፊቱን ከዳር ለማድረስ የወላጆቹ አቅም የሚፈቅድ መሆንና አለመሆኑን ማጤን ይጀምራል። ማለትም ውስጣዊ ግፊቱን ከውጫዊ ነባራዊ እውነታ ጋር የማገናዘብና ውሳኔ የማስተላለፍ ብቃቱ ከጊዜ ወደ

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

ጊዜ እያደገና ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ምክንያታዊነቱን እያዳበረ ይሄዳል፡፡

ይህን የመሰለው የአስተሳሰብ እድገት በወጣትነት ዘመንም የሚቀጥል ቢሆንም ውስጣዊ ግፊትን በአስተዋይነት፣ አዙሮ በማየት፣ በይሉኝታ፣ ወዘተ. የመግራትና የመቆጣጠር ብቃት ጉልቶ የሚታየው በተለይ በጉልማሳነት ዘመን ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በጉልማሳነት ዘመን ውስጣዊ ግፊት ሙሉ በሙሉ ኃይሉን ያጣል ማለት አይደለም፡፡ በመሠረቱ ውስጣዊ ግፊት የውጤታማ ውሳኔ መሠረት ነው፡፡ ውስጣዊ ግፊት ከሌለ ጠንካራ አእምሮአዊ ኃይል ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም ይህን ግፊት ከነባራዊ እውነታ ጋር አገናዝቦ ፈር ከማስያዝ ይልቅ በአብዛኛው ለማፈን መሞከር ውስጣዊ ችግርን ይፈጥራል፡፡ በአንፃሩም ውስጣዊ ግፊትን ሙሉ በሙሉ ወደፍላጎት ማሸጋገርና ከዚያም ባልተገራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ውሳኔን መወሰን ከስህተትና ከጭንቀት ላይ ይጥላል፡፡

ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ድቅን በሚሉባቸው ሀሳቦች ላይ ጊዜ ወስደው፣ በማውጣት በማውረድ ጠቃሚና ጎጂ ጎኖችን በምክንያቶች በመለየት ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ፡፡ በዚሁ መሠረት በተለያዩ ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዴት ከውሳኔ ላይ እንደሚደርሱ ለአብነት ያህል ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

አንድ ሰው ምግብ ለመመገብ ሆቴል ገባ እንበል፡፡ አጠገቡ የተቀመጠው ሰው የሚመገበውን ቁርጥ (ጥሬ ሥጋ) ለመመገብ ቢጐመዥም ይህን ምግብ ለመግዛት የሚያስችል ገንዘብ ኪሱ ውስጥ ከሌለ የሚመገበው አቅሙ የሚፈቅደውን ሌላ ዓይነት ምግብ ይሆናል፡፡ ያም ሆኖ ፍላጎት ወደውሳኔ ከመሸጋገሩ በፊት የሰው አዙሮ የማየትና የማስተዋል ብቃት ፍላጎትን ከነባራዊ እውነታ አኳያ ይገራዋል፡፡ ይህን ከመሰለው

ውስጣዊ ክርክር በኋላም የውስጣዊ ሙግት ውጤት የውጫዊ ተግባር እቅድን ወይም ውሳኔን ያስከትላል፡፡

እስኪ ጉዳዩን ከትምህርት ፍላጎት አንጻር እንመልከተው፤ አንድ የመንግሥት ወይም የግል ድርጅት ሠራተኛ ከፍተኛ ትምህርቱን ለመቀጠል ፍላጎትም ውስጣዊ ግፊትም አለው፡፡ ግን "እንዴት ነው መማር የምችለው?" የሚለው ሐሳብ ዘወትር ያስጨንቀዋል፡፡ "በቀጥታ መደበኛ ተማሪ በመሆን ትምህርቴን ልቀጥል ወይስ በማታ?" በሚሉት ሐሳቦች ላይ ለመወሰን በቀን ወይም በማታ ቢማር የሚኖረውን ጥቅምና ጉዳት ያመዛዝናል፤ ያወጣል፤ ያወርዳል፡፡ በቀን ለመማር ከፈለገ ደመወዝ ሊቋረጥ ነው፡፡ ደመወዝ ተቋረጠ ማለት ደግሞ ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማሟላት እና ለመማር አቅም ማጣት ማለት ነው፡፡

ከዚህ የሐሳብ አዙሪት ለመውጣት ብዙ ይታገላል፡፡ በመጨረሻም በቀን መማር ባጭር ጊዜ ለመጨረስ የሚረዳ ቢሆንም፣ ለኑሮ እጅግ መሠረታዊ የሆነውን ሥራ እና ገንዘብ የሚያሳጣ መሆኑን፣ በዚህም ሊመጣ የሚችለውን ችግር በማመዛዘን ረጅም ጊዜ ቢወስድም፣ በማታው ለመማርና የትምህርት ደረጃውን ለማሳደግ የውሳኔ ሐሳብ ላይ ይደርሳል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

- እስካሁን ካነበባችሁት ውስጥ ስለውሳኔ አሰጣጥ ምን ተረዳችሁ? በቀጣይስ ምን ማወቅ ትፈልጋላችሁ?
- ቀጥሎ በማስረጃነት በሚቀርበው የምንባቡ ቀሪ ክፍል ምን ምን ሐሳቦች ይነሳሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

© MoE, FDRE, Not to be reprinted

ቀጥለን ከስደት ጋር ተያይዞ የሚመጣን ውሳኔ እንመልከት:: አንድ ሰው ከኢትዮጵያ ውጪ ሄዶ ሠርቶ ሀብት ለማግኘትና ወዳገሩ ለመመለስ ይፈልጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ እያሰበበት ሲሄድ፣ ውስጣዊ ግፊቱ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ በዚህም ምክንያት ቤተሰቦቹን በዋስትና አስይዞ ከዘመድ አዝማዱ ሠላሳ ወይም አርባ ሺህ ብር ተበድሮ (ተለቅቶ) አንዳንድ ጊዜ እንደሚደረገው በህገወጥ መንገድ ወደውጭ ይሄዳል፡፡ ጉዳዩን በጽሞና ቢያስበው ኖሮ በሠላሳና አርባ ሺህ ብር እዚሁ አገር ውስጥ ሠርቶ በማትረፍ ቀስ በቀስ እንደሌሎች የሀገራችን ሀብታሞች ሀብታም መሆን ይችል እንደነበረ ይረዳ ነበር፡፡ ሆኖም «ውጪ ሀገር ሄጄ በአጭር ጊዜ ተሯሩጬ ብሠራ ወይም ብነግድ ሀብታም እሆናለሁ» የሚለው ሐሳብ ሚዛን ስለደፋ ወደ ውጪ ለመንዝ የውሳኔ ሐሳብ ላይ በመድረስ ወደዚያው ያቀናል፡፡

በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ አስፈላጊ የሆነና ውሳኔን የሚጠይቅ ሌላ ጉዳይ እድር ነው፡፡ እድር በመግባትና ባለመግባት መካከል የሚኖር ፍላጎትና ውስጣዊ ግፊት በሰዎች ዘንድ ይታያል፡፡ እድር መግባቱ የሚያስከትለው ኃላፊነትና ግዴታ ሲታሰብ ማስጨነቁ የማይቀር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በቤተሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ ሲታሰብ ዙሪያው ገደል ይሆንና ተጠቃሚው ከራሱ ተሞክሮ አንጻር ካወጣና ካወረደ በኋላ ችግር ላይ ከመውደቅ እድር መግባቱ ይሻላል ከሚል የውሳኔ ሐሳብ ላይ ይደርሳል፡፡

እንግዲህ በአጠቃላይ የሰው ልጅ ፍላጎት አለው፤ ፍላጎቱን ለማሟላት ጥረት ያደርጋል። ይህንኑም ለማሟላት ጥረት ብቻውን በቂ አይሆንም፤ ይልቁንም ከጥረት ጋር አቅም፣ የአእምሮ ችሎታና ከልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠናዎች የሚገኝ ችሎታ ሊኖሩ ይገባል፡፡ የእነዚህ መኖር ፍላጎትን ለማሟላት የሚያስችልና ለሕይወት ጠቃሚ የሆነ የውሳኔ ሐሳብ ላይ መድረስ ያስችላል፡፡



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDR Not to be rep

ከዚህ በላይ በማስረጃነት የተመለከትናቸው ሰዎች ከራሳቸው ጋር ክርክር አድርገው የአንድን ጉዳይ ጠቃሚና ጎጂ ጎን በማመዛዘን በራሳቸው ውሳኔ ላይ የሚደርሱባቸውን ሁኔታዎች ነው፡፡ ውሳኔ በግለሰብ ደረጃ ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ በመንግሥት፣ በልዩ ልዩ ተቋማት፣ በድርጅቶች ወዘተ. ውስጥ በሚቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችና ጉባዔዎች በፖለቲካዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ተቋማዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ዲሞክራሲያዊ ውይይቶች ተካሂደው በዲሞክራሲያዊ መርሕ መሠረት በብዙሃኑ ድምጽ ብልጫ ውሳኔ ላይ ይደረሳል፡፡ ይህም የህብረተሰቡ ተወካዮች ተሰብስበው ተወያይተው የውሳኔ ሐሳብ ላይ የሚደርሱበት ዲሞክራሲያዊ አካሄድና ዲሞክራሲያዊ ውሳኔ ማለት ነው፡፡ በዚህ ሂደት የተለያዩ ሐሳቦችና አቋሞች እየተንሸራሸሩ፣ የድጋፍና የተቃውሞ ሐሳብ እየተሰጠባቸው የአብላጫው ተወያይ ድጋፍ ያገኙ ሐሳቦች ተቀባይነት እያገኙ ውሳኔ ላይ ይደረሳል፡፡



*ውሳኔ ላይ ለመድረስ ውይይት አስፈላጊ ነው*

*(ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፡፡ ካልታተመ ጽሑፍ የተወሰደ)*

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

### ፩. የሚከተሉን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ::

1. ውሳኔ ምንድን ነው?
2. «የውሳኔ ሐሳብ ላይ መድረስ» የሚለውን ሐሳብ አብራሩ::
3. ሁሉም ሰው ለሁሉም ነገር ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት የሚችል ይመስላችኋል? ለምን?
4. አንድ ሰው የውሳኔ ሐሳብ ላይ የሚደርሰው እንዴት ነው?
5. በጋራ ተወያይቶ የመወሰን ጥቅሙ ምንድን ነው?
6. ውስጣዊ ግፊት ውሳኔ ላይ የሚያደርሰው እንዴት ነው?
7. ውሳኔ ላይ በመድረስ ረገድ በሕፃናትና በአዋቂዎች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
8. ውጭ ሀገር የሚሄዱ አንዳንድ ሰዎች የሚደርሱበት የውሳኔ ሐሳብ ምንድን ነው ተባለ? የሚያስከትለውስ ጉዳት ምንድን ነው?
9. በአንድ ስብሰባ ላይ ውሳኔ የሚተላለፈው እንዴት ነው;

### ፪. የሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ዐውዳዊ ፍች ግለጹ::

| | |
|---|---|
| 1. ግፊት | 6. ፊር ማስያዝ |
| 2. እርካታ | 7. ሙግት |
| 3. መገራት | 8. ዘመድ አዝማድ |
| 4. መወትወት | 9. ሚዛን ደፋ |
| 5. አዙሮ ማየት | 10. ዙሪያው ገደል |

### ፫. የሚከተሉትን ቃላት ፍች ከመዝገበ ቃላት ፈልጋችሁ የተለያዩ ፍቻቸውን ሲያሳዩ የሚችሉ ዓረፍተነገሮች ሠርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

| | |
|---|---|
| 1. ቀጠና | 4. ጫጩ |
| 2. ዐቃቢ | 5. ደቃ |
| 3. ቀነቀነ | 6. ባዝራ |

© MoE, FDRE Not to be republished

**፬. በሚከተሉት ቃላት በተቃራኒ ፍቻቸው ዓረፍተነገር ሥሩባቸው::**

| | |
|---|---|
| 1. ረሸጥ | 6. አከለ |
| 2. ሰላማዊ | 7. ቀልድ |
| 3. ጭምት | 8. መርዶ |
| 4. ጎታታ | 9. አገባ |
| 5. ጠፈ | 10. አሸገ |

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

**፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ::**

1. ሰው ዕድሜው በገፋ መጠን ውስጣዊ ግፊቱን ዳር ለማድረስ ምን ማድረግ እንዳለበት የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁ::
2. በአንድ ጉዳይ ላይ ጥሩ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ምንምን ነገሮች ታሳቢ ማድረግ ይገባል? የህግ ባለሙያዎችን ጠይቃችሁ ያገኛችሁትን በጽሁፍ አቅርቡ::
3. ውስጣዊ ግፊትና ጠንካራ አዕምሯዊ ኃይል ያላቸውን ግንኙነት በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ አቅርቡ::
4. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የወጣቶች ወይም የሴቶች ሊጎች ከሚያደርጓቸው ስብሰባዎች በአንዱ ላይ አስፈቅዳችሁ በመገኘት አጠቃላይ የስብሰባውን ሂደትና እንዴት ውሳኔ ላይ እንደሚደርሱ የሚያሳይ አንድ ገጽ ዘገባ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ::

**፪. ቃለመጠይቅ አዘጋጅታችሁ ልምድ ላላቸው ሰዎች በማቅረብና ይህን ጉዳይ የሚያብራሩ መጻሕፍትን በማንበብ ያገኛችኋቸውን ሐሳቦች አጠናቅራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::**

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የቃለመጠየቅ ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ቃለ መጠይቅ ፍሬ ሐሳቦችን ለማግኘት ወይም ለመሰብሰብ፣ አሳምኖ ለማስፈፀም፣ ሠራተኛን ለመቅጠር፣ ትምህርት ለመከታተል፣ ጥናታዊ ምርምር ለማካሄድ ወዘተ. የሚቀርብና መልስ የሚሰጥበት የቃል ጥያቄ ነው፡፡

**1. ቀዳሚ ዝግጅት**

1.1. ጥያቄዎችን በቅድሚያ አዘጋጁ፤

1.2. ለቃለ መጠየቁ ቀደም ብላችሁ ቀጠሮ ያዙ፤ ቀጠሮ ለመያዝ በሚከተሉት መጠቀም ይቻላል፡፡

1.2.1. ደብዳቤ በመጻፍ

1.2.2. በቴሌፎን ጥሪ

1.2.3. በግንባር በማነጋገር

1.3 ቦታውን፣ቀኑንና ሰዓቱን ተጠያቂው እንዲወስን አድርጉ፤

1.4 የቀጠሮ ሰዓት አክብሩ፤

**2. የቃለ መጠይቅ አቀራረብ መመሪያ**

2.1 ለተጠያቂው ራሳችሁን በሥርዓት አስተዋውቁ፤

2.2 ጥያቄዎቻችሁ ግልጽና ቀጥተኛ ይሁኑ፤

2.3 በምትጠይቁበት ወቅት ትሁትና ቁምነገረኛ ሁኑ፤

2.4 ጥያቄዎቻችሁን እያቀረባችሁ በጽሞና አዳምጡ፤

2.5 ዋና ዋና ሐሳቦችን ያዙ፤

2.6. በመጨረሻም ተጠያቂውን አመስግኑ፤

2.7 ጠቅላላ ዘገባችሁን ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

፫. ከታች በቀረበው ሠንጠረዥ መሠረት ከሠንጠረዡ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

የአንድን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብዛት በፆታ፣ በእድሜና በክፍል ደረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ (2001 ዓ.ም)

| | የክፍል ደረጃ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 10ኛ | | 11ኛ | | 12ኛ | | 10-12 | | ጠ.ድምር |
| | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | ወ | ሴ | |
| ከ15 ዓመት በታች | 56 | 54 | 0 | 2 | - | - | 56 | 56 | 112 |
| 15 ዓመት | 207 | 315 | 44 | 30 | - | - | 251 | 345 | 596 |
| 16 ዓመት | 272 | 392 | 190 | 277 | 32 | 24 | 494 | 693 | 1187 |
| 17 ዓመት | 168 | 158 | 232 | 319 | 131 | 189 | 531 | 666 | 1197 |
| 18 ዓመት | 123 | 62 | 197 | 140 | 235 | 298 | 555 | 500 | 1055 |
| ከ18 ዓመት በላይ | 60 | 26 | 123 | 35 | 172 | 79 | 255 | 140 | 395 |
| ድምር | 886 | 1007 | 786 | 803 | 570 | 590 | 2112 | 2400 | 4512 |

1. በተለያየ የዕድሜ ክልል የተመለከተውን የሴትና የወንድ ተማሪዎች ብዛት እያነጻጸራችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ።
2. የቀረበውን መረጃ መሠረት አድርጋችሁ፣ የሴት ተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።
3. ከፍተኛና ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በማወዳደር ብልጫው ከመቶ ስንት እንደሆነ የሚያስረዳ ጽሑፍ ጻፉ።
4. ከመረጃው በመነሳት በ12ኛ ክፍል ደረጃ 15 ዓመትና ከዚያ በታች ዕድሜ ያላቸው ተማሪዎች የሌሉበት ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል የግል አስተያየታችሁን በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው። በሚሰጧችሁም አስተያየቶች መሠረት አስተካክላችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

፬. በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ከሚገኙ አንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት ቤቶች አንዱን ምረጡ፤ ከዚያም ባለፈው ዓመት ለደረጃው የተመዘገቡ፣ ዓመቱን ሙሉ ሲማሩ የከረሙ፣ እንዲሁም ያቋረጡ ተማሪዎችን ብዛት መረጃ ውሰዱ። የወሰዳችሁትን መረጃ በጾታና በክፍል ደረጃ ለይታችሁ በሠንጠረዥ አሳዩ፤ ከዚያም በተመዘገቡበትና ትምህርታቸውን በተከታተሉት መካከል ልዩነት መኖሩን አረጋግጡ። ልዩነት ካለ የልዩነቱ ምክንያት ምን እንደሆነ ጠይቁ፤ የራሳችሁንም ሀሳብ በውይይት አዳብሩና እናንተ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር ቦታ ብትሆኑ የምትወስኑትን ውሳኔ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ

፩. ወቅታዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ከሚተላለፉ መልእክቶች መካከል አንዱን ከመገናኛ ብዙኃን በማድመጥ ማስታወሻ ያዙና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፪. ከመምህር መምሪያ ውስጥ መምህራችሁ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ የሚነበብላችሁን ጽሑፍ አዳምጣችሁ፣ ዋና ዋና ፍሬ ሀሳቦችን በማስታወሻ በመያዝ ለመምህራችሁ አቅርቡና የሚሰጧችሁን አስተያየት ተቀብላችሁ አስተካክሉ፡፡ ቀጥሎም የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ከባቢያዊ አየር ምን ማለት ነው?
2. አዲስ የሚሠራው የመንገደኞች አውሮፕላን ወደወጪ የሚያስወጣው ነገር ምንድን ነው?
3. አዲስ የሚሠራው አውሮፕላን የሚንቀሳቀሰው ምንን በመጠቀም ነው?
4. ይህ አውሮፕላን ለመጀመሪያ ጊዜ ለእይታ የበቃው የትና መቼ ነበር?
5. ለአዲሱ አውሮፕላን ፍጥነት ከፍተኛ መሆን መንስዔው ምንድን ነው ትላላችሁ?

## ክፍል አራት፡- መናገር

፩. ወቅታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከመገናኛ ብዙኃን አዳምጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፪. ቀጥሎ በቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በክፍል ውስጥ ተከራከሩ፡፡

1. ወጣቶች በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ላይ የመድረስ ችግር አለባቸው/ የለባቸውም?
2. ወጣቶች ከጋብቻ በፊት የፍቅር ግንኙነት መመሥረት አለባቸው/የለባቸውም?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች በተሰየሙ ዳኞች ፊት የሚያደርጉት ሥርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡

1. የክርክር ዝግጅት

1.1. ርእሱን በሚመለከት ከተለያዩ ምንጮች ሐሳብ መሰብሰብ

**ለምሳሌ:-**

1.1.1.ከባለሙያዎች

1.1.2. ከልዩ ልዩ ጽሑፎች

1.2. በርዕሱ መሠረት ጠይቃችሁ ካገኛችሁትና ካነበባችሁት ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑትን ሐሳቦች በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ያዙ፡፡

1.3. ክርክራችሁን ለአድማጮች ከማቅረባችሁ በፊት ልምምድ አድርጉ፡፡

1.4 ለክርክር ከመቅረባችሁ በፊት ስብዕናችሁን በሥነ ሥርዓት አሟሉ፡፡

2. **የክርክር አቀራረብ**

2.1 የመከራከሪያ ርዕስን ለአድማጮች አስተዋውቁ፤

2.2 የክርክራችሁን ፍሬ ሐሳቦች በቅደም ተከተል አቅርቡ፤

2.3 ክርክር በምታደርጉበት ጊዜ ረጋ ባለመንፈስ፣ በልበ ሙሉነት አቅርቡ፤

2.4. ከክርክራችሁ ጋር የማይስማማ እንቅስቃሴ አታድርጉ፤

2.5. ተቃዋሚያችሁ የሚሰጠውን ሐሳብ በትክክል በማድመጥ፣ ማስታወሻም በመያዝ የተቃውሞ ሐሳብ አዘጋጁ፤

2.6. አነስተኛ ወይም ብጣሽ ወረቀት ለመያዝ ብትችሉም፣ ማንበባችሁና ወረቀት መያዛችሁ እንዳይታወቅ አድርጉ፤

2.7. የምታቀርቡት ሐሳብ ወይም ማስረጃ በአድማጮቻችሁ ችሎታ የተመጠነ ይሁን፤

2.8 ለክርክር የተሰጣችሁን የጊዜ ገደብ አክብሩ፤

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፫. አንድ መኪና ለመንገዱ ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ እየበረረ ይመጣል፤ ትራፊኩ ይህንን አይቶ ፊሽካ ቢነፋም፤ ሹፌሩ ሲያቆም አልቻለም፤ ይባስ ብሎ ቀይ መብራት ጥሶ አለፈ:: ትራፊኩም ሞተሩን አስነስቶ ተከተለውና አስቆመው፤ ወደ መስኮቱ ቀረብ ብሎ ሲያይ፣ አንዲት ህፃን ተጐድታ በፋሻ ተጠቅልላለች:: "ምን ሆና ነው?" ብሎ ትራፊኩ ሲጠይቅ፣ "ከፎቅ ላይ ወድቃ ወደሃኪም ቤት እየወሰድኳት ነው" አለ ሾፌሩ:: እናንተ ትራፊኩን ብትሆኑ ምን ዓይነት ውሳኔ ትወስናላችሁ?:: በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ውሳኔ ከነምክንያቱ አቅርቡ፡

## ክፍል አምስት:- ሥነልሳን

፩. ከዚህ ቀጥሉ ከ1-5 ያሉት ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ጉድለት ይገኝባቸዋል:: ጉድለቱ የቁጥር አለመስማማት ከሆነ - «ሀ»ን፣ የፆታ አለመስማማት ከሆነ - «ለ»ን፣ የቀጥተኛ ተሳቢ ግድፈት ከሆነ ደግሞ - «ሐ»ን በተራ ቁጥሩ ትይዩ አስቀምጡና ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ::

1. አቶ ዘውድነህ በጥይት የመታቸው ሰው ባለመታወቁ ጓደኞቻቸው ሁሉ ተበሳጭተዋል::
2. የጥሩ መምህርን መኖር ተማሪዎቹን ተግተው እንዲያጠኑ ያደርጓቸዋል::
3. የሀገሬን ሰዎች ኢትዮጵያን አስተምራለሁ::
4. ለማንበብ በምፈልግበት ጊዜ ዐይኔን ያለመነጽር ሊያይልኝ አይችልም::
5. በእጅ የሚሠሩ ነገሮች በመኪና ኃይል በመሥራታቸው ብዙ ዓመታት የሚወስደው በአጭር ጊዜ ውስጥ ይከናወናል::

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ውሳኔ ላይ መድረስ በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ በማንበብ ግለሰቦች ከራሳቸው ጋር በመነጋገር፣ የተለያዩ ነገሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ካወጡ ካወረዱ በኋላ እንዴት የተሻለ ወደሚሉት የውሳኔ ሐሳብ ላይ እንደሚደርሱና እንደሚተገብሩ ተረድታችኋል፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ ለተጠቀምንባቸው ቃላት ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች መስጠትን፣ ወቅታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ከብዙኃን መገናኛ መከታተልንና ማስታወሻ መውሰድን ተለማምዳችኋል፡፡ ሰዋስዋዊ ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችኋል፡፡ ዝግጅት በማድረግ ሥርዓትን ተከትላችሁ ክርክር ማካሄድና መመሪያዎችን ተገንዝባችሁ ልዩ ልዩ ሥራዎችን የማከናወን ልምድ አዳብራችኋል፡፡ እንዲሁም ከቃለ መጠይቅ መልሶችና ከሠንጠረዦች ሀሳብ በመውሰድ፣ ከዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻችሁና ከዓለም አቀፍ መገናኛዎች ማስታወሻ መውሰድ ችላችኋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላትን ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች የምናገኝባቸው ልዩ ልዩ ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
2. ወቅታዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመገናኛ ብዙሃን ማድመጥና በማስታወሻ መያዝ የሚኖረው ፋይዳ ምን ይመስላችኋል?
3. በክርክር አቀራረብ ወቅት የተከራካሪን ደካማ ጐን ማወቅና መጠቀም መቻል ወደድል የሚያቀርብ መሆኑን ምክንያት በመስጠት አብራሩ፡፡
4. መመሪያን በትክክል አለመከተል በመድሃኒት አወሳሰድ፣ ወዘተ ምን ምን ችግር እንደሚያስከትል ዘርዝሩ?
5. ከሠንጠረዥና ከቃለመጠይቅ የሚገኙ መረጃዎች ምን ያህል አስተማማኝ ናቸው?
6. በዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቻችሁ ማስታወሻ መውሰድ የሚኖረውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ?

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተራ ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ጽሑፍ አንብቤ መረዳት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | ለቃላት ቀጥተኛ፣ ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች አቀርባለሁ፡፡ | | | |
| 3 | ወቅታዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከመገናኛ ብዙሃን በጥሞና በማዳመጥ የተረዳሁትን እገልፃለሁ፡፡ | | | |
| 4 | በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በክርክር ሥርዓት መሠረት እከራከራለሁ፡፡ | | | |
| 5 | መመሪያዎችን ተከትዬ የተለያዩ ተግባራትን አከናውናለሁ፡፡ | | | |
| 6 | ከቃለመጠይቅና ከሠንጠረዦች መረጃዎችን እወስዳለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ከዕለት ተዕለት የሕይወት ገጠመኞቼ ከዓለምአቀፍ መገናኛዎች የሚገኙ ቁምነገሮችን ማስታወሻ እይዛለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ሰዋስዋዊ ስህተቶችን ማረም እችላለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# ህብረተሰብና ጤና

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- በሳይንሳዊ ግኝቶችና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚተላለፉ መግለጫዎችንና መልዕክቶችን አዳምጣችሁ በቃል ትገልጻላችሁ፡፡
- እውነታንና የግል አስተያየትን ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- በሚሰጣችሁ ርዕስ ሥርዓቱን ጠብቃችሁ ውይይት ታካሂዳላችሁ፡፡
- ከመጻሕፍትና ከሠንጠረዥ የሰበሰባችሁትን ሐሳብ በጽሑፍ ትገልጻላችሁ፡፡
- ከዕለት ተለት ገጠመኛችሁ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- አንድን ጽሑፍ አሳጥራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- አንድን ጽሑፍ ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ትተረጉማላችሁ፡፡
- ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ታብራራላችሁ፡፡
- ቅኔዎችን ትፈታላችሁ፡፡

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. የሕብረተሰብ ጤና መጠበቅ ያለውን ፋይዳ ግለጹ፤
2. በአሁኑ ወቅት በአገራችን የጤና አጠባበቅ አገልግሎት በምን ደረጃ ላይ የሚገኝ ይመስላችኋል?
3. ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጤና ችግር መንስኤዎቹ ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
4. ከምንባቡ ርዕስ ተነስታችሁ ምን ምን ፍሬ ነገሮች ሊገኙ ይችላሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ? የገመታችኋቸው መንፀባረቃቸውን በምንባቡ መጨረሻ ላይ አረጋግጡ፡፡

## ሕብረተሰብና ጤና

በኢትዮጵያ የጤና አገልግሎት በመንግሥት መዋቅር ተደራጅቶ መንቀሳቀስ ከጀመረ ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፡፡ በተለይ ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበረው የጤና አገልግሎት በከተሞች አካባቢ ብቻ ያተኮረና በፈውስ ህክምና ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ስለነበር፣ አብዛኛውን ህብረተሰባችንን ለህመምና ለሞት ከሚዳርጉ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር አላስቻለም ነበር፡፡

በ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ከተደረገ በኋላ፣ 85 በመቶ የሆነውን የገጠር ህብረተሰብ ታሳቢ ያደረገና በመከላከል ላይ ያተኮረ የጤና ፖሊሲ ተነድፎ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ከፖሊሲው በመነሳት የጤናው ዘርፍ በእቅድ እንዲመራ ለማድረግ፣ የሃያ ዓመታት እይታ ያለው የጤና ዘርፍ ልማት መርሐግብር ተዘጋጅቶ፣ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በየአምስት ዓመቱ እየተከፈለ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የአንደኛው ዙር የመርሐግብሩ ትግበራ ሲገመገም፣ በመከላከል ላይ ያተኮረ ሥራ መሠራት እንዳለበት በመታመኑ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተዘጋጅቶ በ1995 ና በ1996ዓ.ም በአምስት ክልሎች በሙከራ ከተፈተሸ በኋላ አመርቂ



© MoE, FDRE
Not to be republished

ውጤት በመገኘቱ፣ በ1997 ዓ.ም በመላ አገሪቱ የአርሶ አደር ሕብረተሰብ አካባቢዎች ሙሉ ተግባራዊ ሆኗል። ከአርሶ አደሩ የተገኘውንም ስኬታማ ተሞክሮ መነሻ በማድረግ፣ ወደ አርብቶ አደር አካባቢዎች በማስፋፋት ውጤታማ ሥራ ለመሥራት ተችሏል። ይህንኑ ተሞክሮ የበለጠ በማዳበር፣ በከተሞች አካባቢ ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ በመተግበር ላይ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት፣ ከተሞችን ጨምሮ በመላ አገሪቱ ከሰላሳ ሰባት ሺህ በላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተሰማርተዋል። "በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ" አተገባበር፣ በግልና የአካባቢ ንጽህና፣ ተላላፊ በሽታዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር፣ እንዲሁም በቤተሰብ ጤና አገልግሎት አበረታች ውጤት ተገኝቷል። በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያችን በምሳሌነት እየተነሳች የምትገኝ ሲሆን፣ የጤና ኤክስቴንሽን መርሐግብሩም የኢትዮጵያ መለያ እየሆነ መጥቷል።

ለጤና አጠባበቅ ኤክስቴንሽን መርሐግብር መነሻ ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ፣ በሀገራችን የሚታየው ሥር የሰደደ ድህነት፣ ያልተመጣጠነ የህዝብ ዕድገት፣ በሕዝባችን መሃል የተንሰራፋው ማይምነት፣ ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነት ወዘተ. በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያስከተሉት ጫናዎች ናቸው። በተላላፊ በሽታዎች መስፋፋትና በጤና አገልግሎት ሽፋን ዝቅተኛነት ወዘተ. ሳቢያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በየዓመቱ ለህመም፣ ለሞትና ለአካል ጉዳተኛነት ይጋለጣል። የዚህ ችግር ተጠቂ የሆኑት ደግሞ፣ በአብዛኛው እናቶችና ሕፃናት ናቸው።

በጥናት እንደታየው፣ በመሠረታዊ የግልና የአካባቢ ንጽህና አገልግሎት ዝቅተኛነት የተነሳ፣ ለህክምና አገልግሎት ከሚመጡት ህሙማን መካከል አብዛኞቹ ከአገልግሎቱ ጋር በተያያዙ ጉድለቶች በሚመጡ በሽታዎች እንደሚሰቃዩ ተረጋግጧል። የንፁህ ውሃ አቅርቦት አነስተኛነትና የመፀዳጃ ቤቶች ቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት የተሟላ አለመሆን፣ የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ትምህርት በተጠናከረ መልኩ አለመስፋፋት፣ በቀላሉ ለመከላከል ለሚቻሉ በሽታዎች ሕብረተሰቡ ተጋላጭ እንዲሆን ምክንያት ሆነዋል።

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

በ2002 ዓ.ም. በውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር በተደረገው ጥናት መሠረት፣ በአገራችን ውስጥ የንፁህ ውሃ አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ 68.5% ሲሆን፣ ይህም በዝርዝር ሲታይ በከተማ ከሚኖረው ሕዝብ መካከል 91.5% እና በገጠር ከሚኖረው ሕዝብ ውስጥ ደግሞ 65.8% የሚሆነው የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ነው፡፡ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በመፀዳጃ ቤት ተጠቃሚ የሆነው አጠቃላይ ሕዝብ 70% ሲሆን፣ ይህም ከከተማ ነዋሪው 88% እና ከገጠሩ ሕዝብ መካከል ደግሞ 60% መሆኑ ታውቋል፡፡

የጤና አገልግሎቱ ዐቢይ ችግር፣ ህብረተሰቡ ስለበሽታው መንስዔ፣ መተላለፊያ መንገዶችና መከላከያ ዘዴዎች ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ለአብዛኛዎቹ ተላላፊ በሽታዎች መከሰት ምክንያቱ ከባህሪይ ለውጥ ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው፡፡ ለዚህም የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅ ልምድ በስፋት አለመዳረሱና አለመለመዱ ለበሽታዎቹ ዋና መንስዔ መሆኑ በተለያዩ ጥናቶች ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ በሽታዎች ሥርጭታቸው ሊቀንስና ብሎም ሊጠፉ የሚችሉት፣ የሕብረተሰቡን የጤና ግንዛቤ በማጐልበትና የባህርይ ለውጥ እንዲያመጣ በማስቻል መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የባህርይ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው እንደመሆኑ፣ ይህንኑ ተግባር እውን ለማድረግ የሚያስችል ስልት መቅረጽ ወሳኝነት አለው፡፡

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በእስካሁን ንባባችሁ በዋናነት የተረዳችሁት ምንድን ነው?
2. በቅድመ ንባብ ከገመታችኋቸው ውስጥ እስካሁን የትኞቹ ተንፀባርቀዋል?
3. በእስካሁን ንባባችሁ መሠረት የጽሁፉ ዓላማ ምንድን ነው?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

በሀገራችን ካሉ የጤና ችግሮች ተላለፊ በሽታዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ፣ ከእነዚህም አንዳንዶቹ ቅጽበታዊ የሆነ የህመምና የሞት አደጋ የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ በአንፃሩ ግን ተላላፊ በሽታዎችን ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች የበለጠ የመከላከልና የመቆጣጠር እድል እንዳለ ይታወቃል፡፡



*የህፃናት ክትባት ለጤናማ ሕብረተሰብ መኖር አስፈላጊ ነው*

እነዚህን ተላላፊ በሽታዎች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የዳበረ የአሠራር ሥርዓት ባለመኖሩ፣ በዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች ማለትም፣ በወባ፣ በቲቢ፣ በኤች.አይ.ቪ.፣ በተቅማጥ በሽታ ወዘተ. የሚሞተው ሰው ብዛት በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል። የወባ በሽታ ሕብረተሰባችንን ለህመምና ለሞት ከሚዳርጉት በሽታዎች ቀዳሚ ሲሆን፣ ከቲቢና ከኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ወረርሽኝ ጋር በቅርብ የተያያዘ ስለሆነ፣ በአሁኑ ጊዜ በሠለጠኑ አገሮችም ጭምር ችግሩ በሚያስደነግጥ ሁኔታ እያሻቀበ ይገኛል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ተላላፊ በሽታዎች በሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የሆነ የህመም፣ የሞትና የአካል ጉዳት ከማድረሳቸውም ባሻገር፣

በአገራችን ኢኮኖሚም ላይ እጅግ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሱ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ተጽዕኖው በሽታዎቹ አምራቹን የሕብረተሰብ ክፍል በማጥቃታቸው፣ ምርታማነትን በመቀነሳቸውና ህሙማንን አክሞ ለማዳን የሚጠይቀው የጤና አገልግሎት ወጪም ከፍተኛ በመሆኑ ጭምር የተከሰተ ነው፡፡

ሌላው የሕብረተሰብ ጤና አገልግሎት አካል የወጣቶች ሥነተዋልዶ ጤና ሲሆን፣ ይህም ወጣቶች ሕይወታቸውን በአግባቡ እንዲመሩ የሚያደርጋቸው ሆኖ በርካታ ጉዳዮችን አካቶ የያዘ አገልግሎት ነው፡፡ ከሕዝብ ቆጠራ ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ ከሀገራችን ሕዝብ 25% የሚሆነው ወጣት ሲሆን፣ የወጣትነት የእድሜ ጣሪያም ከ15-29 ዓመት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉትን ያጠቃልላል፡፡ የወጣቱ የጤና ችግሮች በርካታ ሲሆኑ፣ ከወጣቶች የሥነተዋልዶ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ሕገ ወጥ ውርጃ፣ ዝቅተኛ የቤተሰብ እቅድ ፕሮግራም ተጠቃሚነት፣ የአደንዛዥ እፆች ተገዢ መሆን፣ ልቅ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ እንዲሁም በጠለፋና አስገድዶ መደፈር ሳቢያ የሚመጡ የአባላዘር በሽታዎች፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ጨምሮ፣ ያለእድሜ በሚፈጸም ጋብቻ የሚመጡ የጤንነት ችግሮች፣ በዚህም ሳቢያ የሚመጡ የሥነተዋልዶ አካላት በሽታዎች ወዘተ. ሊጠቀሱ የሚገባቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የሕብረተሰቡን የጤንነት ደረጃ ለማሻሻል፣ የምርት እድገትን ለማሳደግ፣ ሕብረተሰቡ በራሱ ጤና ላይ ቀጥተኛና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ለነገ የማይተው ተግባር ነው፡፡

*ምንጭ፡-* 1. ጤናችን - የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መስከረም ቅጽ 1 ቁ1 2003 ዓ.ም.
2. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የተገኙ ውጤቶች የኤፌድሪ ጤ.ጥ.ሚኒስቴር 2001 ዓ.ም.
3. የውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴር በራሪ ወረቀት-2003 ዓ.ም.
4. ብሔራዊ የወጣቶች የእድገት ፓኬጅና ፖሊሲ 1999 ዓ.ም አዲስ አበባ



© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

### ፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ::

1. በመከላከልና በማዳን መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
2. «የጤና ፖሊሲ ተነድፎ እየተሠራበት ይገኛል» ይላል፤ ፖሊሲ ከሌለ የጤና አገልግሎት ላይሰጥ ይችላል ማለቱ ነው?
3. የጤና ኤክስቴንሽን መርሐግብር የተነደፈበት ዋናው ምክንያት ምንድን ነው?
4. ህብረተሰቡን እየጐዱ ያሉ ተላላፊ በሽታዎች ሊወገዱ የሚችሉት ምን ብናደርግ ነው?
5. በወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና ውስጥ እንደችግር የሚጠቀሱት ምን ምን ናቸው? ለምን?
6. የጤና ኤክስቴንሽኑ ውጤት አመርቂ ይመስላችኋል? ለምን?
7. ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ ትኩረት የተሰጠው የጤና አገልግሎት በምን ላይ ነው?
8. በቀላሉ ለመከላከል በሚቻሉ በሽታዎች ሰበብ፣ ኅብረተሰቡ ለስቃይ የተዳረገባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
9. በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ችግሮች ሆነው የኖሩት ምን ምን ናቸው?
10. ከሁሉም በላይ የኅብረተሰባችን ዓበይት የጤና ችግሮች ምንድን ናቸው?

### ፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን "ሐሰት" በማለት መልሱ:: ምክንያታችሁንም በአጭሩ ገለጹ::

1. በጤና ኤክስቴንሽን ሥራ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው የግልና የአካባቢ ንጽህና አጠባበቅና ተላላፊ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ናቸው::

© MoE, FDRE Not to be republished

2. ህብረተሰባችንን የሚጎዱ ተላላፊ በሽታዎች በጎጂነታቸው ቅደም ተከተል ሲታዩ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ፣ ወባ፣ ቲቢ... ናቸው።
3. ያለ እድሜ ጋብቻ የሚያስከትለው ችግር ጉልህ አይደለም።
4. በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሱ ያሉት በሽታዎች በትክክል ለመጠናታቸው እርግጠኞች አይደለንም።
5. የህብረተሰብ የጤና ሁኔታና የምርት ዕድገት ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው።

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. ከላይ በቀረበው ምንባብ ውስጥ፣ የሕዝቡን የንፁህ ውሃና የመፀዳጃ ቤት ተጠቃሚነትን በተመለከተ ከውሃና ኤነርጂ ሚኒስቴርና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተገኙትን መረጃዎች በሠንጠረዥና በግራፍ ከሠራችሁ በኋላ የሁለቱን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ዘገባ በማነጻጸር አጭር ጽሑፍ ጽፋችሁ አቅርቡ።

፪. ከዚህ የሚከተሉትን ሁለት ሠንጠረዦች በመመልከት ከሥራቸው ያሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

**ሠንጠረዥ ሀ. የጤና ባለሙያዎች ስርጭትና ንጽጽር በኢትዮጵያ**

| የባለሙያው ዓይነት | ከ1939 በፊት | በ1966 የነበረ | በ1983 የነበረ | ከ1984-2002 |
|---|---|---|---|---|
| ሐኪም | 106 | 377 | 1,628 | 2,887 |
| ጤና መኮንን | - | 213 | 24 | 5,000 |
| ነርስ | 88 | 1,162 | 3,575 | 20,765 |
| ጤና ረዳት | - | 4,003 | 9,945 | *2,140 |
| ልዩ ልዩ ጤና ባለሙያዎች | - | 720 | 1387 | 8,721 |

* እየከሰመ የሚሄድ



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ሠንጠረዥ ሰ. የጤና ተቋማት ስርጭትና ንጽጽር በኢትዮጵያ

| የጤና ድርጅቱ ስም | ከ1939 በፊት | በ1966 የነበረ | በ1983 | ከ1984-2002 |
|---|---|---|---|---|
| ሆስፒታል | 46 | 84 | 72 | 205 |
| ጤና ጣቢያ | - | 93 | 153 | 2,540 |
| ክሊኒክ | 92 | 649 | 2229 | *788 |
| ጤና ኬላ | - | - | - | 14500 |
| የጤና ሽፋን | - | - | 38% | 89.6% |
| ጠቅላላ ድምር | 138 | 826 | 77 | 18033 |

*ምንጭ፡- ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት*

* ክሊኒኮች ወደ ጤና ጣቢያ እያደጉ በመሄዳቸው የክሊንኮች ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱን የሚያሳይ

1. በሠንጠረዡ መሠረት የሐኪሞች ቁጥር ዕድገት በመቶኛ በማስላት ዕድገቱን የሚገልጽ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡
2. የጤና ረዳት ቁጥር በ1983 ዓ.ም. ከፍተኛ ቁጥር ላይ ደርሶ፣ ከ1984-2002 ባሉት ጊዜያት ቀንሶ የታየበትን ምክንያት የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ ጻፉ፡፡

### ጽሑፍን የማሳጠር መመሪያ

አንድን በረጅሙ የቀረበ፣ የተብራራ፣ የተተነተነ ጽሑፍ አሳጥሮ ማቅረብ፣ ዋና ዋናውን ፍሬ ሐሳብ ጨምቆ ለማስቀመጥ ይረዳል፡፡ በተለይም ከትላልቅ መጻሕፍትና በስፋት ከተገለጹ ጽሑፎች ውስጥ አንብበን ማስታወሻ መያዝ በምንፈልግበት ጊዜ፣ ፍሬ ሐሳቡን ለይተን በማወቅ መልዕክቱ እንዳይለወጥ ትኩረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ጽሑፉን አሳጥሮ ማቅረብ በጽሑፍ ተግባቦታዊ ሂደት ውስጥ የተለመደ ነው፡፡ ታዲያ አንድን ጽሑፍ በተፈለገው መንገድ አሳጥሮ ለማቅረብ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ያስፈልጋል፡፡

**ሀ. በአንክሮ ማንበብ**

ጥልቅ ንባብ ጽሑፍን አሳጥሮ ለማቅረብ መሠረቱ ነው፡፡ ለማሳጠር የተፈለገውን ጽሑፍ ሐሳብ በትክክል ለመጨበጥ ደጋግሞ በአንክሮ ማንበብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሙም ከመዝገበ ቃላት እያዩ ማንበብም የጥንቃቄው አንዱ ገጽታ ነው፡፡

**ለ. ማስታወሻ መውሰድ**

በንባብ ጊዜ አጫጭር ማስታወሻዎችን መውሰድ ይቻላል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ፍሬ ፍሬ ሐሳቡን በሚያመች መንገድ እየለዩ ማውጣት፣ በሚነበብበት ጊዜ የት የት አካባቢ ላይ በይበልጥ ማተኮር እንደሚገባ ለማስተዋል ይረዳል፡፡

**ሐ. ዋና ሐሳቡን በራስ አገላለጽ መጻፍ**

በጥንቃቄ አንብበን ፍሬ ፍሬ ሐሳቡን ከለየን በኋላ፣ የጽሑፉን ማዕከላዊ ሐሳብ በራሳችን አገላለጽ ማስፈር ያስፈልጋል፡፡ በዚህን ጊዜ፣ ዋናው ሐሳብ ሳይድበሰበስና የጸሐፊው መልዕክት ሳይዛነፍ ተነባቢ በሆነ መንገድ መስፈሩን ማረጋገጥ ያሻል፡፡

ምንጭ፣ ደበበ ኀይለጊዮርጊስ፤1999፡፡ ***ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ***፡ ከሚለው የተወሰደ፡፡

**፫. በቀረበላችሁ የጽሑፍ ማሳጠሪያ መመሪያ መሠረት ከዚህ በታች የቀረበላችሁን ጽሑፍ በሲሶ (በ1/3ኛ) አሳጥራችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡**

በገንዘብ እድገት ሂደት ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ጊዜያት ላይ ውድ በሆኑ የማዕድን ውጤቶች ማለትም በወርቅና በብር ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበር፡፡ ይህም ያለምክንያት አይደለም፤ ወርቅና ብር ውድና ብርቅ ናቸው፡፡ ለመከፋፈል፣ ለመሸረፍ ጥራታቸውን ሳይለውጡ ብዙ ጊዜ ለመቆየት የሚያስችል ባህርይ አላቸው፡፡ ወርቅና ብርን ለማምረት የሚወጣባቸው የሥራ ኃይል ከፍተኛ በመሆኑ ከፍተኛ እሴት አላቸው፡፡ ወርቅና ብር ለብዙ ዘመናት ሁለቱም እንደሁለንተናዊ እኩያ ሲያገለግሉ ቆይተው፣ አንድ ሸቀጥ የልውውጥ አማካይ መሆኑ ይበልጥ ተፈላጊ እየሆነ ሲመጣ፣ ወርቅ ብቻውን ይህን ሚና መጫወት ጀመረ፡፡ ይህ የእሴት የገንዘብ መልክ ይባላል፡፡



© MoE, FDRE, Not to be reproduced

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

እሴት የገንዘብን መልክ በያዘበት ሁኔታ የማናቸውም ሸቀጥ እሴት በአንድ ሸቀጥ የጠቀሜታ እሴት ሊገለጥ በመቻሉ፣ ሁለንተናዊ እኩያ በአንድ ሸቀጥ ማለት በወርቅ ሊከናወን ተችሏል፡፡ ገንዘብ ብቅ ያለው እንግዲህ ከላይ በዝርዝር እንዳየነው በረጅም ጊዜ ልውውጥ ሳቢያ፣ በየጊዜው በታየው የእሴት መልክ መለዋወጥ ነው፡፡ በገንዘብ ብቅ ማለትም የተነሳ ሸቀጦች በሁለት ወገን ሊከፈሉ በቅተዋል፡፡ በአንደኛው ወገን አያሌ ሸቀጦች ሲገኙ፣ በሌላው ወገን ደግሞ አንድ ሸቀጥ ብቻ ማለት ገንዘብ /ወርቅ/ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በአንድ ወገን በብዛት የሚገኙት ሸቀጦች ሁሉ እሴታቸውን በሌላው ወገን ባለው ሸቀጥ ማለትም ገንዘብ /ወርቅ/ ይገልጣሉ፡፡ ስለዚህም ገንዘብ ከሌሎቹ ሸቀጦች ተለይቶ ብቻውን በመቆም ሁለንተናዊ እኩያ በመሆን ያገለግላል፡፡ ማንኛውም ዓይነት ሸቀጥ በገንዘብ ይለወጣል፡፡ ይህ ልዩ የሆነ የገንዘብ ባህርይ ሁሉንም የሸቀጥ ባለቤት የሚያረካ ነው፡፡ የሁሉንም ሰው የተለያየ ፍላጎትም ያረካል፡፡ ሌሎች ሸቀጦች ግን የተወሰነ ፍላጎት ብቻ ነው ሊያረኩ የሚችሉት፡፡ ለምሳሌ በገንዘብ ምግብ፣ የልጆች ደብተርና ጥብቆ፣ ጫማ፣ ልብስ፣ ቤት ወዘተ. መግዛትና የተለያየ ፍላጎትን ማሟላት ይቻላል፡፡ በአንፃሩ፣ ምግብ ወይም ልብስ ወይም ሌላ ሸቀጥ ለየብቻ በተናጠል ሲታዩ ሊያሟሉ የሚችሉት የተወሰኑ ፍላጎቶችን ብቻ ነው፡፡

ለማጠቃለል፣ ገንዘብ /ወርቅ/ ራሱ ሸቀጥ ነው፡፡ ሸቀጥ በመሆኑ ግን ከሌሎች ሸቀጦች የሚለይበት ባህርይ አለው፡፡ ይህም፣ የሁሉም ሸቀጦች እሴት የሚገለጥበት ሁለንተናዊ እኩያ መሆኑ ነው፡፡ ገንዘብ በሸቀጥነቱ ማኅበራዊ ሥራ የፈሰሰበትና በሸቀጥ አምራቾች መካከል ያለውን የምርት ግንኙነትንም የሚገልጽ ነው፡፡ ከገንዘብ መከሠት ጋር የሸቀጦች እሴት ለመጀመሪያ ጊዜ በዋጋ አማካኝነት ሲገለጽና የሸቀጦች የቀጥታ ልውውጥም ቀርቶ ሸቀጦች በገንዘብ አማካኝነት እንዲለዋወጡ አስችሏል፡፡

(ምንጭ፣ የካፒታሊስት ስልተ ምርት ክፍል 2፣ 1974)

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፬. የሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸው ዐውዳዊ ፍች ምን እንደሆነ የሚያሳዩ ዓርፍተነገሮች ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

| | |
|---|---|
| 1. ፈውስ | 5. ሰበብ |
| 2. መርሐ ግብር | 5. የባህርይ ለውጥ |
| 3. አመርቂ | 6. መዳረግ |
| 4. ተሞክሮ | 7. ማሻቀብ |

፭. የሚከተሉትን ቃላት ወይም ሐረጋት በምንባበቡ ውስጥ ካሳዩት ዓውዳዊ ፍች የተለየ እንዲሰጡ በማድረግ የራሳችሁን ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ አቅርቡ::

**ምሳሌ፡-** ተነድፎ

1. ልጁ በእባብ <u>ተነድፎ</u> ነበር
2. እቅዱ በ2002 ዓ.ም <u>ተነድፎ</u> በ2003 ዓ.ም ሥራ ላይ ዋለ::
3. ጥጡ <u>ተነድፎ</u> ፊት ለፊት ተቀምጧል::

| | |
|---|---|
| 1. ተፈተሸ | 6. ተነሳች |
| 2. ዙር | 7. ሰደደ |
| 3. ተንጠለጠለ | 8. መተላለፊያ |
| 4. መዋቅር | 9. ዳሰሰ |
| 5. መቆጣጠር | 10. ማሳደግ |

፮. የሚከተሉትን እንደየትዕዛዛቸው ከአማርኛ ወደእንግሊዝኛ ወይም ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ ተርጉሙ::

ሀ. የሚከተሉትን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ዓረፍተነገሮችን ወደ አማርኛ ተርጉማችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ::

1. There is only one Government school providing free education.
2. It is very crowded with over 2000 pupils and a high teacher pupil ratio of around one teacher to an average of sixty five pupils.
3. The newly built private school alleviates the problem by supplying education for 300 children.

**ሰ. የሚከተለውን ጽሑፍ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሙ**

1. ግለታሪክ አንድ ግለሰብ የራሱን የሕይወት ገጠመኞች የሚጽፍበት ሂደት ነው፡፡
2. በአንድ ግለታሪክ ውስጥ አንድ ግለሰብ ከልደት ጀምሮ ግለታሪኩ እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ ያከናወናቸውን/ያከናወነቺውን በዝርዝር ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት:- ማዳመጥ

ከመምህር መምሪያ ውስጥ መምህራችሁ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ የሚነበብ ላችሁን ጽሑፍ እያዳማጣችሁ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን በማስታወሻ ያዙ፡፡ የያዛች ሁትንም ማስታወሻ ለመምህራችሁ በማቅረብ የሚሰጧችሁንም አስተያየት አድምጡ፡፡ ከዚያም የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ሲጋራ ማጨስ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?
2. አንዳንድ ሰዎች ሲጋራ ለማቆም በመጀመሪያ ፈቃደኝነት ከዚያም ቁርጠኛ ውሳኔ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡ ይህ ምን ያህል ትክክል ይመስላችኋል?
3. ባለታሪኩ "የመጨረሻ ሲጋራዬን ከመኪና ጋራዥ ውስጥ ሆኜ ሦስት ጊዜ ካቦነንኳት በኋላ መሬት ላይ ጥዬ ጨፈላለኳት" አለ፡፡ የሲጋራ ቁራጭ መሬት ላይ ጥሎ በእግር የመርገጥ አስፈላጊነት ምን ይመስላችኋል? ከዚህ ጋር የሚሄድ ገጠመኝ አላችሁ? ካለ ለክፍላችሁ ተናገሩ፡፡
4. በተለያዩ ሙያዎች ላይ በተሰማሩ ሲጋራ በሚያጨሱና በማያጨሱ ሰዎች መካከል በሥራ ቅልጥፍናና ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም ረገድ ምን ዓይነት ልዩነት የሚታይ ይመስላችኋል? ለምን?
5. ሲጋራ አጫሽ ዘወትር "አቆማለሁ" በማለት ይምላል፣ ይገዘታል፡፡ ነገርግን ሁኔታው በአብዛኛው ተግባራዊ ሲሆን አይታይም፡፡ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል አራት:- መናገር

፩. የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አንብባችሁ እውነታ ወይም የግል አስተያየት በማለት ከነምክንያቱ ተናገሩ፡፡

1. የግልና የአካባቢ ንጽህና ኖረም አልኖረም ይህን ያህል ለውጥ አያመጣም፡፡
2. ዱሮ ገበሬዎች እርሻ ቦታ እጃቸውን ሳይታጠቡ በሚበሉበት ወቅት ጀርሞች አልነበሩም፡፡
3. ወተት ቢፈላ ባይፈላ የሚያመጣው ሳንክ የለም፡፡
4. የበሽታ ጀርሞች መሠራጨት ከከተሞች መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው፡፡
5. አንዳንድ ሰዎች ለመታከም ወደጤና ተቋማት ሄደው በሽታ ሸምተው የሚመለሱባቸው ሁኔታዎች ያጋጥማሉ፡፡
6. ወጣት የጤና ባለሙያዎች ልምዱ ባይኖራቸውም፣ ዕውቀቱ ስላላቸው የሚቸገሩበት ሁኔታ ያለ አይመስለኝም፡፡
7. አምራቹ የህብረተሰብ ክፍል በበሽታ ሲጠቃ፣ ምርታማነት ይቀንሳል፤ ምርታማነት ሲቀንስ፣ የጤና አገልግሎት ወጪ ይቀንሳል፡፡
8. የሕዝብ ብዛት ችግር ሳይሆን፣ የሥራ ሃይል በመሆኑ፣ የኤኮኖሚ ዕድገትን የማፋጠን ብቃት ይኖረዋል፡፡
9. ድህነትና ማይምነት፣ ብልጽግናና ዕውቀት ተጓዳኝ ናቸው፡
10. በተላላፊ በሽታዎች ተጠቂ የሆኑት አብዛኞቹ ሴቶችና ሕፃናት የመሆናቸው ጉዳይ በኤኮኖሚ ጥገኝነታቸው ሳቢያ ነው፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be reproduced

፪. ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡላችሁ የውይይት ቅድመ ተግባራትና የአመራር ሥርዓት መሠረት በሚከተሉት ርእሶች ላይ በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

1. የአደንዛዥ እፆች መለመድ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች፤
2. ያልተፈለገ እርግዝና የሚያስከትለው ጉዳት፤
3. የሴቶች ከገጠር ወደ ከተማ መፍለስ ምክንያቶች፣ ጉዳቶችና መፍትሔዎቻቸው፤
4. ህብረተሰባችን በእንዴት ያለ የተደራጀ ሁኔታ እገዛ ቢያደርግ የጤና አገልግሎቱ ችግር ይፈታል?

### የውይይት ሥነ ሥርዓት መመሪያ

ደንቦችን፣ መተዳደሪያዎችን ለመንደፍ፣ ሕጎችን ለማውጣትና ለማጽደቅ፣ እቅድ ለማውጣትና መርሐግብር ለመዘርጋት፣ ችግሮችን ለመለየትና ለችግሮቹ መፍትሔ ለማፈላለግ ወዘተ. ሰዎች ተሰብስበው ይወያያሉ፡፡ በየትኛውም ጉዳይ ላይ የሚደረግ ወይም ሊደረግ የታቀደ መደበኛ ውይይት በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከናወናል፡፡

**1. የውይይቱን አጀንዳ መወሰን**

ተወያዮቹ ከተለዩ በኋላና የውይይቱን ዓላማ የሚገልጽ የጥሪ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ከመደረጉ በፊት፣ አባላቱ በውይይቱ ወቅት ውይይት እንዲደረግበት የሚፈልጉት አጀንዳ መኖር አለመኖሩን አባላቱን በመጠየቅ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የውይይቱን አጀንዳ በጋራ ለመቅረጽ መንገድ የሚከፍት ነው፡፡

**2. የውይይቱን ተሳታፊዎች ማንነት መለየት**

በታቀደው ውይይት ላይ የማይመለከታቸው አካላት ተገኝተው ሂደቱን እንዳያውኩት ሲባል፣ አወያዩ እነማን መገኘት እንደሚኖርባቸው አስቀድሞ መለየት ይጠበቅበታል፡፡ ተሰብሳቢዎቹ ከተለዩ በኋላም

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

የውይይቱን ዓላማ የሚገልጽ የጥሪ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**3. ውይይቱ የሚካሄድበት ቀን፣ ጊዜና ቦታ መወሰን**

አንድ ውይይት ሲታቀድ፣ ውይይቱ ሊፈጅ የሚችለውን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት አስቀድሞ ቀኑን፣ ጊዜውን ቦታውን መወሰን ያስፈልጋል፡፡ በተለይ አወያዩ ጊዜው አጥሮ የመወያያው በቂ ውይይት ሳይደረግበት እንዳይታለፍ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በቂ ውይይት ያልተደረገበት አጀንዳ በአባላቱ ዘንድ እምነት ስለማይጣልበት፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚደረስበት የውሳኔ ሐሳብ ላይ ጥርጣሬ እንዲነሳ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም አወያዩ እያንዳንዱ አጀንዳ በቂ ውይይት እየተደረገበት ማለፉን ማረጋገጥ ኃላፊነቱ ይሆናል፡፡

ከዚህም ሌላ ለውይይቱ የተመደበው ጊዜ ከረዘመ አባላት ከአጀንዳው ውጪ የሆነ ሐሳብ በማምጣት ሂደቱን ሊያውኩት ይችላሉና በዚህ ረገድም ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለዚህም ሲባል በጊዜው አወሳሰን ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ከአወያዩ ይጠበቃል፡፡

**4. የውይይቱን ዓላማና የመወያያ አጀንዳዎቹን መበተን**

ከውይይቱ ቀደም ብሎ፣ የውይይቱን ዓላማና የመወያያ አጀንዳዎችን ለተወያዮች መበተን ሊለመድ የሚገባው አሠራር ነው፡፡ የውይይቱን ዓላማና የመወያያ አጀንዳዎቹን በቅድሚያ መግለፁ፣ አባላቱ ቀደም ብለው በጉዳዩ ላይ እንዲያስቡበትና የሚያነሷቸውን ሐሳቦች ይዘው እንዲቀርቡ ለማድረግ ይረዳል፡፡ አባላቱ በጉዳዩ ላይ አስበውበት የሚመጡ ከሆነ የውይይቱ ጊዜ ያጥራል፤ ነገሮችም በፍጥነት እልባት ያገኛሉ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced/published

## 5. ውይይቱን መምራት

### 5.1 ጸሐፊ ማስመረጥ

ከውይይቱ ተሳታፊዎች መካከል የውይይቱን ሂደት በትክክል የሚመዘግብ ሰው ማስመረጥ ያስፈልጋል፡፡

### 5.2 ውይይቱን በሰዓቱ መጀመር

አንድ አወያይ በሰዓቱ ተገኝቶ ውይይቱን ማስጀመር ይጠበቅበታል፡፡ ሁሉም አባላት በሰዓቱ ባይገኙም እንኳ፣ የአባላቱ ሁለት ሦስተኛው መኖራቸው ከተረጋገጠ ውይይቱን ባሉት አባላት ማስጀመሩ ተገቢ ነው፡፡ ይህን ማድረጉ ለሚዘገዩ አባላት ትምህርት ከመስጠቱም በላይ በተጨማሪ የውይይቱ ሥርዓት መከበሩን ያመለክታል፡፡

ውይይቱ ሲጀመር አወያዩ በቅድሚያ አጀንዳዎቹን ማስተዋወቅና የውይይቱን ዓላማ ግልጽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር የውይይቱን ሂደት አቅጣጫ ለማስያዝና መደረግ ባለበት ነገር ላይ ለማተኮር ይረዳል፡፡

## 6. የውይይቱ መዝገብ

በውይይቱ መዝጊያ ላይ በተወያዮቹ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ውሳኔዎች እንደገና መከለስ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ የክለሳ ሂደት ውሳኔዎቹ እንዴትና ከመቼ ጀምሮ ተፈፃሚ እንደሚሆኑና ማን እንደሚያስፈጽማቸው መገለጽ ይኖርበታል፡፡

ምንጭ፡- ደበበ ኀይለጊዮርጊስ፣1999፡፡ ***ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ*** ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ፡፡

፫. ምንባቡ የሃገራችንን ህብረተሰብ ጤና በመጠበቅ ረገድ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት የነበራችሁን ግንዛቤ በማስፋት ረገድ ምን ምን አዳዲስ መረጃዎችን እንደሰጣችሁ በመጥቀስ ማብራሪያ ስጡ፡፡

## ክፍል አምስት:- ሥነጽሑፍ

### ፩. ከዚህ ቀጥሎ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ያሉባቸውን ዓረፍተነገሮች በዘወትራዊ አነጋገር ለውጣችሁ ጻፉ።

**ምሳሌ:-** አየለ ምን እንደሆነ እንጃ ክንፋን ጥሏል።

ክርፍፍ ብሏል፤ዝሏል፤ ደክሞታል...

1. ምግባችን ተከሽኖ መጣ።
2. ቀኝ እጄን ተነጠቅሁ።
3. ተዋበች አንድ እንጀራ በሬው ናት።
4. ፖሊሱ ሌባውን ለጥብስ አደረሰው።
5. ውይ! ውይ! አየልዬ እኔን ክንብል ያርገኝ ።
6. አየለች እየሳቀች በሾርኒ ነገረችው።
7. የእኔ ኑሮ ጥርኙ ብርኙ ነው።
8. እኔ ሳልደርስ ገበያው ደርቶ ነበር።
9. እጥቤ መሆኑን እኔ መች አውቄ።
10. ዘነበ ለቤተሰቡ የዐይን ብሌን ነው።

### ፪. በዘወትራዊ አነጋገር የቀረቡትን በፈሊጣዊ አነጋገሮች ተኩ።

**ምሳሌ:-** የዛሬውስ እንግዳ እድላም ነው= እንግዳው እግረ ርጥብ ነው።

1. ልጁ በጣም ቀጥኗል።
2. ይህ ሰው የማያድግ፣ የማይሻሻል ነው።
3. ጓደኛዬ ወላዋይ ነው።
4. እንደሱ ዘማዊ የለም።
5. ሎተሪ ስለወጣለት ፈነደቀ።
6. መጥቶ የማያውቅ እንግዳ እቤታችን መጥቷል።
7. ይህን አስመሳይ፣ አቆላማጭ አትስማው።
8. ሰውየው ተንኮለኛ ነው።



© MoE, FDRE
Not to be reproduced

9. ለሁለተኛ ሚዜነት ያጨሁት ፍቃዱን ነው፡፡
10. እሱ የማይወጣበት ችግር ውስጥ ገብቷል፡፡

**፫. የሚከተለውን አጭር ጽሑፍ አንብባችሁ መጨረሻው ላይ ስትደርሱ፣ የጽሑፉን ማጠቃለያ ሐሳብ ወይም ምሳሌያዊ አነጋገር ታገኛላችሁ፡፡ እንግዲህ ከላይ የተነገረው የሁኔታው መግለጫ ወይም ማብራሪያ ነው፡፡ በዚሁ ዓይነት እናንተም እንድትሰሩ ጥያቄ ቀርቦላችኋል፡፡**

ቀኑብሽ ቆንጆ ኮረዳ ናት፤ ጥርሶቿ ነጫጭና የተስተካከሉ ቢሆኑም፣ ድዷ ቀይ ነው፡፡ ለአካለ መጠን ደርሳ በየዕለቱ ጥርሶቿን በመስታወት ማየት ስትጀምር፣ የድዷን ቅላት አልወደደችውም፡፡ በባልንጀሮቿ አነሳሽነት ጥርሷን ለመነቀስ ወሰነች፡፡ እናም ጉራማይሌ ተነቀሰችው፡፡ ይሁንና ከሳምንት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ሊድን ይገባው የነበረው የንቅሳቱ ቁስል በቶሎ አልሽር አላት፡፡ ይባስ ብሎ በአሥረኛው ቀን ድዷ ደም የቀላቀለ ፈሳሽ አመነጨ፡፡ ሐኪም ቤት ስትሄድ አራቱ ጥርሶቿ ባፋጣኝ መነቀል እንዳለባቸው ተነገራት፡፡ ከልቧ ሀዘን ቢሰማትም፣ ፈቃደኛ ሆና ጥርሶቿን አስነቀለቻቸው፡፡ ከሐኪም ቤት ስትመለስ ሁኔታዋን የተመለከቱ ጎረቤቶቿ በምሳሌያዊ አነጋገር ወረፏት፤

- ሲያጌጡ ይመላለጡ፤
- ሹርባ ልትሠራ ሄዳ ፀጉሯን ተላጭታ ተመለሰች፡፡

**ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሠረት አምስት የሁኔታዎች ወይም የድርጊት መግለጫዎች ከጻፋችሁ በኋላ ሁኔታዎቹን የሚገልጹ ምሳሊያዊ አነጋገሮች ጻፉ፡፡**

**፬. በሚከተሉት ቅኔዎች ውስጥ ያሉትን ህብረቃሎች ካወጣችሁ በኋላ ቅኔውን በሰምና ወርቅ ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

***ምሳሌ፡-*** ሐኪም ቤት አልሄደች ያለችው ከቤት፣
እኔ ምን ላድርጋት ያችን ሴት አሟት፡፡

**ህብረ ቃሉ** - አሟት

**ሰሙ** - በሽታ ለክፏት

**ወርቁ-** ቦጨቋት፣ በሌለችበት በክፉ አነሷት

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be reproduced

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

1. ያን ማዶ በረሃ ስፈራው ዱሩን፣
   መልካም ገላለጡት ትሄዱ እንደሆን፡፡
2. እንጀራው ተጋግሮ ወጡ ሳይቀርብልን፣
   የትሄደች ጣይቱ ሳታሳልፍልን፡፡
3. እንጨቱ ተጓሮ ቋሚ እየኮራ፣
   አለማገር ቀረች ቤቴ ተዝምራ፡፡
4. ምነው ብታስጠሪኝ እኔን አስታውሰሽ፣
   እደጅ ተቀምጬ እቤቴ ሳመሽ፡፡
5. እንካ ብላ አለችኝ ደረቁን እንጀራ፣
   እሷ በነካካው በራሰው ልትበላ፡፡
6. የዚህ ጠላ ነገር ጠፋኝ መላቅጡ፣
   አሮጊቷ ናቸው የሚበጠብጡ፡፡
7. አዝን የነበረ ልጄ በማጣቱ፣
   ዛሬስ አገኘ አሉ ባህር ሆነ ቤቱ፡፡
8. ሰፊ ቤት እያለው አዳራሽ ከልፍኝ፣
   ምነው ባደባባይ በሰው ፊት መታኝ፡፡
9. በላሁ ይበቃኛል ከእንጀራ ከወጡ፣
   እግዚአብሔር ይስጥልኝ ከመሶብዎ አይጡ፡፡
10. የተጣደ ምጣድ ከኗላዬ ኖሮ፣
    ለካስ ጥላት ብቻ ሆኛለሁ ዘንድሮ፡፡
11. ከኳስ ጨዋታ ውስጥ ጨዋታው ሲደራ፣
    አይቀርም መድረሱ ፈጽሞ ግፍተራ፡፡
12. መጨነቅ መጠበበብ ለጠጅ ብቻ ነው፣
    ለጠላ መድሃኒት ተወት ማድረግ ነው፡፡
13. ሁል ጊዜ ባሬራ ትበያለሽ ወይ
    አንዳንድ ቀን እንኳ ወጥ አትይም ወይ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

ህብረተሰብና ጤና በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ በማንበብ በሀገራችን ስለሚሰጠው የጤና አገልግሎት ዕድገት በሚገባ ተገንዝባ ችኋል፡፡ በተለያዩ መድረኮች ከሚቀርቡ ንግግሮች፣ ውይይቶች እንዲሁም በሬዲዮና ቤቴሌቪዥን ከሚተላለፉ ፕሮግራሞች ጠቃሚ ሐሳቦችን ማስታወሻ በመውሰድ ልምዳችሁን አዳብራችኋል፡፡ ከተለያዩ ንግግሮችም ይሁን መጻሕፍትም ስታነቡ እውነታንና የግል አስተያየቶችን መለየት ችላችኋል፡፡ በክፍልም ሆነ በህብረተሰብ ውስጥ የውይይት ሥርዓትን በመከተል መደማመጥ በሰፈነበት ሁኔታ መወያየት፣ ከመጻሕፍትና ከልዩ ልዩ ሠንጠረዦችም ሐሳብ ማግኘትና መውሰድ፣ ከዕለት ተዕለት የህይወት ገጠመኞቻችሁም ጠቃሚ ናቸው የምትሏቸውን ገጠመኞች በማስታወሻ መያዝ፣ በረጅሙ የተጻፈን ጽሑፍ በተሰጠው መመሪያ መሠረት አሳጥራችሁ መጻፍና በእንግሊዝኛ የተጻፉትን ዓረፍተነገሮች ወደአማርኛ፣ በአማርኛ የቀረቡ ዓረፍተነገሮች ወደእንግሊዝኛ ቋንቋ መተርጎም ችላችኋል፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሰባስባችሁ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ የሚያስተላልፉትን መልዕክት መግለጽና ማብራራት እንዲሁም በፈሊጣዊ አነጋገር የቀረቡ ዓረፍተነገሮችን በዘወትራዊ አነጋገር፣ በዘወትራዊ አነጋገር የቀረቡትን በፈሊጣዊ አነጋገር መለወጥ ችላችኋል፡፡ በተጨማሪም የቀረቡላችሁን የቅኔ ጥያቄዎች ሕብረቃል በማውጣት ሰምና ወርቅ ፍቻቸውን ለይታችሁ በመጻፍ ማቅረብ ችላችኋል፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced / published

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላት የመዝገበ ቃላት ፍችና አውዳዊ ፍች የሚለዩት እንዴት ነው?
2. እውነታና የግል አስተያየት መለያው ምንድን ነው?
3. አንድን ጽሑፍ ለማሳጠር ስትነሱ በቅደም ተከተል ማድረግ ያለባችሁ ምን ምን ናቸው?
4. ውይይት ከጭውውት እንዴት ይለያል?
5. ፈሊጥንና ምሳሌያዊ አነጋገርን የምትለዩበት ዘዴ ምንድን ነው?
6. አንድ ጽሑፍ ወደ ሌላ ቋንቋ ለመተርጎም ምን ዝግጅት ያስፈልጋችኋል?
7. ቅኔን በሰምና ወርቅ ፍች ለመስጠት ዋናው ትኩረታችሁ ምን ላይ መሆን ይገባዋል?

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

© MoE, FDRE Not to be reproduced

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ (√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ ለሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ተ. ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | (√) | (?) | (X) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቀረበውን ጽሑፍ አንብቤ ይዘቱን መረዳት ችያለሁ፡፡ | | | |
| 2 | በሳይንሳዊ ግኝቶችና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በተለያዩ መድረኮችና መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፉ ትምህርታዊ መግለጫዎችን አዳምጬ ማስታወሻ መያዝ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 3 | እውነታንና የግል አስተያየትን ለይቼ በተጠየቃዊ አስተሳሰብ መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 4 | ሥርዓትን ጠብቄ መወያየትና ከመጻሕፍትና ከሠንጠረዦች ሐሳብ መውሰድ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 5 | ከዕለት ዕለት ገጠመኝ ማስታወሻ እይዛለሁ፡፡ | | | |
| 6 | አንድን ጽሑፍ አሳጥሬ መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 7 | ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ መተርጎም ችያለሁ፡፡ | | | |
| 8 | ምሳሌያዊ አነጋሮችን ሰብስቤ መልዕክታቸውን መግለጽ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 9 | በፈሊጣዊ አነጋገር የተነገረውን በተራ አነጋገር፣ በተራ አነጋገር የተነገረውን በፈሊጣዊ አነጋገር እገልፃለሁ፡፡ | | | |
| 10 | የቅኔን ህብረ ቃል ለይቼ በማውጣት የቅኔውን ፍቺ በሰምና ወርቅ ማቅረብ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 11 | አንድን ጽሑፍ አድምጬ ማስታወሻ መያዝ፣ ስለሳቢነቱ፣ መልዕክቱ በትክክል ስለመተላለፉ አስተያየት መስጠት ችያለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በሰንጠረዡ የ (?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትረዷቸው ድረስ፣ የምእራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

## ለተጨማሪ ንባብ የተመረጡ መጻሕፍት ዝርዝር


1. ሀዲስ አለማየሁ፤(1980)። ***የልምዣት።*** አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።
2. መስፍን ወ/ማሪያም፤(1967)። ***እንጉርጉሮ።*** አዲስ አበባ፤ ኮከብ ተሚያ ቤት።
3. መንግሥቱ ለማ፤ (1961)። ***ጠልፎ በኪሴ።*** አዲስ አበባ፤ ቻምበር ማተሚያ ቤት።
4. ሲሳይ ንጉሡ፤ (1978)። ***ሰመመን።*** አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።
5. በዓሉ ግርማ፤ (1974)። ***ደራሲው።*** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።
6. በዓሉ ግርማ፤ (1975)። ***ሀዲስ።*** አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት።
7. አማረ ማሞ፤ (1970)። ***የቀለም ጠብታ፣ የኢልቦለድ አጻጻፍ።*** አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት።
8. አምሳሉ አክሊሉና ዳኛቸው ወርቁ፤ (1979)። ***የአማርኛ ፈሊጦች።*** አዲስ አበባ፤ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ።
9. ዘሪሁን አስፋው፤ (1992)። ***የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።*** አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።
10. ደበበ ሰይፉ፤ (1980)። ***የብርሃን ፍቅር።*** አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።
11. ዳኛቸው ወርቁ፤ (1977)። ***የጽሑፍ ጥበብ መምሪያ።*** አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።
12. ዳኛቸው ወርቁ፤ (1962)። ***አደፍርስ።*** አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።
13. ዮሐንስ አድማሱ፤ (1990)። ***እስቲ ተጠየቁ።*** አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።
14. ፀጋዬ ገ/መድኅን፤ (1966)። ***እሳት ወይ አበባ።*** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።
15. ፀጋዬ ገ/መድህን፤ (1956)። ***ኦቴሎ።*** አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።
16. እነፈርማዬ አለሙ፤(1990)። ***እኛ -170 ግጥሞች።*** አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

## ዋቢ ጽሑፎች


- ሀዲስ አለማየሁ (1958 ዓ.ም.)። *ፍቅር እስከ መቃብር*።
- መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ (2002 ዓ.ም.)። *ትዝታዬ።*
- መንግሥቱ ለማ (1952 ዓ.ም.)። *የግጥም ጉባዔ*። አ.አ.፣ ብ.ሰ.ማ/ቤት።
- መንግሥቱ ለማ (1949 ዓ.ም.)። "የጥበበ ቃላት ክሪቲክ ፕሮብሌም በኢትዮጵያ"፣ *የዛሬይቱ ኢትዮጵያ* ።
- ሜሮን ጌትነት (1999 ዓ.ም.)። *ዙረት*።
- ሪደርስ ዳይጀስት። ሜይ 1983።
- በእውቀቱ ስዩም (1995 ዓ.ም.)። *ኗሪ አልባ ጎጆዎች።*
- ብርሃኑ ገበየሁ (1999 ዓ.ም.)። *የአማርኛ ሥነግጥም*።
- ባዩ ይማም (1987 ዓ.ም.)። *የአማርኛ ሰዋሰው።* አዲስ አበባ፤ ት.መ.ማ.ማ.ድ.።
- አበበች ጉበና (1972 - 1999 ዓ.ም.) **አጉህልድ**
- አቤ ጉበኛ (1961 ዓ.ም.)። *የሐሜት ሱሰኞች* ።
- አዲስ አድማስ (ሰኔ 2003 ዓ.ም) ቅጽ 10 ቁ 597
- አዲስ ዘመን (ጥር1957 ዓ.ም.)።
- የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር (2001 ዓ.ም) **የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምና የተገኙ ውጤቶች።**
- የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር **ጤናችን** (2003 ዓ.ም.)። መስከረም ቅጽ 1 ቁ 1
- ከበደ ሚካኤል (1994 ዓ.ም.)። *የቅኔ ውበት*። አ.አ.፣ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።
- ዓለም እሸቱ (1991)። **የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ።**
- ዮሐንስ አድማሱ። (1966 ዓ.ም.)። "ቃላትና የኪነት ጽሑፍ"። *አዲስ ዘመን* ።




© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

- ያለው እንዳወቀ (1998 ዓ.ም.)። *የምርምር መሠረታዊ መርሆችና አተገባበር።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።
- ዮናስ አድማሱና ሌሎች (1966 ዓ.ም.)። «አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ»። አዲስአበባ፤
- ዘሪሁን አስፋው (1992 ዓ.ም.)። *የስነጽሁፍ መሰረታውያን።*
- ዘሪሁን አስፋው (1986 ዓ.ም.)። "የበአሉ ግርማ ሴቶች አምስት ሀይለኞች"።
- ደረጀ ገብሬ (1996 ዓ.ም.)። *ተግባራዊ የጽሕፈት መማሪያ።* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ደበበ ሰይፉ (1980 ዓ.ም.)። *የብርሃን ፍቅር።* አ.አ.፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።
- ደበበ ኃይለጊዮርጊስ (1999 ዓ.ም)። *ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ*፡ አ.አ እሌኒ ማተሚያ ቤት
- ጌታሁን አማረ (1990 ዓ.ም.)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበበ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።
- ጥሩ ወርቅ ካሣ (1995 ዓ.ም.)። **ተስፋ የሰነቀ ጉዞ**።
- Bender. M.L. 1976. "Non-Semitic Languages: Nilo-Saharan." In: Bender, M.L. et al. (eds). 1976. ***Language in Ethiopia.*** London: OUP, pp 53-62.
- Bender, M.L. et al. (Eds.). *Languages in Ethiopia*. London: OUP.
- The Children's Heart Fund of Ethiopia. No. 2, November 2000, Addis Ababa University.
- Fleming, H. and M.L. Bender. 1976. "Non-Semitic Languages." In Bender, M.L. et al. (eds.). *Languages in Ethiopia*. London: OUP. Pp 34-62.


© MoE, FDRE Ethiopia
Not to be republished

© MoE, FDR
Not to be rep

## ቃላት ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| ሀጫ | - ነጭ፣ በረዶ የሚመስል |
| ሀኬት | - ስንፍና፣ ረቂቅ ተንኮል፣ ትቢት |
| ሁዳድ | - ሰፊ የእርሻ መሬት |
| ሃሌታ | - ምስጋና፣ የምስጋና ቃል፣ የምስጋና መጀመሪያ |
| ህላዌ | - በሕይወት መኖር |
| ህዳግ | - በወረቀት ላይ በጽሑፍ ዳርቻ የሚተው ባዶ ቦታ |
| ህምህምታ | - ጉርምርምታ፣ የሚያስገመግም የብዙ ሰው ድምፅ |
| ህፀፅ | - እንከን ጉድለት |
| ህሊና | - ክፉንና ደጉን ለመለየት የሚያስችል አእምሮ ወይም ልቦና |
| ህቡዕ | - ድብቅ፣ ስውር፣ ምሥጢራዊ |
| ሆረጠ | - አፍን አቃጠለ፣ ጨው ወይም በርበሬ የበዛበት |
| ለበቅ | - ልምጭ፣ አርጩሜ |
| ለበጠ | - ሸፈነ፣ ጠረዘ፣ ደጐሰ |
| ለበጣ | - ፌዝ፣ ሹፈት፣ ቀልድ |
| ለተተ | - መና፣ ደከመ፣ ዛለ |
| ለውላዋ | - ውልብልብ፣ ከውካዋ |
| ለሴ | - ለከት፣ ሙልሙል፣ ጥቢኛ |
| ለሆሳስ | - ሹክታ፣ ድምፅ አልባ |
| ላንሴታ | - የምላስ ምላስ /ጫፍ/ |
| ለቆጠ | - ቦካ፣ ተለወሰ፣ ተጨማለቀ፣ ጨቀየ |
| ሌጣ | - ነጠላ፣ ብቸኛ |
| ልማም | - የጥርስ እድፍ |
| ልጩኛ | - ውለታ ከፋይ፣ ቁም ነገረኛ |
| ልቀት | - የግጭት መፍትሔ |
| ሎጤ | - ቀላዋጭ |
| ለዛ | - ወዝ፣ ውበት፣ የነገር ጣዕም |
| መሐለቅ | - የክብደት መለኪያ /ለወርቅ/ |
| መሠሪ | - ተንኮለኛ፣ ክፉ |
| መግነጢስ | - የስበት ሃይል |
| መቃን | - በቤት ስር ወይም ግራና ቀኝ ጉበን ተሸክሞ የቆመ እንጨት |
| መረን | - ባለጌ፣ ስድ |
| መቅኖ | - እርባና፣ በረከት |

© MoE, FDR
Not to be rep

| | |
|---|---|
| መነቸረ | - ነጨ፣ በጨቀ |
| መነዘለ | - ሚዛን ደፋ፣ ከበደ፣ ወደአንድ በኩል አጋደለ |
| መረሬ | - ርጥበት ባጣ ጊዜ የሚሰነጣጠቅ ጥቁር አፈር ወይም መሬት |
| ሙዳ | - የሥጋ ጉማጅ |
| መርግ | - ትልቅ ናዳ |
| መተረ | - ሥጋ ከተፈ |
| መድበል | - ጥንቅር፣ ስብስብ፣ ክምችት |
| መራጃ | - ትልቅ መዶሻ፣ የድንጋይ መፍለጫ ድጅኖ |
| መበለት | - ባልቴት |
| ሙዋጥ | - የጆንያ መስፊያ መርፌ |
| ሙና | - የሚያምር ታናሽ ወንድ ልጅ፣ ብላቴና |
| ምፀት | - ቀልድ፣ ለግጥ፣ ቧልት፣ ተረብ |
| ማርጣ | - የዝሆን ጭራ |
| ማፉዳ | - ከቆዳ የተሠራ ኮሮጆ፣ ከረጢት |
| ማጥ | - የሚያሰምጥ ጭቃ |
| መየሰ | - መለሰ፣ ወደኋላ አስኬደ |
| ሚጨ | - ጥርሱን ፋቀ፣ ፈገፈገ፣ ጠረገ፣ አፀዳ |
| ረበበ | - ዘረጋ፣ ጋረደ፣ በላይ አደረገ |
| ረብ | - ጠቀሜታ፣ ፋይዳ |
| ሩህ | - እስትንፋስ፣ ነፍስ |
| ራደ | - ፈራ፣ ተንቀጠቀጠ |
| ሰሃ | - እንከን |
| ሰነበጠ | - በጣ፣ ሰነጠቀ፣ ቀደደ |
| ሰነከለ | - እግርን ሰበረ፣ ቀየደ፣ እንደልቡ እንዳይሄድ አደረገ |
| ሰየ | - ጉመዠ፣ ጓጓ፣ ቋመጠ |
| ሰለጠ | - ቀና ሆነ፣ ተከወነ፣ ቀለጠፈ |
| ሰደድ | - ቋያ፣ የዱር የበረሃ እሳት |
| ሸርጣን | - ብዙ እግር ያለው የባህር ነፍሳት፣ ጉርምጥ |
| ሸብልቅ | - ውሻል፣ ቅርቃር፣ ሹል እንጨት ወይም ብረት |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

| | |
|---|---|
| ሽነቆጠ | - በአርጩሜ፣ በአለንጋ ... መታ፣ገረፈ |
| ሸመጠረ | - ኮመጠጠ |
| ሻሜታ | - ከበሶ የሚዘጋጅ ጌሾና ብቅል የሌለው ወፍራም መጠጥ |
| ሻጠ | - ሰካ፣ ተከለ፣ ሳገ |
| ሻጉራ | - አመሉ ከሰው የማይገጥም፣ አመለ ወልጋዳ |
| ሾተል | - ከሁለት በኩል ስለት ያለው ቀጥ ያለ ቀጭን ሰይፍ |
| ሸንጐ | - ስብሰባ፣ ውይይት፣ ምክክር |
| ሸፍጥ | - ክህደት፣ እብለት |
| ቀልብ | - ማስተዋል፣ ማስታወስ የሚያስችል አእምሮ |
| ቀምጣላ | - ሞልቃቃ፣ ደልቃቃ |
| ቀንጃ | - ነጠላ |
| ቀኖና | - ሕግ፣ ሥርዓት፣ ደንብ |
| ቀጠና | - ረሃብ |
| ቀበኛ | - ልብስና የመሳሰለውን የሚበላ ከብት |
| ቀንዘል | - የዛፍ፣ የተክል ቅርንጫፍ |
| ቀውጢ | - ሽብር፣ ሁከት የበዛበት፣ አስቸጋሪ |
| ቀየደ | - አሰረ፣ ጠፈረ፣ ሰነከለ |
| ቆንዳላ | - ሹሩባ |
| በለተተ | - አረጀ፣ ሸመገለ |
| በተሃ | - ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ |
| ቡፍና | - ጌሾ የሌለው ቀጭን ጠላ፣ ቡቅሬ |
| ተራክቦ | - ግንኙነት፣ ሰጥቶ የመቀበል ተግባር፣ መስተጋብር |
| ተቀናቃኝ | - ባላንጣ፣ ተፎካካሪ- |
| ተቆራቆሰ | - ተጋጨ፣ ተጣላ፣ ጠብ ጦርነት ጀመረ፣ አጫረ |
| ቸልተኝነት | - ግዴለሽነት፣ ምን ቸገረኝ ባይነት |
| ቸነፈር | - የተላላፊ በሽታ ዓይነት፣ ወረርሽኝ፣ ተስቦ፣ እልቂት፣ መቅሰፍት |
| ቻርኔላ | - ዚፕ |
| ነሸጠው | - በል በል አድርግ አድርግ የሚል ስሜት ተሰማው፣ ገፋፋው፣ አነሳሳው |
| ነውጥ | - ሁከት፣ ብጥብጥ፣ ሽብር፣ ርደት፣ ንቅናቄ |
| ነፀብራቅ | - ብልጭታ፣ አንድን ሁኔታ ወይም አስተሳሰብን የሚያመለክት ድርጊት ወይም ሀሳብ |
| አረበረበ | - ውሃ ረጨ፣ አርከፈከፈ፣ ንግግር አበዛ፣ ለፈለፈ |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ተቀጽላ

| | |
|---|---|
| አረፈቀ | - አቅም አጣ፣ ደከመ፣ ወደቀ፣ እቤት ዋለ |
| አርምሞ | - ጸጥታ፣ ዝምታ |
| ከወነ | - አዘጋጀ፣ አሰናዳ፣ ፈጸመ፣ ጨረሰ |
| ክትት አለ | - መዞር ተወ፣ ወዲያ ወዲህ ማለት ተወ፣ ተሰበሰበ |
| ክፍለ ዘመን | - የአንድ መቶ ዓመት ጊዜ |
| ወረግቡ | - ልትወልድ የደረሰች፣ ዘጠነኛ ወሯን የያዘች (ሴት) |
| ውርጭ | - በበጋ ወራት በአየር ቅዝቃዜ የተነሳ ሌሊቱን መሬት ላይ ወይም ሳር ላይ ተጋግሮ የሚገኝ ርጥበት |
| ዐቃቤ ስራይ | - የባህል መድኃኒት አዋቂ |
| ዚቀኛ | - ተረበኛ፣ ተረብ አዋቂ |
| ዛበረ | - ለፋ፣ ባከነ፣ ቃዠ፣ ለፈለፈ |
| የክት | - የዘወትር ያልሆነ |
| ይሙት በቃ | - የሞት ፍርድ፣ የሞት ቅጣት |
| ይፋ | - ገሀድ፣ ግልጽ |
| ደረመን | - እከክ፣ ፎከት |
| ደርግ | - ኮሚቴ |
| ጀሌ | - የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች፣ ተራ ህዝብ፣ መሪ ያልሆነ፣ ተከታይ |
| ጀማ | - ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ የተሰበሰቡ ሰዎች፤ ጉባኤ |
| ጅጊ | - የእያንዳንዱን ሰው ስራ በየተራው ቡድን እየሆኑ ለማከናወን በስምምነት የሚፈጠር ጊዜያዊ የስራ ህብረት፤ ደቦ፣ ወበራ |
| ገርጃፋ | - ያለእድሜው ሰውነቱ የገዘፈ፣ ያለእድሜው ያረጀ የሚመስል |
| ጎነቆለ | - የተነከረ ባቄላ፣ አተር፣... መብቀል ሲጀምር |
| ጥሞና | - እርጋታ፣ ዝግታ |
| ጨረፍታ | - በመጠኑ፣ በከፊል፣ በትንሹ |
| ጽልመት | - ጨለማ፣ ጥቁረት |
| ጽጌ | - የአበባ ወቅት |
| ፈተተ | - ቆረሰ፣ ገመሰ |
| ፈገመ | - ወደቀ፣ ተደፋ፣ ሞተ |
| ፖሊሲ | - በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በኩባንያ የሚዘጋጅ የተግባር መመሪያ |

© MoE, FDR
Not to be rep

# ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው

| | |
|---|---|
| 1. ሀፍረት ለበሰ | በጥፋቱ አፈረ፣ ተሸማቀቀ |
| 2. ሁለተኛ ተሰራ | በጠና ታሞ ዳነ፣ ካበቃለት በኋላ አንሰራራ |
| 3. ሁለት ምላስ | ዋሾ፣ ከሀዲ |
| 4. ሁሉ አገርሽ | የሄደችበት ሁሉ የሚስማማት |
| 5. ሆደ መጋዝ | ክፉ ሰው |
| 6. ሆደ ባሻ | ቶሎ የሚከፋው |
| 7. ሆዱ ሻከረ | ቅሬታ ተሰማው፣ ገባው |
| 8. ሆድ ለሆድ | ሀሳብ ለሃሳብ |
| 9. ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ | ራስን መደለል |
| 10. ለከት የሌለው | መጠን፣ ልክ የሌለው |
| 11. ለጋ ጎበዝ | ልጅ እግር |
| 12. ለጋ ጨረቃ | ብርሃኗ ያልደመቀ |
| 13. ላባ ቀረሽ | እብድ |
| 14. ሌላ ነው | በጣም ጥሩ ነው |
| 15. ሌባ ሚዛን | አዛብቶ የሚመዝን |
| 16. ልቅ ወጣች | ባዶ እጇን ቀረች |
| 17. ልበ ቀላል | ችኩል፣ ትእግስት አልባ |
| 18. ልበ ቢስ | ዝንጉ |
| 19. ልቡ ሞተ | ድፍረት አጣ፣ ሰነፈ |
| 20. ልቡ ረጋ | ከሀሳብ ዳነ |
| 21. ልቡ ሰባ | ተበተ |
| 22. ልቡ ሸፈተ | እምቢ፣ አሻፈረኝ አለ |
| 23. ልቡ ቆመ | ቸኮለ፣ ጓጓ |
| 24. ልቡ ቀዘቀዘ | ሀዘን፣ ትካዜ ገባው |
| 25. ልቡን ማረከው | አስደሰተው፣ ወደደው |
| 26. ልቡ አበጠ | ተኩራራ፣ ተጀነነ |
| 27. ልብስ አስቀደደ | ልብስ አስለካ |
| 28. ልብ አለ | አስታወሰ፣ ተገነዘበ |
| 29. ልብ አቁስል | ጨቅጫቃ፣ ነዝናዛ |
| 30. ልብ አውልቅ | አድካሚ፣ አሰልቺ |
| 31. ልብ አደረገ | አጤነ፣ አስተዋለ |
| 32. ልብ ገዛ | አዋቂ፣ አስተወይ ሆነ |

| | |
|---|---|
| 33. መላ መታ | መላ፣ ዘዴ ያለበት ሀሳብ አቀረበ፣ ተነበየ፣ ገመተ |
| 34. መሬት ቁና ሆነች | ጭንቅ ሆነ |
| 35. መንታ ልብ | ወላዋይ |
| 36. መንገድ አሳበረ | አቋረጠ (በአቋራጭ ሄደ) |
| 37. መከራ ሸመተ | መከራ አተረፈ |
| 38. መከራውን በላ | ተሰቃየ፣ ተጎሳቆለ |
| 39. ሙቀጫ ሰገጠ | ምን ልስራ አለ፣ የሚሰራው አጣ |
| 40. ሙት ለሙት ያለቅሳል | ቢደጋገፍ እርባና የሌለው |
| 41. ሙት ደረቅ አይበላም | ማንኛውም ሙት እንደአቅሙ ይቀረብለታል |
| 42. ማዕድ አማገጠ | የቀረበለትን ምግብ በደንብ ሳይበላ ቀረ |
| 43. ምላሱ ተባ | ተናጋሪ ሆነ |
| 44. ምላሱን አሾለ | ለነገር ተዘጋጀ |
| 45. ምላሱን/ አፉን አዳጠው | ነገር አመለጠው |
| 46. ምራቁን የዋጠ | አስተዋይ፣ ትልቅ ሰው |
| 47. ምርቅና ፍትፍት | ክፉና ደግ |
| 48. ምን ቆርጦኝ | እንዴት ብደፍር |
| 49. ምድር መሸበት | ግራ ገባው |
| 50. ምድር ተፋችው | ከከባድ አደጋ ዳነ |
| 51. ምጣዱ ሰማ | ጋለ |
| 52. ሥራ ተቋረጠ | ሥራ ተዋዋለ |
| 53. ራሱን ቻለ | ራሱን አስተዳደረ |
| 54. ራስ ሳይጠና ጉተና | አቅም ሳይፈቅድ |
| 55. ራስ በራስ | በላይ በላይ /ለመውለድ/ |
| 56. ራስ ተስሞ | በብዙ ልምምጥ |
| 57. ርጥብ ሬሳ | ትኩስ ሬሳ |
| 58. ሰማኒያዋ ወረደ | ተፋታች |
| 59. ሰማይ ተደፋበት | ግራ ገባው |
| 60. ሰማይ ዳሰ | በጣም ረጅም |
| 61. ሰምና ፈትል | ፍፁም ህብረት |
| 62. ሰባራ ስንጥር | ማንኛውም ቁሳቁስ |
| 63. ሰነፍ ምርት | ገና ሙሉ በሙሉ ከገለባው ያልተላቀቀ ምርት |
| 64. ሰነፍ እርቅ | ከልብ ያልሆነ እርቅ |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

| | |
|---|---|
| 65. ሰው ሆነ | ራሱን ቻለ |
| 66. ሰው ለየ | አዳላ፣ አወቀ |
| 67. ሰው መዘርጠጥ | ሰው ማዋረድ |
| 68. ሲፈራ ሲቸር | ሲያመነታ፣ ላድርግ አላድርግ ሲል |
| 69. ስመ ጥር | ገናና፣ ዝነኛ |
| 70. ስምህን ቄስ ይጥራው | ሙት |
| 71. ስም አይጠሩ | እባብ |
| 72. ስም አጠፋ | አማ |
| 73. ስር ሰደደ | ተጠናከረ |
| 74. ስጋ ለስጋ | አጥንት ሳይነካ፣ ዘመድ ለዘመድ |
| 75. ስጋ ያዘ | ወፈረ |
| 76. ሽክሙ ወረደለት | ሃሳቡ ቀለለለት |
| 77. ቀላድ ጣለ | መሬት ለካ |
| 78. ቀኔ ነው | የኔ ጊዜ ነው |
| 79. ቀን ሲያዘነብል | ቀን ሲከዳ |
| 80. ቀን በቀን | በብርሃን |
| 81. ቀን ወጣለት | ጥሩ ጊዜ አጋጠመው፣ አለፈለት |
| 82. ቀን ጎደለበት | መከራ ችግር አጋጠመው |
| 83. ቀን ጣለው | ክፉ ጊዜ አጋጠመው |
| 84. ቁም ስቅል | ጭንቅ፣ ስቃይ |
| 85. ቂም አረገዘ | ቂም ያዘ |
| 86. ቃሉን ሰጠ | መሰከረ |
| 87. ቃሉን አጠፈ | ከዳ |
| 88. ቅስሙ ተሰበረ | ስሜቱ ቀዘቀዘ፣ ሞራሉ ወደቀ |
| 89. ቅቤ ጠባሽ | አከንፋሽ፣ አስመሳይ፣ እወደድ ባይ |
| 90. ቆላ ደጋ ረገጠ | የሚያደርገውን አጣ |
| 91. ቆራጭ ፈላጭ | እንደፈለገው አድራጊ |
| 92. ቆሽቱ አረረ | በጣም ተናደደ |
| 93. ቋሚ ንብረት | የማይንቀሳቀስ ንብረት |
| 94. በሬ ወለደ | ፍፁም ውሸት |
| 95. በረሀብ አለንጋ ተገረፈ | ይልሰው ይቀምሰው አጣ |
| 96. በቁሙ ቀበረው | ደባ ሰራበት |
| 97. በአፍንጫዬ ይውጣ | ፈፅሞ አልፈልግም |
| 98. በእንቅልፍ ልብ | በህልም፣ በሰመመን፣ በግርዛዜ |

| | |
|---|---|
| 99. በገ ፈጅ | አንድ በግ ሙሉ የሚቀቅል ድስት |
| 100. በጣት የሚቆጠር | ጥቂት |
| 101. ባህር መዝገብ | ትልቅ መዝገብ |
| 102. ባላና ደንቆሮ | ባላ ያለውና የሌለው የድር ማድሪያ |
| 103. ባዶ አፉን | ጦሙን |
| 104. ባዶ እንጀራ | መብያ የሌለው |
| 105. ባዶ እጅ | ስጦታ ያልያዘ |
| 106. ቤቱን ሰው አያውቀውም | ንፉግ ነው፣ አያበላም፣ አያጠጣም |
| 107. ቤቱን አሸነፈ | ራሱን ቻለ |
| 108. ቤት ያፈራው | እቤት የሚገኝ ምግብና መጠጥ |
| 109. ብስል ተቀሊል | ጥሩም መጥፎም ያለበት |
| 110. ብቅል አውራጅ | ረጅም ሰው |
| 111. ተባራሪ ወሬ | ምንጩ የማይታወቅ ወሬ |
| 112. ተካይ ነቃይ | ሿሚ ሻሪ |
| 113. ተክሊል ሞላ | በተክሊል አገባ |
| 114. ታጥቦ ጭቃ | ተመልሶ እዚያው፣ የማይለወጥ |
| 115. ትከሻህን አትሽ | አታወላውል |
| 116. ትከሻ ሰጠ | ተኩራራ |
| 117. ነት ይንካው | ይዋል ይደር (ለባል ሚስት እርቅ) |
| 118. ነክረው ያወጡት | ቂል፣ ጅላጅል |
| 119. ነገር ለኮሰ | በነገር ሰው አጣላ |
| 120. ነገር የበላ | የነገር ስልት አዋቂ |
| 121. ነጭ እሾህ | መርዘኛ |
| 122. ነፍስ አወቀ | አደገ፣ ጎረመሰ |
| 123. ናላው ዞረ | አበደ፣ ቀወሰ፣ ግራ ገባው |
| 124. አልጋ ነቀነቀ | ንጉስ ለማውረድ ሞከረ |
| 125. አሞቱ ፈሰሰ | ሰነፈ |
| 126. አራስ ነብር | ሃይለኛ፣ ቁጡ |
| 127. አስብቶ አራጅ | እየታለለ የሚጎዳ |
| 128. አበጥሮ ያውቃል | ጥሩ አድርጎ ያውቃል |
| 129. አንቃር መታው | አስታወከው |
| 130. አንደበቱ የተለቀመ | ሲናገር ጠንቃቃ |
| 131. አንጀቱ ተቆረጠ | ተስፋ አጣ |

© MoE, FDR
Not to be rep

| | |
|---|---|
| 132. አንጀት በላ | አሳዘነ |
| 133. አንገተ ሰባራ | አይነ አፋር፣ ትሁት |
| 134. አንገቱን ነቀነቀ | እምቢ አለ፣ ተቃውሞውን ገለፀ |
| 135. አውራ ሌሊት | ውድቅት |
| 136. ዓይን አውጣ | ባለጌ፣ ደፋር |
| 137. ዓይን አዋጅ ሆነበት | ለመምረጥ ተቸገረ፣ ሁሉንም ፈለገ |
| 138. አይጥና ድመት | አጥፊና ጠፊ |
| 139. አግድም አደግ | ባለጌ |
| 140. አፈር ቀመስ | ተቀበረ |
| 141. አፈ ቅቤ | አንደበተ ልስልስ |
| 142. አፉን ዘጋ | ዝም አለ |
| 143. አፍንጫውን ሠንጎ ያዘው | አንድ ነገር እንዲያደርግ አስጨነቀው |
| 144. እህል በእህል | የፆም ምግብ፣ ማጣፈጫ ያልገባበት ወጥ |
| 145. እርጥብ ልጅ | አራስ፣ ጨቅላ |
| 146. እንባ አድርቅ | ለዛ ቢስ፣ ለሐዘንተኛ የሚቀርብ ምግብ |
| 147. እንባ ጠባቂ | ተቆርቋሪ |
| 148. እንዳልሆነ ሆነ | ተዋረደ |
| 149. እንጀራ ወጣለት | ሀብት አገኘ |
| 150. እጀ ሰባራ | ያልረባ ስራ ሆኖ ሲገኝ |
| 151. እጁን አቆመ | መስጠት ተወ |
| 152. እጅ መንሻ | መታያ |
| 153. እጅ አጠረው | ገንዘብ አጣ፣ ተቸገረ |
| 154. እግረ እርጥብ | መልካም እድል ይዞ የሚመጣ |
| 155. እግር ጣለው | ድንገት መጣ |
| 156. ከርሞ ጥጃ | የማይሻሻል |
| 157. ከቁንጫ ሌጦ ማውጣት | ጥቃቅን ሳንካ በሰው ላይ መፈለግ |
| 158. ከብት ለቀቀ | አሰማራ |
| 159. ከአንድ ወንዝ የተቀዱ | ነገረ ስራቸው የተመሳሰለ |
| 160. ከአንገት በላይ | ከልብ ያልሆነ |
| 161. ኩታ ገጠም | ጎን ለጎን |
| 162. ክብር ነካ | አዋረደ |
| 163. ክፉ ቀን | የችግር ወይም የመከራ ጊዜ |

© MoE, FD
Not to be rep

| | |
|---|---|
| 164. ወተቱ ሸፈተ | ቅቤ ማውጣት ጀመረ |
| 165. ወንበር ሲነሳ | ትምህርት ሲቆም |
| 166. ወገቡን ሞከረ | እዳሪ ወጣ፣ ተጸዳዳ |
| 167. ወፌ ገዝት | ትምህርት የሌለው |
| 168. ዋጋ ሰበረ | ዋጋ አዋረደ |
| 169. ውሀ ቀጠነ | በማያስከፋ ነገር መነጫነጭ |
| 170. ውርድ ከራሴ | አያስጠይቀኝም፣ ሃላፊነት የለብኝም |
| 171. ዓይኑን ሰቅሎ አየ | ትኩር ብሎ አየ |
| 172. ዙሪያ ገባው | መላው |
| 173. የላም ልጅ | ወተት |
| 174. የልመና እህል | ኮስማና |
| 175. የመስቀል ወፍ | ቆይቶ ቆይቶ የሚታይ |
| 176. የማሪያም መቀነት | ቀስተ ደመና |
| 177. የምድር ጉድ | ድንክ |
| 178. የሞተ እህል | የተዘጋጀ ምግብ |
| 179. የሞት ሞት | የመጨረሻ ውድቀት |
| 180. የሰው ልክ | የሰው ችሎታ/ ማንነት |
| 181. የሰው ስጋ መብላት | ማማት |
| 182. የሰው በታች | ወራዳ |
| 183. የሰው ዓይን ወጋው | ቡዳ በላው |
| 184. የሰው ዳር | በጣም ጥሩ ሰው |
| 185. የሰይጣን ቁራጭ | ጨካኝ |
| 186. የሰጠ ነው | የተመቸ ነው |
| 187. የቁም ከብት | የቀንድ ከብት |
| 188. የበላን ያብላላዋል | ሀብት ያለው የበለጠ ይንገበገባል |
| 189. የቀበሮ ባህታዊ | ውስጡ ተንኮል ያለበት፣ አስመሳይ |
| 190. የቢስ የቸር | የክፉ የበጎ |
| 191. የብረት ልጥ | ጠንካራ ክንድ |
| 192. የነገር ቋት | ወሬኛ |
| 193. የእህል ቋት | ሆዳም |
| 194. የእንጨት ምንቸት | ራሱ የማይድን፣ ሌላም የማያድን |
| 195. የውሃ መንገድ | ዘወትር የሚመላለሱበት |
| 196. የውሻ አፍንጫ | በጣም ቀዝቃዛ |
| 197. የዛር በቅሎ | ቀዥቃዣ |

| | |
|---|---|
| 198. የደም ስር | ለህልውና በጣም አስፈላጊ |
| 199. የደም ገንቦ | ቆንጆ፣ ውብ ሴት |
| 200. የጉም ሽንት | በጉም ጊዜ የሚዘንብ ካፊያ |
| 201. የግንባር ስጋ | ደፋር፣ ተጋፋጭ |
| 202. የጋን መብራት | እውቀቱን ለሌላ የማያካፍል |
| 203 ያዞ እንባ | የለበጣ ሐዘን |
| 204. ያይን ምሳ | የሚያምር ነገር |
| 205. ደመ መራራ | ነገር የሚገንበት |
| 206. ደም የላትም | ደመ ግቡ አይደለችም |
| 207. ዱላ መዘዘ | ተጣላ |
| 208. ዱላ ቀመሰ | ተመታ |
| 209. ድርና ማግ ሆኑ | በጣም ተስማሙ |
| 210. ድፍን ራስ | ደደብ፣ የማይገባው |
| 211. ጆሮ ስጠኝ | አዳምጠኝ |
| 212. ጆሮ ዳባ ልበስ | ሰምቶ ያልሰሙ መምሰል |
| 213. ጆሮ ጠቢ | ሰላይ |
| 214. ገላ ነክ | ውስጥ ልብስ |
| 215. ገበታ ረጋጭ | ባለጌ፣ (ገበታ ሳይነሳ/ ሳይከበር ተካልቦ የሚነሳ) |
| 216. ገበያ ቆመ | መገበያየት ተጀመረ |
| 217. ጋኑ ተሾመ | ተሞላ (ተዘጋጀ) |
| 218. ጎጆ ቀለሰ | ቤት ሰራ |
| 219. ጎጆ ያዘ | ትዳር ያዘ |
| 220. ጠላው ተቆጣ | ሆመጠጠ |
| 221. ጡት አስጣይ | ታናሽ እህት ወይም ወንድም |
| 222. ጥርሱን ነከሰ | ዛተ፣ አቄመ |
| 223. ጥፊ ላሰ | ተመታ |
| 224. ጨዋታው ቀለጠ | ደመቀ |
| 225. ፀጉር ስንጠቃ | አጉል መራቀቅ፣ ትችት |
| 226. ፊቱን ቋጠረ | ተኮሳተረ |

© MoE, FDRE Not to be republished